# የሰላም ግንባታ ስልጠና ማኑዋል

## ለኢትዮጵያ



# ማውጫ


ምስጋና ........ 6

መግቢያ ........ 12

የሥልጠና ማኑዋሉ አጠቃቀም መመሪያ ........ 15

ምዕራፍ 1፦ የግጭትን ምንነት መረዳት ........ 17

1.1 የግጭት ምንነት ........ 17

1.2 የግጭት ዓውድ ........ 17

1.3 ግጭትን መተንተን ........ 17

1.4 ግጭትን በሥዕላዊ አቀራረብ መግለጽ ........ 18

1.5 ቀጥተኛ፣ መዋቅራዊ እና ባህላዊ ጥቃት ........ 19

1.6 የግጭት ተለዋዋጭነት እና ዕድገት (dynamics) ........ 21

1.7 የግጭት መቆጣጠሪያ ዘዴዎች ........ 24

ምዕራፍ 2፦የሰላም ግንባታ ........ 29

2.1 የሰላም ግንባታ እና የሰላም ትምህርት ግንኙነት ........ 29

2.2 የሰላም ግንባታ መርሆዎች እና ማዕቀፎች ........ 29

2.3 የሰላም ባህልን መገንባት ........ 30

2.4 ሰላም ግንባታ፣ ማንነት እና ብዝኃነት ........ 32

ምዕራፍ 3፦ የግብረገብ ዕሴቶችን ማጎልበት ........ 36

3.1 የሰላም ትምህርት እና ግብረገብ ........ 36

3.2 ሰብዓዊ መብቶችን መሠረት ያደረገ የሰላም ትምህርት አቀራረብ ........ 37

3.3. በሰላም ትምህርት ግብረገብነትን ማጎልበት ........ 38

ምዕራፍ 4፦ የሰላም ሐዋሪያትን ብቃት መገንባት ........ 40

4.1. ራስን ማወቅ ........ 40

4.2 የተግባቦት ክህሎት ........ 41

4.3 የማዳመጥ ክህሎት ........ 41

4.4 ህብረ-ባህላዊነትና የተግባቦት ክህሎት ........ 43

4.5 ተፈጥሮና የሰላም ግንባታ ትምህርት ትስስር ....44
4.6 በጥልቀት የማሰብ ክህሎት ....44
4.7 የማስታረቅ ክህሎት ....47
4.8 የድርድር ክህሎት ....48
4.9. የግልግል ዳኝነት ....49
4.10. ምላሽ ሰጭነትንና ብዝሃነትን መቀበል ....49
4.11. የሰላም ግንባታ ዕሴቶችን ማጎልበት ....50
4.12 የቡድን ስራ እና የመተባበር ክህሎት ....52
ምዕራፍ 5፡- ሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት .... 53
5.1 የሥርዓተ ጾታ መግቢያ ....53
5.2 ሥርዓተ ጾታን ማካተት ....54
5.3 ሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት ....57
5.4 ሴቶች፣ ህፃናትና የአገር ውስጥ ተፈናቃይነት ....62
ምዕራፍ 6፡- ሁለንተናዊ ለውጥ የሚያመጣ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴ (Transformative Pedagogy) .... 64
6.1 ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ-ዘዴ (Transformative pedagogy) ....64
6.2 ለዓውድ ጠንቃቃ መሆን እና ምላሽ ሰጪነት ....64
6.3 ምቹ የመማር ማስተማር ከባቢ ....65
6.4 አሳታፊ የመማር ማስተማር ሂደትን ማረጋገጥ ....67
6.5 አርአያነት ....70
6.6 ማህበረሰብ አቀፍ የመማር ማስተማር ሂደት ....71
ምዕራፍ 7፡- የሰላም ግንባታ ትምህርት ትግበራ .... 73
7.1 የለውጥ አካል መሆን ....73
7.2 የሰላም ግንባታ የብቃት ማዕቀፍ ....74
7.3 የተሳትፎ ደረጃዎች ....74
7.4. ተማሪ ተኮር የአሠልጣኞች መምሪያ ....76
7.5 የወጣቶች ተሳትፎ በሰላም ግንባታ ....77

7.6 በዓላትን እና ዓውደ ርዕዮችን በመጠቀም ንቅናቄ መፍጠር......79

በሰላም ግንባታ ሂደት ዙሪያ......79

7.7 በወጣቶች የሚመራ ማኅበራዊ ሥራ ፈጠራ......79

ምዕራፍ 8፦ የሰላም ግንባታ ዕውቀት ፤ክህሎትና አመለካከት ምዘና......81

8.1 የምዘናው አስፈላጊነት......81

8.2 የሰላም ግንባታ ትምህርት ብቃቶች......81

8.3 የምዘና ጠቀሜታ......82

8.4 ምዘና መቼ መደረግ አለበት?......83

8.5 የሰላም ግንባታ ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካካት የምዘና ዘዴዎች......83

ምዕራፍ 9፦ የሰላም ግንባታ ትምህርት የተግባር ልምምዶች......92

ዋቢ መጻሕፍት......137

# መቅድም

ይህ የሰላም ግንባታ ሥልጠና ማኑዋል ለኢትዮጵያ ከተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት /ዩኔስኮ/፤ በአፍሪካ የአቅም ግንባታ ዓለም አቀፍ ጥናት ተቋም /UNESCO International Institute for Capacity Building in Africa's (IICBA)/ የ2017 እትም ከሆነው *Transformative pedagogy for peace-building: A guide for teachers* በተባበሩት መንግሥታት የሰላም ግንባታ ፈንድ /United /Nations Peacebuilding Funds (the PBF Project)/ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (ዩኤንዲፒ) /United Nations Development Programme (UNDP)፤ ዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (አይኦኤም) /International Organization for Migration (IOM)/ እና በተባበሩት መንግስታት የሥርዓተ ጾታ እኩልነትና ሴቶችን የማብቃት ኤጀንሲ /UN Women/ መካከል ባለው የአጋርነት ሥራ አንድ አካል የሆነው «የሁሉን አካታች አስተዳደር እና የግጭት ቁጥጥር ፕሮጀክት» ሥር በኢትዮጵያ ማዕቀፍ መሠረት ተጣጥሞ የተዘጋጀ እና ወቅታዊነት እንዲኖረው የተደረገ ማኑዋል ነው።

በጃፓን መንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የተደረገለት ይህ እ.ኤ.አ የ2017ቱ የሥልጠና ማኑዋል የዩኔስኮ ኢክባ (UNESCO-IICBA) «በአፍሪካ ቀንድ እና አካባቢው አገሮች የሰላም ግንባታ የመምህራን ሥልጠና እና ልማት» ፕሮጀክት አንድ አካል ሆኖ በኤርትራ፣ በኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በሶማሊያ፣ በደቡብ ሱዳን እና በኡጋንዳ ከ6,500 በላይ መምህራንን ለማሠልጠን ጥቅም ላይ ውሏል። በኢትዮጵያም ከ31 የመምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጆች ለተውጣጡ የመምህራን አሠልጣኞች ማሠልጠኛነት ጥቅም ላይ ውሏል። በዚህም አጋጣሚ የስልጠና ማኑዋሉን ለኢትዮጵያ በሚመች መልኩ የመከለስ፣ የማዘመን እና ዓውዱን የጠበቀ እንዲሆን የማድረግ ሥራ እና በኢትዮጵያ ውስጥ በሚነገሩ ቋንቋዎች የመተርጐም ሥራው እውን እንዲሆን ተደርጓል።

እ.ኤ.አ የ2017ቱ የስልጠና ማኑዋል የመምህራንን አቅም ለመገንባት ተዘጋጅቶ የነበረ ቢሆንም ይህ እንደ ሁኔታው ተመጥኖ እና ወቅታዊ ተደርጎ የቀረበው ዕትም በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ባለ ድርሻ አካላት የሰላም ግንባታ ለምን እንደሚያስፈልግ እና እንዴት ማስተማር እንደሚቻል በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸውና እንዲበቁ ለማድረግ በሚል የተደራሽነት አድማሱን አስፍቷል። የስልጠና ማኑዋሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ስላሉ ግጭቶች ትንታኔ ይሰጣል፤ በሰላምና ደኅንነት ረገድ ግብረገብነትና ሴቶች ያላቸውን ሚና ይመረምራል፤ ለሰላም ግንባታ ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ-ዘዴ (transformative pedagogy) ፅንሰ ሐሳብን ያስተዋውቃል፤ እንዲሁም የሰላም ግንባታ ፅንሰ ሐሳቦችን እና ክህሎትን ግንዛቤ ለመመዘን ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ዘዴዎችን ይገልጻል። የሰላም ግንባታ ብቃቶችን እና በሁሉም የዕድሜ ክልል በሚገኙ ተሳታፊዎች ላይ ጥልቅ አሳቢነትን፣ አስተዋይነትን እና የፈጠራ አስተሳሰብን ለማጐልበት በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ከመማሪያ ክፍሉ ውጭ ጥቅም ላይ ሊውሉ ከሚችሉ በርካታ አሳታፊ ልምምዶች ጋር ወደ ድምዳሜ ያደርሳል ።

የሥልጠና ማኑዋሉ ግብ ተጠቃሚዎችን በስነምግባር ፣ በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት እና በተነሣሽነት በማብቃት ሌሎችን በመደገፍ ሙሉ አቅማቸዉን በማሳደግ ሰላም ገንቢዎች እንዲሆኑ ማድረግ ነዉ።

# ምስጋና

ይህ የሥልጠና ማኑዋል ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ የተዘጋጀውና የተሻሻለው በዶ/ር ትዕግሥት የሺዋስ የሰላም እና ግጭት ምርምር ረዳት ፕሮፌሰር፣ የአካዳሚያዊ ፕሮግራሞች የጥናትና ምርምር አስተባባሪ፣ የሰብዓዊነት ዓለም አቀፍ የበጐ ፈቃድ አምባሳደር፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሰላምና ደህንነት ጥናት ተቋም (አይፒኤስኤስ) /Institute for Peace and Security Studies (IPSS) መምህርት አማካኝነት ነው፡፡በመሆኑም ዶ/ር ትዕግስት የሺዋስ ምስጋና ይገባቸዋል።

እንዲሁም ቴክኒካዊ ድጋፍ ለሰጡት እና የአርትዖት ስራ ለሰሩት የዩኔስኮ ኢክባ (UNESCO-IICBA) አማካሪ ለሆኑት ሚዝ ቤት ሮዝማን የላቀ አክብሮት አለን። ከዚህም በተጨማሪ ይህ የሥልጠና ማኑዋል በሚዘጋጅበት ወቅት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ላደረጉት ለዶ/ር ዩሚኮ ዮኮዜኪ የዩኔስኮ ኢክባ (UNESCO-IICBA) ዳይሬክተር ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን። የዩኔስኮ ኢክባ (UNESCO-IICBA) ፕሮጀክት ኃላፊ ለሆኑት ለዶ/ር ኢየሩሳሌም አዝመራው እና በዚህ የማኑዋል ዝግጅት አስተዋጽኦ ላደረጉ ለሌሎች የUNESCO-IICBA የሥራ ባልደረቦች ምስጋና ይገባቸዋል።

ዩኔስኮ ኢክባ (UNESCO-IICBA) በዚህ የስልጠና ማኑዋል ዝግጅት አስተዋጽኦ ላበረከቱት ለዩኤንዲፒ (UNDP) ፣ለአይኦኤም (IOM) ፣ ለUN Women፣ ለትምህርት ሚኒስቴር፣ ለኦሮሚያ፣ ለአማራ፣ ለሶማሌ እና ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል (ደብብሕክ) ትምህርት ቢሮዎች ምስጋናውን ያቀርባል።

## ሙዳየ ቃላት

**ግጭት፡-** ግጭት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ብዛት ባላቸው ወገኖች (ግለሰቦች ወይም ቡድኖች) መካከል ባለ ግንኙነት በተጨባጭ የሚስተዋል ወይም በሐሳብ ደረጃ እንዳለ ሆኖ የሚታመን የባሕሪ እና የዓላማ አለመጣጣም ነው። ግጭት የግጭቱ ዓውድ፣ በግጭቱ ሳቢያ የተፈጠሩ አመለካከቶችና ባሕሪያት እንዲሁም የግጭቱ ቅርጽ በየጊዜው የሚለዋወጡበት እና አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፍበት ተለዋዋጭ የሆነ ሂደት ነው (Galtung, 1969) ።

**ግጭትን መተንተን፡-** ግጭትን መተንተን ማለት በግጭቱ ውስጥ ያሉ ተዋንያንን፣ የግጭቱ መሰረታዊ ምክንያቶችን፣ ዓውድን፣ ተለዋዋጭ ባሕሪያትን፣ ችግሮችን፣ የኃይል ግንኙነትን፣ የቢሆንስ መላ ምቶችን እና መዋቅሮችን ለይቶ የማወቅ፣ የመዘርዘር እና በፈርጅ፣ በፈርጁ የመመደብ ተግባር ነው (UNESCO IICBA, 2017) ።

**የግጭት አያያዝ፡-** «በተለይ የከፋ ደረጃ ላይ የደረሱ ግጭቶች የበለጠ እንዳይባባሱ እና አሉታዊ ውጤታቸውን ለመከላከል በአስታራቂዎች የሚደረጉ ጥረቶችን...ወዘተ ያጠቃልላል። የግጭት አያያዝ እንደ አንድ ቀላል፣ ወጥ ወይም በሚገባ የተዋቀረ ሂደት ተደርጎ መታየት የለበትም» (Miller, 2005, ገጽ 23) ።

**ግጭትን መከላከል፡-** "ግጭትን መከላከል ማለት የከፋ ግጭትን ሊያስከትሉ የሚችሉ በማቆጥቆጥ ላይ ያሉ ቅሬታዎችን እና ምልክቶችን በእንጭጭነታቸው ለመከላከል ወይም ያለፉ ግጭቶች መልሰው እንዳያገረሹ አሊያም እነዚህ ችግሮች ተጣምረው ጉዳት እንዳያስከትሉ አስቀድሞ የመጠንቀቅ ተግባር ነው። ግጭትን መከላከል የሚለው ሐረግ አሳሳች ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በንድፈ ሐሳብ ደረጃ አስቀድመው የተገለጹት መንገዶች ግጭትን ለመከላከል ያለሙ ሳይሆኑ ይልቁንም ግባቸው የተከሰተን ችግር መፍታት ወይም በአብዛኛው ግጭቶች ወደ ከፋ ደረጃ እንዳይደርሱ በውጤታቸውም የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ ማተኮር ነው" (Miller, 2005፣ ገጽ 24) ።

**ግጭትን መፍታት፡-** «ግጭትን መፍታት ማለት ግጭትን ከመያዝ ወይም ወደ ከፋ ደረጃ እንዳይሸጋገር ከማድረግ በተለየ መልኩ ገንቢ የሆኑ የችግር አፈታት ዘዴዎችን ተጠቅሞ ችግሮችን የመፍታት ሂደት ነው። የግጭት አፈታት የሚለው ሐረግ ፈርጀ ብዙ ትርጉም ያለው ሲሆን የራሱ የሆነ ሂደት ውጤት እና የጥናት መስክ ያለው እንዲሁም ሐረጉን መጠቀም ሳያስፈልግ ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ተግባራዊ የሚያደርጉት ነው» (Miller, 2005, p. 25) ።

**ግጭትን በበጎነት መለወጥ ፡-** «ግጭትን በበጎነት መለወጥ ማለት ልዩነቶችን እና ክፍፍሎችን ለጊዜው ወደ ጎን በመተው የግጭቱን አጠቃላይ ዓውድ እና የተዛቡ አመለካከቶችን ሙሉ በሙሉ በመቻቻል እና በፍቅር በመቀየር ለውጥ ማምጣት ማለት ሲሆን በተለይ በግጭቱ ተዋንያን የነበሩ አካላት ቀደም ሲል ይከተሏቸው የነበሩ መንገዶችን በመተው

አዳዲስ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን መከተል ይጠበቅባቸዋል» (Miller, 2005፣ ገጽ 26-27)።

**የግጭት ሥዕላዊ አቀራረብ፦** የግጭት ሥዕላዊ አቀራረብ /conflict mapping/ ማለት ግጭትን እንዲሁም እየተጋጩ ያሉትን ወገኖች ከችግሩ ጋር እና እርስ በርሳቸው ካላቸው ዝምድና አንጻር በሐሳብ ወይም በሥዕል ወክሎ የማስቀመጥ ቴክኒክ ነው (UNESCO IICBA, 2017) ።

**ገንቢ የሆነ የማስተማር ዘዴ፦** ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ የትምህርት ቅበላው ስኬታማ ይሆናል ብሎ ያምናል። ንቃት ከጎደለው ተራ የመረጃ መሰብሰብ ድርጊት ይልቅ፣ ተማሪዎች በተጨማሪ የራሳቸውን ትርጉም ሰጥተው በራሳቸው ዕውቀትን የሚገነቡበት ስነ ዘዴ ነው (UNESCO IICBA, 2017)።

**የሰላም ባህል፦** የሰላም ባህል «...ማኅበራዊ መስተጋብርን የሚያንፀባርቁ እና የሚያነሣሡ እሴቶችን፣ አመለካከቶችን እና ባሕሪያትን በውስጡ የያዘ ሆኖ በነጻነት፣ በፍትሕ እና በዴሞክራሲ መርሆዎች ላይ እንዲሁም በሁሉም ሰብአዊ መብቶች፣ መቻቻል እና አንድነት ላይ በመመርኮዝ አንዱ ለሌላው የሚያጋራ፣ የኃይል እርምጃን የማይቀበል እና በድርድርና ውይይት ችግሮችን ለመፍታት የችግሮችን መሠረታዊ ምክንያቶች ዕልባት በመስጠት ግጭቶች ከመፈጠራቸው በፊት ለመከላከል ጥረት የማድረግ ባህል ነው። የሰላም ባህል ሁሉም መብቶች በተግባር እንዲከበሩ ዋስትና የመስጠት እና ሁሉም አካላት በልማት ሂደት ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ባህል ነው» (United Nations General Assembly, 1998፣ ገጽ 1)። የግለሰብን ወይም የቡድንን እሴቶች እና ልማዶች የሚያጠና ጥናት ነው፡፡

**ሥነ ምግባር ፦** ሥነ ምግባር ስለ ትክክል እና ስሕተት፤ ጥሩ እና መጥፎ የሚያጠና የፍልስፍና አካል ሲሆን የግለሰብን ወይም የቡድንን እሴቶች እና ልማዶች እንዲሁም ኃላፊነት የመሳሰሉ ፅንሰ ሐሳቦችን ይተነትናል፤ አፈጻጸማቸውንም ያብራራል። ሥነ ምግባር መመዘኛ መስፈርቶችን ለማስቀመጥ ምቹ ሁኔታዎችን የሚያደላድሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ምላሽ ለመስጠት የሚያገለግሉ እምነቶችን፣ ሐሳቦችን፣ ንድፈ ሐሳቦችን እና መሠረታዊ አረዳዶችን በውስጡ የያዘ ነው (Arigatou International, 2008)።

**ሥርዓተ ጾታ፦** ሥርዓተ ጾታ በቤተሰቦቻችን፣ በማኅበረሰባችን እና በባህላችን ውስጥ የተፈጠሩ ወንዶች እና ሴቶች ያላቸውን ሚና እና ኃላፊነቶች ይመለከታል። ሥርዓተ ጾታ የሚለው ፅንሰ ሐሳብ በተጨማሪ የሴቶች እና የወንዶች (አንስታዊ እና ተባዕታዊ) ጠባያት፣ ችሎታዎች እና ተመሳሳይ ባሕሪያት እንዲሁም ሌሎች እንደዚህ መሆን አለባቸው ተብለው የተቀመጡ ተጠባቂ ሁኔታዎችን ያካትታል (UNESCO, 2003) ።

**የሥርዓተ ጾታን ጉዳይ ማካተት፦** የሥርዓተ ጾታን ጉዳይ ማካተት (gender mainstreaming) «... የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን ለማስፈን እና ሴቶችን ለማብቃት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ ስትራቴጂ ነው» (United Nations Economic and Social Council, 2010, ገጽ 1)።

በተባበሩት መንግስታት የሥርዓተ ጾታ እኩልነትና ሴቶችን የማብቃት ኤጀንሲ /UN Women/ (2019) እንዲህ በማለት ይገልጸዋል «የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ግብን ለማሳካት እንዲቻል ተብለው ተመጥነውና ተመርጠው የተዘጋጁ ውስን፣ ስትራቴጂያዊ አቀራረቦችን እንዲሁም ቴክኒካዊ እና ተቋማዊ ሂደቶች ስብስብ ሲሆን አድሏዊ ማኅበራዊ ተቋማትን፣ የሕግ ድንጋጌዎችን፣ ባህላዊ ልማዶችን እና ሴቶች ንብረት የመያዝ መብታቸውን የሚገድቡ ወይም በሕዝባዊ ቦታ ላይ የመገኘት መብታቸው ላይ ገደብ የሚጥሉ የማኅበረሰብ አሠራር ልማዶችን እና የመሳሰሉትን የመቀየር ዓላማ አለው»።

**ሰብዓዊ መብቶች ላይ የተመረኮዘ አቀራረብ፦** ሰብዓዊ መብቶች ላይ የተመረኮዘ አቀራረብ ቅቡል የሆነ እና በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መስፈርቶች ላይ የተመረኮዘ ፅንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ነው። የሰብዓዊ መብቶችን መከበር ያበረታታል፤ጥበቃ ያደርጋል ብሎም ሰብዓዊ ልማትን ይንከባከባል (OHCHR, 2017)። በትምህርት ላይ የሰብዓዊ መብቶች ላይ የተመረኮዘ አቀራረብ ግቡ የሕፃኑን ወይም የሕፃኗን በክብር የመያዝ እና ተቀባይነት ያለው አስተዳደግን ለማግኘት ያለውን ወይም ያላትን መብት የሚያከበር እና የሚያበረታታ ጥራት ያለው ትምህርት እያንዳንዱ ሕፃን ማግኘት መቻሉን ወይም መቻሏን ማረጋገጥ ነው (UNESCO/UNICEF, 2007)። እ.አ.አ በ1948 የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ታውጆ በሥራ ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የትምህርት መብት እንደ ሰብዓዊ መብት በይፋ ዕውቅና አግኝቷል። የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ (1989) ይህን የትምህርት መብት ፅንሰ ሐሳብ ይበልጥ አጠናክሮ ያስፋፋዋል።

**ባህላዊ መስተጋብር** ባህላዊ መስተጋብር የተለያየ ባህል ባላቸው ወገኖች መካከል እያደገ የሚሄድን ዝምድናና እና ግንኙነትን ይመለከታል። ዩኔስኮ (2006) ይህንን ቃል «የተለያዩ ባህሎች ህልውና እና በመካከላቸው በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ማድረግ እንዲሁም በውይይትና በመከባበር የጋራ የባህል መገለጫዎችን መፍጠር የሚቻልበት ዕድል ነው» በማለት ይገልጸዋል (ገጽ 17) ።

**መድብለ ባህል፦** መድብለ ባህል የሚለው ቃል የተለያዩ ማኅበረሰቦችን ኅብረ ባህላዊነት ወይም ብዝሃነት ይገልጻል። የአንድን ብሔር ወይም ሀገር ባህል ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ሥነ ልሳናዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ማኅበረኢኮኖሚያዊ ብዝኀነትን የሚያካትት ነው (UNESCO IICBA, 2017).

**የሰላም ግንባታ፦** የሰላም ግንባታ አዳዲስ ግንኙነቶችን እና ዝምድናዎችን የመገንባት ወይም መልሶ የመገንባት ወይም ነባሮቹን የመለወጥ ሂደት እንደሆነ ተደርጎ ብያኔ ተሰጥቶታል። የግንባታ ወይም የዳግም ግንባታ ሂደቱ ሌሎች ጉዳዮችን ጨምሮ የፍትሕን እና ሰብአዊ መብቶችን የተመለከቱ ችግሮች ላይ መፍትሔ መስጠትን ያጠቃልላል (UNESCO IICBA, 2017)።

**የሰላም ትምህርት፡-** የሰላም ትምህርት ማለት ሰላማዊ የሆኑ የግጭት መፍቻ ክሕሎትን በማዳበር እንዲሁም ሰላማዊ አመለካከትን በማበረታታት ሰላምን ለማስፈን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን መለየትን የማወቅ ሂደትና ተግባር ነው (UNESCO IICBA, 2017)።

**ዕርቀ ሰላም ፡-** «ከዚህ በፊት የተጋጩ ወይም የተጣሉ ወገኖች መካከል የነበረን የተጧጧፈ ወይም ሥር የሰደደ ጥላቻን በመተው አንዱ ሌላውን የሚቀበልበት እና ያለፉትን የጥላቻ ወይም ጎጂ ድርጊቶች በይቅርታ ወደሚተውበት ደረጃ ለመለወጥ ሙከራ የሚደረግበት ሂደት ነው» (Miller, 2003, ገጽ 66) ።

**አስታራቂ ፍትሕ፡-** የደረሰውን ጉዳት መጠገን፣ የተበዳዩን ቁስል ማዳን፣ የተበዳዩን ፍላጎት ማሟላት እና አጥፊውን ወይም አጥፊዋን ለድርጊቱ ተጠያቂ የማድረግ የቅጣት አማራጭ ነው። ከዚህ ቀደም በጠላትነት ይተያዩ የነበሩ ወገኖች ሰላማዊ ግንኙነታቸውን ወደ ነበረበት እንዲመልሱ ማድረግ ላይ እና ካለፉ ጥፋቶች በተገኙ ትምህርቶች ላይ የሚያተኩር ሚዛናዊ አቀራረብ ነው። አጥፊን ከሚቀጣውና ተበዳይን ከሚክሠው የተለመደ ፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓት የተለየ ነው፤ አስታራቂ ፍትሕ ዝምድና እና ግንኙነትን መገንባት እና መለወጥ ላይ ሲያተኩር የተለመደው አጥፊን የሚቀጣውና ተባዳይን የሚክሠው የፍትሕ ሥርዓት በወንጀል እና ቅጣት ላይ ያተኩራል (UNESCO IICBA, 2017)።

**ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ ዘዴ፡-** ይህ ሥነ ዘዴ ሰልጣኞች የሚኖሩባቸውን ዓውዶች፣ ዕምነቶች፣ ዕሴቶች፣ ዕውቀቶች እና አስተሳሰቦች እንዲገመግሙ እንዲሁም ራሳቸውን የመግለጽ፣ ብዝኀነትን የማድነቅ እና በጥልቀት የማሰብ ክሕሎታቸውን እንዲያጎለብቱ የሚረዳ አዲስ የሆነ አቀራረብ ነው። ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ ዘዴ ዕውን የሚሆነው የመማር ማስተማሩ ሂደት ከአዕምሮ በላይ ልቡናን እና ተግባርን ሲያገናኝ በዚህም የዕውቀት፣ የአስተሳሰብ እና የአመለካከት ለውጥ ሲረጋገጥ ነው (UNESCO IICBA, 2017)።

**ሁሉን አቀፍ የትምህርት አቀራረብ፡-** ሁሉን አቀፍ የትምህርት አቀራረብ በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላው ትምህርት ቤቱ እና የትምህርት ቤቱ አካባቢ የተማሪዎችን፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞችን እና መላውን የአካባቢ ማኅበረሰብ ፍላጎቶችን ለማሟላት ይጥራል። የተማሪዎችን ትምህርት ቅበላ፣ ባሕሪ እና ጤናማ የአኗኗር ዘይቤ እንዲሁም ይህንን የሚደግፉ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በትምህርት ቤት ውስጥ እና በትምህርት ቤት አካባቢ ያለ ማኅበረሰብ የሚወሰድ የጋራ እና የትብብር እርምጃን ያመላክታል (UNESCO-IBE, 2017) ።

**ዐመፅ ፡-** ቃል በቃል በግርድፉ ሲተረጐም፣ «ፅንፈኝነት» የሚለው ቃል «አብዛኛዎቹ ሰዎች ትክክል ነው ወይም ምክንያታዊ ነው ብለው ከሚያምኑት እጅግ የራቁ ሐሳቦችን ማመን እና መደገፍ» ማለት ነው፤ በመሆኑም ከተለመደው ወጣ ያለ አመለካከት ወይም ባሕሪ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህ የመዝገበ ቃላት ፍቺ ላይ የተመረኮዘ መሠረታዊ ግንዛቤ የቃሉን ትርጉም ሁሉም በግሉ

ሊፈታው የመቻሉን እውነታ አጉልቶ የሚያሳይ ሲሆን በዚህም ምክንያት ቃሉ ማን እንደሚፈታው እንዲሁም ማን የትኛው ትክክል ነው ወይ አይደለም እያለ እንደሚወስን ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል (ከ UNESCO, 2017 ተመጥኖ የተወሰደ)።

| | |
|---|---|
| **ዓውድ** | የአንድ ማህበረሰብ የዕለት ተዕለት ነባራዊ እውነታን የሚገልፅ ነው፡፡ ይህም በአንድ አካባቢ ወይም ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ነባራዊ እውነታዎችን እና ክስተቶችን እንድንረዳና እንድንገነዘብ ያስችለናል፡፡ |

# መግቢያ

**በኢትዮጵያ ዐውድ አብሮ መኖርን መማር**

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን እንደ ኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ አስደናቂ የለውጥ ሂደት ላይ የምትገኝ ቢሆንም በከባድ ውጥረት ውስጥ ያለችም ትመስላለች፤ በተለያዩ የተወሳሰቡ ምክንያቶች እና ፈታኝ ሁኔታዎች የተነሣ አገሪቱ በሁሉም ክልሎች ሊባል በሚችል ደረጃ እስካሁን ድረስ በግጭቶች እየታመሰች ነው።

የአንዳንድ ግጭቶች መነሻ የተፈጥሮ ሃብት እጦት ማለትም ከእርሻ እና/ወይም ከግጦሽ መሬት እንዲሁም ከውሃ እጥረት ጋር የተያያዘ ሲሆን ሌሎች ግጭቶች ደግሞ ተገልያለሁ ከሚል ስሜት እና ከታመቀ ቅሬታ ወይም ብሶት የሚመነጩ ናቸው። የከፋ ዐመፅ ወይም ብጥብጥ በዘር ማንነት ላይ በመመርኮዝ የሚደረግ ጭፍን ፍረጃ፣ መገለል፣ እና መነጠል ምክንያት ሊቀሰቀስ ይችላል። በዘውገኝነትና በብሔርተኝነት መካከል በሚፈጠር ጫፍ የወጣ አምባጓሮ ከሁለቱም ጽንፍ ነጻ ሆኖ መሃለኛውን ቦታ ለመያዝ ዕድል ከመነፈግ ወይም ማንነትን ከመነጠቅ የተነሣም ሊመነጭ ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና የማኅበራዊ ግንኙነት አውታሮች (ቴክኖሎጂ) ምክንያቶች ዐመፅን በማባባስ ረገድ የራሳቸው ሚና አላቸው ። በኢትዮጵያ የዚህ ዓይነቱ ዐመፅ ከሚያስከትላቸው በጉልህ ከሚታዩ ውጤቶች መካከል አንዱ ድህነት ነው።

ኢትዮጵያውያን ከድህነት፣ ከብጥብጥና ከስደት ለማምለጥ ሲሉ ወደ ውጭ አገራት ተሰደዋል፣ ከቀያቸው ሸሽተዋል፣ የጥገኝነት ከለላ ለማግኘት ድንበር አቋርጠው ተጉዘዋል ወይም በገዛ አገራቸው የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ሆነዋል፤ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች በመላው ኢትዮጵያ በሚባል ደረጃ የሚገኙ ቢሆንም በተለይ ግን በደ/ብ/ብ/ሕ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ እና በሶማሌ ክልሎች ውስጥ በብዛት ይገኛሉ። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ እንደሚያሳየው፣ የቅሬታ መኖር፣ የፍትሕ መጓደልና የሥልጣን ጥማት በክልሎች ውስጥ እና በክልሎች መካከል ለግጭትና ሁከት ሊዳርግ ይችላል። በክልሎች መካከል የሚፈጠሩት ግጭቶች ብዙውን ጊዜ ለረዥም ጊዜ የሚዘልቁ እና መላልሰው የሚከሰቱ ዑደታዊ ናቸው።

ከዚህ የግጭት አዙሪት ለመውጣት ከሁሉም የተሻለው መንገድ ስለ ብዝኃነት መልካም ስሜትን እያጎለበቱ ሰዎች አንድ ላይ መኖርንና ልዩነቶችን ማክበርን መማር እንዲችሉ ማድረግ ነው። እዚህ ላይ ነው የሰላም ግንባታ ትምህርት የሚያስፈልገው። የሰላም ግንባታ ትምህርት ከግጭት ይልቅ ዘላቂነት ያለውን ሰላም ይበልጥ ተመራጭ የሆነ አማራጭን ያቀርባል። በሰላም ግንባታ ትምህርት ስለ ራስን ማወቅ፣ ተግባቦት፣ የጾታ እኩልነት፣ ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር፣ ውይይት፣ መደማመጥ፣ ድርድር እና ሽምግልና እንማራለን። እነዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ላይ ለመኖር የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው።

**በሰላም ግንባታ ላይ የሰላም ትምህርት ያለው ሚና**

የሰላም ትምህርት ግጭት አልባ ዕውቀትን፣ ክህሎትን እና አስተሳሰብን በማዳበር በጎ አመለካከትን የማስፈን እንዲሁም ሰላምን ለማምጣት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን መረዳት የሚያስችል ሂደትና ተግባር ነው። ይህም የሰላም ግንባታ ዋነኛው አካል ነው። ከዚህ በተጨማሪ እንደ Fountain (1999) አገላለጽ የሰላም ትምህርት እነዚህን ይመለከታል፦

> ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ግልጽ እና መዋቅራዊ ለውጥ ተጠቅሞ ሕፃናት፣ ወጣቶች እና ጎልማሶች ግጭትን እና ዐመፅን ለመከላከል እንዲችሉ የሚያደርጋቸውን የባሕሪ ለውጥ እንዲያመጡ የሚያስችሉ አስፈላጊ ዕውቀቶችን፣ ክህሎቶችን፣ አመለካከቶችን እና

ዕሴቶችን የማስተዋወቅና የማስረጽ ሂደት ነው።ከዚህም በተጨማሪ በግለሰብ፣ በማህበረሰብ፣ በአገር ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሰላም አመቺ የሆኑ ሁኔታዎችን የመፍጠር ዓላማ አለው (ገጽ 1) ።

ለሰላም ግንባታ ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ- ዘዴን ለማስፈን የአሰልጣኞች ሚና እንደገና ሊበየን ይገባዋል። የትምህርት ባለሙያዎች፣ ተማሪዎች ጥልቅ እና ፈጠራ የተሞላ አሳቢነት እንዲኖራቸው የሚያስፈልግ አስተሳሰብ፣ ዕውቀት፣ ክህሎት እና ቁርጠኝነት ሊኖራቸው ይገባል። የትምህርት ባለሙያዎች የሌሎችን የጐሣ፣ የሃይማኖት፣ የሥርዓተ ጾታ እና ማኅበራዊ መደብ የተለያዩ ማንነቶችን ማክበር መቻል አለባቸው። እንዲሁም በተለያዩ ተግባራት እና መስተጋብሮች ወቅት የራሳቸው እና የተማሪዎቻቸው ማንነት ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ መረዳት መቻል አለባቸው።

ይህ የስልጠና ማኑዋል በኢትዮጵያ ውስጥ የሰላም ግንባታን በማስተማር በአገር አቀፍ ደረጃ የተሻለ ሰላምን የመገንባት ሂደት ላይ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል ተብሎ የተዘጋጀ ነው። ይህም በሚከተሉት መንገዶች ተፈጻሚ ሊሆን ይችላል፡-

- በተለያዩ ማህበራዊ ቡድኖች መካከል ውይይት እንዲደረግ በማበረታታት፤
- ኃይልን ከመጠቀም መቆጠብን በማበረታታት፤
- የኃይል እርምጃ ከመውሰዱ በፊት አለመግባባቶችን በውይይትና በንግግር መፍታት እንደሚቻል ግንዛቤን በማሳደግ፤
- የወጣቶችን በጥልቅ የማሰብ ክህሎት በማዳበር፤
- ብዝኀነትን በማክበር፣በሰላማዊ መንገድ አብሮ መኖርን እና ማህበራዊ ለውጥን በማበረታታት።

ሰላም ግልጽ የሆኑ ጥላቻዎች ያለመኖር ወይም የአሉታዊ ሰላም መስፈን እንደሆነ ብቻ ተደርጎ መተርጎም የለበትም። ይልቁንም፣ ዘላቂነት ያለው፣ ርትዓዊ እና አዎንታዊ ሰላምን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሂደቶች እና ሁኔታዎች በተጨባጭ የሚታይበት ነው። ሰላም በትርጉሙ ደኅንነትን የማረጋገጥ አንድምታ ያለው እና ተለዋዋጭ የሆነ ማኅበራዊ ሂደት ሲሆን በዚህም ፍትሕ፣ ርትዕ እና የሰብአዊ መብቶች ክብር ልቀው የሚታዩበት እንዲሁም ስሜታዊ፣ አካላዊ፣ ሥነልቦናዊ እና መዋቅራዊ ዐመፅ የሚቀንሱበት ነው።

ሰላም ሰዎች የመርካት፣ በራስ የመተማመን እና ተስፋ የማድረግ ስሜት በሚሰማቸው ወቅት የሚኖራቸው የአዕምሮ እርካታ ነው። ለሰብአዊ መብቶች አክብሮት የሚሰጥበት፣ ፍትሕ እና ርትዕ በተጨባጭ የሚገኙበት፣ ብዝኀነት ያለበት እና ግጭቶች በሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ መንገዶች የሚፈቱባቸው ሁኔታዎች የሚንፀባረቁበት ሰብአዊ እሴትም ነው።

የሰላምን ፅንሰ ሐሳብ ምንነት ብያኔ ለመስጠት ከግምት መግባት ያለባቸው ስድስት ነጥቦች አሉ እነሱም፡-

1) ሰላም የጦርነት አለመኖር (አሉታዊ ሰላም) መሆኑ፤
2) ሰላም በዓለም አቀፉ ሥርዓት ውስጥ ያለው የኃይል ሚዛን መሆኑ፤
3) ሰላም እንደ አዎንታዊ ሰላም (መዋቅራዊ ግጭት አለመኖር) መሆኑ፤
4) ሰላም በአገር አቀፍ እና በአካባቢ ደረጃዎች በጾታዎች መካከል ያለ እንስታዊ ሰላም መኖር መሆኑ ፤
5) ሰላም ከተፈጥሮ እና ከአካባቢ ጋር ተግባብቶ መኖር መሆኑ፤ እና
6) ሰላም ሁሉን አቀፍ ውስጣዊ እና ውጫዊ ሰላም በግለሰብና በቡድን ደረጃ መኖር መሆኑ ነው።

ከእነዚህ መሠረታዊ አስፈላጊ ነገሮች መካከል አንዱን ካጎደልን የሰላም ዋጋ አደጋ ውስጥ ይገባል። በመሆኑም ዘላቂ ሰላም የመገንባቱ ሂደት በጣም ፈታኝ እና አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

የሰላም ትምህርት ግቡ ለኑሮ ምቹና ለደህንነት አስተማማኝ የሆነ አካባቢን ለመፍጠር እንዲቻል በግለሰቦች አመለካከት፣ የሥነ ልቦና ውቅር እና ባሕሪ ላይ መሥራት ነው። የሰላም ትምህርት ከተለያዩ ትምህርቶች ጋር የሚገናኝ ሆኖ እንደ የጦር ትጥቅ መፍታት፣ ሰብአዊ መብቶች፣ የልማት ዕቅዶች፣ ዜግነት፣ የሥርዓተ ጾታ ግንዛቤ፣ ግብረገብና ዜግነት ትምህርት፣ ዓለም አቀፍ ሕግ እና ለአካባቢ ተቆርቋሪነት ከመሳሰሉ ትምህርታዊ ጉዳዮች ጋር የሚተሳሰር ነው።

# የሥልጠና ማኑዋሉ አጠቃቀም መመሪያ

## የሥልጠና ማኑዋሉን በተመለከተ

*ይህ የሰላም ግንባታ ሥልጠና ማኑዋል ለኢትዮጵያየተባለው ሰነድ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት ፣ የአፍሪካ አቅም ግንባታ ዓለም አቀፍ ጥናት ተቋም* (UNESCO-IICBA) *የ*2017 *እትም ከሆነው* “Transformative pedagogy for peace building: A guide for teachers” *ከተሰኘው ሰነድ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ እና ውጭ ላሉ ለበርካታ ሠልጣኞች በኢትዮጵያ ዓውድ ተመጥኖ ወቅታዊነቱን ጠብቆ የተዘጋጀ ነው። ይህ የሥልጠና ማኑዋል በተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የሚተረጐም ሲሆን የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-*

- *በሰላም ግንባታ ዙሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ባለ ድርሻ አካላት ሥልጠና ለመስጠት እና ያላቸውን ዕውቀት እና ክህሎት ለማነቃቃት የሚጠቅም ተግባር ተኮር መሣሪያ እንዲሆን፤*
- *በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ውስጥ የሰላም ግንባታ ፅንሰ ሐሳቦችን ለማካተት እና እንዴት ማስተማር እንደሚቻል በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ላሉት ዋቢ ጽሑፍ ሆኖ ማገልገል፤*
- *በቤተሰቦች፣ በማኅበረሰቦች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በተቋማት፣ ፕሮግራሞች እና ፖሊሲዎች ውስጥ እንዴት የሰላም ግንባታ ፅንሰ ሐሳቦችን ማስተዋወቅ እንደሚቻል ከትምህርት ሥርዓቱ ውጭ ላሉ እንደ ዋቢ ጽሑፍ ሆኖ እንዲያገለግል እና*
- *የሰላም ግንባታ ብቃትን እንዲሁም ጥልቅ እና ፈጠራ የተሞላበት አስተሳሰብን ለመገንባት በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ከውጭ ላሉ ተሳታፊዎች ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል አሳታፊ ተግባራትን ያካተተ በመሆኑ ማጣቀሻ ሆኖ ያገለግላል።*

## ማንዋሉ የተዘጋጀላቸው ሠልጣኞች/ተማሪዎች

*ይህ የሥልጠና ማንዋል ስለ ሰላም እና የሰላም ትምህርት ለማወቅ፣ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት ወይም ለማስተዋወቅ ለሚፈልጉ ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ለማገዝ እንዲቻል ለኢትዮጵያ ዓውድ እንዲመች ተደርጎ ተጣጥሞና ተሻሽሎ ቀርቧል። እ.ኤ.አ የ*2017*ቱ የስልጠና ሰነድ ዒላማ ያደረገው መምህራንን ቢሆንም ይህ የሥልጠና ማንዋል ግን ከመምህራን አልፎ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ እና ውጭ ያሉ በርካታ ሠልጣኞችን ለመድረስ ያለመ ነው። በመሆኑም መምህራንን፣ የመምህራን አሠልጣኞችን፣ የዩኒቨርስቲ መምህራንን፣ የማኅበረሰብ መሪዎችን፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ መሪዎችን ፣ የመንግሥት ተወካዮችን እና ሌሎችንም ባለድርሻ አካላት ያካትታል።*

## የሥልጠና ማኑዋሉን እንዴት መጠቀም ይቻላል?

*በዚህ የሥልጠና ማኑዋል «አሠልጣኝ» የሚለው ቃል አንባቢውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፤ ለአብነት በትምህርቱ ሥርዓት ውስጥና ውጭ ያሉትን አንባቢዎች ያካትታል። ሁሉም ሰው ራሱን እንደ አሠልጣኝ አድርጎ ላይቆጥር መቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህን የሥልጠና ማኑዋል ከተመለከተ በኋላ አንባቢው በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ሰላም ግንባታ ሌሎችን ለማስተማር የሚያስፈልጉ ዕውቀት፣ ክህሎት እና ሥነ-ዘዴዎች በውስጡ ይኖሩታል።*

*በዚህ የሥልጠና ማኑዋል ውስጥ ያሉትን ምዕራፎች በሙሉ እንዲነበቡ እያበረታታን፣ በተለይ ምዕራፍ* 6 *ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ሥነ-ዘዴ እንዲሁም ምዕራፍ* 8 *ምዘና በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።*

*ምዕራፍ* 1 *ከትንታኔ እስከ ሥነ እንቅስቃሴው* (dynamics) *እና የአያያዝ ዘዴዎቹ ሥዕላዊ አቀራረብ ጋር የግጭትን ምንነት ግንዛቤ ያስጨብጣል። ፤ምዕራፍ* 2 *የሰላም ግንባታን አጠቃላይ ዕይታ ሲያቀርብ፤ ምዕራፍ* 3 *ደግሞ ሥነ ምግባርን እና የተማሩትን ትምህርት እንዴት ማንጸባረቅ እንደሚችሉና እንዴት ማበረታታት እንደሚገባ ያብራራል።ምዕራፍ* 4 *ለሰላም ግንባታ አስፈላጊ*

የሆኑትን ክሕሎቶችን ነቅሶ ያሳያል። ምዕራፍ 5 በሴቶች፣ ሰላም እና ደኅንነት ዙሪያ በዚህ የተሻሻለ የሥልጠና ማኑዋሉ ላይ አዲስ የተጨመረ ርዕስ ሲሆን ከሥርዓተ ጾታ ጋር የተገናኙ ፅንሰ ሐሳቦችን እና በሰላምና ደኅንነት ጉዳዮች ላይ ሴቶችን የማሳተፍ አስፈላጊነትን ያብራራል፣ እንዲሁም አዲስ አመለካከት እና በጣም አስፈላጊ አዳዲስ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ፖለቲካዊ ለውጦችን እና ሂደቶችን በተመለከተ ለወጣቶች፣ ለአገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ለማኅበረሰብ መሪዎች ራሱን የቻለ አንድ ክፍል በውስጡ አካቶ የያዘ ነው። ምዕራፍ 6 ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ሥነ-ዘዴ ቁልፍ አባለ ነገራትን ሲያቀርብ፤ ምዕራፍ 7 ደግሞ አሠልጣኞች፣ ሠልጣኞች/ተሳታፊዎች እና ተማሪዎች የሰላም ግንባታ ክኅሎታቸውን፣ ዕውቀታቸውን እና አመለካከታቸውን ከመማሪያ ክፍል/ ከሥልጠናው አልፈው በመሄድ የአካባቢያቸውን ማኅበረሰብ እና ከዚያም በላይ ለማገዝ እንዲችሉ ተግባራዊ እርምጃዎችን ያብራራል። ምዕራፍ 8 በትምህርቱ ወቅት እና ከትምህርቱ በኋላ ጥቅም ላይ የሚውሉ የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን እና ቴክኒኮችን በማቅረብ በትምህርት ቅበላ ምዘና ላይ እንደ መሠረታዊ መመሪያ ሆኖ ሊያገለግል በሚችል መልኩ ተዘጋጅቷል። በመጨረሻም ምዕራፍ 9 የሰላም ግንባታ ችሎታዎችን፣ ጥልቅ እና ፈጠራ የተሞላ አስተሳሰብን በትምህርት ቤት ውስጥ እና ውጭ ላሉ በሁሉም ዕድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ተሳታፊዎች ላይ ለማጎልበት የተለያዩ ተግባራትን ያቀርባል።

# ምዕራፍ 1፦ የግጭትን ምንነት መረዳት

## 1.1 የግጭት ምንነት

ግጭት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች (ግለሰቦች ወይም ቡድኖች) መካከል በተጨባጭ የሚታይ ወይም በሐሳብ ደረጃ እንዳለ ሆኖ የሚታመን የባሕሪ እና የግብ አለመጣጣም ነው። የነገሩ ዓውድ፣ አመለካከቶች፣ ባሕሪ እና መዋቅር በቀጣይነት የሚለዋወጡበት እና አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፍበት ተለዋዋጭ የሆነ ሂደት ነው።

## 1.2 የግጭት ዓውድ

አገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ምክንያቶች ግጭቶችን እና ብጥብጦችን ስታስተናግድ ቆይታለች፡፡ ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አለመረጋጋት፣ የከፋ ግጭት፣ ጠንካራ የሆኑ ተቋማት አለመኖር፣ ኢ-ፍትሃዊነት፣ ሙስና፣ የአየር ጸባይ ለውጥ እና ከሃብት ጋር የተያያዙ ግጭቶች ናቸው። እንደሚታወቀው ብዛት ያላቸው ብሄር ብሄረሰቦች በተለያዩ አካባቢዎች ይኖራሉ።በዚህም የተነሳ ከጐሣ ጋር የተገናኙ ወይም ምክንያታቸውን ጐሣ ያደረጉ ግጭቶች የተለመዱ የዕለት ተዕለት ክስተቶች በመሆን ላይ ናቸው ። እንዲሁም በጐሣዎች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች በቅርብ ዓመታት እየጨመሩ በመሄድ ላይ ናቸው። ይህም ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍሎች ሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያዎች ንግድ፣ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የተደራጀ ዓለምአቀፋዊ ወንጀሎች መስፋፋት፣ ሕገ-ወጥ የህፃናት ዝውውርና ጠለፋ፣ ጎሳ ተኮር የሆነ ጽንፈኝነት እና ግጭት ተጨምሮበት ችግሩ በየጊዜው እያደገ በመሄድ ላይ ይገኛል።


## 1.3 ግጭትን መተንተን

ግጭትን መተንተን ማለት የግጭት ተዋንያንን፣ የግጭቱን መንስኤዎችን፣ የግጭቱን ዓውድ፣ ተለዋዋጭነት ባሕሪን፣ ጉዳዮችን፣ የኃይል ምጥጥን፣ ሁነቶች እና የግጭት መዋቅሮችን ለይቶ የማወቅ፣ የመዘርዘር እና በፈርጅ በፈርጁ የመመደብ ተግባር ነው ።

ግጭትን ለመተንተን ከሚረዱ ዘዴዎች መካከል አንዱ ግጭትን ገላጭ ዛፍ መጠቀም ነው። ግጭትን ገላጭ ዛፍ በመሠረታዊ ደረጃ፣ በግጭት ዓውድ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለይቶ ለማወቅ ያግዛል። ይህን የግጭት መተንተኛ መንገድ በሦስት ክፍሎ ማየት ይቻላል ይኸውም፦

1) መሰረታዊ ምክንያቶች፣
2) ዋነኛ ችግሮችና
3) ውጤቶች ናቸው።

**ሥዕል 1፦ ግጭትን ገላጭ ዛፍ**




ምንጭ፦ ከ Fisher et al., 2000 ለዚህ ሰነድ ተመጥኖ የተዘጋጀ

በበርካታ ግጭቶች ውስጥ እንደታየው ለሚከተሉት ቁልፍ ጥያቄዎች የተለያየ ዓይነት ምላሽና አስተያየት ሊሰጥ ይችላል፡-

1. እነዚህ ግጭቶች ለምን ተከሰቱ? መሰረታዊ ምክንያቶቻቸው ምንድን ናቸው?

2. እነዚህ ግጭቶች እንዴት ተከሰቱ? የግጭቶቹ ይዘት እንዴት ይገለጻል?

3. የእነዚህ ግጭቶች ውጤቶች ምንድን ናቸው?

4. ቅድሚያ ተሰጥቶት መፍትሔ ማግኘት ያለበት መሰረታዊ ችግር የትኛው ነው?


ግጭትን ገላጭ ዛፍ እንደ መድልዎ፣ ኢፍትሓዊ የሆኑ ሕጎች፣ ድህነት እና ማኅበራዊ መገለል የመሳሰሉ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ዋነኛ ችግሮች የተወሳሰቡ እና የኃይል ሚዛን አለመመጣጠን ወይም የመሬት እጥረት የሚመለከቱ ሊሆኑ ይችላሉ።

ውጤቶቹም እስርን፣ ስድብን፣ ግድያን ጨምሮ ወሲባዊ እና አካላዊ ጥቃትን ሊያካትቱ ይችላሉ። ዋንኛ ምክንያቶች (ልክ እንደ የዛፉ ሥሮች ሁሉ) በዓይን ሊታዩ እንደማይችሉ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ግን ውጤቶቹ ወይም መዘዞቹ ሁልጊዜ በግልጽ የሚታዩ ናቸው።

## *1.4 ግጭትን በሥዕላዊ አቀራረብ መግለጽ*

የግጭት ሥዕላዊ አቀራረብ በግጭቱ እየተሳተፉ ያሉትን ወገኖች ከችግሩ ጋር እና እርስ በርሳቸው ካላቸው ዝምድና አንጻር በምስል ወክሎ የማስቀመጥ ስልት ነው። በግጭት ውስጥ እየተሳተፉ ያሉትን ወገኖች በተመለከተ በመካከላቸው ያሉትን ግንኙነቶች ለማብራራት እንዲቻል የግጭት ሥዕላዊ አቀራረብ በግጭቱ ውስጥ እጃቸው ያለበትን ሁሉንም ወገኖች እና በግጭቱ የተፈጠሩ ጫናዎችን የሚያሳይ የተሟላ እና ገለልተኛ የሆነ ሥዕልን ለማቅረብ ይሞክራል።

**ሥዕል 2 የቤተሰብ ግጭት የግጭት ሥዕላዊ አቀራረብ**




ምንጭ፡- Fisher et al., 2000, ገጽ 24

የግጭት ሥዕላዊ አቀራረብ አስታራቂ እርምጃን ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ሲሆን እንደ የቅስቀሳ ዘመቻዎች ወይም ማስጠንቀቂያ መስጠት በመሳሰሉ አፍላ ደረጃዎች ላይ ጥቅም ላይ ከዋለ በከፍተኛ ደረጃ ጠቃሚነት አለው። የግጭት ሥዕላዊ አቀራረብ የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት።

1. **የግጭትን ዓውድ ዳራውን በግልጽ ለይቶ ለማወቅ።**

   ሀ. የአካባቢውን አስተዳደራዊ ወይም ፖለቲካዊ ካርታ ለመጠቀም፤

   ለ. አካባቢውን በግልጽ ለማወቅ እና

   ሐ. የግጭቱን ታሪካዊ ዳራ ለመለየት።

2. **የግጭቱን ተሳታፊዎች እና ችግሮቹን በግልጽ ለመለየት።**

   ሀ. የግጭቱ ዋነኛ ተሳታፊ ወገኖች እነማን እንደሆኑ መለየት፤

   ለ. በግጭቱ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለይቶ ማወቅ፤

   ሐ. በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን ወገኖች ግንኙነት ለይቶ ማወቅ፤

   መ. የግጭቱ ተሳታፊ ወገኖች ስለ ግጭቱ መንሥዔና ጠባይ ምን እንደሚያስቡ ለይቶ ማወቅ፤

   ሠ. በግጭቱ ውስጥ ያሉትን ወገኖች አሁን ያላቸውን ባሕሪ በተመለከተ የበለጠ ማወቅ እና

   ረ. በግጭቱ ውስጥ ያሉትን መሪዎች እነማን እንደሆኑ ለይቶ ለማወቅ ይጠቅማል።

3. **የግጭቱን ዓውድ በቤተሰብ፣ በአካባቢ፣ በአገር፣ በክፍለ አህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመለየት፦**

   ሀ. **በቤተሰብ ደረጃ፦** በቤተሰብ አባላት መካከል ያለው ግንኙነት በግጭቱ ላይ ያለው ተጽዕኖ እንዴት ይታያል?

   ለ. **በአካባቢ ደረጃ፦** በአካባቢ ባሉ ማህበረሰቦች መካከል ያለው ግንኙነት በግጭቱ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እንዴት ይታያል?

   ሐ. **በአገር ደረጃ፦** የአገሪቱ ህልውና ፈተና ውስጥ ገብቷል?

   መ. **በክፍለ አህጉር ደረጃ፦** በአጎራባች አገሮች መካከል ያለው ግንኙነት በግጭቱ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ እንዴት ይታያል?

   ሠ. **በዓለም ደረጃ፦** በግጭቱ ውስጥ ውጫዊ የሆኑ ጂኦ-ፖለቲካዊ ጥቅምና ፍላጎቶች አሉ? ግጭቱን የሚያባብሱ ውጫዊ ምክንያቶች ምንድን ናቸው እና ምን ሊለውጣቸው ይችላል?

## *1.5 ቀጥተኛ፣ መዋቅራዊ እና ባህላዊ ጥቃት*

«ዐመፅ» የሚለው ቃል በበርካታ አጋጣሚዎች ላይ እንደ ጥቃት ተመሳሳይ ቃል ፍቺ ተደርጎ ጥቅም ላይ ይውላል። ምንም እንኳ ጥቃት እና ዐመፅ እኩል ትርጉም ያላቸው ቢመስሉም በቃላቱ ተፈጥሮ እና ምንጭ ላይ ባለው ልዩነት ላይ የጋራ ስምምነት አለ።

ዐመፅ በሥነ ሕይወት እና በባህል መካከል ባለ መስተጋብር ምክንያት የሚፈጠር ሲሆን ሆን ተብሎ የመፈጸም አንደምታ በውስጡ አለው። እንደ Berkowitz (1996) እና Anderson እና Bushman (2002) ያሉ ደራሲዎች በእነዚህ ሁለት የዐመፅ ባሕሪ ዕይታዎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች እንደሚከተለው ያሳያሉ፦

(ሀ) ሆን ብሎ ጉዳትን ማድረስ ብቸኛ ዓላማው ሆኖ በግልፍተኝነት የሚንጸባረቅ የጥላቻ ጠባይን የመጠቀም አንደምታ ያለው የባህሪ ጽንፍ እና

(ለ) ዐመፅ የአንድን ሰው ወይም ወገን የግል ፍላጎቶች ለማሟላት ጥቅም ላይ የሚውልበት ሆን ተብሎ የሚከናወን ጽንፍ በማለት ይገልጻሉ።


ጥላቻ የተሞላበት ዐመፅ በመባል የሚታወቀው ጽንፍ ብዙውን ጊዜ በትንኮሳ የሚጀምር እና ከተጀመረም በኋላ ዋነኛ ዓላማው ጉዳትን ማድረስ አድርጎ የሚንቀሳቀስ እና ዝግጅት ያልተደረገበት ቁጣ የቀሰቀሰው ግልፍተኛ ባሕሪን ይመለከታል።

ኤቢሲ የግጭት ሦስት ማዕዘን /ABC Conflict Triangle/ በአንድ ግጭት ውስጥ በግጭቱ ውስጥ ቁልፍ የሆኑትን ሦስት ገጽታዎች በውስጥ የያዘ እንደሆነ ይጠቁማል እነዚህንም ገጽታዎች እንደሚከተለው ለይቶ ያስቀምጣቸዋል፦

1) አመለካከቶች/እሳቤዎች (A) attitudes/assumptions
2) ባሕሪያት(B) (behaviors) እና
3) ዓውድ/ተቃርኖዎች(C) (context/contradictions)

ከዚህ ጋር በተገናኘ እያንዳንዱ ግጭት በግልጽ የሚታዩ እና የማይታዩ ገፅታዎች አሉት ። በግልጽ የሚታየው ጎን እንደ ባሕሪ ተለይቶ ሲታይ ስውሩ ገጽታው ደግሞ በአመለካከት እና በተቃርኖ የሚገለጽ ይሆናል (Galtung, 1996፣ Engdaw, 2018) ።

**ሥዕል 3፦ የ ABC (Attitude, Behavior and Context) ግጭት ሦስት ማዕዘን**




ምንጭ፦ Galtung, 1996

የኤቢሲ ግጭት ሦስት ማዕዘን /ABC Conflict Triangle/ ሦስቱ አባለ ነገሮች (elements) ግጭትን ከሦስት አቅጣጫዎች ወይም አቀራረቦች ለመገንዘብ እንዲቻል ያግዛል፦ እነዚህም አቅጣጫዎች

- ቀጥተኛ ጥቃት፣
- መዋቅራዊ ጥቃትና
- ባህላዊ ጥቃት ናቸው።

**ቀጥተኛ ጥቃት፦** አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ እና ስሜትን የሚነካ ሊሆን የሚችል ሲሆን በጉልበት መጠቀምን፣ ማስፈራራትን፣ ማዋረድን፣ ማናናቅን፣ ቸልተኝነትን እና አካላዊ ጥቃትን ያካትታል።

በቤት ውስጥ ከሚፈጸሙ ጥቃቶች መካከል አንዳንድ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ያህል ሚስቱን የሚደበድብ ባል (ወይም ተገላቢጦሹ) እና/ወይም ባለ ትዳሮች እርስ በርስ በቃላት ተጠቅመው አንዱ ሌላውን ሲያንቋሽሽ እና ሕፃናት በወላጆቻቸው ወይም ሞግዚቶቻቸው ሲበደሉ የመሳሰሉ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎችን የሚማታ መምህር ወይም የሚሳደቡ ተማሪዎችን የሚወክለውን የትምህርት ቤት ዐመፅን ያካትታል። የሰፈር፣ የነገድ፣ የብሔር፣ የክፍለ አህጉር ወይም ዓለም አቀፍ ግጭትንም እንዲሁ ያካትታል።


**መዋቅራዊ ጥቃት** ፦ዋነኛ ተዋናይ የሌለበት የዐመፅ ዓይነትን ይመለከታል፤ ይህም ማለት «በመዋቅሩ ውስጥ ሌላውን ግለሰብ በቀጥታ የሚጎዳ ምንም ዓይነት ግለሰብ ላይኖር ይችላል። ዐመፁ በመዋቅሩ ውስጥ የተገነባ ሆኖ ያልተመጣጠነ ኃይልና ሥልጣንን ከልክ ባለፈ መልኩ መጠቀምን ያሳያል። በዚህም የተነሳ ኢ-ፍትሃዊነትን ይፈጥራል (Galtung, 1969, ገጽ 171)። ለምሳሌ እንደ ገቢ ሥርጭቶች፣ ትምህርት እና የሕክምና አገልግሎቶች የመሳሰሉት እኩል ባልሆነ መንገድ ይሠራጫሉ። በዚህም የተወሰኑ ግለሰቦች በዘራቸው፣ ማኅበራዊ መደባቸው፣ ሃይማኖታቸው፣ ጾታቸው ወይም የአካል ጉዳታቸው በቡድን ተለይተው ከፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ተሳታፎ እንዲገለሉ ይደረጋሉ። ይህም በበኩሉ ዐመፅን ሊቀሰቅስ ይችላል። ይህ የማንም ሰው ጥፋት አይደለም፣ ሆኖም በደፈናው ሥርዓቱ (መዋቅሩ) የፈጠረው ችግር ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ድህነት በጣም የተለመደ የመዋቅራዊ ዐመፅ ውጤት ነው። መዋቅራዊ አመፅ በቀጥታ የሚታይ ምንም ዓይነት ተዋናዮች የሉትም። ድህነት ግን በማኅበረሰቡ ሥር ሰዶ በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መገለሎች ላይ በግልጽ ይታያል።

**ባህላዊ ጥቃት** ፦በነገድ(በጎሳ)፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ የአካል ጉዳት፣ በማንነት ላይ በመመርኮዝ መዋቅራዊ እና ቀጥተኛ ዐመፅን ምክንያታዊ እንደሆኑ አድርጎ የማቅረብ ድርጊት ነው። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ሴቶች በአብዛኛው ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ እና ከማኅበራዊ ተሳትፎ ሲገለሉ ኖረዋል። ለዚህም ብዙውን ጊዜ ሲሰጥ የነበረው ምክንያት ሴቶች የማህበራዊ፣የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ መሪዎች ወይም ተዋንያን እንዲሆኑ ባህሉ ወይም ወጉ አይፈቅድላቸውም የሚል ነው። እነዚህ ስለ ሴቶች እና ስለተገለሉ የማኅበረሰቡ አካላት ላይ የሚነገሩ ተራ አነጋገሮች፣ ቀልዶች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ሥነ-ቃሎች እና የመሳሰሉትን እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል።

## 1.6 የግጭት ተለዋዋጭነት እና ዕድገት (dynamics)

ግጭት በአንዲት ትንሽ ገጠመኝ ጀምሮ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ሊያድግ ይችላል። ለምሳሌ አንድ አባት ከዚህ ቀደም ቁርሾ ላለው ቤተሰብ ሴት ልጁን ለመዳር አስቧል ብለን እናስብ። ሆኖም ግን የልጅቱ ሴት አያት በዚህ በወላጆች ስምምነት ባለቀው የግዴታ ጋብቻ ሐሳብ አልተስማሙም። የልጃቸው ልጅ ባል ከዚህ ቀደም ምን እንዳደረገ ሲሰሙ በጣም ይናደዳሉ። ወዲያውኑ ወደ ሌላው የሩቅ ዘመድ ወደፊት ባል የሚሆነው ልጅ ቤተሰቦች፣ ማኅበረሰቡ እና ከዚያም በላይ የእርሳቸው ቅሬታና መከፋት ወሬ ይዳረሳል። ከዚህ ቀደም የደረሰው በደል ሲታወስ ልክ በእሳት ላይ ቤንዚን እንደማርከፍከፍ ቁጣውን አባባሰው። ቁጣው የግጭት ድርጊትን ሊጋብዝ ይችላል። ይህም በተራው በሰዎች መካከል መበቃቀልን ስለሚያስከትል ሌሎች የዐመፅ ድርጊቶችን ይወልዳል። በመሆኑም ይህ አንድ ተራ ገጠመኝ ወደ እርስ በርስ ጦርነት፣ አካባቢያዊ ወይም ወደ አገር አቀፍ ግጭት ሊያድግ ይችላል።

***ሥዕል 4፡- አንድ ግጭት ከትንሽ አጋጣሚ ተነሥቶ እንዴት በፍጥነት ከቁጥጥር ውጭ ወደ ሆነ ደረጃ ሊያድግ እንደሚችል የሚያሳይ ሥዕላዊ ምሳሌ***




***የከፋ ግጭት ደረጃዎች እና ዕድገት***

እንደ Brahm (2003) አገላለጽ፣ የከፋ ግጭት ስድስት ደረጃዎች አሉት፡-

***ደረጃ 1፡- ለእሳቱ የሚሆነውን የማገዶ እንጨት መልቀም/ ድብቅ ግጭት*** በግጭቱ የመጀመሪያው አፍላ ደረጃ ላይ ለእሳቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ይሰበሰባሉ። ከእነዚህ ቁሳቁሶች መካከል አንዳንዶቹ ከሌሎቹ የተሻለ የመንደድ ዕድል አላቸው። ሆኖም ግን አሁንም ድረስ እሳቱ አልተቀጣጠለም፤ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ግጭት ግን ውስጥ ውስጡን እየበሰለ ነው።

***ደረጃ 2፡- እሳቱ መቀጣጠል ይጀምራል (ግጭቱ በግልጽ ይታያል)***

በዚህ ደረጃ ላይ ክብሪቱ ተጭሯል፣ እሳቱም መንደድ ጀምሯል። በአብዛኛው እንደ ትልቅ ሕዝባዊ ሰልፍ ወይም በማኅበራዊ መገናኛ አውታሮች የተለጠፈ ቪዲዮ እና ሥዕል የመሳሰሉ ነገሮች በተወሰኑ ቡድኖች መካከል ለሚፈጠሩ ግጭቶች እንደ ክብሪት ሆነው ያገለግላሉ፣ ይህም የለዘበውን ግጭት የደረቁ ቁሳቁሶች በእሳት እንዲያያዙ ያደርጋቸዋል።

***ደረጃ 3፡- ግጭቱ ይስፋፋል***

እሳቱ ይቀጣጠልና መድረስ እስከሚችልበት ደረጃ ድረስ ይሄዳል፣ ከቁጥጥር ውጭ እስከሚሆን ድረስ ይስፋፋል። በዚህ ደረጃ ግጭቱ ቀውስና ብጥብጥን ያስከትላል።ልክ እንደ እሳቱ ሁሉ እንደ ነዳጅ የሚያገለግሉትን ቁሳቁሶች (ወይም ችግሮች) እያቀጣጠለ ይነዳል።

***ደረጃ 4፡- የጋራ ጉዳት***

ሁለቱም ወገኖች በጋራ ተጎድተው እየደሙ ነው፤ ሆኖም ግጭቱ ቀጥሏል።

***ደረጃ 5፡- መለዘብ /ድርድር***


የሆነ ደረጃ ላይ ሲደርስ እሳቱ መዳከም ይጀምራል፤ ከሰሎች ብቻ ከነፍማቸው ይቀራሉ። አብዛኛው ነዳጅ ነዶ አልቋል። ብዙውን ጊዜ የሦስተኛ ወገን የድርድር ጥረቶች ይጀመራሉ። በዚህ ደረጃ ግጭቶች ሊቀጥሉ ወይም የድርድር ጥረቶቹ ውጤታማ ከሆኑ ስኬታማ ፍጻሜ ሊያስገኙ ይችላሉ።

***ደረጃ 6፡- እሳቱ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል/ድኅረ-ግጭት የሰላም ግንባታ ሥራ ይጀመራል***

በመጨረሻም እሳቱ ጠፍቷል፤ ከሰሎቹም መቀዝቀዝ ጀምረዋል። ይህ ደረጃ ግንኙነት እንደገና መገንባት ላይ የማተኮሪያ እንዲሁም ዕርቀ ሰላምን እና የድኅረ ግጭት የሰላም ግንባታ ሂደቱን

የማስጀመሪያ ጊዜ ነው። ሆኖም ግን የግጭት መፍትሔ አሰጣጡ በሚገባ ካልተያዘ ወይም አያያዙ ደካማ ከነበረ ግጭቱ እንደገና ሊጀምር የሚችልባቸው ዕድሎች አሉ።


**ሥዕል 5፡- የግጭት ደረጃዎች ሞዴል**




ምንጭ፡- Brahm, 2003 **የግጭት ዑደት**

የግጭት ዑደት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የከፋ ግጭት በተመለከተ ያለንን ግንዛቤ ሊያሳድገው ይችላል። ከዚህ ቀደም የነበሩ ግጭቶችን በሚገባ ካልተረዳናቸው እና መፍትሔ ካልሰጠናቸው ሊለወጡ አይችሉም።


**ሥዕል 6፡- የግጭት ዑደት**



## *1.7 የግጭት መቆጣጠሪያ ዘዴዎች*

አራት የግጭት መቆጣጠሪያ ዘዴዎች አሉ፡-

- **ግጭትን መከላከል፡-** ግጭት እንዳይከሰት ቀድሞ የመከላከል ዘዴ ነው።
- **የግጭት አያያዝ፡-** ተሳታፊ ወገኖች አዎንታዊ የባህሪ ለውጦች እንዲያመጡ ወደፊት ሊከሰት የሚችል ጥቃትን ለመገደብ እና ለማስቀረት ያለመ ነው።
- **ግጭት መፍትሔ አሰጣጥ፡-** ለግጭት ምክንያቶች መፍትሔ ይሰጣል፤ እንዲሁም በጠላትነት በሚተያዩ ወገኖች መካከል አዲስ እና ዘላቂነት ያለው ግንኙነትን ለመገንባት ጥረት ያደርጋል።
- **የግጭት ሙሉ ለውጥ፡-** የአንድን ግጭት ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ምንጮች በሰፊው በመዳሰስ የግጭትን አሉታዊ ድርጊቶችን ወደ አዎንታዊ ለውጥ ለመቀየር የሚደረግ ጥረት ነው።




*Making Peace in Ethiopia: Nine Cases of Traditional Mechanism for Conflict Resolution* (2016) እንደተባለው መፀሐፍ ገለጻ በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ የግጭት አፈታት ዘዴዎች አሉ። መጽሐፉ በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ውስጥ የአገር ሽማግሌዎች ግጭቶችን በመፍታት ረገድ ያላቸውን ሚና ያብራራል፤ የሚከተሉትንም ልማዶች እንደ አብነት ያቀርባል፡-

- የደቡብ ኢትዮጵያ የወላይታ ሰዎች አብነት፣
- በአርሲ ኦሮሞ በተለይ የዶዶላ አካባቢዎችን እና አጎራባቾችን አብነት፣
- በሰሜን ወሎ *የአቢጋር* (መለኮታዊ አባት) ሚና፣
- የሲዳማ አብነት፣
- የጉራጌ አብነት፣
- ትግራይ ላይ የተደረገ ጥናት፣
- በአንኮበር ወረዳ የአማራ *ሽምግልና* አብነት እና
- የካምባታ እና የኦጋዴን አካባቢ አብነት።

በተለምዶ ተቀባይነት ያለው ጥበብና ዕውቀት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ከማንም በተሻለ የራሳቸውን ችግር መረዳት እንደሚችሉ እና የራሳቸውን ባህላዊ ዘዴዎች ወይም አገር በቀል የግጭት አፈታት ዘዴ እና ተቋማት በመጠቀም ችግሮቻቸውን ለመፍታት የተሻለ ዕድል እንዳላቸው ይጠቁማል።

ለገጠር መልሶ ግንባታ ዓለም አቀፍ ተቋም፣ የአፍሪካ ክልላዊ ማዕከል ያዘጋጀው *Culture at Crossroads: Ethiopian Women in Peacebuilding* (2009) የሚል መጽሐፍ ሴቶች በሰላም ግንባታ ውስጥ ያላቸውን ሚና ይመረምራል። ሰላምን ለማምጣት እና ግጭትን ለመፍታት ሴቶች ያላቸውን ለየት ያሉ ዕውቀቶች፣ ክኅሎቶች እና ችሎታዎች በተመለከተ ይናገራል። በግለሰቦች፣ በማኅበረሰቦች እና በብሔሮች መካከል ሰላማዊ ግንኙነትን ለማጠናከር በዛሬዋ ኢትዮጵያ ዓውድ ውስጥ ክኅሎቶችን መጠቀም ስለሚቻልባቸው መንገዶች ጠቋሚ ሐሳቦችን ይሰጣል። ሴቶች በሰላም ግንባታ ስላላቸው ሚና የሚያሳዩ አንዳንድ ምሳሌዎች ሴቶች፣ ሰላም እና ደኅንነት በሚለው በምዕራፍ 5 ውስጥ በሰፊው ተብራርተዋል።

## 1.8 ግጭትን መከላከል እና አያያዝ ላይ የባለድርሻ አካላት ሚና

ቤተሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ የኃይማኖት አባቶች እና በእምነት ላይ የተመረኮዙ ድርጅቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ብዙሃኃን መገናኛ እና መንግሥት አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ በማድረግ፤ ግጭትን በመከላከል እና በአግባቡ በመያዝ ለሰላም ግንባታ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ሚና አላቸው። ግጭትን ከተጀመረ በኋላ ለመቆጣጠር ከመሞከር ይልቅ አስቀድሞ መከላከሉ የተሻለ ነው።

በሰላም ትምህርት ላይ አሠልጣኞች፣ ሠልጣኞች እና ተማሪዎች ያላቸው ሚና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሰላም ግንባታ ሂደቶች ወሳኝነት አለው። በተለምዶ መምህራን ትምህርትን ለሌሎች እንደሚያካፍሉ ሰዎች አድርገው እንዲቆጥሩ ተደርገው ሲሠለጥኑ የቆዩ ናቸው። ከዚህ ዕይታ አንጻር «መምህሩ ሁሉንም ነገር ያውቃል እና ተማሪዎች ደግሞ ምንም አያውቁም» (Freire, 1970, ገጽ 73) እንዲሁም ማስተማር እንደ «ባዶ እንስራ»ን የመሙላት ተግባር እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህ የማስተማር ምንነትን የተመለከተ አስተሳሰብ ለረዥም ጊዜ የቆየ እንደመሆኑ ይህ ባዶ እንስራን የመሙላት የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ትክክለኛው የማስተማር ዘዴ ሊመስል ይችላል።

መምህር ተኮር የሆነው የማስተማር ዘዴ መምህራን ሁሉም ዕውቀት እንዳላቸው እና ተማሪዎች ደግሞ ምንም እንደሌላቸው አድርጎ የሚቆጥር እንደመሆኑ ትልቅ ግምት የሚሰጣቸውን ብዙ መዘዞች ሊያስከትል ይችላል። ተማሪው በጥልቅ የሚያስብ እና ራሱን የቻለ አሳቢ ከመሆን ይልቅ እጁን በቀላሉ የሚሰጥ፤ በራሱ የማይተማመን እንዲሁም ምን ማሰብ እና ማወቅ እንዳለበት በተመለከተ እንዲነግረውና በመምህሩ ላይ ጥገኛ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ፣ ተማሪው የኋላ ኋላ ሥልጣን ላይ ባሉ ሰዎች በቀላሉ እንደተፈለገው ሊሽከረከርና በራሱ አቋም ላይመራ ይችላል። ይህ እንደተፈለገው ሊደረግ የመቻሉ አባዜ አለመቻቻልን ለማስፋፋት እና ወጣቶች ከጥያቄ ሊገቡ እንደማይችሉ አድርገው ሊቀበሏቸውና ሊያምኗቸው ለሚችሉ ቀልባሽ/ጽንፈኛ አስተሳሰቦች እንዲማረኩና እንዲቀበሏቸው ሊያደርጋቸው የሚችለውን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።

ለሰላም ግንባታ የተዘጋጀው ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ሥነ-ዘዴ መምህር ተኮር ከሆነው የማስተማር ዘዴ ተቃራኒ ነው። በንቃት የመማር ማስተማር ሁኔታ የሚመራ ተማሪውን ያማከለ ዘዴ ሲሆን ጥልቅ አስተሳሰብን የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅን፣ ራስን መገንዘብ እና ትርጉም ያለው እርምጃ አወሳሰድን አንድ ላይ የሚያጣምር ነው። ባዶውን እንስራ ለመሙላት ከመሞከር ይልቅ በዚህ የማስተማሪያ ዘዴ ላይ ማስተማር እንደ አበቦች እንዲያድጉና እንዲያብቡ የማድረግ ድርጊት ሆኖ ይታያል። ለሰላም ግንባታ የተዘጋጀው ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ሥነ-ዘዴ ተማሪዎች መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከዕድሜ አቻዎቻቸው፣ ከማኅበረሰቡ፣ ከኃይማኖታዊ ተቋማት፣ ኃይማኖታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከመንግሥት እና ከመገናኛ ብዙኃን በሚያገኙት ትምህርት ከትምህርት ቤት አጥር ውጭ ያለውን ዓለም ምን እንደሚመስል እንዲገነዘቡና እንዲያውቁ እንዲሁም

በኃውን ከመጥፎ መለየት እንዲችሉ በማድረግ በጥልቅ እንዲያስቡና ምላሽ ሰጪ መሆን እንዲችሉ ያበረታታቸዋል።

**ሥዕል 7፦ የተለያዩ የማስተማር ዘዴ ሐሳቦች**



ምንጭ፦ Wonderlane/Flicker & Patrick Standish and Creative Commo

በኢትዮጵያ ውስጥ ግጭትን በመከላከል እና በመቆጣጠር ረገድ ቤተሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ የሃይማኖት አባቶች፣ እና እምነት ላይ የተመረኮዙ ድርጅቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ብዙኃን መገናኛ እና መንግሥት ያላቸውን ሚና ከግምት ማስገባት ተገቢ ነው።

**ቤተሰብ**

ቤተሰብ ሰላም ወዳድ የሆኑ ልጆችን፣ ወጣቶችን እና በተለያዩ የሕይወት ዘርፎች የነገ መሪዎችን በሚገባ ቀርጾ በማሳደግ ረገድ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ግጭትን የመቆጣጠርና መከላከል ትምህርት በቤት ውስጥ ይጀምራል። በቤተሰብ ደረጃ ሰላማዊ ተግባቦት መኖር፣ በውይይት ወቅት ተራን መጠበቅ እና መከባበር፣ እርስ በርስ መደማመጥ እና በቤተሰቦች ውስጥ ወንዶች እና ሴቶች ልጆችን እኩል ማየት ሰላማዊ ማኅበረሰቦችን ለመገንባት እጅግ አስፈላጊ የሆነውን መሠረት ይጥላል። አመለካከትን በመቅረጽ፣ እሴቶችን እና እምነቶችን እንዲሁም ሰላም ወዳድ አስተሳሰቦችን ለልጆቻቸው በማስረጽ ረገድ ቤተሰብ እና ለወላጅነት የተሰጠው ኃላፊነት ከፍተኛ የሆነ ድርሻ አለው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ጥንታዊ ባህል ያላቸው አገሮች ውስጥ ግጭትን በመከላከል እና በመቆጣጠር ላይ ቤተሰብ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

**ማኅበረሰብ**

በኢትዮጵያ ውስጥ እርስ በርስ የሚረዳዱ እና አንዱ ለሌላው የሚጨነቁ ማኅበረሰቦች መኖር ግጭትን ለመከላከል፣ ሰላምን ለመፍጠርና ጠብቆ ለማቆየት አስፈላጊ ናቸው። ሁከትና ብጥብጥ ሲፈጠር በርካታ ቤተሰቦች አንድ ላይ ሊሰበሰቡ እና ሰላማዊ በሆነ ውይይት እና መስተጋብር ሊጠመዱ ይችላሉ። ማኅበረሰቡ በተጨማሪ ከዚህ ቀደም በጠላትነት ወይም በባላንጣነት ይተያዩ የነበሩትን አንድ ላይ የማምጣት ሥራ ላይ እና የቆሰሉትን፣ ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ ህጻናት እና ያለ ባል ወይም ያለ ሚስት የቀሩትን በማገዝ ሥራ ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ። ማኅበረሰቡ ከዚህ በተጨማሪ በግጭቶች ወቅት የወደሙ ትምህርት ቤቶችን፣ መንደሮችንና ጤና ጣቢያዎችን ዳግመኛ በመገንባት ሥራ ላይ በማገዝ በሰላም ግንባታ ሂደቱ ላይ ወሳኝ ሚናን በተጨማሪ ይጫወታል።

**ሃይማኖታዊ መሪዎች እና እምነት ላይ የተመረኮዙ ድርጅቶች**

አብዛኛዎቹ ሰዎች አሃዳዊ ሃይማኖቶችን በሚያመልኩባት ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት አባቶች እና እምነት ላይ የተመረኮዙ ድርጅቶች የግጭትን መፈጠር ሊቀንስ የሚችል የግብረገብ ትምህርት

በመስጠት እና በሥነ ምግባር የተማሩትን ትምህርት በማንፀባረቅ ሰላምን ለማጠናከርና ለማጎልበት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። የግጭት ሰለባዎች በግጭት ወቅት ካጋጠማቸው ድንጋጤና አለመረጋጋት እንዲያገግሙ የሚያስችላቸውን ተጨባጭ መንፈሳዊ እርካታና መረጋጋትን ይሰጣሉ፤ እንዲሁም ይቅርታ እና ዕርቀ ሰላምን ያበረታታሉ። ማኅበረሰቡ አንድ ላይ በሰላም እንዲኖር እና በጋራ የተሻለ ቀጣይ ሕይወትን እንዲገነባ የሚያስችለውን መማማሪያ መድረክ ይፈጥራሉ። ሆኖም ግን ሃይማኖት ዐመፅንና ብጥብጥን ለማባባስ እንደ ነዳጅ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችል መዘንጋት የለበትም። ለአብነት ያህል ምንም እንኳ ዐመፅና ብጥብጥ ከሃይማኖቱ ትምህርት ጋር የሚጻረር ቢሆንም ፅንፈኛው የአልሸባብ ቡድን በእስልምና ስም ዐመፅንና ግጭትን ያበረታታል።

## ትምህርት ቤቶች

ለሰላም ግንባታ በሚሰጥ ትምህርት አማካኝነት ትምህርት ቤቶች እና መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ፣ በትምህርት ቤቱ አካባቢ እና በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰላምን ባህል መገንባት ይችላሉ። አሠልጣኞች ሰላማዊ ክርክርን፣ የደቦ ሥራን፣ በወንዶች እና በሴቶች መካከል እኩልነትን ሊያበረታቱ እና ራሳቸው አርአያ ሊሆኑ እንዲሁም ከሁሉም ተማሪዎች ጋር በመከባበር መስተጋብር ሊፈጽሙ ይችላሉ። ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ በሥነ ጥበብ፣ በድራማ፣ በሥነ ግጥም እና በስፖርት አማካኝነት የታመቁ ውጥረቶችን የመፍታትት አቅም አላቸው። ትምህርት ቤቱ እና ቤተሰብ እንደ አንድ ማኅበረሰብ ሆነው በሚገናኙባቸው እና ውይይት የሚያደርጉባቸው ለተማሪዎቻቸው ቤተሰቦች ትምህርት ቤቶች ምቹ ቀናትን በመጠቀም ከተማሪዎች ቤተሰብ ጋር በመወያየት ማኅበረሰባቸውን ማጠናከር ይችላሉ (Engdaw, 2018, ገጽ 194-195)።

## ብዙኃን መገናኛ

ብዙኃን መገናኛ ግጭትን በመከላከል፣ በመቆጣጠር እና በመለወጥ ሂደት ላይ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። የብዙኃን መገናኛ ጠያቂ የሆኑ ክኅሎቶችን በማሳደግ ላይ እና ብዙኃን መገናኛ ካሉት የተለያዩ ቅርጾች ጋር ትርጉም ባለው መንገድ ተሳትፎ ማድረግ የሚያስችል ችሎታ ላይ ያተኩራል። የዚህ ቁልፍ ውጤቶች የሚከተሉትን ያካትታል፦

(1) የከፋ ግጭቶችን ለመከላከል፣ መፍትሔ ለመስጠት፣ ለመቆጣጠር እና ለመለወጥ በማኅበረሰብ ውስጥ ብዙኃን መገናኛ ያላቸውን ሚና እና ኃላፊነት መረዳት፤

(2) ብዙኃን መገናኛ ግዴታቸውን ሊወጡ የሚችሉባቸውን አስገዳጅ ሁኔታዎች ማክበር፤

(3) ከብዙኃን መገናኛ ኃላፊነት አንጻር የብዙኃን መገናኛን ይዘት ሂሳዊ በሆነ መንገድ መመርመር፤

(4) ሐሳብን በነጻነት ለመግለጽና ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ለማድረግ ብዙኃን መገናኛን መጠቀም እና

(5) በተጠቃሚ የቀረበ ይዘትን ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑ ክኅሎቶችን (አይሲቲዎችን) ጨምሮ መገምገም። የመረጃ መሠረተ ልማት ትምህርት ቁልፍ አባል ነገራት እነዚህን ያካትታሉ፦

- ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አስፈላጊ የሆነውን መረጃ መበየን እና በግልጽ መናገር፤
- መረጃ ያለበትን ማወቅ እና መድረስ፤
- መረጃን መመዘን፤
- መረጃን ማደራጀት፤

- *መረጃውን ሥነ ምግባርን ጠብቆ መጠቀም፤*
- *መረጃውን ለሚመለከታቸው ሁሉ ማድረስ እና*
- *መረጃን ወደ ሥራ ሂደት ለማስገባት የአይሲቲ ክኅሎትን መጠቀም።*

*ብዙኃን መገናኛ የግጭት ምንጭ ሊሆኑ ቢችሉም ለሰላም ግንባታም ዓይነተኛ መሣሪያ ሊሆኑ ይችላሉ። ከቴሌቪዥን በተጨማሪ የተለያዩ የራዲዮ ጣቢያዎች፣ አካባቢያዊ፣ ብሔራዊ እና የትምህርት ቤት ሰነዶች ለሚከተሉት ጥቅሞች ሊውሉ ይችላሉ፡-*

- *የሰላም ግንባታ ዜናን እና ቡድኖችን በአንድነት የሚያስተሳስር መረጃን ለማሠራጨት፤*
- *በመደበኛ፣ ኢ-መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ዘዴዎች አማካኝነት የሰላም ትምህርትን ለማስተማር፤*
- *ግጭትን ሊያስጀምሩ / ሊለኩሱ በሚችሉ ችግሮች ዙሪያ የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ እና*
- *ለሰላማዊ ተግባቦት ክኅሎቶችን ለመገንባት ይጠቅማሉ።*

***መንግሥት***

*መንግሥት ግጭትን በመከላከል እና መፍትሔ በመስጠት ረገድ እጅግ በጣም ትልቅ ሚና አለው። እንዲሁም የዜጎችን ደኅንነት የመጠበቅ ኃላፊነት እና የሕግ የበላይነትን የማስከበር ግዴታ አለበት። ከዚህ በተጨማሪ ግጭትን ለመከላከል እና መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችሉ ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ፖሊሲዎችን በማውጣትና ተፈጻሚ በማድረግ ረገድ መንግሥት በጣም አስፈላጊ ነው።*

*ለግጭት አፈታት መንግሥት የሚከተለው ዘዴ ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ መፍትሔ ከማፈላለግ ይልቅ አስቀድሞ በመከላከል ላይ ያተኮረ መሆን አለበት። መንግሥት የግጭቶችን መሠረታዊ እና ቁልፍ ምክንያቶች መፍትሔ ከመስጠት መቦዘን የለበትም እንዲሁም ችግርን ለመፍታት የተሳሰተ ዘዴ ከመጠቀም መቆጠብ አለበት። በኢትዮጵያ ውስጥ ግጭትን ለማስቀረት ኃይልን መጠቀም እንደማያዋጣ ለማሳመን በርካታ ምክንያቶች ሲንሸራሸሩ ቆይተዋል። ለምሳሌ አንዳንድ ግጭቶችን ለመከላከል በተወሰዱ ኦፕሬሽኖች ላይ መንግስት ፖሊስ ወይም ወታደሮችን በሚጠቀምበት ወቅት አግባብነት የሌለው የኃይል እርምጃ ከወሰደ በዜጎችና በመንግስት መካከል ያለውን ክፍተት የበለጠ እንዲሰፋ ያደርገዋል። እንደ አገልግሎት አቅራቢ፣ ጸጥታን፣ መሠረታዊ ሰብአዊ መብቶችን እና የሕግ የበላይነት አስከባሪነትን ጨምሮ የመብቶች ዋስትና ሰጪ ሆኖ ከመታየት ይልቅ መንግሥት እንደ ጠላት ሆኖ ሊታይ ይችላል። በመሆኑም በግጭት መከላከል እና መፍትሔ አሰጣጥ ላይ መንግሥት የሚኖረው ሚና ጥንቃቄ የተሞላው እና ሚዛናዊ መሆንን ያሻል። ችግሮቹ የተሳሰሩ እና አካታች እንደመሆናቸው ሁሉን አቀፍ እና የተቀናጀ አስታራቂ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል* (Engdaw, 2018, ገጽ 194)።1

1 እባክዎ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ይህንን ያንብቡ፡- *Peace Education for Youth Violence Prevention Africa: Holistic and Integrated Approach of Ethiopian Schools*, 2018.

# ምዕራፍ 2፦የሰላም ግንባታ

## 2.1 የሰላም ግንባታ እና የሰላም ትምህርት ግንኙነት

የሰላም ግንባታ እና የሰላም ትምህርት ከፍተኛ የሆነ ትስስር አላቸው። የሰላም ግንባታ አዳዲስ ግንኙነቶችን እና ትስስሮችን የመገንባት ወይም ሰላምን መልሶ የመገንባት እና ነባሮቹን የማዘመን ሂደት ነው፡፡ የሰላም ግንባታው ወይም የመልሶ ግንባታው ሂደት ፍትሕን እና ሰብአዊ መብቶችን ያካተተ ነው። ለምሳሌ ከዚህ ቀደም የነበራቸውን ጤናማ ግንኙነት ወደ ነበረበት በመመለስ ከዚህ በፊት ተጋጭተው የነበሩ ወገኖችን በማስታረቅ ወይም አስታራቂ ፍትሕን በመጠቀም ሰላማዊ ግንኙነት በግለሰቦችና በማህበረሰቡ ዉስጥ እንዲሰፍን ማስቻል ነው፡፡

የሰላም ግንባታ አስከፊ ግጭት ከመከሰቱ በፊት ወይም ግጭቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሊከናወን ይችላል። የሰላም ግንባታው ሂደት ሥር የሰደዱ ወይም መዋቅራዊ የግጭት ምክንያቶችን መፍትሔ በመስጠት ሰላማዊ አብሮነትን ያበረታታል። በአጭሩ የሰላም ግንባታ ሂደት በአካባቢና በብሔራዊ ደረጃ ሰላማዊ እና የተረጋጉ ማኅበረሰቦችን ከመገንባት አንጻር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

የሰላም ትምህርት የሚከተሉትን ሂደት እና ትግበራ ያካትታል፡-

ሀ) ሰላምን ለማስፈን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለይቶ ማወቅ፤

(ለ) ግጭቶችን በመከላከል እና በማስወገድ ሰላማዊ የመፍትሔ አሰጣጥ ክህሎትን ማሳደግ እና

(ሐ) ሰላማዊ አመለካከትን ማጎልበት ናቸው።

እነዚህ ክህሎቶች ከቤተሰብ፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከአቻ ለአቻ ትምህርት፣ ከማህበረሰቡ እና ከብዙኃን መገናኛ በመደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ መንገድ ይገኛሉ። የሰላም ትምህርት የሰላም ግንባታ ዋነኛው አካል ነው። ሰላምን ለመገንባት ይቻል ዘንድ አንድ ሰው ሰላማዊ በሆነ መንገድ መልዕክቱን ማስተላለፍን፣ ሌሎችን ማክበር፣ የሌሎችን ሀሳብ ለመስማት ዝግጁ መሆን፣ በጥልቅ ማሰብን እና ምላሽ ሰጪ መሆንን መማር መቻል አለበት። እነዚህ ክህሎቶች ለሰላም ትምህርት መሰረታዊ መርሆዎች ናቸው።

## 2.2 የሰላም ግንባታ መርሆዎች እና ማዕቀፎች

የሰላም ግንባታ መርሆዎች እና ማዕቀፎች ሰዎች ላይ ያተኮረ፣ መልካም ዝምድና እና ግንኙነትን የሚገነባ እና አሳታፊ የሆነ ሂደትን የሚከተል አቀራረብ ነው። እነዚህ መርሆዎች እና ማዕቀፎች በሰላም አብሮ መኖርን ማበረታታት ላይ እና የግጭትን መዋቅራዊ ምክንያቶች መፍትሔ መስጠት ላይ ያተኩራሉ። በ Joan B. Kroc (2008) ባዘጋጀው ጹሁፍ ላይ ጠቅለል ብሎ እንደቀረበው ሰላም ግንባታ የሚከተሉትን መርሆች ያካትታል፡-

- የሰብዓዊ መብቶች እና ሰብዓዊ ፍላጎቶችን፣ እሴቶች፣ ግቦች፣ እና ቁርጠኝነትን ያቀፈ ነዉ፡፡
- ግጭትን ከመፍታትም ያለፈ ነው፤
- መዋቅራዊ ኢ-ፍትሐዊነት እና ግጭቶችን ችላ ብሎ ማለፍ አይችልም፤
- እርስ በርስ በመረዳዳት፣ በአጋርነት እና ግጭትን አስቀድሞ በመከላከል ላይ የተመሠረተ ነው፤
- በግንኙነት ክህሎት ላይ የተመሰረተ ነው ፤

- ከግጭቱ ጀርባ ያሉትን ተዋናዮች እንዲሁም ባህሎች፣ ታሪኮች፣ የችግሩ ዋነኛ ምክንያቶች እና በፍጥነት ለሚከሰቱ ሁኔታዎች ውስብስብ ትንታኔ አሰጣጥ ሂደትን ያካትታል፤
- ሰዎች በአዳዲስ መንገዶች መስተጋብር የሚፈጥሩባቸው፣ ተሞክሮዋቸውን የሚያሻሽሉበትን እና አዳዲስ የተግባቦት ዘዴዎችን ይፈጥራል፤
- በጥቃት ምክንያት የተፈጠረን ሥነ ልቦናዊ ቁውስ ይፈውሳል፣ ፍትሕን ያበረታታል እንዲሁም ዝምድናዎችን ያጠናክራል፤
- በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ግጭቶችን ለመፍታት አቅምን እና ግንኙነቶችን መገንባት ይጠይቃል፤
- የሰላም ግንባታ ተግባርና ሂደት ውስብስብ እና በርካታ ተዋንያን ያሉት ነው።

**ሣጥን 1፦ የሰላም ግንባታ መርሆዎች እና ማዕቀፍ ተምሳሌታዊ ታሪክ**

አንድ ቀን በኢትዮጵያ ውስጥ አንዲት ሴትዮ በእግሯ እየሄደች እያለ ከአንድ ግንባታ ሥራ ከሚሠራበት ቦታ ላይ ደረሰች እና በቦታው ሦስት ሠራተኞች ተመሳሳይ ስራ ሲሠሩ ተመለከተች። ሁሉንም አንድ በአንድ ምን እየሠሩ እንደሆነ ጠየቀቻቸው። የመጀመሪያው «ድንጋይ እየፈለጥኩ ነው» አላት። ሴትየዋ ወደ ሁለተኛው ሄደችና ተመሳሳይ ጥያቄ ጠየቀችው። ሁለተኛውም «ለዕለት እንጀራዬ እየሠራሁ ነው» አላት። ሴትየዋ በመቀጠል ወደ ሦስተኛው ሄደችና ተመሳሳይ ጥያቄ ጠየቀችው። ሦስተኛውም «ሆስፒታል እየሠራሁ ነው» ብሎ መለሰላት፡፡

ከዚህ የምናገኘው ትምህርት አንዳንድ ጊዜ እጃችን ላይ ባለው ከባድ ሥራ ላይ ብቻ በማተኮር ድንጋይ እየፈለጥን እንደሆንን ብቻ እናስባለን። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለራሳችን እና ለቤተሰባችን ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን እንዴት የዕለት እንጀራችንን ማግኘት ላይ እናተኩራለን። አንዳንድ ጊዜ ሥራችን ከአንድ የበለጠ ትልቅ የሆነ እና ውጤቱም ለሁሉም የሚጠቅም በርካታ ሌሎች ሠራተኞችን የሚያሳትፍ እንደ ሆስፒታል መገንባት የመሰለ ራእይ እንዳለ በተጨማሪ እንረዳለን።

## 2.3 የሰላም ባህልን መገንባት

የባህልን ምንነት መረዳት ተማሪዎች የሰላም ባህልን እንዲገነቡ ያስችላቸዋል። ዩኔስኮ (UNESCO: 2001) ባህልን «የማኅበረሰብን ወይም ማኅበራዊ ቡድን ልዩ ምሁራዊ፣ መንፈሳዊ፣ ቁሳዊ እና ስሜታዊ መገለጫ ባሕሪያት ስብስብ» በማለት ይገልጸዋል። ባህል በትምህርት የሚገኝ፣ የሚጋራ እና ትዕምርታዊ ነው። በሥነ ጥበብ እና በሥነ ጽሑፍ፣ ልማዶች፣ የእሴት ሥርዓቶች፣ ወጎች እና እምነቶች ውስጥ ይገለጻል።

የሰላም ባህል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ያካትታል፦

(1) እሴቶች፣

(2) አመለካከቶች እና

(3) ባሕሪያት ናቸው።

የሰላም ባህል መሠረታዊ መርሆች የሚባሉት ደግሞ፡-

(1) ነጻነት፣

(2) ፍትሕ፣

(3) ዴሞክራሲ፣

(4) ሰብአዊ መብቶች፣

(5) መከባበር እና

(6) አንድነት ናቸው።

የሰላም ባህልን መገንባት ለግጭት መፈጠር ዋነኛ መንሥዔ ለሆኑ ምክንያቶች ዕልባት በመስጠት፣ በውይይት እና በድርድር ችግሮችን በመፍታት ግጭትን ለመከላከል ያግዛል።

የሰላም ባህል በትምህርት ሊገኝ እና ሊጎለብት ይችላል። ተማሪዎች በአክብሮት እና በሰላማዊ መንገድ ልዩነቶቻቸውን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ ሲማሩ የሰላም ባህልን የመገንባት አቅማቸውን ያሳድጋሉ። ተማሪዎች በውይይቶች፣ ምክክሮች፣ እና ድርድሮች ላይ ሲሳተፉ የሰላም ባህልን መገንባት ይጀምራሉ። የትምህርት ባለሙያዎች እንዲህ ያሉትን ድርጊቶች ሲያስተምሩ እና ሲያበረታቱ ይደጋገም እና የዕድሜ ልክ ልማድ ይሆናል።

በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ሌሎች ሀገሮች ሁሉ የሰላም ባህል ፅንሰ ሐሳብ የመንፈሳዊ ዕሴቶች፣ የዕምነት ሥርዓቶች እና ቅርጾችን ያካትታል። በተጨማሪም የሀገር በቀል ዕውቀቶችን፣ ቴክኖሎጂዎችን፣ ባህሎችን እና ሥነ ጥበባዊ ሐሳብ መገለጫ መንገዶችን ያካትታል። የሰላም ባህል የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የባህል ብዝኀነት፣ አንድነት፣ ግጭቶችን የመጠየፍ እና ዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብን በመገንባት ዕኑ ፍላጎት ባለበት ቦታ ሁሉ የሰላም ባህል ይኖራል፡፡

**ኡቡንቱ፡-** ኡቡንቱ የባንቱ ቃል ሆኖ ትርጉሙም «ሰብዓዊነት ለሌሎች» የሚል ሆኖ በአጠቃላይ የአፍሪካን ባህል እና በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያን ባህል በመረዳት ሂደት ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በአርብቶ አደሩ ማኅበረሰብ ውስጥ የመሬት ባለቤትነት የተመሠረተው በወል ይዞታ ወይም በአያት ቅድመ አያት ንብረትነት ነው፡፡ ይህም በአርሶ አደሩ ማኅበረሰብም ተመሳሳይ እንደመሆኑ ኢትዮጵያ የተለያዩ ማኅበረሰቦች በጋራ የሚኖሩባት አገር ተደርጋ ትገለጻለች።

እንዲህ ያለው ጠንካራ ማህበራዊ ትስስር በማህበረሰቡ ውስጥ መኖር በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሰላም ባህል እንደ ማኅበራዊ ጥረት፣ ተግዳሮት እና ስኬት አድርጎ ማየት ጠቃሚ ነው።

**ሣጥን 2፦ በዴዝሞንድ ቱቱ (1999) በ "No Future without Forgiveness" ላይ እንደ ተገለጸው**

'ኡቡንቱ በምዕራባዊያን ቋንቋ ለመተርጐም በጣም አስቸጋሪ የሆነ ቃል ነው። የሰዎች ውስጣዊ የሆኑ ነገሮችንም ይናገራል፡፡ለሆነ ሰው ከፍተኛ አድናቆታችንን ለመግለጽ ስንፈልግ «ዩ፣ ዩ ኖቡንቱ» ("Yu, u nobuntu") እንላለን ትርጉሙም «ስማ፣ እገሌ ኡቡንቱ» አለው እንደ ማለት ነው። ይህ ብቻ ግን አይደለም አንተ ደግ ነህ፣ አንተ እንግዳ ተቀባይ ነህ፣ አንተ ከሰው ጋር ተግባቢ ነህ፣ አንተ ለሰው ታስባለህ፣ ያለህን ታጋራለህ እና ሩህሩህ ነህ ማለትም ነው። ይህም ማለት «የእኔ ሰው መሆን የሚሟላው ወይም የሚያያዘው በአንተ ሰው መሆን ላይ ነው» እንደ ማለት ነው። እየኖርን ያለነው በሕይወት ትስስር ውስጥ ነው፡፡ «አንድ ሰው ሰው የሚሆነው በሌሎች ሰዎች በኩል ነው» እንደሚባለው «አስባለሁ ስለዚህ እኔ፣ እኔ ነኝ» ማለት አይደለም፡፡ እኔ ማለት አንተ ማለት ነኝ። እኔ ያለ አንተ አንተ ያለ እኔ እንደማለት ነው፡፡


«ሰው ነኝ፤ ምክንያቱም ከሰዎች ዘንድ ቦታ አለኝ። እሳተፋለሁ፤ ያለኝን አካፍላለሁ።» ኡቡንቱ ያለው ሰው እሱ ወይም እሷ የአንድ ትልቅ ሙሉ አካል ክፋይ መሆኑን ከማወቁ የተነሣ እሱ ወይም እሷ ተገቢ የሆነ የራስ መተማመን መንፈስ ስላላቸው ግልጽ እና ሌሎችን ለመርዳት ዝግጁ ናቸው፤ ከሌሎች ጋር ተስማምተው ይኖራሉ፤ ሌሎች አቅም ስላላቸው እና ጥሩ በመሆናቸው ስጋት አይገባቸውም እና ሌሎች ሲዋረዱ አብሮ የመዋረድ ስሜት ይሰማቸዋል፤ ሌሎች አካላዊ ስቃይ ሲደርስባቸው ወይም ሲጨቆኑ ወይም ከማንነታቸው ውጭ ዝቅ ተደርገው ሲታዩ አብረው ሕመሙ ይሰማቸዋል» (ገጽ 31-32)።

## 2.4 ሰላም ግንባታ፣ ማንነት እና ብዝኃነት

ኢትዮጵያ ውስጥ ማንነት አንድ ሊያደርግ ወይም ሊከፋፍል ይችላል። ሰዎች በሚጋሯቸው ጥሩ ነገሮች ዙሪያ እንዲሰባሰቡ ወይም በልዩነታቸው ላይ ተመርኩዘው እንዲለያዩ ሊያደርጋቸው ይችላል። ማንነት በበርካታ ገጽታዎች ላይ የሚመረኮዝ ነው። ማንነት አንድ ግለሰብ እኔ ነኝ ብሎ ከሚያስበው ሌሎች እንዴት ግለሰቡን እንደሚመለከቱት እና ግለሰቡ ሌሎች እንዴት አድርገው ይገምቱኛል ብሎ የሚያስበው ነው። ለምሳሌ፦የደቡብ ሱዳን በኢትዮጵያ የስደተኞች ካምፕ ውስጥ ያለ ስደተኛ ሕፃን ራሱን እንደ ወንድ ልጅ፣ ወላጆቹን በሞት ያጡ ህፃን ፣ የዲንካ ጐሣ ተወላጅ እና እንደ ጥሩ ተማሪ አድርጎ ሊያስብ ይችላል። ሌሎች ደግሞ ጥሩ ቁመና ያለው የሱዳን የወደፊት ዕጣ ፈንታ እንደሆነ ወይም ሸክም እንደሆነ አድርገው ሊያስቡት ይችላሉ። በሌላ በኩል ህፃኑ ሌሎች ሰዎች እሱን እንደ ኅበዝ፣ ወጣት እና ስደተኛ አድርገው እንደሚመለከቱት ሊያስብ ይችላል።

አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ብዙውን ጊዜ ከአንድ በላይ ማንነት ይኖረዋል። ሆኖም ግን አንድን ግለሰብ ወይም ቡድን በአንድ ማንነቱ ላይ በመመርኮዝ እንዲህ ነው ብሎ መፈረጅ እና በተለየው ፍረጃ መሰረት ያልተሟላ ወይም ከፊል ግንዛቤ ይዞ አሉታዊ ፍረጃ ከሆነ የግለሰቡን ወይም ግለሰቦችን ስብዕና ሊነካ እና የግጭት መንሥኤ ሊሆን ይችላል።

ሥዕል፡8 የማንነት ቻርት




ማንነት አንድ ግለሰብ ምን ያህል ከሌሎች እንደሚለይ እና እንደሚመሳሰል ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን ብዝኃነት ደግሞ ከሌሎች መካከል እንደ ጐሣ፣ ሥርዓተ-ጾታ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መደብ፣ ዕድሜ፣ አካላዊ ችሎታ፣ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ፣ የፖለቲካ አመለካከት በመሳሰሉ ልዩነቶች እና ተመሳሳይነቶች ላይ ያተኩራል። በኢትዮጵያ ዓውድ ብዝኃነት እንደ ጥንካሬ ምንጭ ሆኖ ሊታይ ይገባዋል። ሆኖም ግን ልዩነቶችን በሚፈሩ ወይም ለሚጠሉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የዐመፅ ወይም ግጭት ምንጭ ሊሆን ይችላል። ብዝኃነት የሰላም ግንባታ መሠረት በመሆኑ ጥንካሬን እንድናሰባስብ እና ለልዩነቶች አክብሮት እንዲኖረን ስለሚያደርገን ምርጥ ሐሳብ ነው።

ከ83 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ባሉባት ኢትዮጵያ ዓውድ ውስጥ ማንነት እና ብዝኃነት አንዱ ከሌላው ጋር የተያያዙ ናቸው። በቀላል አገላለጽ እንደ ቋንቋቸው፣ ኃይማኖታቸው፣ የትምህርት ደረጃቸው፣ ጾታቸው እና ጐሣቸው አንድ ላይ የሚቀመጡ የተለያዩ የማንነት ቡድኖች ብዝኃነት ያለውን ማኅበረሰብ ይፈጥራሉ።

እነዚህ ብዝኃነት ያላቸው ቡድኖች አንድ ላይ ሲሠሩ፣ አንድ ላይ ሲኖሩ እና ለጋራ ግብ ሲተባበሩ ለሰላም ግንባታ በአዎንታዊ መልኩ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ። በሣጥን 3 የቀረበው የስኬት ታሪክ በኢትዮጵያና ኬንያ ድንበር ላይ የሚገኙት ቦረና - ገርባ በመባል የሚታወቁት ማኅበረሰቦች እና አንድ ብዝኃነት ያለውን ማኅበረሰብ የፈጠሩት የተለያየ ማንነት ያላቸው እነዚህ ቡድኖች የተለያዩ ባለ ድርሻ አካላትን በማሳተፍ እንዴት ሰላም ለመገንባት እንደቻሉ በአጭሩ ይቀርባል።

## ሣጥን 3፦ የስኬት ታሪኮች

**ምሳሌ 1፡- ከኢትዮጵያና ኬንያ ድንበር የተገኘ የሰላም ግንባታ ምሳሌ**

በባህላዊ መሪዎች እና ሽማግሌዎች የተጠነሰሰው ዕርቀ ሰላም እና በሴት ሰላም መልእክተኞች፣ በወጣት አርብቶ አደሮች እና በኬንያ እና በኢትዮጵያ መንግሥት የተጠናከረው እና የተደገፈው ስድስት ዓመታትን የፈጀ የሰላም ማስፈን ሂደት በ2009 በኢትዮጵያና ኬንያ ድንበር አካባቢዎች ላይ የሚገኙ ቁጥራቸው ግዙፍ የሆኑ የገጠራማ የቦረና እና የገርባ አርብቶ አደር ማኅበረሰቦችን ለማስታረቅ ችለዋል (Scott-Villiers et al. 2011)። ከስምምነት ላይ የተደረሰበት የሰላም ስምምነት በደረሰው ጉዳት የሥነ ልቦና ጉዳት ለደረሰባቸው እና ወደ ቤታቸው ለሚመለሱ የተፈናቀሉ ሰዎች እና ስደተኞች የይቅርታ እና አስታራቂ ፍትሕ ጭብጦችን ያካተተ ነበረ፤ በዚህ ድርድር መሰረትም ድርቅ በሚፈጠርበት ጊዜ ለግጦሽ የሚሆን ሰፊ ቦታን ዳግመኛ ክፍት እንዲሆን አስችሏል።

በተደጋጋሚ በተደረጉ ከፍተኛ ባለሥልጣናት የተገኙባቸው ስብሰባዎች አማካኝነት የኬንያ እና የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣናት የፖሊስ ሥራ እና ፍትሕ የማስከበር ሥራን በተመለከተ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ያላቸውን አቀራረብ በንቃት በመደገፍ የመንግሥት እና ባህላዊ ሥልጣኖችን ቅንጅት ጥቅም ላይ እንዲውል አድርገዋል። የሰላም ሂደቱን ዋነኛ ጭብጦች በአጭሩ ለማስቀመጥ ያክል ሽማግሌዎቹ ለስኬት ያበቋቸውን አራት አንኳር ነጥቦችን አስቀምጠዋል፡፡ እነርሱም፦

1) ሞራላዊ የማሳመን ሥራ፣
2) ሕግ፣
3) ከዜጎች ጋር መልእክትን በአግባቡ መለዋወጥ እና
4) የዜጎች እና የፖሊስ ክትትል ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ የተገኘው ሰላም ሁሉን አቀፍ እንዳልሆነ እና ፖለቲካዊ ቁርሾ እንዳለ፤ በከተማዎች ውስጥ ያሉ ወጣቶች መገለላቸውን አስታውሰው አሁንም ድረስ በተለይ በሁለቱ ማርሳቢት እና ሞያሌ ከተማ ማዕከላት ውስጥ ግጭት ሊፈጠር የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ አምነዋል።

በክልሉ ውስጥ በሚገኙ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እንደተመሩ በርካታ ከውጭ የተቀነባበሩ የግጭት አፈታት ጥረቶች ሁሉ ተመሳሳይነት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ሂደት የተጠነሰሰው እና የተመራው በባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ ሲሆን ሽማግሌዎቹም ከራሱ ከማኅበረሰቡ ውስጥ በወጡ የቦረና እና የጋብራ የሀገር ሽማግሌዎችን ማኅበራዊ ትንታኔዎችንም ተጠቅመዋል። ዕርቀ ሰላሙም በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ የመወሰን ዝንባሌ ካላቸው ተመሳሳይ ከሆኑ የሰላም ግንባታ ሂደቶች በተለየ መልኩ የቦረና - ገብራ የሰላም ግንባታ ሂደት ሰላም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ ሦስት ችግሮችን ለመቅረፍ ያለመ ነበር እነሱም፦

- መንግሥታዊ አስተዳደር፣
- ከፋፋይ ፖለቲካ እና
- ማኅበራዊ ስምምነትን ማጣት ናቸው።

ምንጭ፦ Pavanello & Scott-Villiers, 2013

**ምሳሌ 2፡- ኢትዮጵያ ውስጥ ፖለቲካዊ ተልዕኮ ያላቸውን ግጭቶችን ማምከን**


ኢትዮጵያ ውስጥ በቅርብ ጊዜ ባጋጠመ የስኬት ታሪክ የጋሞ የአገር ሽማግሌዎች እና የጋሞ ብሔር ተወላጆች አርባምንጭ ላይ አጋጥሞ የነበረውን ውጥረት በማርገብ በአንዳንድ የኦሮሞ ተወላጆች ባለቤትነት ተይዘው የነበሩ ሱቆችን እና ንብረቶችን ለማጥቃት የፈለጉ ተቃዋሚ ሰልፈኞችን ጥቃት እንዳይፈጽሙ

አድርገዋቸዋል፡፡ ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ በርካታ የጋሞ፣ የኦሮሞ እና የሌላ ብሔር ተወላጆች የተገደሉበት እና በሺዎች የሚቆጠሩ እንዲሰደዱ ያደረገ ግጭት መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በፊንፊኔ ልዩ ዞን ከዋና ከተማዋ ከአዲስ አበባ ትንሽ ወጣ ብላ በምትገኘው ቡራዩ ከተማ ውስጥ ከጀርባው የፖለቲካ ተልዕኮ የያዘ ግጭት በመከሰቱ ነበር፡፡

ይህን መነሻ በማድረግ ጋሞ ዞን የአርባ ምንጭ ከተማ ተቃዋሚ ሰልፈኞች በቡራዩና አካባቢው በደረሰው ጥቃት የበቀል እርምጃ ለመውሰድ እና በአርባ ምንጭ ውስጥ ያሉ የኦሮሞ ተወላጆችን የንግድ ሥራ ድርጅቶችን ለማጥቃት ሲንቀሳቀሱ የጋሞ አባቶች በእጆቻቸው እርጥብ ሣርና ቅጠል በመያዝ ጣልቃ በመግባት ወጣቶቹ ንግድ ድርጅቶችን እንዳያጠቁ ለምነዋቸዋል፡፡በዚህ መልኩ ሽማግሌዎቹ ሊፈጠር የነበረውን ጥቃት አምክነውታል። በርካታ ኢትዮጵያውያን በጋሞ አባቶች ጥበብና አስተዋይነት የተደነቁ ሲሆን ይህም በጥሩ ምሳሌነት በመነገር ላይ ይገኛል።

## ሥዕል 9 የጋሞ አባቶች

የኦሮሞ ንግድ ድርጅቶችን እንዳያጠቁ ለመኗቸው፤ በዚህም መልኩ ሽማግሌዎቹ ሊፈጠር የነበረውን ዐመፅ አምክነውታል። በርካታ ኢትዮጵያውያን በጋሞ አባቶች ጥበብና አስተዋይነት የተደነቁ ሲሆን ይህም በበርካቶች እንደ ስኬት ታሪክ ሲወራ ነበር።



# ምዕራፍ 3፦ የግብረብ ዕሴቶችን ማጎልበት

## 3.1 የሰላም ትምህርት እና ግብረገብ

የሰላም ትምህርት ለተማሪዎች/ለሠልጣኞች ዕውቀትን፣ ክኅሎትን እና አመለካከትን ለማሳደግ የሚችሉባቸውን ዕድሎች ይፈጥርላቸዋል። በተጨማሪም ግጭቶች ወደ ዐመፅ ደረጃ እንዳይሸጋገሩ ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑትን እሴቶች እንዲተገበሩ ያበረታታል፡፡ እንዲሁም ከሌሎች ጋር ሰላማዊ የሆኑ መንገዶችን በመጠቀም በትብብር እና በአንድነት በመሥራት ወደ ሰላማዊ ሁኔታ እንዲለውጧቸው ያስችላቸዋል። የሰላም ትምህርት ተማሪዎች/ሠልጣኞች ከራሳቸው እና ከሌሎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲሁም በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን መስተጋብር እንዲገነዘቡት ያስችላቸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በየጊዜው እርስ በርስ በሚያገናኙ እና አንዱ ከሌላው ጋር እየተረዳዱ በሚሄዱ የማኅበረሰቦች ስብስብ እና ብዝኃነት ውስጥ እንኖራለን። ከሌሎች ጋር የሚኖሩን ሁሉም መስተጋብሮች መሠረታዊ እምነትን ከግምት ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡ እርስ በራሳችን የመረዳዳትና የመከባበር ኃላፊነት አለብን። ይህም ለ«ሌላው» ሰው ምላሽ መስጠት እና የእኛን የጋራ ሰብአዊነት ከፍ አድርጎ መያዝን ያካትታል። ሕይወታችን ከሌሎች ጋር እኛ በምናደርገው መስተጋብሮች አማካኝነት ቅርጽ የሚይዝ ነው፣ የእነርሱም እንደዚሁ፡፡ ይህም መከባበርን፣ ኃላፊነት መውሰድን እና አንዱ ለሌላው ከራስ ወዳድነት የጸዳ እንክብካቤ ማድረግ ወይም ፍቅር መስጠትን ይጠይቃል።

በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ላይ ኢትዮጵያዊያን ሥነ ምግባራዊ ተግዳሮቶች፣ ኢፍትሐዊነት እና ግጭቶች ያጋጥሙናል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን የእኛን አስተሳሰብ እና ድርጊት ፈተና ውስጥ የሚከቱና ምን መወሰን እንዳለብን ግራ የሚያጋቡን ተግዳሮቶች እየገጠሙን ይገኛሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች በግጭት ምክንያት ከቤታቸው በመፈናቀላቸው በአዳዲስ ማኅበራዊ ሥነ ምግባር እና ሥርዓት ውስጥ እንዲኖሩ ይገደዳሉ። አንዳንድ ሰዎች ግጭትን እና መድልዎን በየቀኑ ስለሚጋፈጡ ምንም አቅም የሌላቸው ሆነው ሊሰማቸው ይችላል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ አብረው የሚኖሩበት መንገድ ላይ እና ከሌሎች ጋር በሚጋሩት ቦታ ላይ ጫና በሚፈጥር መልኩ ድህነት እና የእኩልነት አለመኖር ችግር ያጋጥማቸዋል። እንደ ዓለም ዓቀፋዊ ዜጋነታችን የሚገጥሙንን የሥነምግባር ጉድለቶችን እየተጋፈጥን በራሳችን ማህበረሰብ ውስጥ ላሉ ሁኔታዎች የሚጠበቅብንን የሥነምግባር ፍላጎት ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ሥነ ምግባር ግንኙነትን የተመለከተ ሲሆን ሰብአዊ እሴቶችን በማስረጽ የማኅበረሰብ አባልነት ስሜትን ለመንከባከብ እና ለመገንባት ያስችላል፡፡ ለሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች፣ ኢፍትሐዊነት እና ግጭቶች በፍጥነት ምላሽ በመስጠት የተሰበሩ ግንኙነቶችን ወደ ነበሩበት ሰላማዊ ግንኙነት መመለስን ይጠይቃል። ሥነ-ምግባር የትኛው ትክክል ወይም ስህተት እንደሆነ የመበየን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ይልቁኑም በጥልቀት የሰው ልጅ ክብር እንደተጠበቀ እና እንደተከበረ የማረጋገጥ ብሎም አንዳችን ላንዳችን በህይወት ዉስጥ ያለን ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥር ሂደት ነው፡፡

ሥነ-ምግባር የሰላም ትምህርት እምብርት ነው። በመሆኑም የሰላም ትምህርት ተማሪዎች/ ሠልጣኞች እርስ በእርስ ባላቸው ግንኙነት አንዳቸው ላንዳቸው ጥንቃቄ በማድረግ ሃይማኖታቸው እና ባህላዊ እምነታቸው ወይም ሕጋዊ ግዴታዎችን ከግምት ሳያስገቡ በሥነ ምግባር ላይ በመመርኮዝ ማድረግ ያለባቸውን እያደረጉ በማህበረሰቡ ዉስጥ ለሚገኙ የግብረገብ ዕሴቶች ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሰላም ትምህርት ተማሪዎች/ሰልጣኞች በመከባበር እና ለብዝሀነት ዕውቅና በመስጠት በመካከላቸው ሰላማዊ ግንኙነት እንዲገነቡ ያግዛቸዋል ፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ ሥነ-ምግባራዊ መርሆችና ዕሴቶችን ማወቅ ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ በሰላም አብሮ ለመኖር ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ሰላም ማለት የጦርነት እና የግጭት ያለ መኖር ከሚል ተራ ትርጉም በላይ ነው። ስለሆነም የሰብአዊ መብቶችን በማክበር እና ለሁሉም ሰው ሰብአዊ

ክብርን በመስጠት ለኢፍትሐዊነት እና መድልዎ ተገቢውን አጸፋዊ ምላሽ ለመስጠት በበቂ ዕውቀት ልንዘጋጅ ይገባናል። በመሆኑም የሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

- የሁሉም ሰው ክብር መጠበቁን በማረጋገጥ ኢትዮጵያዊያን አብሮ መኖር ላይ እና አብሮነት ላይ ለሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ምን ዓይነት ምላሾችን ይሰጣሉ?
- ልዩነቶችን ዕውቅና በመስጠት እና በማክበር ሂደት ላይ ተማሪዎችን/ሰልጣኞችን ምን ዓይነት ምላሽ ይሰጣሉ?
- በተማሪዎች/በሠልጣኞች ውስጥ ሥነ ምግባራዊ እና በጥልቀት ማሰብን እሴቶች እና ብቃቶችን እንዴት ማጎልበት እንችላለን?

አሰልጣኙ ተማሪዎች/ሰልጣኞች በተገቢው ሁኔታ እንዲወያዩበት ከላይ የተቀመጡትን ጥያቄዎች ያቀርብላቸዋል።

## 3.2 ሰብዓዊ መብቶችን መሠረት ያደረገ የሰላም ትምህርት አቀራረብ

የሰላም ትምህርት የሰው ልጆችን ክብር እና ሰላምን በማስጠበቅ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የሰላም ትምህርት የሰብዓዊ መብቶችን    የጥበቃና ደህንነት አካታችነት ለማረጋገጥ ያገለግላል፡፡

**ሣጥን 4፦ ሰብአዊ መብቶችን መሠረት ያደረገ አቀራረብ ምንድን ነው?**

የሰላም ትምህርት በሰብአዊ መብቶች እና ሰብአዊ ክብር ፅንሰ ሐሳቦች ላይ የተመረኮዘ ነው። ሰብአዊ ክብር የሰብአዊ መብቶች አንዱ አካል ነው፡፡ ሰብአዊ መብት ከስብዕና ክብር ተለይቶ ሊታይ የሚችል አይደለም። ሰብአዊ ክብር ወደር የማይገኝለት እንደመሆኑ ሰብአዊ መብቶች በጭራሽ በሕጋዊ መንገድ ሊነጠቁ አይችሉም። ሰብአዊ መብቶች ለሁሉም እኩል የሚደርሱ መብቶች ሲሆኑ ሁሉም የሰው ልጆች ምንም ዓይነት የባህል ልዩነት ቢኖራቸውም እኩል መሠረታዊ መብቶች አሏቸው። በግፍ ማሰቃየት፣ ሰብአዊ ያልሆነ አያያዝ፣ ባርነት፣ በዝባዥ የሥራ ሁኔታዎች ፣ አግላይነት እና በቀጥታ ከሰብአዊ ክብር የሚቃረኑ ሌሎች ልማዶች የሚከለከሉበት ምክንያትም ለዚህ ነው።

የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ (CRC) በአንቀጽ 29 ላይ በተገለጸው መሠረት ለሕፃናት የሚሰጠው ትምህርት በሚከተሉት አቅጣጫዎች ላይ ማተኮር እንዳለበት በግልጽ በማስቀመጥ ጥራት ላለው ትምህርት የሚሆን መብቶች ላይ የተመረኮዘ ማዕቀፍን ያቀርባል፦

- የሕፃኑን ስብእና፣ ተሰጥኦ፣ የአዕምሮና የአካል ችሎታ በተሟላ አኳኋን ማዳበር፤
- ሰብአዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነጻነቶችን እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር ውስጥ የተደነገጉትን መርሆዎች መከበርን ማረጋገጥ፤
- ወላጆችን የራስን ባህል፣ ቋንቋ፣ ወግና ሥርዓት የሚኖሩበትን ወይም የመጡበትን አገር ብሔራዊ ወጎችንና ሥርዓቶችን እንዲሁም ከራሳቸው የሚለዩ ሥልጣኔዎችን የማክበር ዝንባሌን ማዳበር፤
- ለተፈጥሯዊ አካባቢ የሚሰጥ እንክብካቤን ማሳደግ፤

- ስለማህበረሰቡ ሀላፊነት የሚሰማቸውን ህጻናትን ስለሰላም፣ስለመቻቻል፣ ስለጾታ እኩልነት፣ ሁሉን አቀፍ ለሆነ ወዳጅነት፣ ስለ ብሔሮችና የሃይማኖት ቡድኖች እና በአጠቃላይ ለሀገር ፍቅር ተቆርቋሪ የሆኑ ህጻናትን ዕውቀትና ሀላፊነት እንዲኖራቸው ማዘጋጀት፡፡

የህጻናት መብቶች ስምምነት (CRC) ትርጉም ባለው መልኩ ለሕፃኑ መብትና ተሳትፎ ትልቅ ዋጋ ይሰጣል፡፡ ሕፃናት የዴሞክራሲ ግንዛቤያቸውን እያጎለበቱ እና እየጨመረ የሚሄድ ኃላፊነት እንዲኖራቸው አክብሮት መስጠትን እና ንቁ ዜጋ መሆንን እንዲለማመዱ የውይይት እና የሐሳብ ልውውጡ ሂደት ሊበረታታ ይገባዋል።

ሰላማዊ እና አካታች የሆነ ማህበረሰብን ለመገንባት እና ስነምግባራዊ ጉድለቶችን ምላሽ ለመስጠት ትምህርት የሕፃናትን ክህሎት በማሳደግ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ይሁን እንጂ ህጻናትን በቀለም ትምህርት ብቻ ሳይሆን በስሜት፣ በመንፈስ እና በመልካም ግንኙነት ረገድም በትምህርት አማካኝነት ሙሉ አቅማቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

**ሣጥን 5፦ የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ**

የሕፃናት መብቶች ድንጋጌ (CRC) አንቀጽ 12 ሕፃኑን በሚመለከቱት ነገሮች ላይ የሕፃኑን የመናገር እና በሚመለከታቸው ጉዳዮች የመደመጥ መብትን ለይቶ በማስቀመጥ እንደሚከተለው አስቀምጦታል፦ «ሕፃኑ በማኅበረሰቡ ውስጥ እንደ አንድ ግለሰብ በሕይወት ለመኖር ሙሉ በሙሉ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ቻርተር በተደነገገው መሠረት በተለይ ከሰላም፣ ከክብር፣ ከመቻቻል፣ ከነጻነት፣ ከእኩልነት እና ከአንድነት መንፈስ ጋር ማደግ አለበት።» ይህ ማለት ሕፃናት ከሕይወታቸው ጋር ግንኙነት ባለው ጉዳይ ላይ እና በእነርሱ ጉዳይ ላይ በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት ወይም በማኅበረሰብ የሚሰጥ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የበኩላቸውን ጫና ለመፍጠር የመሳተፍ መብት አላቸው።

## 3.3. በሰላም ትምህርት ግብረገብነትን ማጎልበት

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ራሳቸውን እና ሌሎች ሰብአዊ ፍጡራንን የማክበር እና የማድነቅ አመለካከት ኖሯቸው ከሌሎች ጋር አዎንታዊ ግንኙነቶችን ለመመስረት የሚያስችሉ አመለካከቶችን እና የልቦና ውቅሮችን ተፈጻሚ እንዲያደርጉ እንዴት ልናግዛቸው እንችላለን?
- ለሰብዓዊነት ጥያቄዎች እንዴት ምላሽ መስጠት እንችላለን?

በሰላም ትምህርት አማካኝነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ ላለው የማኅበረሰቡ ሥነምግባራዊ ፍላጎት እና ድርጊት ምላሽ መስጠት ይቻላል። አሰልጣኙ ለባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ልዩነቶች ጠንቃቃ መሆን፤ የሕፃናት የኔነት ስሜትን ማጠናከር፤ የመማሪያ ቦታዎች ለደኅንነታቸው ምቹና አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ፤ ሁሉን አካታች ማንነቶች እንዲኖራቸው እና ሲያድጉ መሆን የሚፈልጉትን እንዲሆኑ ማገዝ፤ ከሌሎች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖራቸው መርዳት፤ ራሳቸውን እንዲለውጡ እና በዙሪያቸው ያለውን ዓለም መለወጥ እንዲችሉ ማበረታታት ይጠበቅበታል።

የሰላም ትምህርት የእርስ በርስ ትስስርን የሚያጠናክር እና አንድ ሰው ከሌሎች ጋር ያለውን ግንኙነት በመቅረጽ ረገድ ዋና ምሰሶ ሲሆን ለሰላም ግንባታም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

የእርስ በርስ ትስስር ማለት ሕፃናት እና ወጣቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ራሳቸውን የት ቦታ ማስቀመጥ እንደሚፈልጉና ከሌሎች ጋር ያለውን የእርስ በእርስ ግንኙነት ምን እንደሚመስል ለይተው

እንዲረዱ ሊፈቀድላቸው ይገባል ብቻ ሳይሆን ያሉበትንም ቦታ እና ያላቸውን ሚና እንዲረዱ ንቃተ ሕሊናቸውን እንዲያጎለብቱ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ማለት ነው። በሰብአዊነት እርስ በርስ እንደ ተያያዙ በሰላም መዝለቅ ሁኔታን እና

የምንጋራቸውን ኃላፊነቶች መረዳት ሕፃናት እና ወጣቶችን የሚመለከታቸውን ጉዳይ እንዲረዱ ሊያግዛቸው ይችላል።

የእርስ በርስ ትስስር ማለት «ኡቡንቱ» በሚለው ቃል ሊገለጽ የሚችል ሲሆን ይህም ቃል «እኔ ማለት አንተነህ» እኔን የሆንኩት አንተ ስላለህ ነው በሚል በነጻነት ሊተረጎም ይችላል። ኡቡንቱ በሌሎች ሰዎች ምክንያት ሰው መሆን ላይ አፅዕኖትን የሚሰጥ የአፍሪካ ፍልስፍና ነው። ኡቡንቱ የግለሰብ ምንነት አፍሪካዊ ሐሳብ ነው፤ ግለሰቦች ለማንነታቸው በሌሎች ላይ ጥገኛ ናቸው። ኡቡንቱ በሰው ልጅ አንድነት፣ ርህራሄ፣ ሰብአዊ ክብር እና በእያንዳንዱ ሰው ላይ ባለው ሰውኛነት ላይ እና አንድ ሰው ሰው የሆነው በሌሎች ሰዎች በኩል ነው በሚለው ሐሳብ ላይ አፅዕኖት ይሰጣል።

በኡቡንቱ ፍልስፍና በዋነኝነት እርስ በርስ ትስስር እና ለሁሉም ሰዎች አክብሮትን መስጠት ይገኙበታል። ኡቡንቱ የተለየ ሃይማኖት፣ ባህል እና ሥልጣኔ ላላቸው ሰዎች አክብሮትን መስጠት ራስን በሌላኛው ሰው ጫማ ውስጥ አስገብቶ በማየት ይጎለብታል። አክብሮት እና ርህራሄ በግለሰብ እና በጋራ ኃላፊነት ላይ በመመርኮዝ ወደ ላቀ ግንዛቤ የሚያመራ ሲሆን ይህም በበኩሉ ለዕርቀ ሰላም ዝግጁ ወደ መሆን ያሸጋግራል።

# ምዕራፍ 4፦ የሰላም ሐዋሪያትን ብቃት መገንባት

**ሥዕል 10፦ በሰላም ሐዋሪያት የሚፈለጉ ችሎታዎች**




ምንጭ፦ ከArigatou International, 2008 ተወስዶ ተመጥኖ የተዘጋጀ

## *4.1. ራስን ማወቅ*

በሰላም አብሮ መኖር ከሌሎች ግለሰቦች ጋር ባለን ጤናማ ግንኙነት ላይ የሚመሰረት ሲሆን ስኬታማ የሚሆነውም በቅድሚያ ራሳችን ማን እንደሆን መረዳት ስንችል እና እንዴት ከሌሎች ግለሰቦች ጋር ጤናማ ግንኙነት መመስረት እንደምንችል ስናውቅ ነው። ሁለቱም አሠልጣኝ እና ሠልጣኝ የተለየና ውስብስብ የሆኑ ጠባዮች ወይም ባህሪያት ስለሚኖራቸው በመካከላቸው በሚያደርጉት መስተጋብር አንደኛው ሌላኛው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ራስን ማወቅ ሲባል አንድ ሰው የራሱን ጠባይ፣ ስሜት፣ ዓላማ እና ፍላጎት በመመርመር ለማሻሻል እውነተኛ ጥረት ወይም ሙከራ የሚያደርግበትን ሂደት ያካትታል፡፡ ለሰላም እና ሰላማዊ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ ሆን ተብሎ ታስቦበት የሚሰጥ ውሳኔን መወሰን እንዲችሉ ሠልጣኞች ጥንካሬያቸውን፣ ድክመታቸውን፣ ፍላጎታቸውን እና የማኅበራዊ እገዛ ሥርዓቶችን ማወቅ ያስፈልጋቸዋል።

## 4.2 የተግባቦት ክህሎት

የተግባቦት ክህሎት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል በቃል እና ቃላዊ ባልሆነ መንገድ የሚደረግ መስተጋብር ነው። የእኛ የግል ስኬት እና ደስታ በአብዛኛው የሚወሰነው በግለሰብ ደረጃ ባለን የተግባቦት  ክኅሎት አጠቃቀም እና ውጤት ላይ ነው። የቅርብ ጓደኝነት ወይም ወዳጅነት የሚመሠረተው፣ የሚዘልቀው እና የሚፈርሰው እኛ ከሌሎች  ሰዎች ጋር ባለን የተግባቦት ክህሎት ነው።

በተመሳሳይ መልኩ የእኛ ማኅበራዊ ሕይወት ስኬታማነትም የሚረጋገጠው   ወይም የሚሳካው ከጎረቤቶቻችን፣ ከምናውቃቸው ሰዎች እና በየቀኑ ከምናገኛቸው ሰዎች ጋር ባለን የተግባቦት ክህሎትና ችሎታ ነው። የተግባቦት ክህሎትን (ግለሰባዊ የተግባቦት ክህሎት) ማጎልበት ያሉት ጠቀሜታዎች እንደሚከተሉት ተዘርዝረዋል፦

**መማር፦**ግለሰባዊ የተግባቦት ክህሎት ስለ ሌሎች ሰዎች፤ በዙሪያችን ስላለው አካባቢ እና ስለ ራሳችን እንድናውቅ ያግዘናል።ስለ ራሳችን ከሌሎች ጋር ማውራት ስለ ስሜታችን፣ ሐሳባችን እና ባሕሪያችን በተመለከተ ከሌሎች ጠቃሚ ግብረመልስ እንድናገኝ ይረዳናል። በዚህ መልክ ከሰዎች ጋር በሚኖረን ተግባቦት እና ከሚሰጠን ግብረመልስ በመነሳት እኛ በሌሎች ሰዎች ዘንድ እንዴት እንደምንታይ ለማወቅ ይረዳናል፡፡ በተለይም ስለራሳችን ማን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ አስተሳሰብ እንዳለው ለማወቅ ይረዳናል።

**ማዛመድ፦** የግለሰባዊ የተግባቦት ክህሎት ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት እንዲኖረን ያግዘናል። በግለሰባዊ ግንኙነት  እንደ ጓደኝነት ወይም ፍቅር የመሳሰሉ እሴቶችን እንጋራለን፤ በተመሳሳይ ሌሎች ለሚሰጡን ጓደኝነት እና ፍቅር ምላሻችንን እንሰጣቸዋለን።

**ተጽዕኖ ማሳረፍ፦** በግለሰባዊ ግንኙነቶች ወቅት ሌሎች ሰዎች ባላቸው አመለካከት እና ባሕሪ ላይ የራስዎትን ተጽዕኖ ማሳረፍዎ አይቀርም። ለምሳሌ፡- ሌሎች እኛ በምንፈልገው መንገድ ድምፃቸውን እንዲሰጡ ወይም አዲስ መጽሐፍ እንዲገዙ ወይም ለተወሰኑ ሐሳቦች ዋጋ እንዲሰጡ ተፅዕኖ ልናሳድርባቸው እንችላለን፡፡

**መጫወት፦** የግለሰብ የተግባቦት ክህሎት ከሌሎች ጋር  የመጫወት እድልን ይሰጣል። ለምሳሌ፦ ከጓደኞቻችን ጋር ስለ ሳምንቱ የዕረፍት ቀናት እንቅስቃሴዎች፤ ስለ ስፖርት የመነጋገር፤ ታሪኮችን እና ቀልዶችን ማውራትን ያካትታል።

**ማገዝ፦** አሠልጣኞች ባላቸው የተግባቦት ክህሎት ወይም መስተጋብር ለሠልጣኞች መመሪያን መስጠት ይችላሉ። ምናልባትም እግር ኳስ ሲጫወት እግሩን የተሰበረ ጓደኛችንን ልናፅናና ወይም ለሥራ ባልደረባችን ስለ አንድ አስጨናቂ የሥራ ሁኔታ ምክር ልንለግሥ እንችል ይሆናል። በአጭሩ የግለሰብ የተግባቦት ክህሎት በእኛ ማኅበረሰብ ውስጥ ሰላምን ለመገንባት የሚያስችል የማዕዘን ድንጋይ ነው፡፡

## 4.3 የማዳመጥ ክህሎት

**የማዳመጥ ክህሎት ለሰላም ሐዋሪያት ለምን ያስፈልጋል?**

እያንዳንዱ ስኬታማ ተግባቦት ከማዳመጥ ይጀምራል። በዙሪያችን ያለውን ዓለም ለመረዳት እና በሰላም ግንባታ ላይ የበኩላችንን አስተዋፅኦ በንቃት ለማበርከት እንዲሁም በቤተሰባችን እና በማህበረሰባችን ዘንድ አብሮነትን ለማስፈን ከምንም በላይ በመጀመሪያ ደረጃ ጥሩ አድማጭ መሆን ይኖርብናል። የማዳመጥ ክህሎት መልዕክቶችን የመቀበል ችሎታ ማለት ብቻ ሳይሆን ይልቁንስ አለመግባባትን ለማስቀረት መልዕክቶችን በትክክል የመተርጐም ወይም የመተንተን  ብቃት ማለትም ነው፡፡ ማዳመጥ አንድ ሰው ከሌሎች ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት/ተግባቦት መሠረታዊ ክህሎት ነው፡፡

### እንዴት ማዳመጥ እንዳለብን መማር እንችላለን?

እንደ ሁሉም ብቃቶች ስኬታማ አድማጭ መሆንን መማር ይቻላል። ማዳመጥ ሌሎችን ለመቀበል፣ ርህራሄ እና አክብሮትን ለሌሎች ለማሳየት የመጀመሪያው እርምጃ ነው። ማዳመጥ ለሁሉም ሰዎች በተለይም ለሰላም ግንባታ ሐዋሪያት እና ለስኬታማ ግለሰባዊ ተግባቦት/መስተጋብር/ እንዲሁም ከሌሎች ጋር ለመግባባት የመጀመሪያው እርምጃ ነው።

አሠልጣኞች ለሰልጣኞች አርአያ እንደመሆናቸው ሠልጣኞቻቸው በአካባቢያቸው ያሉትን ችግሮች ተረድተው ማኅበረሰባቸውን እንዲለውጡ ለመኮትኮት በሚያደርጉት ጥረት ላይ ማዳመጥ መቻላቸው እጅግ አስፈላጊ ነው። ሠልጣኞች ለለውጥ እና ለሰላም ግንባታ አስተዋፅኦ ለማበርከት በሚያደርጉት ጉዞ አብረዋቸው ለመዝለቅ አሠልጣኞች የሠልጣኞችን ፍላጎት እና ያሉበትን ዓውድ በትክክል መረዳት ያስፈልጋቸዋል። ውጤታማ የማዳመጥ ክኅሎት በቀላሉ የሚለመድና የሚቻል አይደለም፤ በትዕግሥት ደጋግሞ መለማመድን ይጠይቃል። ከዚህ በታች የማዳመጥ ክኅሎቶችን ለማሻሻል ሊያግዙ የሚችሉ አስር ጠቃሚ ምክሮችን እና የቡድን ልምምዶች ቀርበዋል።

**ሣጥን 6፦ ውጤታማ የማዳመጥ ክኅሎትን ለማዳበር የሚያግዙ ጠቃሚ ምክሮች**

- ተናጋሪው ላይ ማተኮር እና ሐሳብን ከሚሰርቁ ነገሮች መቆጠብ።
- ታጋሽ መሆን፦ ጥሩ አድማጭ መሆን ጊዜን ይጠይቃል።
- ሁሉንም ስሜት ሕዋሳት ማሳተፍ፦ ማዳመጥ አእምሯዊ፣ ምናባዊ፣ የጆሮ እና አካላዊ ትኩረትን ይፈልጋል።
- ከልብ ማዳመጥ፦ ለመከባበር፣ ለርህራሄ እና ለተቀባይነት ማዳመጥ መቻል ቁልፍና አስፈላጊ ነገር ነው።
- በሚገባ ለማዳመጥ እና ለመረዳት በተናጋሪው ጫማ ውስጥ ራስን አስገብቶ ማየት።
- ቃላዊ ያልሆኑ ምልክቶችን (ፈገግታ፣ ጭንቅላትን በመነቅነቅ) እና ቃላዊ ምልክቶችን («አዎ»፣ «ምን ማለት እንደፈለግክ ገብቶኛል») በማለት አበረታች ምላሾችን በመስጠት ለተናጋሪው እያዳመጡት እንደሆነ እየተረዱት እንደሆነ በተግባር ማሳየት።
- እየተላለፈ ያለው መልእክት ምን እንደሆነ ለማረጋገጥ እና አለመግባባትን ለማስቀረት ማብራሪያን የሚጠይቁ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ዝግጁ መሆን።
- ተናጋሪው እየተናገረ ያለውን በአጭሩ አንኳር ነጥቦቹን ለመድገም እና ጠቅለል ያሉ አጫጭር ጥያቄዎችን ለመጨመር ዝግጁ መሆን፤ ይህም ጉዳዩን የተሻለ እንዲረዱ እና እንዲገልጹት ያግዝዎታል።
- ወደ ድምዳሜ አለመዝለል፤ የገባዎት ነገር ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ማብራሪያ ይጠይቁ ወይም የተባለውን በአጭሩ ደግመው ይናገሩ። የተባለውን መረዳት ማለት ተናጋሪው በተናገረው ሐሳብ የግድ ይስማማሉ ማለት አይደለም።
- የተለያዩ ባህሎችን፣ ሥርዓተ ጾታዊ እና ሃይማኖታዊ ልዩነቶችን እንዲሁም የራስዎትን የተዛቡ አስተሳሰቦችን እና ግምቶችን ከግምት ማስገባት የሚሉት ናቸው፡፡

## 4.4 ህብረ-ባህላዊነትና የተግባቦት ክህሎት

በኢትዮጵያ ውስጥ የሰላምን ባህል ለመገንባት የተለያየ ባህል ባላቸው የማህበረሰብ አባላት መካከል ያለ የተግባቦት ክህሎት ለምን አስፈላጊ እንደሆኑ የሚያሳምኑ በርካታ ምክንያቶች አሉ። ከእነዚህ መካከል አራቱ እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡-

1) ሰላም፣
2) ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂያዊ፣
3) ራስን ማወቅ እና
4) ሥነ-ምግባራዊ ምክንያቶች ናቸው። እነዚህም ከዚህ በታች በዝርዝር ተብራርተዋል።

**ሰላም**

ስለ ሰላም ስናነሳ ዋናው ቁልፍ ጉዳይ የተለያየ ፆታ፣ ዕድሜ፣ጎሳ፣ ቋንቋ እና ኃይማኖት ያላቸው ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በሰላም አብሮ መኖርን መማር ይችላሉ ወይ የሚለው ነው፡፡  ያለ ሰላም ምንም ቀጣይ ሕይወት የለም።የተለያዩ የባህል ቡድኖች እርስ በርስ በሰላማዊ መንገድ የሚያደርጉት/የሚኖራቸው ተግባቦት በኢትዮጵያ ሰላምን ለማስፈን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

**ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂያዊ**

የተለያየ ባህል ባላቸው የማህበረሰብ አባላት መካከል ያለ ባህላዊ የተግባቦት ክህሎት በአካባቢ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሥራ ቦታ እንቅስቃሴዎች ላይ አሁን ላሉ እና ወደፊት ለሚኖሩ ለውጦች እጅግ አስፈላጊ ክኅሎት ነው። የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ  እያደገ ባለበት በአሁኑ ወቅት የራሳቸውን ንግድ መጀመር የሚፈልጉ ወጣቶች የተግባቦት ክኅሎትን ማሳደግ አለባቸው። ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን እና አገልግሎቶቻቸውን በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ መሸጥ የሚፈልጉ ከሆነ የተለያዩ አመለካከቶች እና ተሞክሮዎች ያሏቸው በርካታ ሠራተኞች ሊኖራቸው ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ እና በአካባቢው ያሉ አገሮች ቋንቋዎችን እና ባህሎችን የሚያውቁ ከፍተኛ መሪዎች ያስፈልጓቸዋል። ሰዎች፣ ሐሳቦች እና የንግድ ሥራዎች እርስ በርስ በተሳሰሩበት የሉላዊነት ዘመን ላይ እንገኛለን።

በኢትዮጵያ ውስጥ በበርካታ ባህሎች መካከል መግባባት እና መስተጋብር የመፍጠር ችሎታ ለቀጣዩ ትውልድ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፡-የኢትዮጵያ መንግሥት በሴቶች፣ ህፃናት እና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር አማካኝነት  ትምህርት ቤት በሚዘጋበት የዕረፍት ወቅት የባህል ልውውጥ ፕሮግራሞችን ለወጣቶች በማዘጋጀት ቀጣዩ ትውልድ አንዱ የሌላውን ባህል መማር እንዲችል በማድረግ የሰላም ግንባታ ሂደትን ማጠናከር ይቻላል፡፡

**ራስን-ማወቅ**

የተለያየ ባህል ባላቸው የማህበረሰብ አባላት መካከል ያለ ተግባቦትን ማጥናት ከሚያስፈልግባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ የራስን ባህል፣ ማንነት እና ታሪክን  በሚገባ ለመገንዘብ ስለሚያስችል ነው። በመርህ ደረጃ የተለያየ ባህል ባላቸው የማህበረሰብ አባላት መካከል ያለ ተግባቦትን ማጥናት ወደ ሌላ ባህል እና እውነታ በሚደረግ ጉዞ ይጀምርና በራሱ በግለሰቡ ባህል ጉዞው ይጠናቀቃል። በሌላ አነጋገር የሌሎችን ባህሎች ማጥናት እና ማድነቅ የራሳችንን ባህል እንድናውቅ ያደርገናል። የሌሎችን ሰዎች ባህል ካከበርን ሌሎች ደግሞ የእኛን ባህል ያከብራሉ። አንዱ የሌላውን ባህል ማድነቅ እና ማክበር ሲችል የሰላም ባህልን መገንባት እና ማሳደግ ይቻላል። ለሌሎች ሰዎች ባህል አድናቆት እና አክብሮትን ማሳየት የሰላምን ባህል ለመገንባት እና ለማጎልበት መሠረት ነው።

*ሥነ ምግባር*

*የተለያዩ ባህሎች ትስስር ባለባት ዓለም ውስጥ መኖር የሥነ ምግባር/ የግብረገብ ተግዳሮቶችን ስለሚያስከትል ሰላማዊ የተግባቦት ክህሎትን በማጥናት መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል። ሥነ ምግባር የግለሰቦችን እና የቡድኖችን ባሕሪ ለማረቅ የሚያግዝና የጠባይ መርሆዎችን የሚያጠና እንደሆነ ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል። እነዚህ መርሆዎች ብዙውን ጊዜ የሚመነጩት በማኅበረሰቡ እይታ ጥሩ እና መጥፎ ከሚባሉት ጠባዩች ነው። የተለያየ ባህል ባላቸው የማህበረሰብ አባላት መካከል ያለ የተግባቦት ክኅሎትን ለማሻሻል የራስን ሐሳብ መግለጽ፣ የሌሎችን ድምፅ ማዳመጥ እና ማኅበራዊ ፍትሕን የማስፈን ስሜትን ማጎልበት ላይ ማተኮር ያስፈልጋል።*

## *4.5 ተፈጥሮና የሰላም ግንባታ ትምህርት ትስስር*

*የሰላም ባህልን መገንባትና ማጎልበት በተለያዩ ባህሎች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሮ ጋር ባላቸው መስተጋብር ላይ የተመሰረተ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በሰዎች እና በተፈጥሮ ብዝሃ-ሕይወት መካከል ያለው ግንኙነት በኢትዮጵያ ድህነትን ለመቅረፍ እና የሰላም ባህልን ለማጎልበት በሚደረገው ትግል እጅግ አስፈላጊ ነው።*

**ሣጥን 7፦ ዛፍ እና ቅርንጫፎች እንደ ሰላም መሣሪያዎች**

*በበርካታ የኢትዮጵያ ክፍሎች የግራር ዛፍ በሴቶች ዘንድ የሰላም ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። ለምሳሌ፡- ሲንቄ(የሰላም በትር) የኦሮሞ ሴቶች ሥልጣን እንዲሁም ሲቆ(የሰላም በትር) የሲዳማ ሴቶች የሰላም በትር ትዕምርቶች ናቸው፡፡*

*ዋንጋሪ ማታይ የተባሉት የኬንያ ምሁር የ2004 የኖቤል ሽልማት አሸናፊ በእሳቸው አገር ዛፍ እንዴት የሰላም እና የግጭት መፍቻ ምልክት ሊሆን እንደቻለ ያብራራሉ። የአገር ሽማግሌዎች በሁለት የተጋጩ ወገኖች መካከል ከዛፍ ላይ የተቆረጠ እንጨትን ሲያስቀምጡ የተጋጩት ወገኖች ዕርቀ ሰላምን እንዲፈልጉ ያደርጋቸዋል* (Maathai,2004)።

*በመሆኑም የተለያየ ባህል ባላቸው የማህበረሰብ አባላት መካከል ያለ የተግባቦት ክኅሎት የእንጨቶችን ትዕምርታዊ አጠቃቀም ጨምሮ በኢትዮጵያ እና በአካባቢው አገሮች ውስጥ የሰላም ባህልን በመገንባት እና በማጎልበት ላይ ጉልህ ሚና ይጫወታል።*

## *4.6 በጥልቀት የማሰብ ክህሎት*

*በጥልቀት ማሰብ የተለያዩ ሐሳቦችን በንቃት ለመርመርና ነፃ አስተሳሰብን ለማጎልበት፤ የሌሎችን ሐሳብ ለመረዳት እና ስለ ዓለም ያለንን የግል አመለካከት ለመፈተሽ የሚያስችል ችሎታ ነው። ለሰላም ግንባታ በጥልቀት የማሰብ ክህሎት መኖር ማለት የግጭቱን ዓውድና መሰረታዊ ምክንያቶች የመገንዘብ፤ በተለያዩ ቡድኖች መካከል ያሉትን ተመሳሳይነት እና ልዩነቶች የማየት ችሎታ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ የራሳችን አመለካከት እና ባሕሪያት እንዴት የእኛን እውነታ ሊቀርጹ እንደሚችሉ የመረዳት ችሎታ መኖር ማለት ነው። በጥልቀት ማሰብ የተለያዩ መጠነ ሰፊ ክኅሎትንና አመለካከትን የሚያካትት በርካታ ዘርፎችን በውስጡ የያዘ ሂደት ሲሆን በሚከተሉት ላይ ያተኩራል።*

- *የሌሎችን ሰዎች አቋም፣ መከራከሪያ ነጥቦች እና ድምዳሜዎች ለይቶ ማወቅ፤*
- *በተለያዩ አማራጮች ማስረጃን መመርመር፤*
- *ተቃራኒ መከራከሪያ ነጥቦችን እና ማስረጃዎችን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መመዘን፤*

- ፊት ለፊት ካለው እውነታ ይልቅ አዙሮ ለማየት መቻል እና ሐሰተኛ ወይም ፍትሐዊ ያልሆኑ ግምቶችን ለይቶ ለማወቅ መቻል፤
- እንደ ሐሰተኛ ሥነ አመክንዮ ነጥብ እና ማሳመኛ ዘዴዎች የመሳሰሉ የተወሰኑ አቋሞችን ይበልጥ አሳማኝና አማላይ ለማድረግ ጥቅም ላይ የዋሉ ቴክኒኮችን ለይቶ ማወቅ፤
- ሥነ አመክንዮን እና ግንዛቤን በመጠቀም በተዋቀረ መንገድ በጉዳዮች ላይ የግል ምላሽን ማንፀባረቅ፤
- መከራከሪያ ነጥቦች ተቀባይነት ያላቸው እና አሳማኝ መሆናቸውን ጥሩ ማስረጃ እና ትርጉም ሰጪ ግምቶች ላይ በመመርኮዝ ከድምዳሜ ላይ መድረስ፤
- በአንድ ጉዳይ ላይ ያለ አተያይን ሌሎችን በሚያሳምን በተዋቀረ፣ ግልጽ እና በቂ በሆነ አመክንዮ  ማቅረብ።

**በጥልቀት የማሰብ ዋነኛ ባህሪያት**

በጥልቀት ማሰብ ለተጠየቁ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ለመስጠት ትክክለኛነትን፣ እንከን አልባነትን እና ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል።

- **ለዝርዝር ጉዳዮች ትኩረት መስጠት፡-** አጠቃላዩ ችግር ይበልጥ ግልጽ እንዲሆን የሚያስችሉ ትናንሽ ፍንጮችን ለማስተዋል በቂ ጊዜን መስጠት።
- **አዝማሚያዎችን እና አካሄዶችን ለይቶ ማወቅ፡-** ይህም የመረጃ ምንጮችን በማስፋት እና መረጃን በመተንተን  በጥንቃቄ  ሊከናወን ይቻላል።
- **ድግግሞሽ፡-** ምንም ነገር እንዳልጎደለ ለማረጋገጥ ተመሳሳይ መነሻ   ነጥብን ለበርካታ ጊዜ ደጋግሞ እና ተመላልሶ ማየት።

**በጥልቀት ማሰብን እንዴት ማበረታታት ይቻላል?**

- አሠልጣኞች በሚከተሉት መንገዶች በጥልቀት ማሰብን ማበረታታት ይችላሉ፡-
- ለመስተጋብር ትርጉም ያለው የውይይት መድረክ መፍጠር፤
- ጠንካራ ውይይቶችን ለመፍጠር ፈታኝ እና ጥልቀት ያላቸውን ጥያቄዎች መጠቀም፤
- ሠልጣኞች በነጻነት እንዲጠይቁ እና መልስ እንዲሰጡ እንዲሁም ደጋግመው ለምን የሚል ጥያቄን እንዲጠይቁ መፍቀድ፤
- ከሠልጣኞች ሕይወት እና ተሞክሮ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ማስተማሪያ ቁሳቁሶችን እና የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም፤
- የተለያዩ አመለካከቶችን ማስተናገድ፡- ተመሳሳይ መረጃን ከበርካታ የዕይታ አቅጣጫዎች ማየት፤
- ጥልቅ ግንዛቤ ለማግኘት ግላዊ ዕምነቶችን እና ፍላጎቶችን  ወደ ጎን መተው እና
- እንደምታዎችን እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ውጤቶችን ከግምት ማስገባት፤ በአጭር ጊዜ ጥሩ ሐሳብ መስሎ የሚታይ  ነገር የረዥም ጊዜ ያልተጠበቁ አሉታዊ ውጤቶችም ሊኖሩት ይችላሉ።

## በጥልቀት የማሰብ ስድስት ደረጃዎች

የተለያዩ ደራሲያን ስድስቱን በጥልቀት የማሰብ ደረጃዎችን ለመግለጽ የተለያዩ ዝርዝሮችን ይጠቀማሉ። የዓለም የምግብ እና የእርሻ ድርጅት /FAO/ (1990) የሚከተሉትን ደረጃዎች እንደ ሐሳብ ያቀርባል፦

(1) ሁኔታውን መመልከት፣
(2) ችግርን ለይቶ ማወቅ፣
(3) መፍትሔዎችን መጠቆም፣
(4) የተጠቆሙትን መፍትሔዎች መመዘን፣
(5) ምርጡን መፍትሔ በምክረ ሐሳብነት ማቅረብ እና
(6) መተግበር።

በጣም ተቀባይነት ያላቸው በጥልቀት የማሰብ ስድስት ደረጃዎች የብሉም የመማር ማስተማር ሂደት ሳይንሳዊ ምደባ /Bloom's Taxonomy of Learning Domains/ (1956) ነው።

- **ዕውቀት፦** መግለጽ፣ መዘርዘር፣ ማብራራት፣ ለይቶ ማወቅ፣ ማሳየት፣ መሰየም እና መጥቀስ
- **ግንዛቤ፦** ማብራራት፣ በአጭር ማጠቃለል፣ መለያየት፣ መወያየት እና መተርጐም
- **መተግበር፦** በሥዕል መግለጽ፣ መረጃን መጠቀም፣ ተፈጻሚ ማድረግ፣ በተግባር ማሳየት፣ ማመላከት፣ መፍትሔ መስጠት፣ መመደብ፣ አዲስ ግኝት ማግኘት
- **ትንታኔ፦** መዘርዘር፣ ለይቶ ማወቅ፣ የአንደምታ ትርጒም መስጠት፣ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣ ምክንያት መስጠት፣ መመደብ፣ ማደራጀት እና መከፋፈል
- **አስተጻምሮ፦**ማዋሐድ፣ ማሻሻል፣ ዳግም ማደራጀት፣ መተካት፣ ማቀድ፣ መፍጠር፣ ንድፍ ማዘጋጀት፣ መፍጠር እና ማካተት
- **መመዘን፦**መወሰን፣ ደረጃ መስጠት፣ መፈተሽ፣ መለካት፣ ምክረ ሐሳብ መስጠት፣ መመዘን እና ሐሳብን ማሳመን።

**ሥዕል** 11፦ **የብሉም የመማር ማስተማር ሂደት ሳይንሳዊ ምደባ** /Bloom's Taxonomy of Learning Domains/



ከታች በሥዕል 12 ላይ የተቀመጠው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ከብሉም ሳይንሳዊ ምደባ እና ከአንዳንድ ሌሎች አተያዮች የተወሰዱ ክፍሎች አሉት። የውሳኔ አሰጣጥ የችግሮችን ምንነት በመግለጽ ትንታኔ መስጠት፣ አማራጭ መፍትሔዎችን ማዘጋጀት፣ መፍትሔዎቹን መመዘን እና በእጅ ላይ ላለው ችግር ይበልጥ ተገቢነት ያለውን መፍትሔ መምረጥ፣ ትግበራ እና ክትትልን ያካትታል። በጥልቀት ማሰብ ምክንያታዊና እንዴት ተቀባይነት ያለው ውሳኔ ለመስጠት መሠረት እንደሆነ ለማየት ይቻላል።

**ሥዕል 12፦ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት**




ምንጭ፦ ከ Covey, 2013 ተመጥኖ የተወሰደ

## *4.7 የማስታረቅ ክህሎት*

ማስታረቅ አወዛጋቢ ግንኙነት ያስከተሉትን ችግሮች ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ እና ለተፈጠረው ቀውስ የመጨረሻ እልባት ወይም ፍጻሜ ለማምጣት ታቅዶ የሚሰራ ነው። በሦስተኛ ወገን የሚደረግ የአስታራቂነት እንቅስቃሴ ሲሆን ተቀዳሚ ዓላማውም ችግሮችን ከዕልባት ለማድረስና መቻቻልን ለማስፈን ነው፡፡ ሦስተኛው ወገን ብዙውን ጊዜ በመጀመሪያ ችግሩ ምን እንደሆነ ይመረምርና ምንነቱን ያስቀምጣል፣ በመቀጠልም በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው መፍትሔዎች ላይ ለመድረስ እያንዳንዱን ቡድን ከምክረ ሐሳቦች ጋር ለየብቻ አግኝቶ ያነጋግራል። ማስታረቅ በአገራት መካከል፣ በአገራት ውስጥ ባሉ ቡድኖች፣ ድርጅቶች፣ ማኅበረሰቦች እና በግለሰቦች መካከል ሊደረግ ይችላል።

**ሣጥን 8፡- የማስታረቅ ክኅሎት መገለጫ ባሕሪያት**

- ማስታረቅ  ግጭትን በሰላም የመፍታት አንድ አካል ነው።
- ማስታረቅ ገለልተኛ የሆነ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል በተፈጠረ ግጭት ላይ ከራሳቸው እሴቶች፣ ግብአቶች እና ፍላጎቶች አንፃር ጣልቃ መግባትን ያካትታል።
- ማስታረቅ  አስገዳጅነት የሌለው ሰላማዊ የሆነ እና አሳሪ ያልሆነ ክዋኔ ነው።
- አስታራቂዎች ሰላማዊ የሆኑ መፍትሔዎችን ለማግኘት ግጭትን ለመለወጥ፣ መፍትሔ ለመስጠት፣ ለማሻሻል ወይም ተጽዕኖ ለማሳረፍ ጥረት ያደርጋሉ።
- አስታራቂዎች ከራሳቸው የተዛቡ አመለካከቶች፣ ሐሳቦች፣ ዕውቀት፣ ሃብት እና ከሚወክሉት ቡድን ወይም ድርጅት ፍላጎቶች ጋር ይመጣሉ፤ አስታራቂዎች ብዙውን ጊዜ በጥያቄ ላይ ባለው ግጭት ዙሪያ የራሳቸው ግምቶች እና አጀንዳ አላቸው።
- ማስታረቅ  በበጎ ፈቃድ የሚደረግ የግጭት  መፍቻ  ዓይነት ነው። በግጭቱ ተሳታፊ የሚሆኑት የግጭቱ ተዋንያን የግጭቱን ውጤት በበላይነት ይቆጣጠራሉ። ዕርቁ ላይም ብዙውን ጊዜ የበላይነት ይኖራቸዋል፡፡ እንዲሁም ዕርቁን ወይም የመፍትሔ ሐሳቦቹን ለመቀበል ወይም ውድቅ ለማድረግ ነጻነቱ አላቸው።
- ማስታረቅ ብዙውን ጊዜ ሲፈለግ ብቻ ይከወናል።

## 4.8 የድርድር ክህሎት

ድርድር በግጭቱ ውስጥ ያሉ ወገኖች ያለ ሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት በራሳቸው ዕልባት ለመስጠት ወይም መፍትሔ ለማግኘት የሚጥሩበት ሂደት ነው። ድርድር በርካታ የተለያዩ ትርጉሞች አሉት፡፡ ሂደቱን አንዳንዶች መፍትሔ ለመስጠት አስቸጋሪ እንደሆነ አድርገው ያዩታል፤ ለሌሎች ደግሞ ልውውጥን የሚሻ የክርክር ጨዋታ ነው፤ አንዳንዶች በድርጅቶች ውስጥ እና መካከል ያሉ ልዩነቶችን የማስታረቂያ መንገድ እንደሆነ አድርገው ይቆጥሩታል፤ ሌሎች ደግሞ የመንግሥት ፖሊሲዎች ማስፈፀሚያ እንደሆነ አድርገው ያስቡታል። በድርድሩ ሂደት ሁሉም ወገኖች ስኬታማ የሚሆኑት በሚከተሉት ነጥቦች ውሳኔ ላይ መድረስ ሲችሉ ነው።

- ወደ ድርድር መግባት ካለመግባት ለእነርሱ የተሻለ መሆኑ፤
- ስምምነት ላይ መድረስ ካለመድረስ ለእነርሱ የተሻለ መሆኑ እና
- ስምምነትን ተፈጻሚ ማድረግ ካለማድረግ ለእነርሱ የተሻለ መሆኑን ሲገነዘቡ ነው።

ማስታረቅ እና ድርድር በኢትዮጵያ ውስጥ ግጭትን ለመቀነስ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ናቸው። ለምሳሌ፡- በአሪ ብሔረሰብ መካከል ኮይሻ የሚባል የሰላም ልብስን ይለብሳሉ። ይህ ረዥም የሆነ ልብስ ከዛፍ ግንድ ቅርፊት የሚዘጋጅ ሆኖ ሰላም ሰፍኖ ደስታቸውን ለመግለጽ በሚጨፍሩበት ጊዜ ብዙውን ጊዜ ሴቶች ወገባቸው ላይ ያስሩታል። ከዚህ በተጨማሪ ሴቶቹ ባህላዊ የጥጥ ጨርቆቻቸውን መሬት ላይ በማድረግ ሰላም እንዲወርድ ይለማመናሉ። አንዲት ሴት ሻሽዋን መሬት ላይ ከጣለች እየተጋጩ ያሉት ወገኖች ለመደራደር ቁጭ እንዲሉ እንደምትፈልግ ጠቋሚ ድርጊት ነው (IRR, 2009, ገጽ 7-8)።

## 4.9. የግልግል ዳኝነት

የግልግል ዳኝነት «እየተወዛገቡ ያሉት ወገኖች ያለመግባባቱን ፍሬ ነገር ገለልተኛ ለሆነ ሦስተኛ ግለሰብ የሚሰጡበትና ለሚሰጠው ውሳኔ ተገዢ እንደሚሆኑ የሚስማሙበት ሂደት ሆኖ ውሳኔው የሚሰጠው ለሁለቱም ወገኖች የመናገር ዕድል ከተሰጣቸው በኋላ ነው» (Professional Warranty Service Corporation, 2016) ።

የግልግል ዳኝነት በሚገባ የተደራጀ እና አለመግባባቶችን ለመፍታት በሰፊው ጥቅም ላይ የሚውል ዘዴ ነው። የተጋጩ ወገኖች ወደ ክስ ከመሄድ ይልቅ ለአንድ ውዝግብ ሌላ አማራጭ የሚያቀርብ ከበርካታ አማራጭ የመፍትሔ አሰጣጥ ዘዴዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ የግልግል ዳኝነት ከፍርድ ቤት ውጭ የሚከናወን በመሆኑ ከክስ የተለየ ነው። በግጭት ውስጥ ያሉት ሁለቱም ወገኖች ገለልተኛ የሆነ ሦስተኛ ወገን በጋራ ይመርጣሉ፡፡ ይህ የሚመረጠው ወገን የግልግል ዳኛ በመባል ይታወቃል። ሁለቱም ወገኖች የግልግል ዳኛው በሚሰጠው ውሳኔ ተገዢ ለመሆን ይስማማሉ። ሁለቱም ወገኖች ማስረጃ እና ምስክሮችን የሚያቀርቡበት ቀን ቀጠሮ ላይ በአካል ይገኛሉ። የግልግል ዳኛው የሚሰጠው ውሳኔ አብዛኛውን ጊዜ የመጨረሻ ውሳኔ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች እንዲህ ያለውን ፍርድ ወይም ውሳኔ መልሰው አያዩም።

## 4.10. ምላሽ ሰጭነትንና ብዝሃነትን መቀበል

ለሥርዓተ ጾታ፣ ለሃይማኖት፣ ለስደተኛ፣ ለባህላዊ ልዩነቶች እና ለብሔር፣ ለችሎታ እና ለመሳሰሉ ጉዳዮች ምላሽ ሰጭነትንና ብዝሃነትን መቀበል አግላይነትን ወይም አድሎን ለመቀነስ እና አክብሮትን ለማስረፅና ለማበልጸግ ቁልፍ ዘዴ ነው። የምላሽ ሰጪነት መሻሻል ከጭፍን ፍረጃና ጥላቻ መቀነስ እና ከመገለል፣ ከመነጠል፣ ከአድልዎ እንዲሁም ከጭቆና መወገድ ጋር የተገናኘ ነው።

ብዝሃነትን መቀበል የሌሎች ሰዎችን ዓውድ፣ ፍላጎት እና በነሱ ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመረዳት አስፈላጊ ነው። ሠልጣኞች የተለያዩ እና ብዝኀነት ያላቸውን እውነታዎች መረዳት እና ኢፍትሐዊነት እና መድልዎ ሲያጋጥማቸው ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ማወቅ ይኖርባቸዋል።

ሁላችንም የየራሳችን የተዛባ አመለካከት አለን፤ ሁላችንም ለሌሎች ሰዎች የማይጠቅም እሳቤዎችን ልናስብ እንችላለን። በዚህ የማሰልጠኛ ማኑዋል ላይ የሰፈሩት አብዛኛዎቹ ልምምዶች የራሳችንን የግል አመለካከቶች እና እምነቶች እንዴት በሌሎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ እንደሚችሉ በራሳችን እንድንመረምር ያበረታቱናል። እነዚህ ልምምዶች ሁለቱንም አሠልጣኞችን እና ሠልጣኞችን «የተለየ መነፅር እንዲያደርጉ» እና እነሱን የሚያውቁበትን መንገድ እንዲጠይቁ ለማበረታታት የታለሙ ናቸው።

ሁሉም ልምምዶች ብዝሃነትን ለመኮትኮት፤ እንቅፋቶችን ለማስወገድ፤ ስለ ዓለም የሚታሰቡ ተራ አስተሳሰቦችንና ዕሳቤዎችን ለመጋፈጥ የሚያስችሉ ውጤታማ ስትራቴጂ፣ አሳታፊ እና የሳይንሳዊ ሙከራ ትምህርትን ያካትታሉ። ዓላማው አሠልጣኞች እና ሠልጣኞች የራሳቸውን የተዛቡ አመለካከቶች እንዲያስወግዱ እና እንዲያስተካክሉ ማድረግ እንዲሁም የተለዩ እውነታዎችን ለማሰብ እንዲችሉ ማድረግ ነው።

ብዝሃነትን መቀበል ለአሠልጣኞች እጅግ አስፈላጊ ሚናን ይጫወታል። አሉታዊ አስተሳሰብ ብዙውን ጊዜ ካሉን የተዛቡ የማስተማርና የማሰልጠን ሥነ-ዘዴዎች ጋር የተገናኘ ሊሆን ይችላል። በትምህርት ቤት ድባብ ውስጥ፣ ይህ ለመድልዎ እና ለአግላይነት ከመማሪያ ክፍል ውጭ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች ለግጭት እንዲሁም በማኅበረሰቡ ውስጥ ላለው እርስ በርስ አለመግባባት አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል። በእነዚህ ምክንያቶች የተነሣ አሠልጣኞች በገዛ ራሳቸው የተዛቡ አስተሳሰቦች ላይ ማሰብ እና እንዴት እነዚህ የተዛቡ አስተሳሰቦች አሉታዊ ውጤቶችን እና መድልዎን ለማራመድ

አስተዋፅኦ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ራሳቸውን መጠየቅ ያስፈልጋቸዋል። ከዚህ አኳያ አሠልጣኞች የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርባቸዋል፦

- የገዛ ራሳቸውን የተዛቡ አስተሳሰቦች ለይቶ ማወቅና ማመን፡፡
- በጉልበት የማስፈራራት፣ አድሏዊነት እና ግጭቶች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወይም ከመማሪያ ክፍል ውጭ ሲታዩ ቶሎ ማወቅ፣ ምላሽ መስጠት እና ጠንቃቃ መሆን ያስፈልጋል። ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ የመድልዎ ሰለባ የሚሆኑ ሰዎች ከተገለሉ ቡድኖች የመጡ ሊሆኑ ስለሚችል ነው።
- ለልዩነቶች ጠንቃቃ መሆን መቻልን ለማጎልበት እና ሌሎችን ለመረዳት ብሎም ልዩነትን ለመቀበል ዝግጁ መሆን፣ ማዳመጥ እና መናገር እንዲችሉና ሠልጣኞች በእውነተኛ ውይይት ላይ እንዲሳተፉ አድርጎ ማብቃት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 4.11. የሰላም ግንባታ ዕሴቶችን ማጎልበት

የሰላም ትምህርት ለምን አክብሮትን፣ ርህራሄን፣ ኃላፊነትን፣ ዕርቀ ሰላምን እና ይቅርታን ተንከባክቦ ማጎልበት አለበት? እነዚህ ብቃቶች ለምን በጣም አስፈላጊ ሆኑ?

ከሌሎች ጋር አዎንታዊ ግንኙነቶችን ለማጠናከር እና ለእኛ ማኅበረሰቦች ሥነ ምግባራዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልገውን መሠረት ስለሚጥሉ አክብሮት፣ ርህራሄን፣ ዕርቀ ሰላም እና ይቅርታ የሰላማዊ ማኅበረሰብ መገንቢያ ዘዴዎች እንደሆኑ ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ። እነዚህ ቁልፍ እሴቶች የጋራ መግባባትን ለመንከባከብ፣ ሠልጣኞች ለብዝኃነት እና አክብሮት እንዲሁም የሰላም ባህልን ለመገንባት በሚያደርጉት ጉዞ ላይ አብሮ ለመዝለቅ እጅግ አስፈላጊ እንደመሆናቸው በዚህ የማሰልጠኛ ማንዋል ላይ በሙሉ እንዲካተቱ ተደርገዋል። አሠልጣኞች አክብሮትን፣ ርህራሄን፣ ኃላፊነትን፣ ዕርቀ ሰላምን እና ይቅርታ አድራጊነትን ሊታለፉ የማይችሉ አመለካከቶች እና ብቃቶች እንዲንከባከቧቸው እና እንዲያጎለብቷቸው ሠልጣኞችን ማበረታታት አለባቸው። ተማሪዎች የትኞቹ መልካም ሥነ ምግባር አስፈላጊ እንደሆኑ አውቀው ለመተግበርእና ለሁሉም ሰው ክብርን ለመስጠት የራሳቸውን  እሴቶች በአዎንታዊ መንገድ ማጎልበት ይጠበቅባቸዋል።

**መከባበር**

መከባበር ሁለንተናዊ ሰላምን፣ ሰብዓዊ መብቶች እና ሰብዓዊ ክብርን ለማስፈን ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ መከባበር ሰላምን ለመገንባት መሠረታዊ ብቃት ሲሆን በዙሪያችን ከሚገኙ ግለሰቦች ጋር ግንኙነቶችን ለመፍጠርና ለመገንባት አስፈላጊ ክህሎትና ችሎታ ነው። በመሆኑም ከሌሎች ጋር ጓደኝነትን መገንባት የምንችለው ለሌሎች ክብርና  ዕውቅና መስጠት ስንችል ነው።

መከባበርን እንደ ታዛዥነት ልናየው እንችላለን። መከባበር ማለት በዙሪያችን ላሉ ሰዎች ለባህላቸው፣ ለእምነታቸው እና ለአስተሳሰባቸው አክብሮትን እና አድናቆትን ማሳየት ነው። ከበላይ አካል የሚሰጥ መመሪያን አክብሮ መተግበርም ማለት ነው። ይሁን እንጂ መከባበር ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት በዓውድ ውስጥ ሆኖ ማየት አስፈላጊ በመሆኑ አሠልጣኞች ሠልጣኞች ሰውን አክባሪ እንዲሆኑ ለማገዝ የኢትዮጵያውያን ዓውድ ምን እንደሚመስል በሚገባ መረዳት ይኖርባቸዋል።

**ሣጥን 9፦ የመከባበር እና ታዛዥነት ንጽጽር ተግባራዊ ምሳሌ**

አስቴር የ14 ዓመት ኢትዮጵያዊት ነች ። እናቷ ለእራት አትክልት ገዝታ እንድትመጣ ትልካታለች። አስቴር ሁልጊዜ እንደምታደርገው ከአንዳንድ የሰፈሯ ልጆች ጋር እየተጫወተች ነበር። ወላጆቿ ከትምህርት ቤት ስትመለስ ለሁለት ሰዓታት ብቻ ከጓደኞቿ ጋር እንድትጫወት ይፈቅዱላታል። የጨዋታ ጊዜዋ ገና ስላላለቀና 20 ደቂቃ ስለሚቀራት ተጫውታ ስትጨርስ ወደ ገበያው እንደምትሄድ ነገረቻት። እናቷ አትክልቱን ምግብ ለማዘጋጀት በአስቸኳይ ያስፈልጋት ስለነበረ በአስቴር መልስ በጣም ተናደደች። በአፋጣኝ ወደ ገበያው እንድትሄድ አስቴር ላይ ጮኸችባት። አስቴር አሁንም ተጫውታ ለመጨረስ 20 ደቂቃ እንደሚቀራት እና ልክ ስትጨርስ እንደምትሄድ ከቅሬታ ጋር መልስ ሰጠች።

አስቴር አክብሮት ወይስ ታዛዥነት የጎደላት ነች?

**ሩህርህነት**

ሩህርህነት ከሌሎች ጋር በስሜት የመገናኘት እና ሌሎች ሰዎች ምን እየተሰማቸው እንደሆነ ለመረዳት የመሞከር ድርጊት ነው። ሩህርህነት በጭንቅላታችን እና በልባችን በሁለቱም በማዳመጥ ይጀምራል። ከራሳችን የግንዛቤ ማዕቀፍ ወጥተን ለመሄድ ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል። ሩህርህነት በተጨማሪ «ራስን በሌሎች ጫማ ውስጥ ከቶ የማየት» ብቃት ነው፡፡ እንዲሁም እንዴት ዓይነት ጠባይ ለሌሎች ማሳየት እንዳለብን፣ ምን ምላሽ መስጠት እንዳለብን እና ሌላው ሰው እየተሰማው ያለውን ስሜት እንዲሰማን ማድረግ ማለት ነው። ሌሎች ሰዎች ቢያስቀይሙን እንኳን አዛኝነት በውስጣችን ካለ ሩህርህነትን እና ሰብአዊነትን በመፍጠር ራሳችንን በሌሎች ቦታ አድርገን ማየት እንድንችል ያስችለናል።

**ኃላፊነት**

ብቻችንን ተነጥለን መኖር አንችልም፣ እያንዳንዱ እርምጃችን በሌሎች እና በዙሪያችን ባለው ዓለም ላይ የሚያስከትለው ውጤት አለ። ኃላፊነት የግለሰብ ዕሴት የመሆኑን ያክል ለማኅበረሰባችን እና ለዓለማችን እንክብካቤ የማድረግ የጋራ ኃላፊነት አለብን። በተጨማሪም ኃላፊነት ለማኅበረሰባችን ሥነ ምግባራዊ ፍላጎቶች ብሎም ለእኛ የጋራ ሰብአዊነት እና የርስ በርስ ግንኙነት ምላሽ የመስጠት ችሎታ እንደሆነ ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል።

**ይቅርታ**

የተቋረጡ ግንኙነቶችን ማስተካከል፣ ሌሎችን ይቅር ማለት ካልቻልን እና ግንኙነቶችን ወደ ነበሩበት መመለስ ካልቻልን እንዴት ሰላምን መገንባት እንችላለን? ይቅርታ ማድረግ የወደፊቱን ሕይወት በማየት እና ራሳችንን ለመፈወስ በሌሎች የተፈጠረውን ሕመም ዕውቅና ለመስጠት እና የተፈጠረውን ችግር እስከ ወዲያኛው እንዳይመለስ አድርጎ ለመሸኘት የሚያስችል ዓይነተኛ መንገድ ነው።

**ዕርቀ-ሰላም**

ዕርቀ ሰላም የተሰበረ ግንኙነትን ለመጠገን፣ አስቸጋሪ ሁኔታን ወደ ነበረበት ጥሩ ደረጃ ለመመለስ እና ግንኙነቶችን እና ራሳችንን ወደ መልካም ደረጃ ለማሸጋገር ንግግርን እና ፈቃደኝነትን ይፈልጋል። ረዥም እና ዘላቂነት ያለውን ሰላም ለመገንባት እና በተከፋፈሉ ማኅበረሰቦች መካከል

መተማመንን ለመፍጠር ዕርቀ ሰላም ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ዕርቀ ሰላም ለውጥን እና ሽግግርን ዋጋ ለሚሰጥ ሕይወት፣ ልዩነቶችን እና ግጭቶችን መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችልና ሁሉን አካታች ሰላማዊ ማኅበረሰብን በመገንባት ወደፊት ለመገሥገሥ እንዲቻል የሚያግዝ የአቀራረብ ዘዴ ነው።

## 4.12 የቡድን ስራ እና የመተባበር ክህሎት

የትብብር እና የቡድን ሥራ ግለሰቦች የጋራ ግባቸውን አንድ ላይ  በቀላሉ ለማሳካት ይጠቅማል። ሰላማዊ እና አካታች ማኅበረሰብ ለመገንባት በሚደረገው ጉዞ ትብብር እና የቡድን ሥራ  አዎንታዊ ግንኙነቶችን እና ለሰላም ግንባታ ኅብረቶችን ለመገንባት የሚያስችሉ ቁልፍ ብቃቶች ናቸው። የሰላም ግንባታ ሰፋ ተደርጎ ሲታይ ግንኙነትን በመገንባት አንድ የጋራ ግብ ላይ ለመድረስ ብዝኃነት ባለባቸው ቡድኖች በመተባበር እና አንድ ላይ በመሥራት ለሰላም ግንባታ አስፈላጊ የሆኑትን ብቃቶች ለማጎልበት ቁልፍ የሆነ ሚና ይጫወታል።

አብዛኛውን ጊዜ ትብብርን እና የቡድን ሥራ ብቃቶችን ለማጎልበት የተጠቆሙት ልምምዶች የኅብረት ጨዋታዎችን እና ስፖርቶችን ያካትታል።  የኅብረት ጨዋታዎች እና ስፖርት ሠልጣኞች ከአንድ ግብ ላይ ለመድረስ ተማሪዎች የተቀመጡ ተግባራትን አንድ ላይ እንዲያከናውኑ ያስችላቸዋል። ሆኖም ግን ሁሉም ሰው ካልተባበረ እና አስተዋፅኦ ካላደረገ በቀር ዒላማውን መምታት አይቻልም። የኅብረት ጨዋታዎች አሠልጣኞች እና ተማሪዎች መከናወን ያለበትን ተግባር ለማከናወን ሲቃረቡ ልዩነቶችን እና ተመሳሳይነቶችን አሠልጣኞች እና ሠልጣኞች እንዲያስሱ ያስችላቸዋል። ሆኖም ግን ማንንም እንደ አሸናፊ እና እንደ ተሸናፊ በማይገልጽ መልኩ አሠልጣኞች ለትብብር እና የቡድን ሥራ ፍትሐዊ እና አክባሪ የሆነ ለሁሉም ምቹ ድባብን መፈጠር ይኖርባቸዋል። ከዚህ ይልቅ የትብብር እና የቡድን ሥራ እንደ የሰላም ብቃቶች ስኬት ላይ አፅዕኖትን ይሰጣል።

# ምዕራፍ 5፦ ሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት

## *5.1 የሥርዓተ ጾታ መግቢያ*

እንደ ዩኔስኮ (2003) አገላለጽ፣

> *ሥርዓተ ጾታ በቤተሰቦቻችን፣ በማኅበረሰባችን እና በባህላችን ውስጥ የተፈጠሩ ወንዶች እና ሴቶች ያላቸውን ሚና እና ኃላፊነቶች ይመለከታል። ሥርዓተ ጾታ የሚለው ፅንሰ ሐሳብ በተጨማሪ የሴቶች እና የወንዶች ጠባይ፣ ችሎታ እና መሰል ባሕሪያት እንደዚህ መሆን አለባቸው ተብለው የተቀመጡ ተጠባቂ ሁኔታዎችንም ያካትታል።*

ስለ ሴቶች እና ወንዶች፤ ተባዕትነት እና እንስትነት ያሉ ልማዶችና ዕሳቤዎች በግለሰቦች አመለካከት እና ግለሰቦች ህይወታቸውን ሊመሩበት በሚችሉበት መንገድ እንዲሁም በውስጣዊ ፖሊሲዎችና ፖለቲካ ላይ ሰፊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡


ድሮም ሆነ ዛሬ በዓለም ዙሪያ ያሉ ወንዶች እና ሴቶች እኩል የሆነ ኃይል እና መብት ጨብጠው አያውቁም። እ.ኤ.አ 2018 በኢትዮጵያ ካቢኔ ውስጥ ሴቶች 50% ቦታ የያዙ ሲሆን ሴት የኢትጵያ ፕሬዝዳንት፣ የ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና የምርጫ ስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው ተሹመዋል። ምንም እንኳ እነዚህ ታላላቅ ስኬቶች ቢኖሩም ሴቶች ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ኋላ ቀርተዋል። ሴቶች በሁሉም ዋነኛ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ዘርፍ ውስጥ ዝቅተኛ ሚና ይጫወታሉ፤ እንዲሁም በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚዊ እና በፖለቲካዊ መስኮች ከወንድ አቻዎቻቸው አንጻር ሲታዩ ማግለልና መድልዎ ይፈጸምባቸዋል።

የሥርዓተ ጾታ እኩልነት መሠረታዊ ሰብአዊ መብት ነው። የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ሲባል «ወንዶችና ሴቶች ሙሉ ሰብአዊ መብቶቻቸውን ለማረጋገጥ እና በኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ልማት አስተዋፅኦ ለማድረግ እና ተጠቃሚ ለመሆን እኩል ዕድል ይኖራቸዋል» ማለት ነው (UNESCO, 2003)። የተባበሩት መንግሥታት 5ኛው የዘላቂ ልማት ግብ «ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ለትምህርት፣ ለጤና እንክብካቤ፣ ተቀባይነት ላለው ሥራ፣ እና በፖለቲካ እና በኢኮኖሚ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ውክልና ለማግኘት የሚችሉበትን እኩል ዕድል በመስጠት ዘላቂነት ያለውን ልማት ያቀጣጥላል፤ እንዲሁም ማኅበረሰቦችን እና በአጠቃላይ የሰው ልጅን መጥቀም» የሚል ዓላማ አለው (United Nations, 2019)።

የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ከሥርዓተ ጾታ ርትዓዊነት የተለየ ነው። የሥርዓተ ጾታ ርትዓዊነት ስንል «ለወንዶች እና ለሴቶች ፍትሐዊ የመሆን ሂደት» ማለታችን ነው። ፍትሐዊ መሆን ማለት ሴቶች እና ወንዶች በእኩል የመጫወቻ ሜዳ ላይ እንዳይጫወቱ ለተከላከሏቸው ታሪካዊ እና ማኅበራዊ አጉል ሁኔታዎች ካሣ እንዲያገኙ ማድረግ ማለት ነው (UNESCO, 2003)።

በሥርዓተ ጾታ እኩልነት እና በሥርዓተ ጾታ ርትዓዊነት ፅንሰ ሐሳቦች መካከል ያለውን ልዩነት በተሻለ መንገድ ለመረዳት ምስል 1ን ይመልከቱ። እኩልነትን በመጠቀም አንድ ሕፃን፣ ታዳጊ ወጣት እና ጎልማሳ ወንድ እያንዳንዳቸው የስፖርት ግጥሚያን በአጥር አሻግሮ ለማየት አንድ ዓይነት መጠን ያላቸው ሣጥኖች ተሰጥቷቸዋል። የሣጥኖችን አሰጣጥ ብቻ ከተመለከትን የተሰጡት ለሁሉም እኩል በሆነ መንገድ ነው፡፡ ሆኖም ከእነዚህ ሰዎች መካከል ሕፃኑ (በቁመት አጭሩ) በአጥሩ አሻግሮ ለማየት አልቻለም እና ይህ በመሆኑም ሦስቱም አንድ ላይ የስፖርት ግጥሚያውን ማየት አልቻሉም። ስለዚህ ርትዓዊነት ጥቅም ላይ ውሎ ቢሆን ኖሮ ሕፃኑ ሁለት ሣጥኖች በተሰጡት፤ ታዳጊውም አንድ ሣጥን ባገኘ እና ጎልማሳው ሰው ምንም ሣጥን ባልተሰጠው ነበረ። እንዲህ ዓይነቱ የሣጥኖች ክፍፍል ሦስቱም አንድ ላይ ከአጥሩ ባሻገር እንዲያዩ ያስችላቸዋል።

**ምስል1፦ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት እና የሥርዓተ ጾታ ርትዓዊነት ንጽጽር**




*ምንጭ፦* Angus Maguire

## *5.2 ሥርዓተ ጾታን ማካተት*

እንደ ተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ምክር ቤት /United Nations Economic and Social Council (2010) አገላለጽ የሥርዓተ ጾታ ማካተት ማለት «...የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን ለማስፈን እና ሴቶችን ለማብቃት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘ ስትራቴጂ» ነው (p. 1)። በተባበሩት መንግስታት የሥርዓተ ጾታ እኩልነትና ሴቶችን የማብቃት ኤጀንሲ /UN Women/ (2019) እንደሚከተለው ይገልጸዋል፦

> «የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ግብን ለማሳካት እንዲቻል ተብለው ተመዋነውና ተመርጠው የተዘጋጁ ውስን ስትራቴጂያዊ አቀራረቦችን እንዲሁም ቴክኒካዊ እና ተቋማዊ ሂደቶች ስብስብ ሲሆን አድሏዊ ማኅበራዊ ተቋማትን፣ ሕግ ድንጋጌዎችን፣ ባህላዊ ልማዶችን እና እንደ ሴቶች ንብረት የመያዝ መብታቸውን የሚገድቡ ወይም በሕዝባዊ ቦታ ላይ የመገኘት መብታቸው ላይ ገደብ የሚጥሉ የማኅበረሰብ አሠራር ልማዶችን የመቀየር ዓላማ አለው»።

የሥርዓተ ጾታ ማካተት ሴቶች እና ወንዶች በሃብት ክፍፍል፣ በልማት ጥቅማ ጥቅሞች እና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እኩል መብት እና የበላይነት እንጻላቸው የማረጋገጥ ሂደት ነው። በሕግ፣ በፖሊሲዎች እና በመርሐ ግብሮች አቀራረጽ፣ አፈጻጸም እና ምዘና ላይ የሴቶች እና የወንዶች ፍላጎቶች እና ተሞክሮዎች ከግምት እንደገቡ ማረጋገጫ ስትራቴጂ ነው። ይህም ስትራቴጂ ሴቶች እና ወንዶች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና የእኩልነት መነፈግ እንዳይቀጥል ሁሉንም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ያካትታል።

የሥርዓተ ጾታ ማካተት ፅንሰ ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ የተደረገው እ.አ.አ 1985 ናይሮቢ፣ ኬንያ ውስጥ በተዘጋጀው በተባበሩት መንግሥታት ሦስተኛው የሴቶች ጉዳይ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ ላይ የነበረ ቢሆንም ፅንሰ ሐሳቡ ይበልጥ እስኪጎለብት ድረስ አስርት ዓመታትን ወስዶበታል። በ1995 የተደረገው የተባበሩት መንግሥታት አራተኛው የሴቶች ጉዳይ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንስ የሴቶችን መብት በማስከበር እንቅስቃሴ ላይ በጣም ተራማጅ ከሆኑት ፅቅዶች እንደ አንዱ የሚቆጠረውን የቤጅንግ መግለጫና የድርጊት መርሐ ግብር /Beijing Declaration and Platform for

Action/ በማጽደቅ ተጠናቋል። የቤጅንግ መግለጫና የድርጊት መርሐ ግብር የሚከተለውን ደንግጓል፦

> «ውሳኔዎች ከመወሰናቸው በፊት በሴቶች እና በወንዶች ሊኖራቸው የሚችለው ተጽዕኖን በተመለከተ በቂ ትንታኔ እንዲሰጥ መንግሥታት እና ሌሎች ተዋንያን በሁሉም ፖሊሲዎች እና መርሐ ግብሮች ላይ ሥርዓተ ጾታን ለማካተት ንቁ እና በግልጽ የሚታይ ፖሊሲን ማበረታታት አለባቸው» (ገጽ 46) ።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሥርዓተ ጾታ ቅንጅት ከሥርዓተ ጾታ ማካተት ጋር እንደ አቻ ብያኔ ተቆጥሮ ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል፡፡ አሁን ያለው አዝማሚያ ባለበት ከቀጠለ የሥርዓተ ጾታ ቅንጅት ይበልጥ ጥቅም ላይ የሚውል ቃል ሊሆን ይችላል። ለዚህ ውይይት ዓላማ ሲባል የሥርዓተ ጾታ ማካተት የሚለውን ቃል እንጠቀማለን።

### ስለ ሥርዓተ ጾታ ማካተት  የተዛቡ አመለካከቶች

ሥርዓተ ጾታን ማካተት የራሱ ተቀናቃኞች አሉት። አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች ግን ክርክራቸውን መሠረት የሚያደርጉት በተዛቡ አመለካከቶች እና እውነተኛ ባልሆኑ ምክንያቶች ነው። ሥርዓተ ጾታን በማካተት ዙሪያ ያሉት ዋነኛ የተዛቡ አመለካከቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

- **ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች ያደላል፦** በእርግጥ ሥርዓተ ጾታን ማካተት የሴቶች ብቻ ጉዳይ ሳይሆን ወንዶችንም ይመለከታል። ሥርዓተ ጾታን በማካተት ወንዶች እና ሴቶች እኩል ተጠቃሚ መሆን መቻላቸውን እና መርሐ-ግብሮችና  ፖሊሲዎች ማናቸውም ላይ ጫና እንዳላሳረፉ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ሴቶች በተለየ በደል የሚደርስባቸው እንደመሆኑ ይበልጥ ተጠቂ ሊሆኑ ይችላሉ። የማካተት ውጤቶች የወንዶችን ተሳታፊነት የሚያበረታቱ ፖሊሲዎች እንዲወጡ የሆኑበት ገጠመኞች አሉ። ለምሳሌ፦ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ እንዳለችው ሌሴቶ በመሳሰሉ አንዳንድ አገሮች ወንዶች በበዓል ቀን እንስሳትን እንዲያግዱ ኃላፊነት ስለሚጣልባቸውና በዚህም ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ ስለሚከለከሉ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲያስመዘገቡ የሚያበረታቱ መርሐ ግብሮች ያስፈልጓቸዋል። የእኩልነት አለመኖር በሁለቱም ፆታ ላይ ተፈጻሚ ሊሆን ስለሚችል  ሁለቱም ፆታዎች በሥርዓተ ጾታ ማካተት ሊታቀፉ ይገባል።

- **ሴቶች እና ወንዶች ድሮም ቢሆን እኩል ናቸው፦** ሴቶች በበርካታ ማኅበረሰቦች ውስጥ ለመብታቸው ረዥም መንገድ መሄዳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጤና፣ በትምህርት፣ በሥራ ቅጥር እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ አሁንም ድረስ ከወንዶች አንፃር ወደ ኋላ እንደቀሩ ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በሁሉም መስኮች በጾታዎች መካከል እኩልነትን ያሰፈነ አንድም አገር የለም።

- ***ሥርዓተ ጾታን ማካተት ጠቀሜታው ከሴቶች እና ከችግሮቻቸው ጋር ለተገናኙ ፖሊሲዎች ብቻ ነው፦*** የማካተት ዋናው ነጥብ ሴቶችን ከማግለል እና ወደ ጎን ከመተው ይልቅ በሁሉም ፖሊሲዎች እና መርሐ-ግብሮች ላይ የሴቶችን አመለካከቶች እና ፍላጎቶች እንዲካተቱ ማድረግ ነው።

### የሥርዓተ ጾታ ማካተት  ማስጀመሪያ ነጥቦች

ለሥርዓተ ጾታ ማካተት በርካታ ማስጀመሪያ ነጥቦች አሉ። የዓለም ባንክ ሦስቱን ያስቀምጣል፤ እነዚህም በተቋም፣ በፖሊሲ እና በመርሐ-ግብር ደረጃ የተለዩ ናቸው።

### ሣጥን 10፦ የሥርዓተ ጾታ ማካተት አንዳንድ መርሆዎች

- **ሥርዓተ ጾታ ተኮር ቋንቋን መጠቀም፦** ለምሳሌ ሴቶች ደካማ እና ለስላሳ እንደሆኑ እና ወንዶች ደግሞ ደፋር እና ኃይለኛ እንደሆኑ አድርጎ ቋንቋ መሰየም የለበትም።
- ሥርዓተ ጾታ ተኮር የመረጃ አሰባሰብ እና ትንታኔ።
- አገልግሎቶችን ለማግኘትና እና ለመጠቀም እኩል ዕድል ማግኘት።
- ሴቶች እና ወንዶች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሁለቱም እኩል መሳተፍ አለባቸው።
- በአመራር ሂደት ላይ በእኩልነት መስተናገድ ይኖርባቸዋል።

የሥርዓተ ጾታ ማካተት በተቋም ደረጃ ቢተገበር በከፍተኛ ደረጃ ተመራጭ ነው ። ሥርዓተ ጾታ በዚህ ደረጃ ላይ እንዲካተት ከተደረገ ሁሉም የተቋሙ ፖሊሲዎች እና መርሐ-ግብሮች ሥርዓተ ጾታን ያካትቱታል። እንዲህ ሲባል ተቋማትን መለወጥ በጣም ፈታኝ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ከአመራሩ ቁርጠኝነት ካልኖረ፣ በግልጽ ተፈጻሚ የሚሆኑ ፖሊሲዎች ከሌሉ እና አስፈላጊው የሰው ሃብት እና የገንዘብ ምንጮች ካልተገኙ በቀር ብዙውን ጊዜ ቀስ በቀስ ተፈጻሚ የሚሆን ነው።

በፖሊሲ ደረጃ የሥርዓተ ጾታን ማካተት ስንል ፖሊሲዎችን የሚደግፉ መርሐ ግብሮችን በማስፋፋት ሥርዓተ ጾታን ለማካተት የተሻለ አማራጭ ነው። በመርሐ-ግብር ደረጃ ሥርዓተ ጾታን ማካተት በጣም የተለመደና ለትግበራም ቀላል የሆነ ማስጀመሪያ ነጥብ ነው።

በመርሐ-ግብር ቀረጻ ላይ የሥርዓተ ጾታ ማካተት የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፦

- በፕሮጀክት ቀረጻ ምክክሮች እና ትንታኔ ላይ ወንዶችን እና ሴቶችን ማሳተፍ፣
- ጥናትና ትንታኔው ላይ በጾታ የተከፋፈለውን መረጃ ማካተት እና የመርሐ ግብሩን ምክንያታዊነት ማካተት እና
- ሥርዓተ ጾታ ተኮር ወይም በሥርዓተ ጾታ የተወሰኑ ዓላማዎችን፣ ጠቋሚዎችን እና እንቅስቃሴዎችን መቀመር።

ሥርዓተ ጾታ የተካተተበት ፕሮጄክት በሠራተኞች እና ከፍተኛ ባለሙያዎች ምልመላ እና በፕሮጄክቱ ሥር በሚገነባው ተቋማዊ መዋቅር ውስጥ ባለው ውክልና ላይ የሥርዓተ ጾታ ሚዛን እንዲጠበቅ ለማድረግ ይጥራል። ሴቶች እና ወንዶች እኩል ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል። ፕሮጄክቱ በተጨማሪ በሥርዓተ ጾታ እኩልነት ላይ የውጤት ምዘናን ያካትታል። እንዲሁም በሥርዓተ ጾታ ላይ ከፍተኛ ዕውቀት ያለው ሰው በፕሮጄክቱ የምዘና ቡድን ውስጥ አባል ይሆናል።

**የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ ጥያቄ**

- በፕሮጀክት ዑደት ውስጥ ለሥርዓተ ጾታ ማካተት ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ስትራቴጂዎችን አብራሩ፡፡

## *5.3 ሴቶች፣ ሰላም እና ደህንነት*

ሴቶች በሰላም እና በደህንነት ጉዳይ ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመሆኑም የሚከተሉትን ከግምት ማስገባት አስፈላጊ ነው፦

- ሴቶች በሰላም ማስፈን ሂደት ውስጥ ለምን መሳተፍ እንዳለባቸው መረዳት፤
- በሰላም እና የደህንነት ኦፕሬሽኖች ላይ ሴቶች እንዴት ሊሳተፉ እንደሚችሉ ከግምት ማስገባት፤
- ከሴቶች፣ ከሰላም እና ከደህንነት ጋር የተገናኙ ዓለም አቀፍ ሕጎችን የተመለከተ ግንዛቤን ማሳደግ።

በጦርነት ወቅት ሴቶች በከፍተኛ ደረጃ ጉዳት ይደርስባቸዋል። ብዙውን ጊዜ ለመረጋጋት፣ ለተሐድሶ እና ወደፊት ግጭት እንዳይቀጥል ይከራከራሉ። ሴቶች ለየት ያለ አመለካከትን ማንፀባረቅ ስለሚችሉ በሰላም እና ደህንነት ኦፕሬሽኖች ላይ ሊሳተፉ እና ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። የሰላም ስምምነቶች፣ ድኅረ ግጭት መልሶ ግንባታዎች እና በሕዝብ አስተዳደር ላይ ሴቶች እንዲሳተፉ ከተደረጉ ለረዥም ጊዜ ስኬታማ የመሆን ዕድላቸው ከፍ ይላል። በተጨማሪም ዘላቂ የሆነ ሰላምን መመሥረት ይበልጥ ርትዓዊ የሆነ የሥርዓተ ጾታ ዝምድናን ማረጋገጥን ጨምሮ የኃይል ዝምድናዎችን መለወጥን ይጠይቃል።

በድኅረ ግጭት እና ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ወቅቶች እንዲሁም በድርድር ጊዜ ሴቶች ውክልና እንዲያገኙ እና እኩልነትን እንዲጎናፀፉ መደረግ አለበት። ስርዓተ ፆታን ማካተት ሴቶች እንደ ማኅበረሰቡ አባልነታቸው ለእነርሱ ቅድሚያ ሰጪ በሆኑ ጉዳዮች፣ ውክልናዎችና ፖሊሲዎች ላይ እንዲከራከሩ ስትራቴጂያዊ እና እንደቀላል የማይታዩ ዕድሎችን ያጎናጽፋቸዋል።

> «ሴቶች ከሰላም ስምምነት ድርድሮች እና ከአስፈጻሚ አካላት በስልታዊ መንገድ" እንዲገለሉ የማድረግ ድርጊት እንዲህ ያሉት የሰላም ስምምነቶች በስተመጨረሻ የሚፈርሱበት እና አገሮች ወደ ግጭት ተመልሰው ከሚገቡባቸው ምክንያቶች አንዱ ምክንያት ነው።»
>
> *Don Steinberg, USAID*

### ሣጥን 11፡- ፊልም *Pray the Devil Back to Hell*

የ2008ቱ *Pray the Devil Back to Hell* የተባለው ዘጋቢ ፊልም ሁለቱም ሙስሊም እና ክርስቲያን በሺሕዎች የሚቆጠሩ የላይቤሪያ ሴቶች እንዴት የአገሪቱን የእርስ በርስ ጦርነት በመቃወም አንድ ላይ እንደቆሙ አንድ በአንድ ነቅሶ ያሳያል። ሴቶቹ የወሰዷቸው እርምጃዎች ሰላም እንዲመጣ አግዟል። ይህ ግጭት በሚኖርበት ጊዜ ለሰላም ግንባታ ሴቶች ሊጫወቱትን የሚችሉትን አስፈላጊ የሆነ ሚና የሚያሳይ ምሳሌ ነው።




ላይቤሪያ ውስጥ ሰላም እንዲከበር ሰልፍ የወጡ ሴቶችን የሚያሳይ

ሴቶችን ማሳተፍ ማለት ከዚህ ቀደም በግጭት ምክንያት ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች ሥነ ልቦናዊ እና ማኅበራዊ ድጋፍ መስጠት፤፣ የጤና እና የትምህርት ሥርዓቶችን ወደ ነበሩበት መመለስ፣፤ የተፈናቀሉ ሰዎችን እና የሕገወጥ ሰው ዝውውር ሰለባዎችን ወደ ቀዬቸው እንዲመለሱ ማድረግ ነው።

ሴቶች በአንዳንድ በአፍሪካ ኅብረት እና ሌሎች ተቋማት በተዘጋጁ ውይይቶች ላይ የሽምግልና ቡድኖችን ተቀላቅለው ያውቃሉ፤ ሆኖም ግን በማናቸውም በተባበሩት መንግሥታት በተዘጋጁ የሰላም ውይይቶች ላይ አንድም ጊዜ ዋና ወይም መሪ የሰላም አሸማጋይ ሆነው ተሹመው አያውቁም። በቅርብ ጊዜ ያጋጠመ አዎንታዊ ነገር ቢኖር የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ኒልሰን ማንዴል ባለቤት  ግራሺያ ማሼል የሠሩት ሥራ ነው። ሚዝ ማሼል በ2008 ኢጋጥሞ በነበረው የኬንያ ቀውስ ከተመረጡት ሦስት አሸማጋዮች መካከል አንደኛዋ ሆነው አገልግለዋል። ሌላኛው አዎንታዊ ምሳሌ፡-በአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር የሴቶች፣ የሰላም እና የደኅንነት ልዩ ልዑክ ሆነው በ2014 የተሾሙት የቢኔታ ዲዮፕ ሹመት ነው።

**ምስል 2፡- ሴቶች በሰላም ሂደቶች ውስጥ**




ምንጭ፡- IPSS/AAU, 2017

በሣጥን 12 ላይ ያሉት ምሳሌዎች፡- ከ Culture at Crossroads: Ethiopian women in peace-building የተወሰዱ ጽሑፎች በኢትዮጵያ ውስጥ ሴቶች በሰላም እና በሰላም ግንባታ ላይ እንዴት አስፈላጊ ሚና እንደሚጫወቱ ያሳያሉ። በግጭት ወቅት ሴቶች ብቻ የግጭቱ ሰለባ እንደሚሆኑ አድርጎ የሚያየውን ትርክት መለወጥ እጅግ አስፈላጊ ነው። ሴቶች ለሰላም ግንባታ፣ ሽምግልና ድርድር ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

**ሣጥን 12፦ ከ *Culture at Crossroads: Ethiopian women in peace-building* ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ**

ሴቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም እና ሰላም ግንባታ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ የሰላም ትርጉም በኢትዮጵያ ሰፊ የሆነ ፅንሰ ሐሳብ ነው። በሰሜን ኢትዮጵያ፣ በአማራ እና በትግራይ፣ ሰላም «የማሰብ ነጻነት እና በሰላም መንቀሳቀስ መቻል» የሚል ግርድፍ ትርጉም አለው። የአሩሲ ኦሮሞዎች በተወሰነ መልኩ ከዚህ ትንሽ ለየት የሚል የሰላም ምንነት ትርጉም አላቸው፦ እንደነሱ እምነት የሰላም መኖር በ Nageengaa መኖር የሚመረኮዝ ነው ይህም ቃል በግርድፉ እንደ «የባህል ዕሴቶችን ጠብቆ ማቆየት» በሚል ሊተረጐም ይችላል። በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ካሉት ከቦረናዎች ጋር የሚዋሰኑት አርብቶ አደሮቹ የሐመር ጐሣ አባላት በበኩላቸው ሰላምን የቡድን ማኅበራዊ ሕይወት የሚያብብበት፣ የአገር ሽማግሌዎች በጡረታ ዘመናቸው እፎይ የሚሉበት፣ ሕፃናት የሚጫወቱበት እና እንስሳት በሰላም የሚራቡበት ሁኔታ ነው በማለት ይገልጹታል።

በደቡባዊ ኦሞ ዞን ካሉት አርብቶ አደር ጎሣዎች መካከል አንዱ የሆነው የዳሰነች ጎሣ ተወላጆች ሰላምን *Shimit* በማለት ይገልጹታል፤ እንደነርሱ ትርጓሜ የመረጋጋት ምንጭ፣ የጦር መሣሪያዎች በእንስሳት ማገጃ በትር መቀያየር እና ወደ ማኅበረሰብ ልማት ትኩረትን ማዞር ማለት ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ የኛጋቶም አርብቶ አደር ማኅበረሰቦች ሰላምን *Excil* የሚሉት ሲሆን «ሃብት፣ ጤና፣ ዝናብ እና እርካታ» ከሚሉት ቃላት ጋር እኩል ትርጐም አለው።

በሶማሌ ክልል የሚኖሩ ሶማሌዎች ሰላምን *Nabadgalyo* የሚሉት ሲሆን «ሰላም» በሚል ሊተረጐም ይችላል። በጋምቤላ ክልል አኙዋኮች ሰላምን *Beet Meer* ይሉታል፤ የዚህም ትርጉም «በፍቅር መኖር» ማለት ነው። ኑዌሮች ደግሞ ሰላምን *Mal,* ሲሉት ትርጉሙም «ሙሉእነት» ማለት ነው።


እነዚህ በጥቂቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ የሰላም ትርጉም ምሳሌዎች ናቸው። ሰላም ሰፊ ፅንሰ ሐሳብ እንደ ሆነ እና ትርጉሙ እና ከስኬት ላይ መድረሻ ዘዴዎቹ ከቦታ ወደ ቦታ እንደሚለያዩ ያሳያሉ። በመሆኑም ሰላም በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ትርጉም እንዳለው መረዳት ይቻላል። በተጨማሪም ሰላም ማለት ሰዎች የት እንደሚኖሩ፣ የሚያጋጥማቸው ችግር፣ ሥርዓተ ጾታቸው እና ሃይማኖታዊ እምነታቸው ላይ የሚመረኮዝ ነው (IIRR, 2009, ገጽ 4-6)።

ሰላም ግንባታን በተመለከተ ሲንቄ የኦሮሞ ሴቶች የሥልጣን ትዕምርት ነው። በተለምዶ እናት ለልጇ በሠርጓ ቀን የምትሰጣት ረዥሙ ከዝግባ ዛፍ የተቆረጠ በትር በሴቷ ቁመት ልክ የሚቆረጥ ሆኖ ሴቷም በትሩን በቀኝ እጇ ትይዘዋለች። *የሲንቄ* ጠቀሜታ ብዙ ነው።ለምሳሌ፦ ግጭት በሚኖርበት ጊዜ የሚጋጩ ወገኖችን በማሸማገል *ሲንቄ* የሰላም ግንባታ ሚናን ይጫወታል።በተመሳሳይ መልኩ፣ የሲዳማ ሴቶችም ሲቄዋ የሚባል የሰላም በትር አላቸው። ሆኖም ግን ይህ በትር ጥቅም ላይ የሚውለው የሴትን ክብር ለመግለጽ ነው። የሲቄዋ ጥቅም በተጨማሪ የሴት የግጭት መፍቻ ዘዴ ከሆነው *ያካ* የሚባለው የሴቶች ቡድን መቋቋም ጋር አብሮ ጥቅም ላይ ይውላል (IIRR, 2009, ገጽ 12-13)።

ምንጭ፦ ከ IIRR, 2009 እንደ አስፈላጊነቱ ተመርጠውና ተመጥነው የተወሰዱ ጽሑፎች

በተባዕትነት እና በእንስትነት ዙሪያ በተገነቡ ማኅበራዊ ሥርዓተ ጾታዊ ሚናዎች ምክንያት በበርካታ የኢትዮጵያ ክፍሎች ውስጥ ሴቶች ወንዶችን ጀግና፣ ተዋጊ እና ኃይለኛ እንዲሆኑ ያበረታታሉ፤ በተጨማሪም ከጀግንነት ጋር የተያዘ ተባእታዊ ማንነትን በዘፈኖች፣ በሽለላዎች እና በግጥሞች ያበረታታሉ። ነገር ግን ሴቶች የግጭት መንሥዔ እና ራሳቸውም በግጭቱ በቀጥታ ተሳታፊዎች ሲሆኑ ይስተዋላል።

ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ የ IIRR ን የ 2009 ዕትም የሆነው Culture at Crossroads: Ethiopian women in peace-building የሚለውን ይመልከቱ።




**በሴቶች ላይ የሚደርስ ማናቸውንም ዓይነት ማግለል ለማስወገድ የወጣ ድንጋጌ**

በሴቶች ላይ የሚደርስ ማናቸውንም ዓይነት ማግለል ማስወገድ የሚለው ድንጋጌ /Convention on the Eliminatin of All Forms of Discriminiation Against Women (CEDAW)/ በተባበሩት መንግሥት ጠቅላላ ጉባዔ በ1979 ጸድቋል። ብዙውን ጊዜ የሴቶች መብቶች ዓለም አቀፍ ሰነድ እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል። በሴቶች ላይ የሚፈጸም መድልዎን ይገልጻል፤፣ በሁሉም ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ሕይወት ውስጥ በሴቶች ላይ የሚፈጸም መድልዎን በማስወገድ የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን ለማሳካት የሚያስፈልጉትን ሕጋዊ መመዘኛዎች ያስቀምጣል። በሴቶች ላይ የሚደርስ ማናቸውንም ዓይነት ማግለል ማስወገድ ድንጋጌ /CEDAW/ ያጸደቁ ወይም የተስማሙ አገሮች በስምምነቱ የመገዛት ሕጋዊ ግዴታ አለባቸው። ሴቶች ላይ የሚደርስ ማናቸውንም ዓይነት ማግለል ማስወገድ ድንጋጌ /CEDAW/ በየአገሩ ሕግ ላይ እንዲካተት የታለመ ሲሆን መንግሥታት የሴቶችን መብቶች ሙሉ በሙሉ ለማስከበር እንዲቻል የሚያስፈልጉ ስልቶችን ተፈጻሚ እንዲያደርጉ እና እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይጠበቅባቸዋል።

ኢትዮጵያ ይህን ድንጋጌ ተስማምታ የፈረመች ሲሆን  አንዳንድ አገሮች ግን በጭራሽ አላጸደቁትም። ኢራን፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ እና ደቡብ ሱዳን ለምሳሌ የሴቶች ላይ የሚደርስ ማናቸውንም ዓይነት ማግለል ማስወገድ ድንጋጌን /CEDAW/ አልፈረሙም። ከ50 በላይ አገሮች ብሔራዊ ሕጋቸው፣ ባህላቸው፣ ሃይማኖታቸው ወይም ልማዳቸው ከተወሰኑ አንቀጾች ጋር የሚጣጣሙ አለመሆናቸውን በመግለጽ በተወሰኑ አንቀጾች ላይ «ባለመስማማት ልዩነት» አስመዝግበው CEDAWን ፈርመዋል፤ በዚህም የስምምነቱን ጥንካሬ እና ሊያስገኝ የሚችለውን ውጤት እንዲዳከም አድርገዋል። ሌላኛው ድክመት የ CEDAWን ድንጋጌ የሚጥሱ አገሮችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችል ምንም ዓይነት ስርዓት አልተዘረጋለትም።

**አሳታፊ ጥያቄዎች**

1. ኢትዮጵያ በCEDAW የተቀመጡትን የደረጃ መስፈርቶች በማሟላት ረገድ ጥሩ ሥራ እየሠራች ነውን?
2. ዋነኛዎቹ ስኬቶቿስ ምንድን ናቸው?
3. ተፈጻሚ ያልሆኑ ግዴታዎቿስ የትኛዎቹ ናቸው?
4. በኢትዮጵያ ውስጥ ሥርዓተ ጾታ ላይ የተመረኮዙ ምን ዓይነት ችግሮች አሉ?
5. በእርስዎ ክልል ውስጥ ምን ዓይነት ሥርዓተ ጾታ ላይ የተመረኮዙ ችግሮች አሉ (የሴት ልጅ ግርዛት፣ ጠለፋ፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻ ወዘተ)?

**በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት ውሳኔ** (UNSCR 1325)

ሴቶችን ከሰላም እና ደህንነት አጀንዳ ጋር ማገናኘት እንደሚያስፈልግ በመጀመሪያ የተወሰነው በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታ ምክር ቤት ውሳኔ /United Nations Security Council Resolution (UNSCR)/፣ UNSCR 1325 ሲሆን ይህም ውሳኔ በተባበሩት መንግሥታት በጸጥታው ምክር ቤት በሙሉ ድምፅ ጸድቋል። በብሔራዊ፣ ክልላዊ እና ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ በግጭት መከላከል፣ መቆጣጠር እና መፍትሔ መስጫ ዘዴዎች፣ የሰላም ድርድሮች፣ የሰላም ኦፐሬሽኖች፣ እንደ ወታደሮች፣ ፖሊስ እና ሲቪል ዜጎች፣ እንደ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ልዩ ተወካዮች ጨምሮ በሁሉም የውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ላይ ሴቶች ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀርባል።

እንደ የስደተኛ ካምፖች ባሉ በድንገተኛ እና በሰብአዊ ቀውስ ወቅት UNSCR 1325 የሴቶችን መብቶች በማጠናከር ተጠያቂነትን ጨምሮ ሕግን በማስከበር በሴቶች ላይ ጥቃት እንዳይፈጸም ጥበቃ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ያቀርባል፦

- በጦር ወንጀል፣ በዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በሰው ዘር ላይ የሚፈጸም ወንጀል እና ሌሎች ዓለም አቀፍ ሕጎችን የጣሱ ሰዎችን ለሕግ ማቅረብ፤
- የስደተኞች ካምፖችን ሲቪላዊ እና ሰብአዊ ተፈጥሮ ማክበር፤
- በሰው ላይ የሚፈጸም ወንጀል፣ የጦር ወንጀል ወይም የዘር ማጥፋት ወንጀል ተደርገው ሊቆጠሩ ስለሚችሉ ወሲባዊ ጥቃቶችን የተመለከቱ ወንጀሎች በምህረት ስምምነቶች ላይ እንዳይካተቱ ማድረግ፤
- በብሔራዊ ሕጎች ሥር የሴቶችን መብቶች ማጠናከር እና
- የአካባቢ ሴቶችን የሰላም ሐሳቦች እና የግጭት መፍትሔ መስጫ ሂደቶችን መደገፍ።

እነዚህ ውጤታማ የጥበቃ ዘዴዎች እና የሴቶች እና የልጃገረዶች መብቶች ከስምሪት በፊት እና በሥልጠና ወቅት የሰላም ኦፖሬሽን ሠራተኞች እንዲማሯቸው ይደረጋል። ከዚህም በተጨማሪ UNSCR 1325 በሰላም ኦፐሬሽኖች ወቅት የሥርዓተ ጾታ አመለካከት እንዲካተት ይጠይቃል። ይህ ለሁሉም የተባበሩት መንግሥታት የሰላም ኦፐሬሽኖች የሥርዓተ ጾታ አማካሪዎችን መመደብ፣ በሁሉም መስኮች በፖሊሲ ዝግጅት እና ዲዛይን ላይ የሴቶችን እና ልጃገረዶችን የተለዩ ፍላጎቶችን ግምት ውስጥ ማስገባት እና በፖሊሲ እና መርሐ-ግብር ዝግጅት ላይ የሴቶች ድርጅቶችን አመለካከቶች፣ አስተዋፅኦዎች እና ተሞክሮዎች ማካተትን ይጨምራል።

ከ UNSCR 1325 በተጨማሪ የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት በሴቶች፣ ሰላም እና ደኅንነት ዙሪያ አራት ውሳኔዎችን አስተላልፏል፦

- ውሳኔ 1820 (2008) ከግጭት ጋር የተገናኘ ወሲባዊ ጥቃት ስለ መኖሩ ዕውቅና ይሰጣል።

- ውሳኔ 1888 (2009) የውሳኔ 1820 ትግበራን ያጠናክራል።
- ውሳኔ 1889 (2009) በሰላም ሂደት እና ሰላም ግንባታ ላይ በሴቶች ተሳትፎ ላይ ያሉ መሰናክሎችን የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል።
- ውሳኔ 1960 (2010) ለውሳኔ 1820 እና 1888 ትግበራ ተጠያቂነትን ያስቀምጣል።

አንድ ላይ እነዚህ ውሳኔዎች በግጭት በተጠቁ አገሮች ውስጥ ያሉ ሴቶችን ሁኔታ ለማሻሻል የሚጠቅም ወሳኝነት ያለውን ማዕቀፍ ያቀርባሉ ። በአብዛኛው የሴቶች ተሳትፎ እና እኩልነት እንዲሰፍን በተደረገባቸው ሁኔታዎች ላይ ሴቶች ራሳቸው ጠንካራ እና አስፈላጊ ሚና ተጫውተዋል። ከሲቪል ማኅበረሰብ፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከተመረጡ አካላት ወይም ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ አንድ ላይ በቡድን በመንቀሳቀስ ሴቶች ከወንድ አጋሮች ጋር አብሮ በመሥራት በሰላም እና ደህንነት አጀንዳ የሴቶችን ተሳትፎ ለማበረታታት በ CEDAW እና UNSCR 1325 ዙሪያ ተሳትፎ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይገልፃል።

**የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቂያ ነጥቦች**

1. ሴቶችን በሰላም ሂደቶች እና የደኅንነት ኦፕሬሽኖች ላይ ማሳተፍ አስፈላጊ እንደሆነ የሚያስገድዱ በርካታ ምክንያቶች አሉ ፡፡ ከምክንያቶቹም አንዱ ሴቶች ካልተሳተፉ እነዚህ ሂደቶች ብዙውን ጊዜ ሳይሳኩ መቅረታቸው ነው።
2. ሴቶችን ማሳተፍ የሚያስገኘው ጥቅም ዕውቅና እያገኘ ያለ ቢሆንም አሁንም ድረስ ሴቶችን የማሰተፉ ጉዳይ በቂ ትኩረት አልተሰጠውም።
3. እንደ CEDAW፣ እና የተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት 1325 ያሉ ውሳኔዎች የሴቶችን ተሳትፎ ያበረታታሉ። ሆኖም በአብዛኛዎቹ ተዋንያን ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ መደረግ ይኖርባቸዋል።
4. የእነዚህን ዘዴዎች ትግበራ ለማበረታታት እንዲችሉ እና በሰላም እና የደኅንነት አጀንዳ ውስጥ ሴቶችን ለማካተት ለሴቶች በርካታ ዕድሎች አሉ።

## *5.4 ሴቶች፣ ህፃናትና የአገር ውስጥ ተፈናቃይነት*

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ፣ በአፍሪካ ብሎም በመላው ዓለም ከቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎችን ብዛት የሚያሳይ አስደንጋጭ ቁጥርን ማየት ይቻላል። እንዲህም ሆኖ ግን የእነዚህን ተፈናቃይ ሰዎች ትክክለኛ ብዛት በተመለከተ በትክክል የተቀመጠ ከስምምነት የተደረሰበት ቁጥር የለም።

ግጭቶች የሚከናወኑባቸው መንገድ በጊዜ ሂደት እየተለወጠ እንደ መሄዱ ሴቶች፣ ሕፃናት እና ሌሎች ሲቪሎች ላይ የከፋ ጉዳት ያስከትላል። አሁን ላይ እየተደረጉ ባሉ ግጭቶች የግጭት ሰለባዎቹ አብዛኛዎቹ ሰዎች ሲቪሎች ሲሆኑ ሴቶች እና ሕፃናት ይበልጥ ተጎጂ ናቸው። የማኅበረሰብ ወይም የአንድ ብሔር አባላትን ለማጥቃት፣ የበላይነትን ለማግኘት፣ ፍርሃትን ለመንዛት፣ ለመቅጣት እና በኃይል ለማፈናቀል ሴቶች እና ሕፃናት የግጭቱ ዒላማ ይሆናሉ።

ሴቶች እንደ ሰላም መልእክተኞች ዕውቅና እንዲያገኙ በሰላም ማስፈን ሂደት ውስጥ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን በተለይም ሴቶች እና ወጣቶችን ማካተት አስፈላጊ ነው። የእነርሱ የውሳኔ መስጠት ሥልጣን ለሰላማዊ አብሮ መኖር እና በማኅበረሰብ ውስጥ ማኅበራዊ ስምረትን ለመፍጠር ከግምት ሊገባ ይገባል። እንደ አለማቀፍ የስደተኞች ድርጅት (IOM) (2019) አገላለጽ፡-

«ለአገር ውስጥ ተፈናቃዮች እና ተመላሽ ስደተኞች ዘለቄታ ያላቸው መፍትሔዎችን መስጠት ሰፋ ባለ አነጋገር 3 አማራጮችን እንደሚይዝ ተደርጎ ይቆጠራል፡-

(1) ወደ ትውልድ ቦታ በፈቃደኝነት መመለስ፣

(2) በተሰደዱበት ቦታዎች ላይ አካባቢያዊ ውህደትን መፍጠር እና

(3) ወደ ሌላ ቦታ ወስዶ ዳግም ማስፈር ናቸው።

ለመፈናቀል መፍትሔ መስጠት በደህንነት እና ጥበቃ፣ ሕይወትን እና ኢኮኖሚን እንዲያገግም ማድረግ፣ መንግሥታዊ አስተዳደር እና ማኅበራዊ ትስስር ረገድ በሁሉም ሰብአዊ ልማቶች ላይ የተቀናጁ እና የተናበቡ ተስማሚ እርምጃዎችን ማጣመር የሚጠይቅ የጋራ ኃላፊነት ነው።»

ማኅበራዊ ትስስር ዘላቂ የሆነ የአገር ውስጥ ተፈናቃዮችን መፍትሔ ለመስጠት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ሊደረግ ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱ እንደ ስፖርት የመሳሰሉ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን መጠቀም ነው። አይኦኤም ኢትዮጵያ /IOM Ethiopia/ ከፍካት የሰርከስ ቡድን ጋር በመተባበር አይኦኤም በ WASH ፕሮግራሙ በንቃት በሚሳተፍባቸው የተለያዩ ቦታዎች ላይ ተከታታይ ዝግጅቶችን አቅርቧል። እነዚህ እንቅስቃሴዎች በጉጂ እና ጌዴኦ ዞኖች የተደረጉ ነበሩ። የቀረበው ትርዒት ቲያትርን፣ ትዕይንቶችን እና በዝግጅቱ ከታደሙ ከማኅበረሰብ አባላት ጋር በንጽሕና አጠባበቅ ጉዳዮች አሳታፊ ውይይቶችን ያቀፈ ነበር (IOM, 2019)።

**ምስል 3፦ በምዕራብ ጉጂ፣ ጌዴኦ ዞን የቀረበ የፍካት ሰርከስ ቡድን ትርዒት**




ምንጭ፦ አይኦኤም ኢትዮጵያ

**አሳታፊ ጥያቄዎች**

- በአካባቢዎ የተለያዩ ግጭቶች ካሉ የግጭቶቹ መንስኤና ባህሪያት ምን ይመስላል?
- ይህ ሁኔታ በሴቶች እና ሕፃናት ላይ ምን ዓይነት ችግሮችን አስከትሏል?

# ምዕራፍ 6፦ ሁለንተናዊ ለውጥ የሚያመጣ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴ (Transformative Pedagogy)

## 6.1 ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ-ዘዴ (Transformative pedagogy)

ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ ዘዴ ትምህርት ከአዕምሮዋዊ ዕውቀት ማስጨበጥ አልፎ ከድርጊት ጋር በማገናኘት ዕውቀትን፣ አመለካከትን እና ክኅሎትን ለማጎልበት የሚያስችል የማስተማሪያ ዘዴ ነው። በተለይም ከሰላም ትምህርት ዓውድ አንጻር ሲታይ ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ ዘዴ ውጤታማ እንዲሆን በውል ከሚታወቀው ሁሉን አቀፍ የትምህርት አቀራረብ ጋር መጣመር ይኖርበታል። ይህ አቀራረብ ከአካታችነት፣ ከዴሞክራሲያዊነት ፣ሐሳብን በነጻነት ከመግለጽ መብት፣ ልዩነቶችን ከማክበር እና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ከመፍታት ጋር ግንኙነት ካላቸው የትምህርት አማራጮች ጋር መገናኘት ይኖርበታል። በመሆኑም በአንድ ወር ውስጥ ለጥቂት ሰዓታት በሚሰጥ በአንድ የትምህርት ዓይነት የሚወሰን ወይም የሚገደብ ሳይሆን ይልቁንም ስነ-ዘዴው በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ላይ የሚገለጽ እና መላውን የትምህርት ቤት እና የአካባቢውን ማኅበረሰብ የሚያሳትፍ የትምህርት አሰጣጥ ሥነ-ዘዴ ነው።

ይህ የማሰልጠን/የማስተማር ሥነ-ዘዴ ዕውቀትን እና መረጃን ከመስጠት ይልቅ የተማሪዎችን የማወቅ ጉጉት ማሳደግ ላይ ይበልጥ ትኩረት ይሰጣል። ይህ የትምህርት አቀራረብ በይበልጥ ጥያቄና መልስ ተኮር ሥነ-ዘዴን በመከተል ይታወቃል። ይህ የማስተማር ሥነ ዘዴ ዕውቀትን በራስ የመገንባት ንድፈ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ሲሆን እያንዳንዱ ተማሪ የራሱን/የራሷን መንገድ በመከተል የግል ዕውቀት፣ክህሎት እና አመለካከትን እንዲያዳብር/እንድታዳብር የሚደግፍ ነው። ጥያቄን በማቅረብ የመማር ማስተማር ዘዴ ዕውቀት የሚገነባው በተለይ ዓውድን እና ማበራዊ መስተጋብርን መሠረት ያደረገ ተሞክሮ እና ሂደት ላይ እንደሆነ በግልጽ ያስቀምጣል። በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተማሪዎች የራሳቸውን አቅጣጫ እንዲይዙ የሚያደርግ ንቁ የሆነ የመማር ማስተማር ዘዴ ነው።

ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ-ዘዴው ተማሪዎች የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን ለይተው እንዲያውቁ እና የበኩላቸውን ሐሳብ እንዲያንፀባርቁ ፣ኃላፊነትን እንዲጋሩ፣ ራሳቸውን ለማወቅ እና ከሌሎችም ጋር ለመተዋወቅና ለመቀራረብ ዕድሎችንና አጋጣሚዎችን እንዲፈጥሩ ይረዳል። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች የሌሎችን አመለካከቶች እንዲያውቁ፣ ገጠመኞችን አንድ ላይ እንዲያጣጥሙ፣ የሌላውን ሐሳብ እንዲሞግቱ እና መልካም ግንኙነቶችን እና ዝምድናዎችን እንዲፈጥሩ የሚያስችሉ ተጨባጭ ዕድሎችን ይፈጥራሉ። በመጨረሻም ይህ ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ሥነ ዘዴ ተማሪዎች የጋራ ግባቸውን ለማሳካት በጋራ እንዲንቀሳቀሱ፣ የራሳቸውን ጥንካሬ እንዲያጎለብቱ እና በዙሪያቸው ያለውን ብዝኃነት በቀናነት እንዲያዩ የሚያስችላቸውን ዕድል የመፍጠር ዓላማ አለው።

## 6.2 ለዓውድ ጠንቃቃ መሆን እና ምላሽ ሰጪነት

ውጤታማ የሆኑ ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ወይም የማሰልጠን ስነ ዘዴዎችን መጠቀም ተማሪዎች የራሳቸውን ዓውድ እና ማኅበራዊ እውነታ ከግምት ማስገባትን እና መረዳትን ይጠይቃል። በመሆኑም አሠልጣኞች የኢትዮጵያን ዓውድ እንዲያውቁ ይመከራሉ። መርሐ ግብሮች እና ልምምዶች ከተማሪዎች የተለየ ዓውድ አንጻር ተጣጥመው መዘጋጀት አለባቸው። ይህም ተማሪዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚስተዋሉ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎችን (dynamics) እና ማኅበረሰቡ ላይ ጫና እያሳረፉ ያሉ ችግሮችን መረዳትና መገንዘብን ይጠይቃል። ለምሳሌ፦የጎሣ መድልዎ፣ ስደተኝነትን፣ የጎሣ ግጭቶችን እና አካባቢውን

የሚያውኩና ቤተሰብ ላይ የሚያጋጥሙ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ አሠልጣኞች በቂ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል።

በተጨማሪም ለዓውድ ጠንቃቃ መሆን ብዝኃነትን እና በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ቡድኖች ውክልናን የሚያበረታቱ የሰላም እና ዕርቅ ድባቦች መኖርን ይጠይቃል። በዚህ መንገድ የዐመፅን፣ የፍትሕ መጓደልን እና በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ግጭቶችን መሠረታዊ ምክንያቶች ለማወቅ እና ለመረዳት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ይኸው ድባብ ሊያገለግል ይችላል።ይህ ድባብ በሥርዓተ ጾታዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ጎሣዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶች ላይ በሙሉ ውይይት ለማድረግ እና መስተጋብር ለመፍጠር የሚያስችል መድረክ ሊሆን ይችላል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው ዓውድ ጠንቃቃ መሆን በተለይም በቀላሉ ወደ ግጭት ሊገቡ በሚችሉ፣ ለግጭት ተጋላጭ በሆኑ እና በግጭት በተሞሉ ዓውዶች ውስጥ አሠልጣኞች «ሌሎችን አትጉዳ» የሚለውን መርህ ተፈጻሚ እንዲያደርጉ ሊያግዟቸው ይችላሉ። ይህ መርህ የሚያተኩረው ያልተፈለጉ እየሰፉ የሚሄዱ ክፍፍሎችን ወይም የሚባባሱ ግጭቶችን የሚያስከትሉ ትምህርታዊ የማስተካከያ እርምጃዎች የሚያስከትሉትን ስጋት መቀነስ ላይ ነው። እነዚህ በተለይም በግጭቶች ወቅት የደረሱ ማኅበራዊ ቁስሎች አሁንም ድረስ ባልዳኑባቸው ድኅረ ግጭት እና አንዳንድ ጊዜ ገና በመጠዝ ላይ ባሉ ውጥረቶች ላይ እውነትነት አላቸው።

በቃላት፣ በሐረጎች እንዲሁም ቃላዊ ባልሆኑ የተግባቦት ዘዴዎች በሚሰጡ የተለያዩ ትርጉሞች ምክንያት ማናቸውም አዎንታዊ የማስተካከያ እርምጃ ያልተፈለጉ አሉታዊ ውጤቶች ሊኖሩት ይችላሉ። ከግጭት እና ከምክንያቶቹ አንጻር የኢትዮጵያን ዓውድ እና ጥንቃቄ የሚያሻቸውን ሁኔታዎች መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።

## 6.3 ምቹ የመማር ማስተማር ከባቢ

ለዓውድ ጠንቃቃ መሆን ለደኅንነት አስተማማኝ የሆኑ የትምህርት ድባቦችን መፍጠርን ይጠይቃል። እነዚህ ድባቦች በመርሐ ግብሮቹ ላይ የሠልጣኞችን እና አሠልጣኞችን ንቁ፣ አካታች፣ እውነተኛና ሁሉን አሳታፊ መሆን ይገባቸዋል። ሰላማዊ የመማር ማስተማር ድባቦች ሠልጣኞች ራሳቸውን እንዲሆኑ እና ሐሳባቸውን፣ ስሜታቸውን፣ እምነታቸውን እንዲያጋሩ እንዲሁም እርስ በርስ እንዲገናኙ ለመደገፍ እና ለማበረታታት አስፈላጊ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ።ለእያንዳንዱ ግለሰብ እና ለመላው ማኅበረሰብ ዕድገት  ተማሪዎች ደኅንነት እንዲሰማቸው እና እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው ዓይነት በጎ ስሜት እንዲያድርባቸው የሚያስችል ድባብን  ፈጥሮ መቀበል ተገቢ ነው።

ለዓውድ ምላሽ ሰጪነትን እና ጠንቃቃነትን ለማመቻቸት የሚጠቅሙ ጥቂት በተግባር የተፈተሹ ጠቃሚ ምክረ-ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ማኅበረ-ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ታሪኮችን እና የግጭት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ጠቅለል ባለ መልኩ መተንተን፤
- የተማሪዎችን/የሠልጣኞችን ፍላጎቶች እና የሚጠብቋቸውን ነገሮች መለየት፤
- የእርስዎን የትምህርት ክፍል ጊዜዎች እና መልመጃዎች  የተገለሉ ወጣቶች፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆች፣ ስደተኛ እና የአካል ጉዳት ያለባቸው ሕፃናት የመሳሰሉትን የተለያዩ ቡድኖችን ድምፆች እንዲያካትቱ አድርገው ያቅዱ። የሁሉንም ሰው ሐሳቦች እና አስተያየቶች እንዲጋሩ እና እንዲደመጡ መድረክ ይፍጠሩ፤
- የቋንቋን፣ አነስተኛ እና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የማህበረሰብ አካላት ግንኙነቶችን፣ የሥርዓተ ጾታን፣ የዕድሜን፣ የባህልን፣ የብሔርን እና የሃይማኖትን ብዝኃነት ከግምት ያስገቡ፤
- ሁሉም የመማር ማስተማር መሳሪያዎች ከቋንቋ እና ከሥዕላዊ መግለጫ አንጻር ዓውድ ተኮር መሆናቸውን ያረጋግጡ። መሳሪያዎቹ ለአንድ ቡድን የማይወግኑ እና የተሳሳተ

ዕሳቤ የማያንፀባርቁ መሆናቸውን ያረጋግጡ። በተጨማሪም መሳሪያዎቹን በሚገባ በመገምገም ማግለል እና መድልዎን የሚያበረታቱ ልማዳዊ አባባሎችን ላለመጠቀም ጥንቃቄ ያድርጉ።

በመማር ማስተማር ሂደቱ ደኅንነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ ነገሮች በሥልጠና መስጫ ቦታ ውስጥ እና ውጭ አለመከሰታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። ምቹ የመማር ማስተማር ከባቢ መፍጠር አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ አካባቢያዊ፣ አስተሳሰባዊ እና መንፈሳዊ ደኅንነትን ለማረጋገጥ ይረዳል። ከዚህ በተጨማሪ በግጭት በተጎዱ እና በቀላሉ ለግጭት ተጋላጭ በሆኑ ዓውዶች ውስጥ አሠልጣኞች በአደጋ ጊዜ ለሚፈጠር የሠልጣኞች ከፍተኛ ድንጋጤ እና የደህንነት ስጋት ይበልጥ ጠንቃቃ መሆን ይኖርባቸዋል። አንዳንድ የመማር ማስተማር መልመጃዎች በሠልጣኞች ላይ አሉታዊ ትውስታን ሊፈጥሩ እና ስሜታቸውን ሊነኩ ይችላሉ። እነዚህ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ወዲያውኑ አፋጣኝ ድጋፍ መስጠት እና ከመማሪያ ክፍል ውጭም እገዛው መቀጠል እንዳለበት አሠልጣኞች ማስታወስ አለባቸው።

ይህ የስልጠና ማኑዋል በደኅንነት አጠባበቅ ጉዳይ ዙሪያ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች አይገባም። በመማሪያ ክፍል ውስጥ ወይም በሥልጠናው አካባቢ ለተሳትፎ፣ ዕውቀትን ለመቅሰም እና ለማሰስ ምቹ የሆኑ መድረኮችን መፍጠር ላይ ያተኩራል። እንዲህ ያሉት ለደኅንነት አስተማማኝ መድረኮች ሠልጣኞች ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው እና ዓውዳዊ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችን እንዲያደርጉ አሠልጣኞች እንዲመሯቸው እና በእነዚህ ዙሪያ ብዙውን ጊዜ የሚኖሩ ውስብስብ እውነታዎችን እንዲረዱ እና የሚሰማቸውን ሐሳብ እንዲያንፀባርቁ ያስችሏቸዋል።

**ሣጥን 13፦ የመማር ማስተማሩን ድባብ ደኅንነት አደጋ ውስጥ የሚጥሉ ሁኔታዎች**

1) **አካላዊ ደኅንነት፦** የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛን፣ ፆታዊ ጥቃትን፣ የሕፃናት ሕገወጥ ዝውውርን፣ የሕፃን ወታደሮች ምልመላን፣ ወደ ዘራፊ ቡድኖች እና ፅንፈኛ ቡድኖች አስገድዶ መመልመልን፣ አካላዊ ቅጣትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ጨምሮ ሥርዓተ ጾታን ማዕከል ያደረገ ጥቃት፤

2) **ሥነ-ልቦናዊ ደኅንነት፦** ስድብ፣ ማግለል፣ መለየት፣ መድልዎ፣ በሃይል ማስፈራራት እና መበዝበዝ፤

3) **አካባቢያዊ ደኅንነት፦**ተገቢነት ያለው የሥልጠና ቦታ ወይም ትምህርት ቤት አለመኖር፣ ለሥርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የሆነ የትምህርት ቤት ድባብ አለመኖር (ለልጃገረዶች መታጠቢያ ቤቶች፣ መጸዳጃ ቤቶች፣ የንጽሕና መጠበቂያዎች አለመኖር)፣ የቤተ መጽሐፍት፣ ቤተ ሙከራዎች እና ደረጃቸውን የጠበቁ መጫወቻ ቦታዎች አለመኖር፣ ጥቃቶች፣ ግጭቶች፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ የአካባቢ ብክለቶች፣ ድህነት እና ሌሎች የእኩልነት መዛባት ችግሮች፤

4) **አዕምሮአዊ ደኅንነት፦** ያልተመጣጠነ ምግብ፣ የመማር ማስተማር ዕድሎች በቂ ያልሆኑ አቅርቦቶች፣ የፕሮፓጋንዳ ሰለባ መሆን እንዲሁም ሥነጥበብን፣ ስፖርትን፣ ክበቦችን፣ ድራማን እና ሌሎች የክህሎት ማጎልበቻዎችን ጨምሮ የተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴዎች አለመኖር

5) **መንፈሳዊ ደኅንነት፦** ለጸጥታ እና የውስጥን ስሜት ለማንፀባረቅ የሚያስችል ዕድል አለመኖር፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ራስን በመግለጽ እና ጥያቄ በማቅረብ አስፈላጊነት ላይ ትኩረት አለመስጠት፣ ለሥነጥበብ፣ ለተፈጥሮ፣ ለስፖርት ቅድሚያ አለመስጠት ወይም ማበረታቻ አለመኖር ናቸው።

*እነዚህ ከላይ በቅደም ተከተል የተገለፁት ሁኔታዎች አንዱ ሌላኛው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፉ እና እርስ በርስ እንደሚገናኙ ለማስገንዘብ ነው።*

## 6.4 አሳታፊ የመማር ማስተማር ሂደትን ማረጋገጥ

ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴ አሳታፊ እና ትብብራዊ፣ መማር ማስተማርን የሚደግፍ ሆኖ አካታችነትን፣ ዴሞክራሲያዊ ዜጋ ማፍራትን፣ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን፣ ልዩነቶችን ማክበርን እና ለግጭቶች ሰላማዊ መፍትሔዎችን ማፈላለግን ያካትታል። የተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴ ማዕከል የሚያደርገው የተማሪውን /የሠልጣኙን ንቁ ተሳትፎ ነው። ይህ የሰላም ግንባታ ትምህርት የማስተማር ሞዴል ተግባር ተኮር የሆነ መማር ላይ አጽንኦት በመስጠት ተማሪው ዕውቀትና ክህሎት እንዲያገኝ ዴሞክራሲያዊ እና አሳታፊ የሆነ የማስተማር ዘይቤን መጠቀም ይጠይቃል (Freire, 1970)።

እዚህ ላይ ያለው ሐሳብ አሠልጣኞች የአመለካከት ለውጥ፣ ስለ ግብረ-ገብነት እና ስለ መልካም እሴቶች ምንነት ያውቃሉ ተማሪዎች ደግሞ ምንም አያውቁም ማለት አይደለም። በዚህ ሂደት አሠልጣኙ ሁሉን ነገር የሚገልጽና የሚያቀርብ ሳይሆን የአመቻችነትና የመማር ማስተማር ስራውን የማደራጀት ሃላፊነት አለበት። ስለሆነም አሰልጣኞች ሰልጣኞች ያላቸውን ዕውቀት፣ አመለካከት እና ባሕሪ በመፈተሽ የመማር ማስተማሩን ሂደት የመምራት እና ቅርጽ የመስጠት ሥራን ይሠራሉ። በዚህ መልኩ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ምን ማለት እንደሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው። የሰላም ግንባታ ትምህርት ቁልፍ ዓላማ ዕውቀትን፣ ክኅሎትን እና ብቃቶችን ከመቅሰም ተነሥቶ ለማኅበረሰቡ ደኅንነትና ጠቀሜታ ወደ መምራት እና ውሳኔ መስጠት ብቃት ደረጃ ላይ ማድረስ መቻል ነው። በዚህ ሥነ-ዘዴ ተሳትፎ በአንድ ግለሰብ የሚከወን ሂደት ተደርጎ የሚታይ ሳይሆን በተማሪዎች/ሠልጣኞች በወል ተሳትፎ ላይ የሚያተኩር ነው።

**የመማር ማስተማር ምቹ ሁኔታዎች የሚከተሉትን ለማሳካት የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፦**

- ሠልጣኞች በንቃት እርስ በርስ እንዲረዳዱ እና እንዲተባበሩ ማበረታታት፤
- በተለያዩ አመለካከቶች ላይ ለመነጋገር የሚያስችሉ ዕድሎችን መፍጠር፤
- በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነትን ማበረታታት እና
- ሥራን ለማጠናቀቅ ብቻ ሳይሆን ችግርን ለመፍታት በቡድን ትኩረት አድርጎ መስራት ናቸው።


ከተመሳሳይ ቡድኖች በመጡት መካከል ብቻ ሳይሆን ከሌሎች አብረው ሊሄዱ የማይችሉ ተደርገው ከሚወሰዱ ቡድኖች ጋር ተባብሮ መስራት የሚያስችሉ ዕድሎችን መፍጠር ያስፈልጋል። ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴ እና ውስን የመማር ማስተማር ሂደት ብቻ በመጠቀም አሰልጣኞች አሳታፊ የሆኑ የትምህርት ዕድሎችን እንዲፈጥሩ እና በሰላም ግንባታ ትምህርት ላይ የሚያጋጥሟቸውን ዋነኛ ተግዳሮቶችን በአሸናፊነት እንዲወጡ ሊያግዙ ይችላሉ።ይህ ሂደት አዲስ ዕውቀትን ከማስጨበጥ ጀምሮ በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ በሰላም ግንባታ ሂደት ላይ ግንዛቤ መፍጠርን እና ተሳትፎ ማድረግን ያስችላል።

ይህ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ዕውቀትን፣ ክህሎትን፣ እና ብቃትን ከመቅሰም ተነሥተው በማኅበረሰባቸው ውስጥ በሰላም ግንባታ ሥራ ላይ በንቃት መሳተፍ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። እነዚህ የመማር ማተማር ሂደቶች የተቀረፁት ሰልጣኞች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉና በአሰልጣኞች እንዲመሩ ለማስቻል ነው።

ትምህርቱ ተሳታፊዎች በአዲስ ግኝት ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ ያደርጋቸዋል፤ ውጤቱም ወደ አዲስ የራስን ሐሳብ ማንፀባረቅ እና ወደ ቀጣይ ትምህርት ፍላጎት ያመራል። የመማር ማስተማር ሂደቱ መርሐ ግብሮችን እና ልምምዶችን በማዘጋጀት ላይ እና ተማሪዎች ስለራሳቸው የትምህርት ተሞክሮ ይበልጥ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ እንደ ሞዴል ሆኖ ያገለግላል።

የሚከተለው ንድፍ የተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴ በሥዕል ያስቀምጣል (Arigatou International, 2008)። ትምህርቱን ለመማር ወይም በልምምዱ ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስችል ማነቃቂያን በመጠቀም ይጀምርና በአሰሳ፣ በውይይት፣ በአዲስ ግኝት፣ የተማሩትን ሐሳብ በማንፀባረቅ እና እርምጃ በመውሰድ የድርጊቶቹ ሂደት ወደፊት ይቀጥላል። በተጨማሪም ሂደቱ ወደ ጎን በቀጥታ የማይሄድ እንዲሁም ፊት ለፊት ያልሆነ መሆኑን ማስተዋል ጠቃሚ ነው። በአዲስ ግኝት ላይ የተመረኮዘ እንደ መሆኑ ወደ ፊትም ሆነ ወደ ኋላም ሊሄድ ይችላል።

**ሥዕል** 12፦ የተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴ




**ቁልፍ አባለ ነገሮች**(elements) ፦

**ማነቃቂያ**

ሠልጣኞች ለምን መሳተፍ ያስፈልጋቸዋል?

ሠልጣኞች ተሳትፎ እንዲያደርጉ እና ሰላምን ለመገንባት አንድ ርዕሰ ጉዳይ ወይም ልምምድ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ እንዲረዱ አሠልጣኞች በሠልጣኞቹ ዘንድ ውስጣዊ እና ውጫዊ ማነቃቂያ ዘዴዎችን መገንባት ያስፈልጋቸዋል። የማነቃቂያ ተግባራት የማወቅ ፍላጎትን ይፈጥራሉ፤ እንዲሁም አንድን ርዕሰ ጉዳይ እንዲያውቁ እና እንዲያስሱ ጠንካራ ፍላጎትን ይገነባሉ።

**አሰሳ**

በዚህ ምዕራፍ ላይ ለሠልጣኞች ርዕሰ ጉዳዩን እንዲያስሱ በመፍቀድ አሠልጣኙ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ የተወሰነ መረጃን ወይም ስለሚያከናውነው ተግባር የተወሰኑ ማብራሪያዎችን ይሰጣል።

**ውይይት**

ሠልጣኞች በተመሳሳይ ጊዜ ሌላ አመለካከቶችን እያዳመጡ የራሳቸውን አቋም ለሌሎች እንዲያካፍሉ በመፍቀድ አሠልጣኙ ለውይይት ምቹ የሆነ መድረክን ይፈጥራል። ይህ ምዕራፍ ጥልቅ አሳቢነትን ለማጎልበት በጣም ወሳኝነት አለው። መምህራን የውይይት ጥያቄዎችን በማቅረብ ውይይቱ ይበልጥ ጥልቀት እንዲኖረው ማድረግ ይችላሉ።

**አዲስ ግኝት**

ከውጤታማ ውይይት በኋላ ሠልጣኞች አዳዲስ የአስተሳሰብ አቅጣጫዎች እንዳሉ ከማወቅ ባሻገር ስለ ራሳቸው አዲስ ነገር እንደተረዱ ይሰማቸዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች የተለያዩ አስተሳሰቦችን እና ሐሳቦችን መርጠው

ሊይዙ ይችላሉ። ይህ የሚፈጠረው ሠልጣኞች ወደ አዲስ የዕውቀት ግንዛቤ እና ግንኙነቶችን ለመፍጠር ወደሚያስችላቸው «አሃ! እንዲህ ነው ለካ?!» ወደሚሉበት ደረጃ ሲደርሱ ነው።

**ፅብረቃ**

አሠልጣኙ ሠልጣኞች ባገኙት ተሞክሮ እና አሰሳ በተደረገበት ርዕሰ ጉዳይ ላይ የተገኙትን ቁልፍ ነጥቦች በተመለከተ ሐሳባቸውን እንዲያንፀባርቁ ይመራቸዋል። ይህንን እንዴት ከራሳችን ዓውድ ጋር እናገናኘዋለን? በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከመማር ባለፈ በማኅበረሰባችን ውስጥ ሰላምን ለማስፈን ወደሚያስችል ተግባር እንዴት ልናመራ እንችላለን? ጥልቅ አሳቢነትን ማጎልበት ቀጣይ የሆነ ሙያዊ ዕድገትን ይጠይቃል። ለዚህም ነው የመማር ማስተማር ሂደት በጽብረቃ ጠቀሜታ ላይ ትኩረት የሚሰጠው። ሂደቱ ሠልጣኞች ለመወሰን አዳጋች የሆኑባቸው መንታ ሐሳቦችን እንዲያስሱ እና ውሳኔዎቻቸው እንዴት በራሳቸው እና በሌሎች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳርፉ እንዲረዱ ያስችላቸዋል።

**ተግባር/ድርጊት**

ተማሪዎች በንድፈ-ሃሳብ ያወቁትን በተግባር መፈፀም መቻላቸው ለሰላም ግንባታ ትምህርት ጠቃሚ ክፍል ነው። ሠልጣኞች ማኅበረሰባቸውን ለመለወጥ በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ከትምህርት ቤት ውጭ በንቃት ሊሳተፉባቸው የሚችሉባቸውን መንገዶች እንዲያስቡ እንዴት አሰልጣኞች ሊያበረታቷቸው ይችላሉ?

ምንጭ፡- Arigatou International, 2008

ማነቃቂያ፣ የሐሳብ ልውውጥ ማድረግ ፣ መስተጋብር፣ ችግርን መጋፈጥ፣ አዲስ ግኝትን ማግኘት፣ ጥልቅ አሳቢነት እና የተማሩትን በተግባር ማንፀባረቅ ዕውን መሆን ይችሉ ዘንድ የተወሰኑ የትምህርት ዘዴዎች ተጠቁመዋል። እነዚህ የትምህርት ዘዴዎች ሠልጣኙ ከሌሎች ጋር በተነፃፀረ ሁኔታ በራስ ተነሣሽነት ወደሚመራበት ሂደት ያደርሱታል። ከፍ ሲል የተገለጹት ውስን ዘዴዎች ክህሎት ለማሳደግ፣ የተማሪዎችን ዕውቀት ለማበልጸግ፣ ብዝኃነት ባለበት ማኅበረሰብ ውስጥ መኖር እና መንቀሳቀስን መማር እንዲችሉ የሚያበቋቸውን አመለካከቶች ለማበልጸግ ያግዛሉ።

ለሰልጣኞች ይበልጥ ተገቢነት ያለውን የትምህርት ዘዴ መምረጥ የእያንዳንዱ አሠልጣኝ ኃላፊነት ነው። ይህ የሥልጠና ማኑዋል በመጨረሻም ለተግባራት እና ለትምህርት ዘዴዎች በርካታ ጠቃሚ ሐሳቦችን ያቀርባል። እነዚህ የትምህርት ዘዴዎች በጣምራ ወይም ከኢትዮጵያ ዓውድ እና ከተሳታፊዎች ዕድሜ አንጻር እንዲጣጣሙ በማድረግ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። እነዚህ የጥቆማ ሐሳቦች ብቻ እንደሆኑ እና አሠልጣኞች እንደ አስፈላጊነቱ መጥነው ለመጠቀም እንደገና አሻሽለው ለማዘጋጀት ነጻ መሆን እንዳለባቸው ያስታውሱ።

ትምህርትን ለብቻ መማር ይቻላል፤ ሆኖም ግን ወጣቶች የተለያዩ አመለካከቶችን መታገል፣ አዳዲስ ሐሳቦችን ማፍለቅ እና የራሳቸውን ማንነት እየፈለጉ የራሳቸውን አመለካከት ማስፋት የሚችሉት ከሌሎች ጋር በመተባበር ነው። አሳታፊ እና በትብብር የሚካሄድ የመማር ማስተማር ሂደት እያንዳንዱ ግለሰብ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ ዕድል ከመፍጠሩም በላይ ልምምዶችን፣ ብዝኃነትን፣ አካታች የትምህርት ዘዴዎችን እና ቴክኒኮችን ያካትታል። እንዲሁም ለእያንዳንዱ ተሳታፊ የመማር እና የመግባባት ችሎታ አክብሮትን ይሰጣል።

**ምስል 4፡- በተግባር መማር**



ምንጭ፡- Arigatou International, 2014

ወጣቶች እና ሕፃናት በራሳቸው የማወቅ ፍላጎት እና ውስጣዊ ተነሣሽነት እየተመሩ የራሳቸውን ትምህርት ይመርጣሉ። ሰልጣኞች ከአሠልጣኞቻቸው ጋር የጀመሩትን አዲስ የመማር ማስተማር ሂደት መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ስለሆነም ሰልጣኞች ለማሰስ፣ ተሳትፎ ለማድረግ፣ ለማሰብ፣ ለመወያየት እና ጥያቄ ለመጠየቅ ያላቸውን ነጻ ስሜትና ፍላጎት መለየት ይኖርባቸዋል።የአሠልጣኞች ኃላፊነት ሕፃናት እና ወጣቶች በመርሐ ግብሮች ዝግጅት ላይ በንቃት ሊሳተፉ የሚችሉበትን መድረክ መፍጠር፣ ጠቋሚ ሐሳቦችን መስጠት እና የሚያውቋቸውን ግብዓቶች መጠቀም ነው። አሠልጣኞች ለትምህርቱ ግልጽ የሆኑ ዓላማዎችን መንደፍ አለባቸው። በራሳቸው ተነሣሽነት የሚማሩ ተማሪዎች በሕይወታቸው ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ውስጣዊ እና ውጫዊ ገጠመኞችን በመመርመር ለትምህርት ድጋፍ ማድረግ ቢኖርባቸውም ሁኔታዎችን የማቀናበር እና መርሐ ግብሩን የመምራት እንዲሁም የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤቶች በቅድሚያ የማዘጋጀት ሃላፊነትን አሠልጣኞች ሊወስዱ ይገባል ።

## 6.5 አርአያነት

ዓርአያ (exemplary) የሆኑ ወይም መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸውን ሰዎች በመጠቀም ትምህርትን ውጤታማ ማድረግ ይቻላል፡፡ ሁላችንም ዓርአያነት ካላቸው ሰዎች ብዙ ነገር እንማራለን። በመሆኑም አሠልጣኞች ዕውቀትን፣ አመለካከትን እና እሴቶችን በማስረጽ ረገድ በሰልጣኞች ሕይወት ውስጥ ቁልፍ ሚና ከሚጫወቱ ተዋንያን መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ አሠልጣኞች መልካም አርአያ በመሆን ተማሪዎችን ያነሳሳሉ። ቀደም ሲል በትምህርት ቤት ካስተማሩህ/ሽ መምህራን መካከል ቢያንስ አንድ አስተማሪን የማያስታውስ ማን አለ?

መርሐ ግብሮችን እና ተግባራትን በምናከናውንበት ጊዜ ተማሪ/ሰልጣኝ ተኮር የማስተማር ሥነ-ዘዴዎች እና ዓርአያነት ያላቸው ተግባራትን በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን ውጤታማ ማድረግ ነው።

የሰላም ግንባታን ስልጠና ውጤታማ ለማድረግ አሠልጣኞች የሚከተሉትን ተግባራት ትኩረት ሰጥተው ማከናወን ይኖርናቸዋል።

1) ግብረገባዊ የሆኑ ዕሴቶችን፣ አመለካከቶችን፣ ባሕሪያትን እና ድርጊቶችን በተግባር ማሳየት፤

2) የጋራ መግባባት፣ መከባበር እና ለሌላው አድናቆትን ማሳየት፤

3) ብዝኃነትን ማክበር፤

4) በቃላት፣ በባሕሪ እና በድርጊት መካከል ወጥነትን በተግባር ማሳየት እና

5) አሰልጣኞች የሚያሳዩት ባህሪና አመለካከት በተማሪዎቻቸው ላይ የሚፈጥረውን ተፅዕኖ መረዳት እና ማንፀባረቅ ነው።

አሠልጣኞች ምንጊዜም በባሕሪያቸው ግብረገባዊ አንደምታዎች ላይ ሐሳባቸውን ማንጸባረቅ እና መተግበር እንዲሁም ተማሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲፈፅሙ ማድረግ ይኖርባቸዋል። የሰው ልጅ በሕይወት የማይነጠሉና አብረውት የሚኖሩ አዎንታዊ እና አሉታዊ የሕይወት ገጠመኞች አሉት። ስለሆነም አሰልጣኞች ስኬትን በአርአያነት እንደሚያሳዩ ሁሉ ውድቀትንና ተጋላጭነትንም ማንፀባረቅ ይኖርባቸዋል። መሳሳት የመማር ማስተማሩ ሂደት አንዱ ገፅታ መሆኑን አሰልጣኞች ለሰልጣኞች ማስገንዘብ አለባቸው ።

## 6.6 ማህበረሰብ አቀፍ የመማር ማስተማር ሂደት

ማህበረሰብ አቀፍ የመማር ማስተማር ሂደት የሰላም ትምህርት በሠልጣኞች እና በአሠልጣኞች መካከል ግንኙነት ላይ ያልተገደበ ሁሉን አቀፍ አቀራረብ እንዲኖር ጥሪ ያቀርባል። ተማሪዎችን፣ መምህራንን እና ወላጆችን በትምህርት ቤት አስተዳደር እና ዕቅድ አወጣጥ ላይ መላውን የትምህርት ቤት ማህበረሰብ የማሳተፍ ዓላማ አለው። በአጠቃላይ የትምህርት ማህበረሰቡን በዕቅድ ዝግጅት፣ ትግበራ እና ግምገማ ሂደት ላይ ያሳትፋል ፡፡ ሁሉን አቀፍ የትምህርት ቤት አቀራረብ የትምህርት ቤት ባህሎች፣ መዋቅሮች፣ የዲስፒሊን እርምጃ አወሳሰድ ቴክኒኮች፣ አስተዳደር እና ግጭትን መፍትሔ ለመስጠት ስለሚቻልባቸው መንገዶች በተመለከተ መላውን የትምህርት ቤቱን ማኅበረሰብ ያሳትፋል፤ ይህም ተማሪዎች እንዲለወጡ በማድረግ ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

ሁሉን አቀፍ የትምህርት ቤት አቀራረብ የትምህርት ዕድሎች ከአካታችነት፣ ዴሞክራሲያዊነት /ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት እና ልዩነቶችን ማክበር/ እና ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት ጋር መገናኘታቸው እና በሰላም ትምህርት ላይ ብቻ አለመገደባቸውን ያረጋግጣል። በምትኩ የሰላም ግንባታ እና የሰላም ትምህርት መርሆዎች የሁሉን አቀፍ ትምህርት ቤት እና በዙሪያው ያለው ማኅበረሰብ አንድ አካል ናቸው። ይህ ማለት ሁሉን አቀፍ የትምህርት ቤት አቀራረብ ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ መምህራን እና ተማሪዎችን የሚያካትት እና የትምህርት ቤት ሕይወት መስኮችን የሚነካካ ነው።

የግለሰቡ አስተሳሰባዊ እና አካላዊ አቅም፣ ቋንቋ፣ ብሔር፣ ባህላዊ ዳራ፣ ሃይማኖታዊ ድህረ ታሪክ፣ ጾታ፣ ሥርዓተ ጾታ ምንነት ወይም ዕድሜ ከግምት ሳይገባ ሁሉን አቀፍ የትምህርት ቤት አቀራረብ በትምህርት ቤት ውስጥ ያለው ሁሉም ሰው ደኅንነትና ተቀባይነት እንዳገኘ ሆኖ እንዲሰማው የሚያደርግ የመማር ማስተማሪያ ድባብ መፍጠርን ያበረታታል።

በሌላ አነጋገር ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች ሰላምን እና ዴሞክራሲን የሚለማመዱበትን ቦታና መድረክ ሊያቀርብላቸው ይገባል ማለት ነው። በውሳኔ አሰጣጥ፣ አመራር እንቅስቃሴዎች እና የዕለት ተዕለት የትምህርት ቤት አስተዳደር ሥራዎች ላይ ተማሪዎችን የሚያሳትፍ ዕቅዶችን ያካተቱ ትርጉም ያለው አስተዋፅዖን በማጎልበት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ከዚህ በተጨማሪ እንደ ተማሪዎች መማክርት ጉባዔ የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች የማኅበረሰብን መዋቅሮች በመፍጠር እና ዴሞክራሲያዊ ብቃቶችን በማጎልበት ላይ ትልቅ ድርሻ አላቸው።

ሁሉን አቀፍ የትምህርት ቤት አቀራረብ ስንል ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ የአስተዳደር ሠራተኞችን፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትን፣ ወላጆችን፣ የወላጅ መምህር ህብረትን እና ሌሎች የማኅበረሰብ አባላትን በሙሉ የትምህርት ቤቱን ማኅበረሰብ ያካትታል። ትምህርት በመደበኛ ሥርዓት ትምህርት ብቻ ሳይሆን በሌላ መንገድም ማለትም ተማሪዎች በትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት ውጭ ባላቸው ሕይወት ከሚያገኙት ተሞክሮም ጭምር እንደሚገኝ ያመላክታል። ትምህርት ቤቶች

የሰላም ግንባታ እና የሠራተኞቻቸውን፣ የተማሪዎቻቸውን፣ የወላጆች/የሞግዚቶች እና ሰፊው ማኅበረሰብ ያሉባቸውን ችግሮች በመፍታት የተሻለ ውጤት ማግኘት እንዲችሉ ሦስቱ አካላት በአንድ ላይ ተጣምረው መስራት ይኖርባቸዋል።

- **ሥርዓተ ትምህርት**
- **ባህል እና አካባቢ፦** ቁሳዊ አካባቢዎች፣ የሥነ ምግባር ሕጎች እና ዕሴቶች እንዲሁም ፖሊሲዎች እና መዋቅሮች ለመኖር፣ ለመማር እና ለመሥራት ምቹ የሆነ አካባቢን ይፈጥራሉ።
- **አጋርነት እና የማኅበረሰብ ግንኙነቶች፦** ከወላጆች፣ ከሠራተኞች እና ከተማሪዎች ጋር የሚመሠረቱ ውስጣዊ ግንኙነቶች እና ከሌሎች ትምህርት ቤቶች፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሚመሠረቱ ውጫዊ ግንኙነቶችን ያካትታል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ ለማኅበረሰቡ ጠቃሚ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ውጥን ሥራዎች ሙሉ በሙሉ ተቀናጅተው፣ ተደግፈውና ተበረታተው ሁሉን አቀፍ የትምህርት አቀራረብ ዘዴው ለሰላም ትምህርት ቁልፍ ሚና እንዲጫወት ወላጆች፣ የማኅበረሰብ መሪዎች፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትና የትምህርት ባለሞያዎች አንድ ላይ ሆነው ሰላምን ለማስፈን በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ሚና መጫወት አለባቸው፡፡

# ምዕራፍ 7፦ የሰላም ግንባታ ትምህርት ትግበራ

## 7.1 የለውጥ አካል መሆን

የሰላም ግንባታን በንድፈ ሀሳብ ማነብነብ ውጤታማ አያደርግም፡፡ በዘርፉ ተዋናይ መሆን የሚፈልጉ አካላት በተግባር የለውጥ አካል ሊሆኑ ይገባል፡፡

የሰላም ትምህርት ግብ የለውጥ ሐዋርያና ጥልቅ አሳቢዎች ሆነው ለሰላም ለመቆም ዝግጁ የሆኑ እንዲሁም በሥነ ምግባራዊ እሴቶች ላይ በመመርኮዝ የሁሉንም ሰዎች ክብር ለማስጠበቅ የሚችሉ ሠልጣኞችን እና አሠልጣኞችን ማብቃት ነው።

የለውጥ አካል መሆን ሊመጣ የሚችለው ሰልጣኞች አሳታፊ በሆነ የማስተማር ሂደት ሲያልፉና ተግባራዊ ተሞክሮ ሊኖራቸው ሲችል ነው፡፡በዚህ የስልጠና ማኑዋል መሰረት ስልጠና የሚሰጥበት ቦታ ወይም መማሪያ ክፍል አሳታፊ መማር ማስተማርን ለመተግበር ሃሳብን ለማስተላለፍ እና ለማጎልበት የሚያስችል መሆን ይገባዋል፡፡ ሥልጠናው ትርጉም ያለው እና አሳታፊ እንዲሆን ማህበራዊ ኃላፊነት ያላቸውን ድርጅቶች የትምህርት አሰልጣኞችን እንዲያግዙ ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነዉ፡፡

አሰልጣኞች/መምህራን ግባቸው ከክፍል ውስጥ ባለፈ የአካባቢውን ማህበረሰብ ያካተተ በመሆኑ ስልጠናው ሰልጣኝ መር ሊሆንና የፈጠራ ስራዎች /ፕሮጀክቶች ላይ ሊያተኩር ይገባል፡፡

ለሰልጣኞች ውጤታማ ተሳትፎና ለሚያልሙት አብሮ የመለወጥ ተግባር ስኬት አሰልጣኞች ምቹ ቦታ በማመቻቸት ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡ ለዚህም ሲባል አሠልጣኞች አሳታፊ ሥነ ትምህርትን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ዕውቀቶች እና ክሂሎች ሊኖሯቸው ይገባል።

ይህም አሳታፊ ዘዴዎችን በመጠቀም ሠልጣኞቹን ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፤ ለንግግር እና ሐሳብን ለማካፈል ምቹ የሆነ የመማሪያ ድባብን ይፈጥራል፤ ከዚህም ሌላ ሠልጣኞች የእርስ በርስ መተባበርን አስፈላጊነት እንዲማሩ እና በግል ከመማር ወደ አንድነትና በጋራ ወደ መተግበር ደረጃ እንዲሸጋገሩ ይረዳቸዋል። ሰልጣኞች በራሳቸው ተነሳሽነት ወደ ፈጠራ እና ወደ ተግባር ሲገቡ ተጠቃሚነታቸው ከፍ ይላል፡፡የሚከተሉትን ክሂሎችም ያፈራሉ፡፡

**ሥዕል 13፦ ሰልጣኞች ፕሮጀክቶችን ወይም ፈጠራዎችን ሲሰሩ ክሂላቸዉን ያጎለብታሉ፡፡**




## 7.2 የሰላም ግንባታ የብቃት ማዕቀፍ

ማዕቀፍ አንድ ተግባር ሁሉ አቀፍ በሆነ ሁኔታ እንዴት እንደሚመራ አቅጣጫ የሚሰጥ ሰነድ ነው፡፡

የHOPPE /Holistic, Ownership,Participation & Partnership and Empowerment/ በሰላም ግንባታ ትምህርት ሁሉ አቀፍ፣ የባለቤትነት፣ የአጋርነት ፣ የተሳትፎ እና የማብቃት ማዕቀፉ ሠልጣኞች የራሳቸውን ፕሮጀክቶች እና ተግባራት በሚያጎለብቱበት ሂደት ላይ ለሚደግፉ አሠልጣኞች የተግባር መመሪያን ያቀርባል። ማዕቀፉ በዝርዝር ሲታይ የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

**ሥዕል 14፦ የHOPE ማዕቀፍ**




**ሁሉ- አቀፍ/Holistic/፦**ሁሉ- አቀፍ ሲባል ለችግሮች መፍትሔ ለመስጠት እና እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያስፈልጋቸውን ክግምት ለማስገባት የተቀናጁ ዘዴዎች እንዴት መተግበር እንደሚቻል የሚያብራራ ቃል ነው::

**ባለቤትነት /Ownership/፦** ፕሮጀክቶች በሠልጣኞች በራሳቸው የሚመሩ መሆናቸውን እና ሠልጣኞች ኃላፊነት መውሰዳቸውን ያረጋግጣል::

**ተሳትፎ እና አጋርነት /Participation & partnership/**

**ተሳትፎ /፦** አሳታፊ የመማር ማስተማር ልምምዶችን እና ዘዴዎችን ማበረታታትን ይመለከታል::

**አጋርነት** በሠልጣኞች፣ በትምህርት ቤቱ እና በማህበረሰቡ መካከል ያለውን ትስስር እና መደጋገፍ ይመለከታል::

**ማብቃት/Empowerment/፦** ማብቃት ተማሪዎች የተለያዩ ክሂሎችን እና የመሪነት አቅምን እንዲያጎለብቱ የሚያስችል ሂደት ነው::

ምንጭ፦ በ ACCU-UNESCO Innovation Programme for Education for Sustainable Development የተዘጋጀ

በሠልጣኞች ባለቤትነት እና ተሳትፎ የሚሰሩ የፈጠራ ሥራዎችና ፕሮጀክቶች ትምህርት ተኮር እንዲሆኑ እንዲሁም አሰልጣኞች የሰላም ትምህርት ፕሮግራም በሰልጣኞች ላይ ያለውን አስፈላጊነት/ለውጥ እንዲረዱ የሚያግዙ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ቁልፍ አካላት ናቸው፡፡

የፕሮጀክቶች እና የፈጠራ ሥራዎች ባለቤትነት እና ዝግጅት የሠልጣኞቹ ለውጥ አመልካቾች ከመሆናቸውም በላይ በእነርሱና በማህበረሰባቸው ላይ ጫና በሚፈጥሩ ችግሮች እና በሰላም አብሮ በመኖር ላይ በሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ዙሪያ ሠልጣኞች የሚሰጡትን ምላሽ ለአሠልጣኙ ጠቋሚዎች ናቸው።በአጠቃላይ ማዕቀፉ የተማሪዎች/የሰልጣኞች ባለቤትነት እንዲረጋገጥ የሚያስችል ነው፡፡

## 7.3 የተሳትፎ ደረጃዎች

በተግባራትና በፕሮጀክቶች እቅድ እና ትግበራ ላይ ሰልጣኞች ትርጉም ያለዉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማገዝ እንዲችሉ አቅም እንዲኖራቸው አሰልጣኞች የተለያዩ የተሳትፎ ደረጃዎችን መረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የሮጀር ሃርት /Roger Hart/ የተሳትፎ መሰላል አሠልጣኞችን የሚመራ ጠቃሚ እና ለትግበራ ምቹ የሆነ ዘዴ ነው።

**ማጥን 16፦ ትርጉም ያለዉ ተሳትፎ ምንድን ነው?**

*Children’s Participation: The Theory and Practice of Involving Young Citizens in Community Development and Environmental Care* Roger Hart(1997) በሚለው ስራው ሮጀር ሃርት( Roger Hart) የሕፃናትን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ዕንሰ ሐሳቦች እና የይዘት ምንነትን ዘርዝሯቸዋል። ሮጀር ሃርት ይህን«የሕፃናት ተሳትፎ መሰላል» /“Ladder of Children’s Participation”/ ወይም «የወጣቶች ተሳትፎ መሰላል» /"Ladder of Youth Participation"/ የሚል በጣም ጠቃሚ የሆነ የትምህርት መሳሪያ አዘጋጅቷል። መሰላሉ የወጣቶችን ተሳትፎ ለመረዳት እና መርህ-ግብሮች እና የፈጠራ ስራዎች ለመንደፍ እንዲሁም በዓለም ዙሪያ የሕፃናትን እና የወጣቶችን ትርጒም ያለው ተሳትፎ ለማጎልበት የሚረዳ መሠረታዊ ዘዴ መሆን ችሏል፡፡

መሰላሉ የተለያዩ የተሳትፎ ደረጃዎች እንዳሉ በመግለፅ ማስመሰል፣ ማሳመር እና ማዉራት በአካል መገኘት እንጂ መሳተፍ አለመሆናቸውን እና ትርጉም ያለዉ ተሳትፎ የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት በተግባር የሚገለፅ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም መረጃን ከማወቅ እና የተወሰነ ተልዕኮን ለመወጣት ከመመደብ ባለፈ ምክረ ሐሳብን ወደ መጠየቅ እና ከአዋቂ ሰዎች ጋር በጋራ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ዕድል እስከ ማግኘት ድረስ ይሰፋል።

ከፍተኛ የተሳትፎ ደረጃዎች ላይ የሚደረሰው ወጣቶች ተግባራትን ራሳቸው ሲያዘጋጁ እና ሲመሩ ሆኖ በዚህ ላይ ዐዋቂ ሰዎች በደጋፊነት የሚሳተፉበት ወይም በውሳኔ አሰጣጥ በወጣቶች እና በትላልቅ ሰዎች መካከል በጋራ የሚሰራበት ሁኔታ ተግባራዊ ሲሆን ነው፡፡ በመጨረሻም ሥራ ፈጣሪዎች ከበይነ ትውልዳዊ የመማር ዕድሎች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

የሮጀር ሀርት የተሳትፎ መሰላል ስምንት ደረጃዎች አሉት፡፡እነዚህ የተሳትፎ ደረጃዎች ከዝቅተኛ ተሳትፎ እስከ ከፍተኛ ተሳትፎ (ወጣት መር ተሳትፎ) ይደርሳሉ፡፡ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማድረግ ካሉት ደረጃዎች እንደተጨባጭ ሁኔታው የተሻለ ይጠቅማሉ የሚባሉትን መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡

**ሥዕል 15፦ የወጣቶች ተሳትፎ መሰላል**

**የሮጀር ሃርት /Roger Hart/ የወጣቶች የተሳትፎ መሰላል**




ምንጭ፦ Hart, 1992

**ደረጃ 8፦በወጣቶች የተወጠኑ ተግባራት እና ከጎልማሶች ጋር የተጋራ ውሳኔ አሰጣጥ**

ይህ ደረጃ ፕሮጀክቶች ወይም መርሐ ግብሮች በወጣቶች ተዘጋጅተዉ ውሳኔው በወጣቶች እና በአዋቂዎች በጋራ የሚሰጥበት ነው። እነዚህ ፕሮጀክቶች ወጣቶችን ከማብቃት በተጨማሪ በተመሳሳይ ጊዜ ከአዋቂዎች ሕይወት ተሞክሮ እና ከፍተኛ ልምድ የማግኘት አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል። ይህ ደረጃ በወጣቶች/አዋቂ ሰዎች አጋርነት የሚመራ ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

**ደረጃ 7፦ በወጣቶች የሚጀመርና የሚመራ**

ይህ ደረጃ ወጣቶች አንድን ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ራሳቸው ጀምረው ራሳቸው የሚመሩበት ሂደት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ አዋቂዎች የሚኖራቸዉ ሚና የመደገፍ ብቻ ሲሆን በየደረጃዉ በወጣቶች የሚመራ ተግባር ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

**ደረጃ 6፦በጎልማሶች የተወጠነ እና ከወጣቶች ጋር በጋራ ውሳኔዎች የሚሰጡበት**

ይህ ፕሮጀክት እና መርሐ ግብር በጎልማሶች ተወጥነው ውሳኔ አሰጣጡ ግን ከወጣቶች ጋር በጋራ የሚከናወንበት ደረጃ ነው። ይህ ደረጃ አሳታፊ ተግባራዊ ምርምር ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

**ደረጃ 5፦የወጣቶችን ምክር እና መረጃ መቀበል**

ይህ ደረጃ  በጎልማሶች በተዘጋጁ እና በሚመሩ ፕሮጀክቶች ወይም መርሐ ግብሮች ላይ ወጣቶች ምክር የሚሰጡበት ሂደት ነው። ወጣቶቹ የሰጡት ግብዓት እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ እና በአዋቂዎች ውሳኔ የተገኙ ውጤቶች ምን እንደሆኑ እንዲያውቁዋቸው ይደረጋሉ። ይህ ደረጃ በወጣቶች አማካሪ ምክር ቤቶች ሊመራ ይችላል።

**ደረጃ 4፦ወጣቶችን መመደብ እና መረጃ መስጠት**

ይህ ደረጃ ወጣቶች የተወሰነ ተግባር ተሰጥቷቸዉ እንዴት እና ለምን እንደሚሳተፉ መረጃ እንዲያገኙ የሚደረግበት ነው። በመሆኑም ደረጃው በማህበረሰብ የወጣት ቦርዶች የሚካተት ተግባር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

**ደረጃ 3፦ ወሬ ብቻ**

ወጣቶች ድምፃቸውን እንዲያሰሙ እድል ከተሰጠ በኋላ በተግባር ግን ምን እንደሚያደርጉ ወይም እንዴት እንደሚሳተፉ ምንም ምርጫ ሳይኖራቸው ሲቀር የሚያጋጥም የተሳትፎ ደረጃ ነው።

**ደረጃ 2፦ማሳመር**


ይህ ደረጃ ወጣቶች አንድን ፍሬ ነገር በአንጻራዊነት ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ እንዲያግዙ ወይም «እንዲያሳኩ» መጠቀሚያ ሲሆኑና አዋቂ ሰዎች የጉዳዩ ፍሬ ነገር በወጣቶች የተነሣ ስለመሆኑ እንደማያውቁ ሆነው የሚቀርቡበት ሂደት ነዉ፡፡

**ደረጃ 1፦ማስመሰል**

ይህ የሚያጋጥመው ጎልማሶች ወጣቶች አንድን ጉዳይ እንዲደግፉ ካደረጓቸው በኋላ ሐሳቡ በወጣቶች የተጠነሰሰ እንደሆነ አድርገው ሲቀርቡ ነው።

## 7.4. ተማሪ ተኮር የአሠልጣኞች መምሪያ

ሰላም ግንባታ ሂደትን የተሳካ ለማድረግ ሰልጣኞች በዘርፉ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችን እና ተግባራትን ቀርጸው ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በፕሮጀክቶች ያጋጠሙንን ችግሮች ለመፍታት መፍትሄ የምንሰጥባቸው አማራጮች ናቸው፡፡




ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አሰልጣኞች ከሰልጣኞች ጋር ወጣት መር በሆኑ ፕሮጀክቶችና ተግባራት ግንዛቤ ፣ እቅድና እንቅስቀሴ  ላይ በጋራ ሲሰሩ  ተግባራዊ የሚያደርጓቸዉ ደረጃዎች ናቸው፡፡እነዚህ ደረጃዎች ጠቅለል ተደርገው የተቀመጡ እንጂ የፕሮጀክትን አፈጻጸም ሙሉ በሙሉ የሚሳዩ አይደሉም፡፡ ጠቅለል ያለውን ደረጃ በአራት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡

**ደረጃ 1፦ ፕሮጀክትን ለይቶ ማወቅ**

ሰልጣኞች የተወሰኑ ችግሮችን በራሳቸዉ እንዲለዩ እና መለወጥ እንዲችሉ ቦታና እድሉን መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም  ለሰልጣኞች ድጋፍ በማድረግ ችግሮችን ወይም ሁኔታዎችን  በግልም ይሁን በቡድን የሚያንፀባርቁበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ነው፡፡

**ደረጃ 2፦ የፕሮጀክቱን ዕቅድ ማዘጋጀት**

ሰልጣኞችን በጠቅላላው የዕቅድ ዝግጅት ሂደት ላይማሳተፍ እና መምራት ያስፈልጋል፡፡ ፕሮጀክታቸውን መለየትና መቅረፅ እንዲችሉ፤ ማሳካት የሚፈልጉዋቸውን ግቦች እንዲለዩ፣ ማከናወን ያሉባቸውን የተለያዩ ድርጊቶች እና የፕሮጀክታቸውን መጠነ ስፋት ለይተው እንዲያውቁ በቂ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። ከትምህርት ቤቱ ውጭ ያሉ ሌሎች ባለ ድርሻ አካላትን ማሳተፍ ይፈልጋሉ? ከመማሪያ ክፍልና ከትምህርት ቤት በተጨማሪ ሌሎች ተዋንያንን ማሳተፍ እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውን ግብዓት ለሠልጣኞች ማቅረብ ወይም ማመቻቸት ይገባል።

**ደረጃ 3፦ የፕሮጀክት ቡድኖችን እና የመሪነት ሚናዎችን መለየት**

እያንዳንዱ ፕሮጀክት እና ተግባር የተለየ እና ግልጽ መዋቅርን ይፈልጋል፤ ፕሮጀክቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ መፈጸም ይችሉ ዘንድ የእያንዳንዱ ሰልጣኝ ሚና የጋራ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በትግበራ ቡድን ውስጥ ማን አባል ይሁን? የተለያዩ  ኃላፊነቶችን የማስተባበር እና ሁሉም ተግባራት መከናወናቸዉን የመከታተል ሥራን ማን ይሥራ? እያንዳንዱ ሰው የሚጫወተው ሚና አለው? እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እንደ አሠልጣኝ የእርስዎ ሚና  ሰልጣኞች በቡድኑ እንዲሳተፉ እድል መስጠትና  ሁሉም ሰልጣኞች የራሳቸዉን  አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችሉበት አጋጣሚ መፍጠር ነዉ፡፡

**ደረጃ 4፦ ምክረ ሐሳብን መስጠት፣ መደገፍ እና የሂደት ግምገማ ማድረግ**

የእርስዎ ከሰልጣኞች ጋር መሆን እነሱን ለመደገፍ ፣ የፕሮጀክቱን ሂደት ለማሳለጥ እና ለመምራት፣ በፕሮጀክት አፈፃጸም ሂደት ላይ በውሳኔ አሰጣጥ  ምክረሃሳብ ለማካፈል እንደሆነ እንዲሰማቸዉና ይህንንም እንዲረዱ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም አፈፃፀሙን ለመገምገም መደበኛ ስብሰባዎች በዕቅድ መካተታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

## 7.5 የወጣቶች ተሳትፎ በሰላም ግንባታ

ወጣቶች የሰላም ግንባታ ሂደትን ለማሳካት የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ተሳትፎ ሊያደርጉባቸው ከሚችሉባቸው ሂደቶች መካከል የዴሞክራሲ ግንባታ ልምምድ ማድረግ እና በማህበረሰቡ ተሳትፎ ከትምህርት ቤት ውጭ የሰላም ክበብ ማቋቋም ተጠቃሾች ናቸው፡፡

**ዴሞክራሲ በተግባር፦** በትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪዎች መማክርትእና የተማሪዎች ፓርላማ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለአብሮነትና ሰላማዊ ማህበረሰብን ስለመፍጠር ለመማር በተለያዩ አካባቢዎች ዴሞክራሲን በተግባር  ከመለማመድ  ሌላ የተሻለ አማራጭ የለም፡፡

በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ዲሞክራሲያዊ አሠራርን እንዲለማመዱ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ፓርላማ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የተማሪዎች መማክርት ክበብ ያደራጃሉ፡፡ አደረጃጀቶቹ ወጣቶች እንዲበቁ፣ ለመብታቸዉ ተከራካሪና ለት/ቤቱ አስተዳደር እነሱን በተመለከተ ለሚሰጡ ውሳኔዎች ግብዓቶችን እንዲሰጡ የሚያስችል ዕድል ይፈጥራሉ፡፡ አደረጃጀቶቹ ተማሪዎች ሐሳቦችን ለማጋራት እና የተለያዩ ድምፆች በውሳኔዎች ላይ እንዲካተቱ ለማድረግ የሚችሉበትን መድረክ ያመቻቹላቸዋል። በተጨማሪም የተማሪዎች ምክር ቤቶች ለግል ዕድገት፣ የተማሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ፣ ለወጣት መሪዎች ምቹና አስተማማኝ መድረኮችን ለመፍጠር ይረዳሉ፡፡ እንዲሁም በትምህርት ቤት እና ከት/ቤት ውጭ ለውጥ እንዲመጣ ለመሞገት እንዲችሉ በማህበረሰቡ ውስጥ ካሉ ውሳኔ ሰጪዎች ጋር እንዲገናኙ ያደርጉዋቸዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የተማሪ ፓርላማዎች ወጣቶች የምርጫ ውድድርን እንዲለማመዱ ያስችሏቸዋል። ክበቦቹ ወጣቶች ገንቢ የሆኑ የምርጫ ሂደቶችን እንዲለማመዱ፣ በቡድን ሆነው እንዲተባበሩ፣ ፕሮግራሞችን እና ተግባራትን እንዲነድፉ እንዲሁም የራሳቸውን የፈጠራ ችሎታዎች እና ክህሎት እንዲጠቀሙ የሚያስችላቸውን ዕድል ይፈጥሩላቸዋል፡፡ (Engdaw, 2018, ገጽ 172) ።

**በማህበረሰቡ ተሳትፎ ከመማሪያ ክፍል ውጭ የሰላም ክበብ ማቋቋም**

የሰላም ክበቦች የጋራ መግባባትን ለመፍጠር እና የሰላም ባህልን ለመገንባት የተለያየ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ዳራ ያላቸውን ወጣቶች አንድ ላይ የሚያሰባስቡና ሥር ነቀል ለውጥን ለማምጣት የሚያነሳሱ ናቸው። ክበቦች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተለዋዋጪነትን እንዲሁም ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ፡፡

ሁሉም ማህበረሰብ የተለያዩ የቤተሰብና የማህበረሰብ ልዩነቶችን ያለ ግጭት በሰላም በመወያየት ለመፍታት እና አንድነትን ለመፍጠር እንዲችል በሰላም ክበብ ዉስጥ እንዲሳተፉ መጋበዝ ተገቢ ነዉ፡፡ለምሳሌ በኢትዮጵያ ውስጥ የዩኒቨርስቲ ማህበረሰብ ከአሥርት ዓመታት በላይ በሰላም ክበቦች ውስጥ አንድ ላይ ተደራጅተው ከብሄርና ከሃይማኖት አክራሪነት ጋር በተያያዘ በተለያዩ ጉዳዮች በሚካሄዱ የውይይት መድረኮች ከ600 በላይ የሚሆኑ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በየዓመቱ ተመልምለዉ ተሳትፈዋል፡፡

ተማሪዎች የተዛቡ አስተሳሰቦች እና ተራ አነጋገሮች የሚያስከትሉትን ጉዳት ለመቅረፍ አንዳቸዉ ከሌላኛቸው በሚያደርጉት ዉይይት ይማማራሉ።በተጨማሪም ክበቦች የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ፡፡ለምሳሌ እንደ ወርሃዊ ፎረሞችና ዉይይቶች፣ ማካሄድ እንዲሁም አገር አቀፍና ዓለምዓቀፍ የሰላም በዓላትን (መስከረም 11 / ሴፕቴምበር 21) ማክበር ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡

በትምህርት ተቋማት ያሉ የሰላም ክበቦች ወጣቶች በማህበረሰባቸው ዉስጥ እና ዉጭ በሚያደርጉት ተሳትፎ አርአያ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ የሰላም ክበቦች አንድን ማህበረሰብ ለመቀየር እንዴት ወጣቶችን ለማብቃት እና መስተጋብራዊ የትምህርት ዘዴዎችን እና የጋራ ራዕይን በመጠቀም ሰላምን ለማጎልበት እንደሚቻል የሚያሳዩ ተጨባጭነት ያላቸው ሞዴሎች ናቸው።

## 7.6 በዓላትን እና ዓውደ ርዕዮችን በመጠቀም ንቅናቄ መፍጠር

## በሰላም ግንባታ ሂደት ዙሪያ

የክብረ በዓል ዝግጅቶችን ማድረግ ማህበረሰቡን ለማነቃነቅ የሚያስችል ትልቅ ጉልበት አለው። ለምሳሌ በሰልጣኞች የሚመሩ ሰላማዊ ሰልፎችን በማዘጋጀት፣ በሙዚቃዎችና በሰላም መልዕክቶች ግጭትን፣ የኃይማኖት መገለልን፣ ሙስናን እና ሌሎች መሰል ጉዳዮችን በማህበረሰቡ፣ በክልሉ ወይም በአገር ደረጃ ለመቀነስና ለማስቆም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸዉ፡፡ ሰልጣኞች በሂደቱ መቅረብ ያለባቸዉ ወሳኝና አንገብጋቢ ጉዳዮች የትኞቹ እንደሆኑ መምረጥ ወይም መወሰን ይችላሉ፡፡

ዓውደ ርዕዮች ሰላማዊ የሆነ መንገድን፣ በመማር ማክበርን እና ለሰላም አንድ ላይ መቆምን የሚያንፀባርቁ መልእክቶችን በይፋ ለማሳየት እንደ አንድ አማራጭ ሆነው ያገለግላሉ። በዚህ በኩል ተጠቃሽ የሆነን ክንዋኔ እንመልከት፡፡ በኬንያ ውስጥ በሚገኘዉ የጣና ወንዝ ካዉንቲ በተባለ ቦታ በዩኔስኮ የምሥራቅ አፍሪካ ቢሮ፣ በኬንያ የትምህርት ሚኒስቴር እና በአሪጋቶ ኢንተርናሽናል በጋራ በተዘጋጀው 'አንድ ላይ አብሮ መኖርን መማር' ፕሮግራም/Learning to Live Together Pilot Programme/ወቅት የሴሚካሮ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሕፃናት ለማህበረሰባቸው ዓውደ ርዕይ አዘጋጅተው ነበር። የሰውን ልጅ የጋራ መገለጫዎች እና በኬንያ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ብሔሮች ያላቸውን ጥብቅ ግንኙነት የሚወክል እና የሚያብራራ የድር ሥዕልን ተጠቅመው ነበር። ከዚህ በተጨማሪ ልቡ ላይ ስፒሎች የተሰኩበትን የሰው ምስል አቅርበዋል። ጎብኚዎች ስፒሎቹን እንዲያነሡ እና ስፒሎች በተነቀሉበት ቦታ ላይ ያሉትን ቀዳዳዎች እንዲያስተውሉዋቸው ተጠይቀዋል። ምንም እንኳ አስቸጋሪ ቢሆንም ዕርቀ ሰላም ምን ያክል ጠቃሚ እንደሆነ በኋላ ላይ ተብራርቷል።

## 7.7 በወጣቶች የሚመራ ማኅበራዊ ሥራ ፈጠራ

ሰላምን ለማምጣት ከሚያስችሉ ሂደቶች አንዱ ወጣቶች የስራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡ ይህ ሂደት በውጤታማነት መከናወን እንዲችል በወጣቶች የሚመራ ማህበራዊ ስራ ፈጠራን ማበረታታት ተገቢ ነው፡፡

በወጣቶች የሚመራ ማኅበራዊ ሥራ ፈጠራ የሰው ልጆችን ሕይወት ለማሻሻል እና የሰላምን ባህል ለማስተዋወቅ ሊያግዝ ይችላል። ከዚህ በታች ከደቡብ ሱዳን እና ከኡጋንዳ የተገኙ ሁለት በወጣቶች የሚመሩ ውጤታማ የሆኑ ፕሮጀክቶች እንደ አብነት ቀርበዋል።

በ2016 የሰላም ግንባታን እና ማኅበራዊ ሥራ ፈጠራን የሚያገናኘው የደቡብ ሱዳን በወጣቶች የሚመራው 64 Hands SACCO የተባለ ፕሮጀክት በዩ.ኤን.ዲ.ፒ/UNDP/ የማኅበረሰብ ደህንነት እና የጦር መሣሪያ ቁጥጥር ፕሮጀክት /UNDP's Community Security and Arms Control Project/ የተዘጋጀውን የወጣት ሥራ ፈጠራ ውድድርን /Youth Innovation Challenge/ አሸንፏል። 64 Hands SACCO ለአነስተኛ እና ለመካከለኛ የደቡብ ሱዳን የንግድ ድርጅቶች ማኅበረሰብ ተኮር የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጥ የቁጠባ እና የብድር የኅብረት ሥራ ማኅበር ነው።ከዚህ ፕሮጀክት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ነጋዴዎች ህይወታቸውን መለወጥ ችለዋል፡፡

ኡጋንዳ ውስጥ የወደፊቱ ተስፋ ፋውንዴሽን /Future Hope Foundation/ የሚባል መንግሥታዊ ያልሆነ በወጣቶች የሚመራ ድርጅት አለ። ድርጅቱ ስራዉን የጀመረዉ ክህሎት ለወጣት ተቀጣሪ ፕሮግራም በሚል ሲሆን ይህም የወጣቶችን ፍላጎትና ክህሎትን ለማሳደግና በስልጠና ዕውቀትና መረጃ የመለዋወጥ፣ የማስተዋወቅና አውታረ መረብ የመዘርጋት ክህሎትን በማሳደግ ነበር፡፡

**አሳታፊ ጥያቄዎች**

- በኢትዮጵያ ውስጥ  በወጣቶች ከሚመሩ ፕሮጀክቶች ጥቂት ምሳሌዎችን ጥቀሱ?
- በእናንተ ማኅበረሰብ ውስጥ ምን ዓይነት ፍላጎቶች አሉ?
- ለጎዳና ተዳዳሪዎች፣ ለሥራ አጦች፣ ለድሆች እና በበሽታ ለተጠቁ ሰዎች  ምን ዓይነት ሥራ ፈጠራዎች ወይም ፕሮጀክቶች ያስፈልጋቸዋል?

# ምዕራፍ 8፦ የሰላም ግንባታ ዕውቀት ፣ክህሎትና አመለካከት ምዘና

## *8.1 የምዘናው አስፈላጊነት*


ምዘና የማናቸውም የመማር ማስተማር ሂደት አንዱ ቁልፍ አካል ነው። አሠልጣኞች እና ሠልጣኞች ራሳቸውን እንዲመረምሩ፣ ግንኙነቶች እንዲፈጥሩ እና በትምህርቱ በስልጠናው ሂደት ላይ የት ላይ እንዳሉ እንዲረዱ፣ እንዴትስ ወደዚህ ሊደርሱ እንደቻሉ እና አሁንም ድረስ ምን ጥያቄዎች እንዳሉዋቸው እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል። ምዘና አዲስ ነገርን የማግኘት ሂደት የመሆኑን ያህል ራስን የመመርመርና የውስጥ ስሜትን አውጥቶ የመግለጽ ሂደትም  ነው። ለአሠልጣኞች ምዘና የማስተማር ክህሎታቸውን ለማሻሻል የሚጠቅምና በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ያሉ ክፍተቶችን እንዲሞሉ የሚያስችል መንገድ እንደሆነ ተደርጎ መታየት አለበት።

ምዘና የተናጠል እና የቡድን የትምህርት/ስልጠና/ ግንዛቤ መለካትን ማካተት ይኖርበታል፡፡ የዚህ ዓላማ ተማሪዎች የግል ኃላፊነትን ከመወጣት ተነሥተው የቡድን ኃላፊነትን እንዴት እንደሚወጡ ለመገንዘብ ነው፡፡ አሰልጣኞች /መምህራን ምዘናዎች የመማር ማስተማር ሂደቱ  የዕለት ከእለት ክንዋኔዎች  እንደሆኑ መገንዘብ እና ማቀድ ይኖርባቸዋል። በማሰልጠኛ ማዕከል ወይም በመማሪያ ክፍል የትምህርት ዕቅድ ወይም የሥልጠና እንቅስቃሴ ላይ ምንጊዜም ለምዘና የተወሰነ ጊዜ ሊመደብ ይገባል።

## *8.2 የሰላም ግንባታ ትምህርት ብቃቶች*

በሰላም ትምህርት ውስጥ በበርካታ ደረጃዎች እና በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች አማካኝነት ትምህርት ይቀሰማል። ይህም የምዘና ዘዴዎች ዕውቀትን፣ ክህሎትን፣ አመለካከቶችን እና እሴቶችን ጨምሮ በርካታ መጠነ ስፋት ያላቸውን ትምህርቶች  እንዲያካትቱ ሆነው  መቀረጽ እንዳለባቸው ያመለክታል።

**ሥዕል 16፦ የሰላም ትምህርት የመማር ማስተማር መጠነ ስፋት**




## 8.3 የምዘና ጠቀሜታ

ምዘና አሠልጣኞች/መምህራን የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ሊያግዛቸው ይመከራሉ፦

- ሠልጣኞች/ተማሪዎች በተናጠል እና በቡድን ያላቸውን የለውጥ ሂደት እና ግስጋሴ በተጠና መንገድ መከታተል፤
- የሠልጣኞችን/የተማሪዎችንበሠልጣኞች ባሕሪ፣ የእርስ በርስ ግንኙነቶች፣ አመለካከቶች እና ብቃቶች ያሉትን ለውጦች መለየት እና መገንዘብ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የሠልጣኞች ዓውዳዊ ፍላጎቶች በሚመጥን መልኩ አሠልጣኞች የትምህርት መርሐ ግብራቸውን እንደ አስፈላጊነቱ ማዘጋጀት እንዲችሉ ምን ማስተካከያዎች ማድረግ እንደሚያስፈልግ መለየት እና
- ሠልጣኞች/ተማሪዎች በእርስ በእርስ ግንኙነቶች፣ በአመለካከቶች እና በብቃቶች ላይ ያሉ የራሳቸውን ለውጦች እንዲረዱ እና እንዲያንፀባርቁ መድረኮችን እና ዕድሎችን መፍጠር ናቸው።

እነዚህን ግቦች ለመለካት አሠልጣኞች/መምህራን ተጨባጭ የሆኑ (SMART)የትምህርት /የስልጠና ዓላማዎች ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ (SMART) የሚለው የእንግሊዝኛ አህፅሮተ ቃል ሲተነተን specific /የተለየ/፣ measurable /ሊለካ የሚችል/፣ achievable /ሊሳካ የሚችል/፣ realistic /ተጨባጭ/ እና time-bound /በጊዜ የተወሰነ/ ማለት ነው። ለምሳሌ፡-የትምህርቱ /የስልጠናውን ዓላማ ሠልጣኞች/ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ኢ-ፍትሀዊነት ወይም ግጭት ሲኖር ሰላማዊ የችግር መፍቻ አማራጮችን ለይተው ማወቅ ይችላሉ የሚል ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ዓላማ ኢ-ፍትሀዊ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው ሰላማዊ በሆነ መንገድ ምላሽ መስጠት ይችላሉ የሚል ሊሆን ይችላል።

**ሥዕል 17፦ SMART ዓላማዎች**



አሠልጣኞች የትምህርቱ ዓላማዎች መሳካታቸውን ለመመዘን የለውጥ አመልካቾች ሊኖሯቸው ይገባል። የለውጥ አመልካች ለውጥ መኖር አለመኖሩን የሚያመለክት መረጃ ነው። አመልካቾቹ አሃዛዊ ወይም አይነታዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፦ ሦስት እና ከዚያ በላይ ግጭት መፍቻ ሰላማዊ መንገዶች ለይተው ለማወቅ የቻሉ ተማሪዎችን ብዛት መመዝገብ አሃዛዊ አመልካች ሲሆን ለግጭቶች በሰላማዊ መንገድ ምላሽ ለመስጠት በሠልጣኞች የተወሰዱ እርምጃዎችን ዓይነት መመዝገብ አይነታዊ  አመልካች ነው።

አሠልጣኞች/መምህራን የትምህርቱን ዓላማዎች እና አመልካቾች ለሠልጣኞች/ለተማሪዎች ማስተዋወቅ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ መንገድ አሠልጣኞች የሠልጣኞቹን ፍላጎት ሊገነዘቡ እና ምናልባትም ዓላማዎቹን እንደ አስፈላጊነታቸው ሊገመግሙ ወይም ተስማሚ እንዲሆኑ ሊያደርጓቸው ይችላሉ።

**እንዴት ትምህርት/ስልጠናው እየተከናወነ እንዳለ መመዘን እንችላለን?**

- የስልጠናውን/ የትምህርት ዓላማዎችን በማስቀመጥ፤
- አሠልጣኞች/መምህራን ትምህርቱ መከናወኑን እና እንዴት እንደተከናወነ ለይተው እንዲያውቁ የሚያስችሏቸውን ጠቋሚዎች በማዘጋጀት፤
- ቀላል፣ ተማሪን/ሰልጣኝን ያማከሉ እና አሳታፊ አቀራረቦችን እና ዘዴዎችን በመጠቀም እና
- ውጤቶቹን በመመዘን እና በመተንተን ብሎም ውጤትን በማሳወቅ ይሆናል፡፡

## 8.4 ምዘና መቼ መደረግ አለበት?

ምዘና የማሰልጠን/የመማር ማስተማር ሂደቱ አንድ አካል እንደሆነ አድርጎ መገንዘብ እና ማቀድ ያስፈልጋል።ለምዘና የሚሆን የተወሰነ ጊዜ መስጠት ሁልጊዜ የትምህርት ዕቅዱ አንድ አካል ሆኖ መታቀድ አለበት።ለምሳሌ በስልጠናው መጨረሻ ላይ አሠልጣኙ ሰልጣኞች የሚከተሉትን እንዲያደርጉ በቂ ጊዜ ሊመድብ ይገባል፡፡

- በስልጠናቸው/በትምህርታቸው ላይ የራሳቸውን አስተሳሰብ እንዲያንጸባርቁ፤
- ሊያከናውኑ የሚችሉትን ተግባር  እንዲለዩ፤
- እንደ ቡድን ሐሳባቸውን እንዲያንጸባርቁ እና የአቻ ለአቻ ምዘናን እንዲያካሂዱ እና
- በትምህርቱ/በልምምዱ ምን ያህል ያለምንም ችግር መስራት እንደቻሉ ስሜታቸውን እንዲገመግሙ ማስቻል ይገባል፡፡

## 8.5 የሰላም ግንባታ ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የምዘና ዘዴዎች

የሰላም ግንባታ ትምህርት/ስልጠና መርሐ ግብሮች ውጤቶችን ለመመዘን፣ አሠልጣኞች/መምህራኖች ተግባሮቻቸው ያሳደሩትን ተፅዕኖ መረዳት እንዲችሉ  እንዲያግዟቸው ተግባራዊ የምዘና መሳሪያዎችን መጠቀም ይኖርባቸዋል። ጥቂት ተግባራዊ ዘዴዎች በዚህ ክፍል ላይ ተጠቅሰዋል። በሚቀጥሉት ገጾች ላይ የተጠቆሙት የምዘና መሳሪያዎች በሰላም ትምህርት ላይ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉትን ሁሉንም ዓይነት የምዘና ዘዴዎች የሚያካትቱ አይደሉም። ሌሎች መመዘኛ ዘዴዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡

- ምልከታ
- የተግባራትክትትል ማድረጊያ ማረጋገጫ ዝርዝሮች
- በማስታወሻ መዝግቦ መያዝ
- መመዘኛ ደረጃዎች
- የግብረገብ/የሥነምግባር የድርጊት ገለጻ መገለጫ ዝርዝሮች
- ምስሎች/ሥዕሎች
- ጥልቅ ጥናት
- ታሪክ
- የተደራጀ የግል መረጃ ሰነድ
- መገለጫዎች (ፕሮፋይሎች)
- ማመንታት

ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ በዚህ ምዕራፍ የቀረቡትን የምዘና መሣሪያዎች በአጭሩ ያቀርባል።

**ሠንጠረዥ 1፡- የመመዘኛ መሳሪያዎች ማጠቃለያ**

| መመዘኛ ዘዴ | ዓላማ | መቼ መጠቀም እንደሚያስፈልግ |
|---|---|---|
| **የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር** | (ለተማሪዎች) የተማሪዎችን የግል ተሞክሮዎች ይለካል፡፡ (ለአሠልጣኞች) ስለ ክፍለ ትምህርቶች ለመመዝገብ እና በተማሪዎቻቸው ላይ የመጡትን ለውጦች ለመረዳት እንዲሁም ራሳቸው የቀሰሙትን ትምህርት እና ያንፀባረቁትን ሐሳብ ለመያዝ | ከእያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት በኋላ |
| **ስሜቶችን መረዳት** | ዕውቀት ማጋራቱ ምን ያህል ግንዛቤ እንደተያዘበት እና በትምህርት ክፍለ ጊዜው ተማሪዎች ምን ያክል ተሳትፎ እንዳደረጉ መረዳት | በክፍለ ትምህርቱ ወቅት ማስተካከያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ/ወይም ከክፍለ ጊዜው በኋላ እንደ ፈጣን የምዘና ዘዴ ለመጠቀም |
| **የራስን ሐሳብ ማንጸባረቂያ ዘዴዎች** | ታዳጊ ወጣቶች የተዘጋጁ ከውስጣዊ እና ውጫዊ ወሳኝ ሁኔታዎች ጋር የተዛመዱ ችግርን የመቋቋም ችሎታዎች መለካት | ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ በተወሰነ ጊዜ የሚሞላ መጠይቅ |
| **የወደድኩት እና አልወደድኩትም ብዬ የማስበው ነገር** | መማር ማስተማሩን መመዘን እና ክፍለ ጊዜውን መገምገም | ከክፍለ ትምህርቱ በኋላ አፈጻጸሙን ለመገምገም እና ምን ሊሻሻል እንደሚችል ለይቶ ለማወቅ |
| **በቡድን ሆኖ ሐሳብን መለዋወጥ** | በግል ስለ መማር ያለውን ተሞክሮ ለሌሎች ማካፈል እና በልምምዶች ወቅት ስለ ቡድን እና ስለ ሥነ እንቅስቃሴዎች የግል ሐሳብን ማንፀባረቅ | ከክፍለ ትምህርቱ በኋላ አሰልጣኞች በልምድ መጋራቱ እንዲሳተፉም ይጋበዛሉ፡፡ |
| **ማረጋገጫ ቻርት** | የነፍስ ወከፍ ተማሪን ትምህርት አቀባበል መለካት | ከክፍለ ትምህርቱ በኋላ |
| **ስሜቶችን፣ ዕውቀትን እና ድርጊትን ለሌሎች ማጋራት** | ዕውቀትን እና ክህሎትን መሰረት በማድረግ በተማሪዎች የግል ትምህርት አቀባበል ላይ አስተያየት መስጠት | ከክፍለ ትምህርቱ በኋላ |
| **የለውጥ ተሞክሮዎች ስብስብ** | አሠልጣኞች የተማሪዎቹን ለውጥ ለማሳየት የተማሪዎቹን ገጠመኞች መሰብሰብ | ከመርሐ ግብሩ ሙሉ ትግበራ በኋላ (ከ 6 እስከ 12 ወራት) |

## የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር

የራስን ሪፖርት የማዘጋጀት ዘዴዎች ብዙውን ጊዜ በጣም ተገቢነት ያላቸው የአንድ ግለሰብ የግል ተሞክሮዎች መለኪያ ተደርገው ይቆጠራሉ። በመሆኑም ለተማሪው እና ለአሠልጣኙ ለሁለቱም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ ከችግሮች ከመላቀቅ አንጻር የተማሪዎችን ዕድገት ለመመዘን ስለሚረዳቸው በዚህ ላይ አሠልጣኞች የራሳቸውን ሐሳብ ማንፀባረቅ ይጠበቅባቸዋል።

## የተማሪዎች የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር

በመጀመሪያው ክፍለ ትምህርት አሠልጣኙ ለተማሪዎቹ የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተርን መስጠት አለበት። ከሁሉም በፊት ይህ ደብተር ተሞክሮን እና ስሜትን ለመግለፅ የሚያገለግል የግል ማስታወሻ መሆኑን ማሳወቅ ያስፈልጋል። ይህም የትምህርት ሂደታቸውን ለመገንዘብ ከመማሪያ ክፍሉ ትምህርት ወይም ከሥልጠናው ተግባር በኋላ ሰልጣኞች የራሳቸውን የውስጥ ስሜትና ሐሳብ እንዲገልጹ የሚጋበዙበት ቀላል ዘዴ ነው። በቡድን የልምድ ልውውጥ ወቅት ሰልጣኞች የራሳቸውን የውስጥ ስሜትና ሐሳብ በፈቃደኝነት ለሌሎች እንዲያጋሩ ይጋበዛሉ፤ ሆኖም ግን በፈቃደኝነት ካልሆነ በስተቀር ማካፈል የማይፈልጉትን ማናቸውንም ነገር ለሌሎች እንዲያካፍሉ መገደድ የለባቸውም።

ይህንን የውስጥ ስሜትን እና ሐሳብን የማንፀባረቅ ሂደት እንዲቀላቀሉ አሠልጣኞች አስቀድመው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን እና ገላጭ ዓርፍተ ነገሮችን ተማሪዎች ከግምት እንዲያስገቡ እና የተሰማቸውን ስሜትና ያላቸውን ሐሳብ እንዲያንፀባርቁ ሊጋብዟቸው ይችላሉ። የተወሰኑ መሪ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ ቀርበዋል፡፡

1. የተግባሩ/የትምህርቱ ርዕሰ ጉዳይ ምን ነበር?
2. ትኩረት የሚያሻቸው ዋነኛ ነጥቦች ምን ነበሩ?
3. ከዚህ ተግባር የተማርኩት ምንድን ነው?
4. በዛሬው ክንዋኔ ላይ በጣም ደስ ያለኝ ነገር ምንድን ነው?
5. ከዚህ ተግባር በኋላ እኔን የለወጠኝ ነገር አለ? ሐሳቦቼን ለውጫለሁ? እንደዚህ ከሆነ እንዴት?
6. በትግበራ ወቅት እኔ ከጠበቅኩት ውጭ የሆነ ነገር አጋጥሟልን? ያጋጠመውን ችግር ለመፍታት ችዬ ነበር? ከሆነ እንዴት ነው ችግሩን ልፈታው የቻልኩት?
7. ምን አዲስ ነገር አገኘሁ፤ ስለ ራሴስ ዛሬ ምን አዲስ ነገር ተምሬያለሁ? በዙሪያዬ ስላሉ ሰዎችስ ምን አዲስ ነገር ተምሬያለሁ?
8. ዛሬ የተማርኩትን እንዴት ልጠቀምበት እችላለሁ?
9. እንዲህ ብዬ አስብ ነበር/እንዲህ አደርግ ነበር...... እና አሁን እንዲህ አስባለሁ/እንዲህ አደርጋለሁ... የሚሉትን ያካትታል፡፡

ይህ የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር ዓላማው ሁሉን አቀፍ አንጸባራቂ የመማር ችሎታዎችን ማዳበር በሆነው አጠቃላይ ጽብረቃ ላይ ስለሚያተኩር በማናቸውም ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሊያገለግል ይችላል።

### የአሰልጣኞች ምልከታ ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር

የአሰልጣኞች ምልከታ ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተሩ በክፍለ ትምህርቶች ወቅት ስለተገኙት ተሞክሮዎች፣ ተግዳሮቶች እና ስኬቶች ስሜትን እና ሐሳብን ለማንፀባረቅ እና ለምልከታ ዕድል ይፈጥራል። ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተሩ የትምህርትን ስርጸት እና የራስን ሐሳብና ስሜት ማንፀባረቂያን ለመጻፍ የሚያስችል ዕድል እንደመስጠቱ በተማሪዎች ላይ የተስተዋሉትን ለውጦች እና ሽግግሮች አሠልጣኞች ለመመዝገብ እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።

### ስሜትን ማወቅ

በአንዳንድ ሁኔታዎች አሠልጣኞች የትምህርት ስርፀቱን ለመገምገም እና ለመጠቀም ምቹ የሆነ የተናጠል (የግል) እና የቡድን ግምገማ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል። የተማሪዎችን «ውስጣዊ ስሜት» መለካት የተማሪዎችን አሁናዊ የተሳትፎ እና ከፍተኛ የመማር ፍላጎት ደረጃን ለክቶ ለማወቅ የሚያስችል ዘዴ ነው።

ይህ የሚካሄደው ተማሪዎች እጃቸውን እንዲያወጡ የማድረግ ልምድ እንዲያዳብሩ በማድረግ ነው። ተማሪዎች ይህን ሲያደርጉ አሠልጣኞች ራሳቸውን እንዲህ ብለው መጠየቅ አለባቸው:: እጃቸውን እያወጡ ያሉት በጋለ ስሜት ነው? ለመናገር ወይም ፍላጎታቸውን ለመናገር ወይም ለማሳየት እውነተኛ ስሜት አላቸውን? ተሳትፎ እያደረጉ ነውን? እጆች በደንብ አልተዘረጉም ወይስ ከናካቴው አልተነሱም?

እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች የቀረቡላቸውን ርዕሰ ጉዳዮች መረዳታቸውን ወይም አለመረዳታቸውን በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ባላቸው ምልክቶች እንዲያሳዩ በመጠየቅ ሊመዘኑ ይችላሉ።

ይህ ልምምድ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ በክፍል ትምህርቱ ላይ ማስተካከያ ማድረግ ያስፈልግዎት እንደሆነ እንዲረዱ ሊያግዝዎት ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ እርስዎ ለተማሪዎቹ ያጋሯቸው ዕውቀት ሙሉ በሙሉ ግንዛቤ እንዳገኘ እና ለተማሪዎች ጠቃሚ እንደሆነ ለመረዳት ተግባራዊ ዘዴም ነው።

### የራስን ሐሳብ የመግለጽ ዘዴዎች

የራስን ሐሳብ እንደመጻፍ ወይም በግል መጠይቅ እንደመሙላት ያሉየራስን ሐሳብ የመግለጽ ዘዴዎች ተማሪዎች የግል እና ጥብቅ መረጃዎችን እንዲያጋሩ ስለሚጠይቁ በከፍተኛ ደረጃ ምስጢርን መጠበቅ ይፈልጋል።

መጠይቅ ተማሪዎች እንዲሞሉ ሲሰጥ የቃላት አመራረጡን ከተማሪዎቹ ፍላጎት እና የአገላለጽ መንገድ ጋር በሚስማማ መልኩ በጥንቃቄ የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። የመጠይቅ ምርጫዎች ከ1 (ሁልጊዜ) እስከ 5 (በጭራሽ) የሚል ባለ አምስት ነጥብ መለኪያ ደረጃ ሊሰጣቸው የሚችል ሆኖ ዝቅተኛ ድምር ውጤት በተማሪዎቹ ዘንድ ችግርን ከመቋቋም ጋር የተገናኙ ውስጣዊ እና ውጫዊ ሁኔታዎች እንዳሉ በከፍተኛ ደረጃ ጠቋሚ ይሆናል።

ለተማሪዎች የተዘጋጀ መጠይቅ ምሳሌ እንዲሆን ከዚህ በታች የቀረበውን ሠንጠረዥ 2 እባክዎ ይመልከቱ። እዚህ ላይ እንደምሳሌ ሦስት የብቃት መለኪያዎች ብቻ የቀረቡ ቢሆንም ሁሉም ዓይነት የብቃት መለኪያዎች በመጠይቅ ውስጥ መመዘን እንዳለባቸው እባክዎ ልብ ይበሉ። በመሆኑም ለተቀሩት የብቃት መለኪያዎች እንዴት ጥያቄዎችን ማዘጋጀት እንደሚቻል ለመረዳት ከዚህ በታች የቀረቡትን ሦስት የብቃት መለኪያዎች እንደ ምሳሌ ይጠቀሙባቸው።

መመዘኛ ደረጃዎች 1= ሁልጊዜ፣ 2= ብዙ ጊዜ፣ 3= አንዳንድ ጊዜ፣ 4= አልፎ አልፎ፣ 5= በጭራሽ

**ሠንጠረዥ 2፦ የራስን ሐሳብ የመግለጽ ዘዴ ናሙና**

| ብቃቶች | ጥያቄዎች | ደረጃ አሰጣጥ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ራስን መገንዘብ | ለማህበረሰቤ አዎንታዊ አስተዋፅኦ ማድረግ የምችል መስሎ ይሰማኛል። | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | በዙሪያዬ ያሉ ሰዎች የሚወዱኝ እና የሚያግዙኝ መስሎ ይሰማኛል። | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| በራስ መተማመን | ምንም ነገር ቢያጋጥመኝ ራሴን ችዬ ልቋቋመው እንደምችል እርግጠኛ ነኝ። | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| በጥልቀት ማሰብ | በውይይቶች እና በክፍል ውስጥ በሚደረጉ ክዋኔዎች ወቅት የራሴን ሐሳብ ለማንጸባረቅ ደህንነት እና በራስ የመተማመን ስሜት ይሰማኛል። | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

**የወደድኩት እና ያልወደድኩት ነገር**

ተማሪዎቹን ክብ ሠርተው እንዲቀመጡ ያድርጓቸው፤ በክቡ ዙሪያ በመዘዋወር  እያንዳንዱ ተማሪ ከክፍል ትምህርቱ የወደደውን ነገር፤ ያወቀውን ነገር፣ ያልወደደውን  ነገር እንዲሁም በትምህርት ክፍለ ጊዜው ቢሻሻል ጥሩ ነው የሚለውን ነገር እንዲናገር ይጋብዙ።

**በቡድን ሆኖ ሐሳብን መለዋወጥ**

ሐሳባቸውን የሚያካፍሉት ለዕድሜ አቻዎቻቸው ከሆነ ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች ስለ ባሕርያቸው፣ ስለሐሳባቸው እና እያጋጠሟቸው ስላሉ ለውጦች የራሳቸውን ሐሳብ ለማንፀባረቅ ቀላል ይሆንላቸዋል። ሁሉም ተማሪ ለመናገር ዕድል እንዳገኘ እና ቡድኑ በጥቂት ተናጋሪዎች ብቻ እንዳልተዋጠ ያረጋግጡ። ከዚህ በተጨማሪ ለደህንነት አስተማማኝ የሆነ የሐሳብ ማጋሪያ መድረክ መፍጠርዎትን ማረጋገጥ ጠቃሚ ነው፡፡ ሐሳብ እንዲጋራ የሚደረግበት ዘዴ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ዘዴው ግንኙነቶችን ለመፍጠር እና የለውጥን እና የሐሳብ ማንፀባረቅን የግል ተሞክሮዎች ለማጋራት የተመቸ መሆን አለበት።

በቡድን ውስጥ ሆኖ ሐሳብን ለሌሎች ማጋራት አንድ ሰው በግል የቀሰመውን ትምህርት ለሌሎች እንዲያካፍል ያስችላል፡፡ይህ ሂደት ተሳታፊው በልምምዶቹ ወቅት በቡድኑ እና ባለው እንቅስቃሴ ላይ የሚሰማውን የግል ስሜትና ሐሳብ እንዲያንፀባርቅ የሚያስችል ዕድል ይፈጥራል።

ውይይቱን እርስዎም ይቀላቀሉ! እንደ አሠልጣኝነትዎ መጠን ከቡድኑ ጋር ቁጭ እንዲሉ እና የራስዎትን ታሪክ እና የራስዎትን ልምድ እንዲያካፍሉ ይጋበዛሉ። ይህም ለተማሪዎቹ ደህንነት አስተማማኝ የሆነ ድባብን ለመፍጠር ከማገዙ ባሻገር አርዓያ መሆን ከሚሉት መርሆዎች ጋር አብሮ የሚሄድ ነው።

**ሣጥን 17፦ በኬንያ ውስጥ በማሳይ ጎሣ እና በኢትዮጵያ ምዕራባዊ ክፍሎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው «መናገሪያ በትር»**

«መናገሪያ በትሩን» የያዘው ግለሰብ ብቻ እንዲናገር ይፈቀድለታል። በትሩ በእጅዎ ላይ እስካለ ድረስ መናገር የሚፈልጉት ነገር ሌሎች እንደገባቸው ሆኖ እስኪሰማዎትና እስኪረኩ ድረስ እርስዎ ብቻ መናገር ይችላሉ። ሌሎች የራሳቸውን ሐሳብ እንዲገልጹ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲስማሙ ወይም እንዲቃወሙ አይፈቀድላቸውም። የሚያደርጉት ነገር ቢኖር እርስዎ የሚሉትን ነገር ለመረዳት መሞከር እና በመቀጠል የገባቸውን በቃል መግለጽ ብቻ ነው። እንደተረዱዎት እርግጠኛ ሲሆኑ በትሩን ለቀጣዩ ተናጋሪ ያስተላልፋሉ።

ቡድኖች ውይይት ሊያደርጉባቸው እና ሐሳብ ለመለዋወጥ ሊያቀርቧቸው የሚችሉ አንዳንድ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል፡፡

- ለየትኛው ተግባር/መርሐግብር ይበልጥ ዋጋ ትሰጣላችሁ? ይህንን ሂደት ለምን ወደዳችሁት? ይህ ለእናንተ ለምን አስፈላጊ እና የተለየ ሆነ?
- መመስከር የምትችሉት የመድልዎ ወይም የአክብሮት መነፈግ አጋጣሚ አለ? ማን ተጽዕኖ አርፎበት ነበር? በዚህ ሁኔታ ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ ከነበራችሁ ምን ዓይነት ስሜት ተሰማችሁ? አፃፋ ምላሽ እንዴት ሰጣችሁ?
- ኢ-ፍትሐዊነት፣ ማግለል እና መድልዎ ወይም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ያለበትን ሁኔታ ለመለወጥ እንደ ግለሰብ ወይም እንደ ማኅበረሰብ ምን ማድረግ እንደምትችሉ ማሰብ ትችላላችሁ? ሐሳባችሁን ልታጋሩ ትችላላችሁ?
- የተማራችሁት ዋናው ነገር ምን ነበር? ለምን?

ይህን ጊዜ የእርስ በርስ ግንኙነትን ለመፍጠር፣ ሐሳብን ለሌሎች ለማጋራት፣ ለመተሳሰብ እና ለአንድነት መፍጠሪያ መድረክ እንዲሆን ይጠቀሙበት። የግል ገጠመኞቻቸውን እንዲተርኩ፣ ተሞክሮዎቻቸውን እንዲናገሩ ያድርጉዋቸው።ታሪክን በመናገር ትርጉም እንደሚፈጠር ያስታውሱ፤ እንዲሁም አሠልጣኞች በአስተሳሰብ ላይ ያሉ ለውጦችን በዚህ አጋጣሚ ለይተው ማወቅ ይኖርባቸዋል። ገጠመኝ ሲናገሩ ወይም ተሞክሮዎቻቸውን ለሌሎች ሲያካፍሉ ስሜታዊ ጫና ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ሊያጋጥምዎ ይችላል። ስሜታዊ ጫና ያለባቸው ተማሪዎችን እንዴት መደገፍ እንደሚቻል ጠቃሚ ምክሮችን ለማግኘት ሣጥን 18ን ይመልከቱ።

በቡድን ሆኖ ሐሳብን መለዋወጡ እንዳበቃ ሐሳብን ለሌሎች በማካፈሉ ክፍለ ትምህርት ከራሳቸው ሐሳቦች እና ስሜቶች ጋር ምን ለሌሎች እንዳካፈሉ በራሳቸው የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር ላይ እንዲጽፉ  ይጋብዟቸው።

## ማጥን 18፦ ስሜታዊ ጫና ያለባቸው ተማሪዎችን ለመደገፍ አሰልጣኞች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

በዚህ የሥልጠና ማኑዋል ውስጥ ያሉት አብዛኛዎቹ ክንዋኔዎች ከሰልጣኞች ስሜት እና የግል ተሞክሮዎች ጋር የተያያዙ ናቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች የራሳቸውን ስሜትና ሐሳብ፣ የተዛቡ አመለካከቶች፣ ተራ አነጋገሮች እና ከእሴትና ከማንነት ጋር የተያያዙ ችግሮችን በተመለከተ ሐሳባቸውን ሲያጋሩ ተማሪዎች ስሜታዊ ጫና ሊያጋጥማቸው ይችላል። ስሜታዊ ጫናን የሚያንፀባርቅ ሁኔታ ከተፈጠረ ተማሪዎችን እንዴት ማገዝ እንደሚችሉ ለአሠልጣኞች የቀረቡ ጠቃሚ ምክሮች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

- ሰልጣኞች ስሜታቸውን ለቡድኑ እንዲያጋሩ ወይም እንደ አሠልጣኝነትዎ ከእርስዎ ጋር በግል ስሜታቸውን እንዲያካፍሉዎት የሚያስችላቸውን መድረክ እና ጊዜ ይስጧቸው።
- ሰልጣኞች በተለየ ሁኔታ ስሜታዊ ጫና ውስጥ ከሆኑ  በግል ለማዳመጥ ዝግጁ ይሁኑ። ስሜታዊ መሆን ምንም ችግር እንደሌለው እንዲያውቁት ያድርጓቸው። አስጨናቂው ስሜት ለምን እንደመጣ እንዲረዱ እና ለምን በዚህ ስሜት እንደተጎዱ  ለሰልጣኞች ይንገሯቸው።
- በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ሰልጣኞች ከልምምዱ በኋላ የእርስዎን ድጋፍ ሊፈልጉ ይችሉ ይሆናል። ሰልጣኞች ያጋጠሟቸውን ችግሮች በአግባቡ ለመፍታት እንዲችሉ ምክርና መመሪያ ይስጡ።
- በልዩ ልዩ ክንዋኔዎች ወቅት ወይም በቡድን ሐሳብ ልውውጥ ሂደት  በመካከሉ አንዳንድ ሰልጣኞች ስሜታዊ ጫና ውስጥ እንዳሉ ካንፀባረቁ ችግሩን ይገንዘቡላቸው። ምን እንደተፈጠረ ይጠይቁ፤ ስሜታቸውን እንዲገልጹ ይፍቀዱ፤ ከዚህም ሌላ ተሳታፊዎች እንዲያዳምጡ እና የግለሰቦቹን ውስጣዊ ስሜት ለመረዳት እንዲሞክሩ ይጠይቋቸው።
- በጥልቅ መተንፈስ፣ መዘመር፣ መዝፈን ወይም ጋደም እንዲሉ ማድረግ የመሳሰሉ ቀላል የመዝናኛ ስልቶች በስሜት ጫና ውስጥ ያለ ሰው እንዲረጋጋ ሊያግዙ ይችላሉ።
- ሁልጊዜም የሰልጣኞችን ምስጢር በማክበር መጠበቅ መቻልዎን ያረጋግጡ።

ከ Arigatou International የ 2008 ኅትመት ከሆነው *Learning to Live Together: An Intercultural and Interfaith Programme for Ethics Education*፣ ገጽ 41 ላይ ተወስዶ ለዚህ ሰነድ በሚመች መልኩ የተዘጋጀ

## ማረጋገጫ ቻርት

ማረጋገጫ ቻርት ከአንድ ክፍል ትምህርት በኋላ የግል ምዘናን ለማድረግ የሚጠቅም ሌላ ጠቃሚ መሳሪያ ነው። ቻርቱ የግል ትምህርት ቅበላን ለመለካት የሚረዱ ጥያቄዎችን በማሰባሰብ ይዘጋጃል። እነዚህ ጥያቄዎች ለተማሪዎች በሰሌዳ ላይ ሊጻፉላቸው፣ በማስታወሻ ደብተሮቻቸው ወይም በትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ መልስ ሊሰጡባቸው ወይም በወረቀት ታትመው ለተማሪዎች እንዲሞሏቸው ሊታደሉ ይችላሉ። በቻርቱ ላይ የሚሰፍሩት ጥያቄዎች የግል ስሜትን እና ሐሳብን ማንፀባረቅን ማነቃቃት እንዲቻል ማድረግ ያለባቸውን ያህል ተማሪዎች እርምጃ እና ኃላፊነት ለመውሰድ የሚያስችሏቸውን መንገዶች እንዲያገኙ መጋበዝ መቻል አለባቸው። ሰልጣኞች በዙሪያቸው የሚያጋጧቸውን ሁከት፣ ማግለልና መድልዎ እንዲሁም ኢፍትሐዊነት ለማሻሻል እና ለመለወጥ እንዲቻል ምን አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ? የዕድሜ አቻዎቻቸው በተግባር እንዲያግዟቸው እንዴት ሊያንቀሳቅሷቸው ይችላሉ?

## የእኔ ማረጋገጫ ቻርት

| ማሻሻል ያለብኝ የተወሰነ ሁኔታ አለ? እባክዎ በዝርዝር ይጻፉ፡፡ | ይህን ሁኔታ ለምን ማሻሻል ያስፈልገኛል? | ይህን የተለየ ሁኔታ ለማሻሻል እንዳልችል የሚያደርገኝ ነገር አለ? ካለ ምንድን ነው? እባክዎ በዝርዝር ይጻፉ፡፡ | ይህ ሁኔታ አሉታዊ በሆነ መንገድ ተፅዕኖ እያሳረፈ ያለው በእኔ ላይ ብቻ ነው ወይስ ሌሎችንም ሰዎች እያስቸገራቸው ነው? እንዴት?<br><br>እባክዎ በዝርዝር ይጻፉ፡፡ | ይህን ሁኔታ ለማሻሻል የሌሎችን እገዛ እፈልጋለሁ? ማን ሊያግዘኝ ይችላል?እባክዎ በዝርዝር ይጻፉ፡፡ |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

ይህን የማረጋገጫ ቻርት ለእርስዎ ተማሪዎች እና ክዋኔዎች የሚመች እንዲሆን አድርገው ሊያስተካክሉት ይችላሉ። ለምሳሌ ከአካባቢ ግጭት (በመማሪያ ክፍል፣ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ) ጋር በቀጥታ እንዲገናኝ በማድረግ ለሰላም ግንባታ የሚዘጋጀውን የሰላም ትምህርት እንደ አስፈላጊነቱ ሊያስተካክሉት ይችላሉ።ከዚህ በመቀጠል ተማሪዎች ግጭቱን እንዲተነትኑ እና እንደ ሰላም ትምህርት ዋነኛ አካል ሰላማዊ በሆነ መንገድ ግጭቱ ሊፈታ ወደሚችልበት አቅጣጫ እንዲያመሩ ይጠይቋቸው።

### ዕውቀትን፣ ስሜትን እና ድርጊትን ለሌሎች ማጋራት

ተማሪዎች የሰውን ቅርፅ በመጠቀም ያገኙትን ዕውቀት (ጭንቅላት)፣ ስሜቶች (ልብ)፣ ተሳታፊነት እና እርምጃዎች (እጆች) የተሰማቸውን ስሜት እና ሐሳባቸውን ማንፀባረቅ ይችላሉ። ይህ ቅርፅ ( የሰው ቅርፅ ጠቋሚ ምስል ) በጥቁር ሰሌዳው  ወይም በወረቀት ላይ ተስሎ ሁሉም ተማሪዎች በሚያዩት ቦታ ላይ ሊሰቀል ይችላል። ሰልጣኞች ከዕውቀት፣ ከመንፈስ፣ ከስሜቶች እና በድርጊት ላይ ካላቸው ተሳትፎ አንጻር ያጋጠማቸውን ለውጥ ለማንፀባረቅ በወረቀት ላይ እንዲለጥፉ ወይም በሰሌዳው ወይም በፖስተሩ ላይ ምልክት እንዲያደርጉ አሠልጣኞች መጋበዝ ይችላሉ።

ተማሪዎች የቀሰሙትን ትምህርት ለሌሎች እንዲያጋሩ ሊጠይቋቸው የሚችሉ ጥቂት ርዕሰ ጉዳዮች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

| ጭንቅላት | ልብ | እጆች |
|---|---|---|
| ራስን ማወቅ | ከሌሎች ጋር መገናኘት | የቡድን-ሥራ |
| ሰላማዊ አማራጮችን ፈልጎ ማግኘት | የራስን ስሜት መቆጣጠር | የማኅበረሰብ ተሳትፎ |
| ጥልቅ አሳቢነት | ርህራሄ | ችግር አፈታት |

## የለውጥ ታሪኮች ስብስብ

የመማር ማስተማሩን ዕድገት መዝግቦ ለመያዝ የሚያስችለው ሌላኛው መንገድ የተማሪዎችን መለወጥ የሚያሳዩ ገጠመኞችን (ታሪኮችን) መሰብሰብ ነው። ይህ ዘዴ «ይበልጥ አስፈላጊ ለውጥ» /Most Significant Change (MSC)/ በመባል ይታወቃል፡፡ የፕሮጀክትን/የመርሐ ግብርን ውጤት ለመረዳት በሰፊው ዕውቅና የተቸረው ዘዴ ነው። የ«ይበልጥ አስፈላጊ ለውጥ» (MSC) መሠረቶች የሚጣሉት ከተወሰነ መርሐ ግብር ተጠቃሚ ከሆኑ ግለሰቦች መካከል ገጠመኞችን /ታሪኮችን/ በመሰብሰብ ነው።

ይህ የሰነዳ ሂደት በአሠልጣኙ ከተቀመጡት የትምህርት ዓላማዎች በስርዓት እና በጥንቃቄ ከተመረጡት ይበልጥ ጠቃሚ ታሪኮች( ገጠመኞች) አንጻር በጉልህ የሚታዩ ለውጦችን የሚያንፀባርቁ የተማሪዎች ታሪኮች/ገጠመኞች ስብስብ  በጥንቃቄ መምረጥን  ያካትታል።

**ምስል 5፡- የለውጥ ታሪኮች እንደ አመልካቾች**




ምንጭ፡- Davis & Dart, 2000

# ምዕራፍ 9፦ የሰላም ግንባታ ትምህርት የተግባር ልምምዶች

ይህ ምዕራፍ ቀደም ባሉት ምዕራፎች በዝርዝር ከተገለጹት ቁልፍ የሰላም ግንባታ ፅንሰ ሐሳቦች፣ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎችና ተዛማጅ ምዕራፎች ጋር ተማሪዎች ወይም ሠልጣኞች ራሳቸውን በልምምድ እንዲያዋህዱ ምሳሌዎችን ያቀርባል።

ትምህርት ለተማሪዎች/ለሠልጣኞች በተግባር የተደገፈና ከሰልጣኞች/ ከተማሪዎች ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተስማማ ከሆነ በቀላሉ ዕውቀትን፣ ክህሎትን እና አመለካከትን መገንባት ይቻላል። በመሆኑም አንድን የተማሪ /የሠልጣኝ ቡድን የትምህርት ፍላጎት ለማሟላት እነዚህን እና ሌሎች ትምህርታዊ ልምምዶችን እንደ አስፈላጊነቱ አስማምቶ ማዘጋጀት የሚያበረታታ ጉዳይ ነው።

ከዚህ በታች የቀረበው ሠንጠረዥ ልምምዶችን፣ ከመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎቻቸው እና ተዛማጅነት ያላቸውን ምዕራፎች ያቀርባል።

| ልምምዶች | ማስተማሪያ ሥነ-ዘዴዎች | ተዛማጅ ምዕራፎች | ገጽ |
|---|---|---|---|
| የግጭት ገላጭ ዛፍ | በውይይት እና በችግር ፈችነት ላይ የተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት | 1 | |
| የማምንበት | በውይይት ላይ የተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት | 1 እና 2 | |
| ማኅበረሰቡ ችግርን የሚቋቋምበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ | በውይይት የመማር ማስተማር ሂደት | 1 እና 4 | |
| ግጭትን በጨዋታ መግለጽ | በግጭት አፈታት ዙሪያ የተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት | 1 እና 4 | |
| አዋልድጌሳ(ዓይጠ-ሞገዋ) እና ዝሆን | በሙከራ ላይ የተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት | 2 እና 4 | |
| የሰላም ግንባታ ዜና | ተሞክሮ እና ችግር አፈታት ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 2 እና 5 | |
| እየጠፉ ያሉ ደሴቶች ጨዋታ | በጨዋታ ላይ የተመሰረተ የመማር ማስተማር ሂደት | 3 | |
| መንታ አስተሳሰብ መኖር | በውይይት ላይ የተመረኮዘ የመማር ማስተማር ሂደት | 3 | |
| ራስን ማወቅ | በልምምድ ላይ የተመሰረተ መማር ማስተማር ሂደት | 3 እና 4 | |
| ራስን በሌሎች ቦታ አስቀምጦ ማዬት | ውይይት እና ማሰላሰል ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 3 እና 4 | |
| የሚያመሳስሉንን ነገሮች መለየት | ማሰላሰልና በመመራመር ላይ የተመረኮዘ የመማር ማስተማር ሂደት | 4 | |
| የራስ መለያ ምልክት | በተሞክሮ ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 4 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጭንብል መልበስ | በልምምድ ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 4 | |
| ድር ቢያብር | ትብብርን ወይም አንድነትን የሚያጠናክር የመማር ማስተማር ሂደት | 4 | |
| ወንዙን መሻገር | ችግሮችን በትብብር ማሸነፍ ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 4 | |
| በባህሎች መካካል ያለ ግንኙነት | በተሞክሮ ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 4 | |
| ማኅበረሰብን አሳታፊ ፕሮጀክቶች | አሳታፊ እና በትብብር የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 4፣ 6 እና 7 | |
| በትውልዶች መካከል የሚደረግ ውይይት | በውይይት ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 7 | |
| የ2030 ዘላቂ የልማት ግቦች | በውይይት ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 7 | |
| የምርጫ ልምምድ | በሙከራ በተሞክሮ ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 7 | |
| የባህል ብዝኃነት ክብረ በዓላት | በልምምድ ላይ የተመረኮዘ መማር ማስተማር ሂደት | 7 | |
| የሰላም ክበብን ማቋቋም | ንድፈ ሃሳብን በተግባር የሚገልጹበት የመማር መማር ማስተማር ሂደት | 7 | |

## የግጭት ገላጭ ዛፍ

**ዓላማ**

የግጭት ገላጭ ዛፍ በመጠቀም በግጭት መሠረታዊ ምክንያቶች፣ በዋነኛ ችግር እና በውጤቶች መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ ለማወቅ።

**የሚጠበቅ ውጤት**

ተማሪዎች ወይም ሰልጣኞች የግጭትን ገላጭ ዛፍ በመጠቀም የግጭትን መሰረታዊ ምክንያትን፣ ዋነኛ ችግርን እና ውጤትን መተንተን መቻል።

**የማስተማሪያ መሳሪያዎች**

- ጥቁር ሰሌዳ፣ ነጭ ሰሌዳ እና ፍሊፕቻርት
- ጠመኔ፣ ማርከር፣ወረቀት ወይም እስኪብርቶ
- ምስለ የግጭት ገላጭ ዛፍ

**ልምምድ፡-**

- በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚያጋጥሙ የግጭት ምሳሌዎችን ተማሪዎች እንዲዘረዝሩ በማድረግ አዕምሮን ማነቃቃት። መልሶችን በሰሌዳው ወይም በፍሊፕቻርት ላይ በመጻፍ

እና መልሶቹን ወደ ተለያዩ ምድቦች በመከፋፈል ማስቀመጥ (በቀጥተኛ፣ በመዋቅራዊ ወይም በባህላዊ- ለተጨማሪ መረጃ ክፍል 1ን ይመልከቱ)።

- ሠልጣኞችን/ተማሪዎችን ከአምስት እስከ ስድስት አባላት ባሉት ቡድኖች በማደራጀት፣ ለእያንዳንዱ ቡድን የሚወያይበትን የተለያዬ የግጭት ዓይነት መመደብ፤ ለውይይት የሚቀርቡ የግጭት ርዕሶች የሚያስቆጡ አለመሆናቸውን በማረጋገጥና እንዲወያዩ በማድረግ ተማሪዎችን ወደአላስፈላጊ ግጭት እንዳያስገባቸው ማረጋገጥ መቻል።

- ምሳሌ በመጠቀም የግጭትን ገላጭ ዛፍ ያስተዋውቁ። የግጭትን ገላጭ ዛፍ ቁልፍ የሆኑ የግጭት ነጥቦችን ለይቶ ለማሳየት የሚጠቀም ሥዕላዊ መግለጫ ነው። ይህ ምስል በግል ከሚደረግ ልምምድ ይልቅ በቡድን ልምምድ ላይ ይበልጥ የተሻለ ጠቀሜታ አለው። በበርካታ ግጭቶች ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ሃሳቦች ይኖራሉ፡፡ እነሱም፦

    ሀ. የግጭቱ ዋነኛው መንስኤ ምንድን ነው?
    ለ. በግጭቱ ምክንያት የተፈጠረው ችግር ምንድን ነው?
    ሐ. በግልፅ የሚታዩ የግጭቱ ውጤቶች ምንድን ናቸው?

- እያንዳንዱ ቡድን የዛፉን ሥሮች፣ ግንድ እና ቅርንጫፍ በትልቅ ወረቀት ላይ እንዲስሉ ያድርጉ።

- ሰልጣኞች ወይም ተማሪዎች የግጭት ገላጭ ወይም መተንተኛ ዛፉን በመጠቀም ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በመወያየት መልስ እንዲሰጡ ያድርጓቸው፡፡

    ሀ. በግጭት መተንተኛ ዛፉ መሰረት የግጭቱ ዋና ዋና መንስዔዎች ምንድን ናቸው?
    ለ. በግጭት መተንተኛ ዛፉ መሰረት ግጭቱ ያስከተላቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?
    ሐ. በግጭት መተንተኛ ዛፉ መሰረት የግጭቱ ውጤቶች ምንድን ናቸው?

- ሁሉም ቡድኖች የግጭት ገላጭ ዛፍን በግልጽ ስሩን፣ ግንዱንና ቅርንጫፎችን በሚያሳይ መልኩ በትልቅ ወረቀት ላይ እንዲስሉ ያድረጉ። የተወያዩበትን የግጭት ዓይነት በግጭት መተንተኛ ዛፍ መሰረት በቡድን ተወካዮች አማካኝነት ለተሳታፊዎች ገለጻ እንዲሰጥ ያድርጉ።

- በግጭት መተንተኛ ዛፍ መሰረት የግጭቱን መሰረታዊ ምክንያቶችን፣ ዋና ዋና ችግሮችንና ያስከተሉትን ውጤቶች ማጠቃለያ ይስጡበት።

**ማስታወሻ፦ ይህን ግጭትን ገላጭ ዛፍ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል**

- ሥሮች፣ ግንድ እና ቅርንጫሮች ያሉትን የግጭት ገላጭ ዛፍ ይሣሉ (በትልቅ ወረቀት፣ በጥቁር ሰሌዳ፣ በፍሊፕ ቻርት፣ በግድግዳ ወይም በመሬት ላይ)።

- ለእያንዳንዱ ተማሪ በእያንዳንዱ ካርድ ላይ መመሪያዎች የተጻፉበት ጠቋሚ ካርድ ወይም ተመሳሳይ ወረቀት ይስጡ፤ ተማሪዎች ግጭቱን ሲያዩ ቁልፍ ችግሮችን ለመጠቆም አንድ ወይም ሁለት ቃል ይጽፋሉ፤ ወይም ምልክት ያደርጋሉ፤ ወይም ሥዕል ይሥላሉ።

- በመቀጠል እያንዳንዱ ተማሪ ካርዶቹን ከግጭት ገላጭ ዛፉ ላይ እንዲያጣብቅ ይጋብዙ፡፡
  1. ዋነኛ ችግር ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ ግንዱ ላይ፤
  2. መሰረታዊ ምክንያት ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ ሥሩ ላይ፤
  3. ውጤት ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ላይ።
- እያንዳንዱ ተማሪ ካርዶቹን በግጭት ገላጭ ዛፍ ላይ ካጣበቀ በኋላ በዋነኛው ችግር ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የካርዶቹን አቀማመጥ ትክክለኛነት ከአንድ የተወሰነ የጋራ ስምምነት ላይ እንዲደረስ ቡድኑ ውይይት እንዲያደርግ ከተማሪዎቹ ወይም ከሰልጣኞቹ መካከል አንዱ ውይይቱን እንዲመራ ያድርጉ።

- ተማሪዎች/ ሠልጣኞች አንድ ዓይነት ስምምነት ላይ እንደሚደርሱ ከወዲሁ በመገመት የትኞቹን የግጭቶች ዓይነቶች በመጀመሪያ መፍትሔ መስጠት እንደሚፈልጉ ከውሳኔ ላይ ከመድረሳቸዉ በፊት ያረጋግጡ። ይህ ሂደት ረጅም ጊዜ ሊወስድ የሚችል ቢሆንም በአሰልጣኙ ፍላጎት ላይ በመመስረት ቡድኑ ተከታታይ ስብሰባዎችን በማድረግ ዉይይቱን ሊያጠናቅቅ ይገባል ።

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች በቡድን ተከፋፍለው የራሳቸዉን የግጭት ገላጭ ዛፍ በመለጠፍ ማብራሪያ ሊሰጡ ይገባል።

**ተማሪዎች/ ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ፦**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የቀሰሙትን የሰላም ግንባታ ትምህርት ለመግለጽ በዕለታዊ ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ሥዕል ወይም ጥቂት ምልክቶችን እንዲሥሉና ማብራሪያ እንዲሰጡ ያድርጉ።

## የማምንበት ዓላማዎች

- አንድ ሰው ለሚያምንበት ነገር እንዲቆም የሚያስችለውን ተሰሚነት ለማዳበር።

- የሌላውን ሐሳብ በአክብሮት የማዳመጥ አስፈላጊነትን ለማሳየት ወደ ግጭት ሊያመሩ የሚችሉ አባባሎች ላይ ክርክር ለማድረግ።

**ውጤቶች**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች አመለካከት፣ እምነት እና ሐሳብ ከሌሎች ሰዎች አመለካከት፣እምነት እና ሐሳብ እንዴት ሊለዩ እንደሚችሉ አውቀዋል።

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የሌሎችን ሐሳብ፣ አመለካከት እና እምነት ከአክብሮት ጋር ለማዳመጥ ያላቸውን ችሎታ አበልፅገዋል።

**የትምህርት/የሥልጠና መሣሪያዎች**

- የሚነበቡ አባባሎች አስቀድመዉ በዝርዝር ያዘጋጁ፣

- በአግራሞትነት የሚታይ መሃል ለመሃል መሥመር ለመሥራት የሚያስችሉ እንደ ጠመኔ፣ ፕላስተር ወይም ክር ያሉ የትምህርት/የሥልጠና መሣሪያዎች «እስማማለሁ» እና «አልስማማም» የሚሉ ሁለት ትላልቅ ምልክቶች ይጠቀሙ፣

**ልምምድ**

*ያሉበት ቦታ የትም ይሁን (መመሪያ ክፍል፣ መጫወቻ ሜዳ፣ ወዘተ) በክፍሉ ወይም በቦታው አንደኛው ጥግ «እስማማለሁ» ማለት እንደሆነ እና ሌላኛው ጥግ ደግሞ «አልስማማም» ማለት እንደሆነ ለተማሪዎች/ ለሠልጣኞች ይገልጹላቸዋል።*

*በአማራጭነት የቀረቡ የትምህርት/የሥልጠና መማሪያዎች ካሉ ምልክቶቹ በሁለቱም ወገን መሃል ላይ መሥመር ተሥሎባቸው ሊሰቀሉ ይችላሉ። ከክፍሉ «እስማማለሁ» ወይም «አልስማማም» ወደሚሉት አባባሎቹ በተከታታይ ሲነበቡ እንደ ምላሽ መስጫ ዘዴ ተማሪዎች/ሠልጣኞች ወይም በራሳቸው ሐሳብ መሠረት መሥመሩ ላይ እንዲቆሙ ያድርጓቸው።*

*በተማሪዎች/ በሠልጣኞች መካከል የሐሳብ ልዩነትን ሊፈጥሩ የሚችሉ ጥቂት አባባሎችን ጮክ ብለው ያንብቡላቸው። ለምሳሌ፡-*

- *በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሁሉም ሕፃናት ትምህርት ቤት መግባት መቻል አለባቸው።*
- *የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በአጥጋቢ ውጤት ያጠናቀቁ ተማሪዎችሁሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመማር መብት ሊኖራቸው ይገባል።(ይህ ሀሳብ ትክክል አይመስልም)*
- *በማናቸውም ምክንያት ሰው መግደል ስሕተት ነው።*
- *በኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎች ለሚያምኑበት የመዋጋት መብት አላቸው።*
- *ሁሉም ሰው በሰላም የመኖር መብት አለው።*
- *የአየር ብክለት መቆጣጠር የኢትዮጵያ መንግሥት ኃላፊነት ነው።*
- *ሁሉም ሰው የፈለገውን ሃይማኖት የመከተል መብት አለው።*
- *አንዳንድ ግለሰቦች በሀይማኖቶች መካከል ግጭት እንዲፈጠር ጥረት ያደርጋሉ፡፡*
- *አባባሉን ካነበቡ እና ተማሪዎች/ሠልጣኞች እንደየምላሻቸው እንዲሰለፉ ከተደረገ በኋላ ለምን በዚህ ሰልፍ (በእስማማለሁ፣ በአልስማማም ወይም በመሃል ላይ) ላይ እንደቆሙ እንዲያብራሩ ጥቂት ተማሪዎች ይጠየቁ። በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከቆሙ ተማሪዎች መካከል የሚሰጡ መልሶችን ይቀበሉ እና ሁሉም ተማሪዎች ለመናገር ዕድል እንዲያገኙ ማድረግዎትን ለማረጋገጥ ይሞክሩ።*
- *ሁሉንም አባባሎች አንብበው ከጨረሱ በኋላ ተማሪዎች ክብ ሠርተው እንዲቀመጡ ያድርጓቸው። በአጋጠሚቸው አንዳንድ ችግሮች እና ይህ ሁኔታ ምን ዓይነት ስሜት እንዲሰማቸው እንዳደረገ ተወያዩ ። ተማሪዎች ለጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ላይ ከተቸገሩ ይህ ለምን ሊሆን እንደቻለ እንደሚያስቡ ተማሪዎቹ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። ከውይይቱ ነጥሮ መውጣት ያለበት ዋነኛ ነጥብ ዓለም ለኑሮ ቀላል*

እንዳልሆነች እና ምን መታመን እንዳለበት እና መቼ አቋም መያዝ እንደሚያስፈልግ መወሰን ሁልጊዜ ቀላል እንዳልሆነ ነው። ተማሪዎች ከእነርሱ በተቃራኒ በሌላ ጥግ ሲሰለፉ ሲያዩ ምን እንደተሰማቸው እንዲገልጹ ይጠይቋቸው። ስለ ራሳቸው እና ስለ እምነታቸው ምን ተሰማቸው?

- የሰዎች አመለካከት፣ እምነት እና ሐሳብ እንዴት እንደሚለያዩ እና ይህም አንዳንድ ጊዜ እንዴት ወደ ግጭት ሊመራ እንደሚችል አፅዕኖት በመስጠት ልምምዱን ያጠናቁ። ተመሳሳይ አመለካከት፣ እምነት ወይም ሐሳብ የሌላቸውን ሌሎች ሰዎች ከአክብሮት ጋር የማዳመጥን አስፈላጊነት ያብራሩ።

**ተማሪዎች/ ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ፦**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ ከልምምዱ ያገኙትን ሐሳብ እንዲጽፉ ያድርጓቸው።

## ማኅበረሰቡ ችግርን የሚቋቋምበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ

## ዓላማዎች

1. የአንድን ማኅበረሰብ ለግጭት ተጋላጭነት እና ጥንካሬዎች በሥዕላዊ መግለጫ በኩል ለመመርመር፤
2. በሥዕላዊ መግለጫ በኩል ማኅበረሰቡ ይበልጥ ችግርን የሚቋቋሙ እንዲሆኑና እንዴት ዘዴዎችን መቀየስ እንደሚቻል ለማወቅ።

**ውጤት፦**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የማኅበረሰባቸውን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ዕድሎችን እና ሊከሰቱ የሚችሉ የአደጋ ስጋቶችን ለመከላከል እንዲችሉ ግንዛቤን አጎልብተዋል።
- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የማኅበራዊ፣ የልማት፣ የባህል እና የፖለቲካ ችግሮች ከግጭት መፈጠር ጋር እንዴት እንደሚተሳሰሩ ደርሰውበታል።
- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የልዩነት ክፍተቶችን እና የማኅበረሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ መውሰድ የሚችሏቸውን እርምጃዎች ለይተው አውቀዋል።

**የትምህርት/የሥልጠና መሣሪያች**

- ፍሊፕ-ቻርት ወይም መሣያ ወረቀት
- የተለያዩ ቀለማት ያሏቸው ማርከሮች

ልምምድ፦

- ተማሪዎችን/ሠልጣኞችን ከአራት እስከ ስድስት የሚደርሱ አባላት ባሉዋቸው ቡድኖች ይክፈሏቸዉ እና ለእያንዳንዱ ቡድን ትልቅ ወረቀት እና የተለያዩ ቀለማት ያሏቸውን ማርከሮችን ይስጧቸው።

- ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ከልክ በላይ ብዙ ጊዜ ሳያጠፉ ማኅበረሰባቸውን የሚያሳይ ካርታ እንዲሥሉ ይጋብዟቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የማኅበረሰቡን ዋነኛ መገለጫ ባሕሪያት የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ያዘጋጁ።

- ተማሪዎችን/ ሠልጣኞችን ከግጭት አንጻር ማኅበረሰባቸው ምን ዓይነት ተጋላጭነቶች ወይም የአደጋ ስጋቶች እንዳሉባቸዉ እንዲመለከቱ ይጠይቋቸው። አብዛኞቹ ላይ እነዚህን ለማመላከት የተወሰኑ ቁልፍ ቃላትን ወይም ምልክቶችን በመጠቀም የተለየ ቀለም መቀባት አለባቸው። ለምሳሌ በርካታ ከማኅበረሰቡ ውጭ ያሉ ሰዎች ሊገኙባቸው ስለሚችሉ እና ብዙውን ጊዜ በሰው የሚጨናነቁ እና ግርግር የሚበዛባቸው የገበያ ቦታዎች ወይም አውቶቡስ ተራዎች ከፍተኛ ተጋላጭነት ያለባቸው ቦታዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ብዙዎቹ ላይ ማህበረሰባቸው ግጭትን ለመከላከል ያሉትን ጥንካሬዎች፣ ግብዓቶች እና ዕድሎች ለማሳየት በተለየ ቀለም ምልክት እንዲያደርጉ ይጠይቁዋቸው። ለምሳሌ፡- ፖሊስ ጣቢያ ጸጥታን፣ ሕግ እና ሥርዓትን ከማስጠበቅ ረገድ እንደ የማኅበረሰቡ ጥንካሬ ሆኖ ሊታይ ይችላል። አንዳንድ ቦታዎች ወይም ግብዓቶች እንደ ሁኔታው የሚወሰን ሆኖ የተጋላጭነት ስጋት እና ጥንካሬ ሁለቱንም መሆን እንደሚችሉ ልብ ይበሉ።

- በሂደቱ ላይ ተማሪዎች/ሠልጣኞች አንዳቸው ከሌላኛቸው ጋር በንቃት ውይይት እንደሚያደርጉ ያረጋግጡ፤ እንዲሁም ለተወሰኑ ቡድኖች ወይም ለሁሉም ቡድኖች በጋራ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተጨማሪ ውይይቶች እንዲደረጉ ያነሳሷቸው።

- ከእያንዳንዱ ቡድን አንድ ተማሪ/ሠልጣኝ በመጋበዝ የውይይቱ መሪ እንዲሆን እና የተወያዩት ምን እንደሆነ እንዲያብራራ ያድርጉ። ሌሎች ምን ጉዳይ ላይ እንደተወያዩ ለማወቅ በሌሎቹ ቡድኖች የተሠሩትን ፖስተሮች እንዲያዩ እና በቡድኖቹ ውይይት መሪ የሚሰጠውን ማብራሪያ እንዲያዳምጡ ያድርጓቸው። ተማሪዎች የሌሎችን ቡድኖች የተለያዩ አመለካከቶችን መስማት እንዲችሉ የውይይት ሂደቱ በተወሰኑ ጥቂት ደቂቃዎች እንዲቀጥል ያድርጉ።

- ሁሉንም አንድ ላይ መልሶ በመሰብሰብ፣ ከልምምዱ ያገኙትን ተሞክሮ በተመለከተ ተማሪዎች/ሠልጣኞች የተሰማቸውን ስሜት እና በውስጣቸው ያለውን ሐሳብ

እንዲያንፀባርቁ  እና ተጋላጭነቶችን ለይቶ በማወቅ ማኅበረሰቡ ይበልጥ ችግርን ተቋቋሚ እንዲሆን ማድረግ የሚለውን ሐሳብ እንዲያዳብሩ ያድርጓቸው።

**ተማሪዎች/ ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ለማኅበረሰባቸው አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ የሚያስችላቸው የራሳቸው ጥንካሬ ምን እንደሆነ የሚሰማቸውን እንዲያንፀባርቁ ይጋብዟቸው።

## ግጭትን በጨዋታ መግለጽ

**ዓላማ**

- የሰላም ግንባታ ክህሎትን፣ ፈጠራ የተሞላበትና ጥልቅ አሳቢነትን በእውነተኛ ሕይወት ላይ የተመሠረቱ መላ ምቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ።

**ውጤት**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ለግጭት ምክንያት የሆኑሁኔታዎችን ይለያሉ፡፡ ለተፈጠሩ ችግሮች አዎንታዊ መፍትሔዎችን ይፈልጋሉ፡፡።

**የትምህርት/የሥልጠና መሣሪያዎች**

- ምንም አያስፈልግም።

**ልምምድ፡-**

- ተማሪዎችን/ሠልጣኞችን በአነስተኛ ቡድኖች ያደራጁዋቸው፤በመቀጠል  በእርስዎ ማኅበረሰብ ወይም አገር ውስጥ ያለ ችግር ጋር ግንኙነት ላለው የተወሰነ የቢሆንስ መላ ምት እያንዳንዱን ቡድን ይመድቡ። እነዚህ ግጭቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ እርስ በርስ ወይም ከማኅበረሰቡ ውጭ የሚያጋጥሙ ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ግጭቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

<table>
<tr><td>
የግጭት ምሳሌ፡- በአንድ ቤት ውስጥ ያሉ አንድ ወንድም እና አንዲት እህት በቤቱ ውስጥ የቀረውን አንድ ብርቱካን ማን መውሰድ እንዳለበት በተመለከተ እየተጋጩ ነው። ሁለቱም ብርቱካኑ የሚገባው ለኔ ነው ባዮች ናቸው። በጣም የሚወዱት የአጎታቸው ልጅ ቤት መጥቷል እና ወንድምዬው ለእንግዳው ጭማቂ ለመሥራት ብርቱካኑን መጠቀም ይፈልጋል።  እህትየዋ ደግሞ ለአጎታቸው ልጅ የብርቱካን ኬክ ለመሥራት አስባለች።<br><br>
በግጭቱ ውስጥ ያሉ ወገኖች፡-  ወንድም እና እህት<br><br><br>
የወንድምዬው አቋም፡- ብርቱካኑን እፈልጋለሁ<br>
የእህትዬው ፍላጎት፡- ብርቱካኑን እፈልጋለሁ<br><br>
የወንድምዬው ፍላጎት፡- ቤት የመጣው የአጎታቸው ልጅ ደስ እንዲለው የብርቱካን ጭማቂ ማዘጋጀት።<br>
የእህትየዋ ፍላጎት፡- ቤት የመጣው የአጎታቸው ልጅ ደስ እንዲለው የብርቱካን ኬክ መጋገር።
</td></tr>
</table>

- እያንዳንዱን ሁኔታ የሚያሳይ የተለያዩ ተዋንያን የሚሳተፉበት እና የተለየ ችግሩ የተፈታበትን መንገድ የሚያሳይ ከሦስት እስከ አራት ደቂቃ ርዝማኔ ያለው አጭር የግጭት ሚና የሚወክል ጨዋታ እንዲያዘጋጁ ያድርጓቸው። የግጭት ሚናን የሚወክለውን ጨዋታ እንዲያዘጋጁ ለቡድኖቹ እስከ 20 ደቂቃ ያህል ጊዜ ይስጧቸው።

- እያንዳንዱ ቡድን የግጭት ሚናን ወክሎ ጨዋታውን በትወና እንዲያሳይ ያድርጉ።

- እያንዳንዳቸው የግጭት ሚናን ወክለው ከተጫዎቱ በኋላ ምን እንደተፈጠረ ውይይት ያድርጉ፡፡ ለምሳሌ፡- በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የነበሩት ወገኖች እነማን እንደነበሩ፣ አቋማቸው እና ፍላጎታቸው ምን እንደነበረ፣ ምን እንደተሰማቸው፣ ተዋንያኑ ለምን እንደዚያ አድርገው እንደተወኑ እና የቢሆንስ መላ ምቱን እንዴት በሌሎች መንገዶች መጫወት ይቻል እንደነበረ እንዲያብራሩ ያድርጓቸው።

- በቂ ጊዜ ካለ ቡድኖቹ የግጭት ሚናን ወክለው ጨዋታዎችን መልሰው እንዲጫወቷቸው ማድረግ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን አሁን የቢሆንስ መላ ምቱ በተለየ መንገድ ሊያጋጥም እንደሚችል ለማሳየት ሌሎች ቡድኖች ጣልቃ እንዲገቡ ወይም ተዋንያንን በሌላ እንዲተኩ መፍቀድ አለበት።

- ሁሉም ጨዋታዎች ከተጠናቀቁ እና ውይይት ከተደረገባቸው በኋላ ከልምምዱ የተማሩትን ትምህርት ተማሪዎች/ሠልጣኞች ጥቂት ነጥቦችን በማስታወሻ እንዲይዙ ይጋብዟቸው።

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት በተመለከተ የያዟቸውን ነጥቦች ለሌሎች እንዲያጋሩ ጥቂት ተማሪዎችን/ሠልጣኞችን ይጋብዙ፤ ተሳታፊዎች ከልምምዱ ምን ትምህርት እንደቀሰሙ ውይይት እንዲያካሂዱ ያድርጉ።

**ተማሪዎች/ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- ተማሪዎች/ ሠልጣኞች በግጭት ውስጥ በሚገኙበት ጊዜ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ሐሳባቸውን ለማንፀባረቅ የራሳቸውን የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር እንዲጠቀሙ ይጋብዟቸው።

## አዋልድጌሳ (ዓይጠ-ሞገጥ) እና ዝሆን

**ዓላማ**

- የቃል ማብራሪያ በመከተል የአንድን ሰው ንቁ የማዳመጥ ክህሎት ለማበልጸግ።

**ውጤት**

- ተማሪዎች/ ሠልጣኞች የማዳመጥን አስፈላጊነት ተገንዝበዋል ።

**የትምህርት/የሥልጠና መሣሪያዎች፦**


- ወረቀት/ማስታወሻ ደብተር
- እስክርቢቶ ወይም እርሳስ
- ጥቁር ሰሌዳ ወይም ፍሊፕ ቻርት

**ልምምድ፦**

- ይህንን ልምምድ ሁሉም ተማሪዎች/ ሠልጣኞች ወረቀት እንዲያወጡ በመጠየቅ ይጀምሩ ። የአንድ እውነተኛ እንስሳን ዝርዝር መግለጫ ሊያነቡላቸው እንደሆነ እና እነርሱም ይህንን እንስሳ ከሚሰሙት ላይ ተነሥተው መሣል እንዳለባቸው ይንገሯቸው።

- ሥዕል ለመሣል እንዲችሉ በቂ ጊዜ በመስጠት ከእያንዳንዱ መሥመር በኋላ ላፍታ ንባቡን ይግቱ (ሥዕል እየሣሉ እንደሆነ በምናብ ማሰብ፤ ሥዕሉን የሚሥሉት እርስዎ ቢሆኑ ኖሮ በእያንዳንዱ መሥመር መሃል ምን ያህል ጊዜ ሊያስፈልግዎት ይችል እንደነበረ ይገምቱ)። ቶሎ ከአንዱ መሥመር ወደ ሌላው የሚሄዱ ከሆነ ይህ ልምምድ ዋጋ የለውም። ዝርዝር መግለጫ የሚከተለው ነው፡፡

    - በአፍሪካ ውስጥ በብዛት የሚገኝ እንስሳ
    - እንደ ቱቦ የመሰለ ረዥም አፍንጫ ላይ ያለ ክብ ነገር (ያብራሩ - አፍንጫው ቱቦ ዓይነት ነው)
    - ትናንሽ ዓይኖች
    - ትላልቅ ጆሮዎች
    - ረጅም ጭራ
    - ከሰውነት አቋም ጋር ሲነጻጸር በጣም የቀጠኑ እግሮች
    - ግራጫ ቡናማ  ቆዳ
    - እንደ መቆፈሪያ የሚያገለግሉ ወፋፍራም ጥፍሮች



- አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ዝሆንን ይሥላሉ። የመጨረሻውን ፍንጭ ሲሰሙ በጣም ግራ ይጋባሉ። አንዳንዶች በዝሆኑ ላይ ረጃጅም ጥፍሮችን ይሥላሉ፤ ሌሎች ደግሞ ሥዕላቸውን ሰርዘው እንደገና አዲስ ሥዕል መሣል ይጀምራሉ። ለእርስዎ እንደ ዋቢ እንዲያገለግልዎት የእንስሳው ሥዕል እዚህ ላይ ተሰጥቷል፤ እንስሳው አዋልድጌሳ የሚባል ጉንዳን እና የመሳሰሉትን የሚመገብ በምሽት ብቻ የሚንቀሳቀስና በጉድጓድና ዋሻ የሚኖር አጥቢ እንስሳ ነው፡፡

- ምን እንደሣሉ ሌሎች ማየት እንዲችሉ ተማሪዎች/ሠልጣኞች የሣሉትን ሥዕል ከፍ አድርገው እንዲያሳዩ ይጠይቋቸው።

- በመቀጠል እንዲህ በማለት ተማሪዎችን/ሠልጣኞችን  መጠየቅ ይችላሉ፦
    - በዚህ ልምምድ ላይ ምን ያደረግን ይመስላችኋል?
    - ከዚህ ምን ልንማር እንችላለን?
    - ሳነብላችሁ የነበረውን ነገር መሣል ለናንተ ቀላል ነበር ወይ?
    - በሣላችሁበት መንገድ እንድትሥሉ የገፋፋችሁ ምክንያት  ምንድን ነው?

- ከተማሪዎች/ከሠልጣኞች መልስ ካልተገኘ ትምህርቱ ስለ ማዳመጥ እና የውስጥ ድምፅን/ስሜትን ስለመግለጽእንደሆነ ለተማሪዎቹ ያብራሩላቸው (የሁለቱንም ማብራሪያ ከዚህ በታች ይመልከቱ)።

    - **ማዳመጥ፦**  ይህ የሰው ልጅ የተወሰነ መረጃን ለማዳመጥ ያለውን ዝንባሌለማወቅ እና እንዴት ወደ ድምዳሜዎች እንደሚደርስ ሐሳብን ለማንፀባረቅ የሚያስችል ነው። ይህ እንቅስቃሴ በተለይ ተማሪዎች/ሠልጣኞች ራሳቸውን እንዴት እንደሚያዳምጡ እንዲያስቡ የሚያስችል ጠቀሜታ አለው። በአጠቃላይ አነጋገር በመጀመሪያ ሰዎች ከሚናገሩት መካከል የተወሰነውን ክፍል እናዳምጣለን፤ ከዚያም በጎደለው ቦታ ከራሳችን እንሞላለን። ሰዎች የሚሉትን ሁሉ ማዳመጥ በጣም ወሳኝነት አለው።

    - **ውስጣዊ ድምፅ/ስሜት፦** በምናዳምጥበት ጊዜ በአጠቃላይ ሌላው ሰው የሚለው ነገር ላይ አስተያየቶችን የሚሰጥ እና ተጨማሪ መረጃዎችን ከራሱ በማሟላት የሚጨማምር ውስጣዊ ድምፅ/ስሜት ጭንቅላታችን ውስጥ እንዳለ በማብራራት የ«ውስጣዊ ድምፅ»ን ፅንሰ ሐሳብ ምንነት ማስተዋወቅ ይችላሉ። ምናልባትም አሁን በያዝነው ልምምድ ላይ ሙሉ ማስረጃውን ከማግኘታቸው በፊት «ዝሆን ነው» ብሎ የነገራቸው ይኸው ድምፅ/ስሜት ሊሆን ይችላል።

- ተማሪዎችን/ሠልጣኞችን «እንዴት በተሻለ ሁኔታ  ማዳመጥ እንችላለን?» በማለት ይጠይቋቸው እና መልሶቻቸውን በሰሌዳው ላይ ወይም በፍሊፕ ቻርቱ ላይ ይጻፏቸው። ራሳቸው መልሱን ካላገኙ አንድ ሰው እነርሱን በደንብ እያዳመጣቸው እንደሆነ ለማረጋገጥ ምን ዓይነት በዓይን ሊታዩ የሚችሉ ምልክቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ይጠይቋቸው።

- በመጨረሻም ጥንድ ጥንድ ሆነው ንቁ የማዳመጥ ልምምድ እንዲያደርጉ ይጠይቋቸው። ከጥንድ ተማሪዎች/ ሠልጣኞች መካከል አንዱን ደስተኛ ስሜት የተሰማውን አጋጣሚ እንዲተርክ እና ሌላው ደግሞ በንቃት እንዲያዳምጥ ይጠይቋቸው። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ሚናቸውን ይቀያይሩ። በቂ ጊዜ ካለ ንቁ ማዳመጥን የተመለከተው ውይይት እንዴት እንደነበረ ይጠይቋቸው እና ውይይት ያድርጉ።

**ተማሪዎች/ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ የሚያስቡትን ነገር እንዲጽፉ ያድርጓቸው። በተጨማሪ በሕይወታቸው በተሻለ ሁኔታ ሊያዳምጡት የሚፈልጉትን ግለሰብ ለይተው እንዲያውቁ ይጠይቋቸው እና በሚቀጥለው ጊዜ ከግለሰቡ ጋር ሲገናኙ ንቁ የማዳመጥ ክህሎትን እንዲለማመዱ ያድርጉ።

## የሰላም ግንባታ ዜና

**ዓላማዎች**

- ለገሃዱ ዓለም የቢሆንስ መላ ምቶች የችግር አፈታት እና የግጭት መፍትሔ አሰጣጥ ክህሎትን ተፈጻሚ ለማድረግ።
- አክብሮት እና መግባባት በጎደሉባቸው ሁኔታዎች ውስጥ መፍትሔዎችን ለመፈለግ።

**ውጤት**

- የአክብሮት መጓደል ላለባቸው ሁኔታዎች የሚሆኑ አዎንታዊ መፍትሔዎችን ተማሪዎች/ሠልጣኞች አስሰው በራሳቸው ሕይወት ውስጥ ያሉና ወደፊት ሊከሰቱ በሚችሉ ግጭቶች ላይ ተፈጻሚ አድርገዋል።

**የትምህርት/ የሥልጠና መማሪያዎች፡-**

- የሰላም ዜና ካርዶች (ከዚህ በታች ይመልከቱ)

**ልምምዶች፡-**

- ተማሪዎችን/ሠልጣኞችን ከ4 እስከ 5 በሚደርሱ ቡድኖች ይክፈሏቸው። ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ የሰላም ካርድ ይስጡ። ልክ በቴሌቪዥን ላይ እንደ ቀረበ አርዕስተ ዜና በመቁጠር መፍትሔ ይዘው መምጣት እና ሪፖርት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ይንገሯቸው።
- እያንዳንዱ ቡድን መፍትሔ ለማግኘት እና የዜና መጽሔቱን ለማዘጋጀት ሠላሳ ደቂቃ ጊዜ ይኖረዋል። ሁኔታውን እንዲመረምሩ ወይም በጉዳዩ ላይ ተሳትፎ ያላቸውን ሰዎች ቃለ መጠይቅ እንዲያደርጉ እና መፍትሔውን ሪፖርት እንዲያደርጉ ይጠይቋቸው።
- እያንዳንዱ የዜና መጽሔት ከተደመጠ በኋላ ውይይት አድርጉ። በዚህ ላይ ሊጠየቁ የሚገባቸዉ አንዳንድ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡
  - ለቀረበው ሁኔታ ሌላ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች አሉ?
  - ሁኔታው በተፈጥሮ አደጋ ቢባባስ ምን ሊፈጠር ይችላል?

- እንደ መፍትሔ የቀረበው ሐሳብ የሌሎችን መብት አይጥስም?
- በዚህ ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?
- ሰዎች እንዴት ሊታረቁ ይችላሉ? በዓለም ላይ ሰላምን ለማምጣት ዕርቀ ሰላም አስፈላጊ ነውን?

- አዳዲስ እና አወዛጋቢ ሐሳቦችን በማበረታታት ተማሪዎች/ሠልጣኞች አዕምሯቸውን እንዲያሠሩ እና ስለ መፍትሔዎቹ በነጻነት እንዲያስቡ ያድርጓቸው። ሌሎች ሰዎችን የማይጎዱ ሰላማዊ መፍትሔዎችን እንዲያስቡ ያበረታቱዋቸው። ተማሪዎች/ሠልጣኞች በመብት አጠባበቅ፣ በአክብሮት እና በኃላፊነት አንጻር ክስተቶቹን እንዲመለከቱዋቸው ይጠይቋቸው።

  - የማን መብት እየተረገጠ ነው?
  - የማን መብት እየተከበረ ነው?
  - ሰዎች እርስ በርስ እየተከባበሩ ነውን?
  - መፍትሔው ሰዎች ኃላፊነትን ለራሳቸው እና ለሌሎች ሲወስዱ ያሳያል?
  - የሌሎችን ሰዎች መብቶች ያከብራሉ? ያስከብራሉ?

## ተማሪዎች/ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ

- ተማሪዎች/ ሠልጣኞች ሰላም እና የሰላም ግንባታ ማለት ለእነርሱ ምን እንደሆነ የሚሰማቸውን ስሜት በእነርሱ የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ።

### የሰላም ግንባታ ትምህርት ዜና ካርዶች

- የሰላም ግንባታ ትምህርት ዜና ካርዶች ጥቂት ምሳሌዎች ከዓውዱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የራሳቸዉን ካርዶች ለማዘጋጀት ከፈለጉ በነጻነት ማዘጋጀት ይችላሉ።

**የሰላም ግንባታ ዜና ካርድ 1**

በማኅበረሰቦች መካከል የተቀሰቀሰ ግጭት ካለበት አካባቢ የመጡ ዐርባ ወጣቶች በሌላ ማኅበረሰብ መኖሪያ አካባቢ ባለ ትምህርት ቤት እንዲማሩ በቅርቡ ተመድበዋል። አዲሱ ትምህርት ቤት እና ማኅበረሰቡ የእነዚህ አዳዲስ ወጣቶች ወደ እነርሱ መምጣት በእንቅስቃሴያቸው እና አፈጻጸማቸው ላይ ሁከትን የሚፈጥር እንደሆነ አድርገው ቆጥረውታል።

መምጣታቸው በጥሩ ዓይን እንዳልታየ እና እየተገለሉ መሆኑ ስለ ተሰማቸው አንዳንዶቹ አዳዲስ ወጣቶች ወደ ትምህርት ቤት አንሄድም ብለዋል። በርካታ ወላጆች ስለዚህ ችግር ለአካባቢው የትምህርት ባለሥልጣናት ይህን በተመለከተ አቤቱታ አቅርበዋል። በአካባቢው ትምህርት ቢሮ ሽምግልና ችግሩ መፍትሔ አግኝቶ ይህ መፍትሔ አርዕስተ ዜና ሆኗል።

**የሰላም ግንባታ ዜና ካርድ 2**

በአካባቢያችሁ ከሚኖረው ህዝብ መካከል አምስት በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ስደተኛ ነው። ከአንድ ሁለት ሳምንት በፊት በስደተኞች እና በነባር የአከባቢዉ ሰዎች መካከል ከፍተኛ ግጭት ተፈጥሮ ነበር። ሦስት የስደተኛ ልጆች ከሱቅ ቦርሳ ሲሰርቁ ተያዙ። የአካባቢው ነባር ነዋሪዎች እንዲህ ያለው ነገር ሲያጋጥም የመጀመሪያው ጊዜ አለመሆኑን በመግለጽ እና በአካባቢያቸው ከእንግዲህ ስደተኞች እንዲኖሩ እንደማይፈልጉ በመግለጽ "ሆ" ብለው ተነሡ።

የአካባቢው ሰዎች መንግሥት ስደተኞቹን የራሳቸውን ማኅበረሰብ መመሥረት ወደ የሚችሉበት ሌላ ቦታ እንዲያዛውራቸው ጥያቄ አቀረቡለት። ተጨማሪ ስደተኞች መምጣት ከጀመሩ ጊዜ ወዲህ የደኅንነት መታጣት እና ወንጀል እንደ ተስፋፋ በመጥቀስ መከራከሪያ ነጥባቸውን አቀረቡ። ስደተኞቹ በበኩላቸው ማግለልና መድልዎ እየተፈጸመባቸው እንዳለ እና ሥራ ለማግኘት እና ከማኅበረሰቡ ጋር መዋሃድ ለእነርሱ ቀላል እንዳልሆነ አቤቱታቸውን አቀረቡ። ባለፈው ሳምንት በየቀኑ በማዘጋጃ ቤቱ ፊት ለፊት የተቃውሞ ሰልፍ ሲያደርጉ ነው የሰነበቱት። መንግሥት መፍትሔ አገኘ፤ ይህም አርዕስተ ዜና ነው።

## እየጠፉ ያሉ ደሴቶች ጨዋታ

**ዓላማ**

- በግጭት ወቅት በእውነተኛ ሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙ  የግብረገብነት ፈተናዎችን ለመቋቋምና ተፈፃሚ ለማድረግ።

**ውጤት**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ግብረገባዊ የግጭት ተግዳሮቶች ላይ የሚሰማቸውን ውስጣዊ ስሜት ገልፀዋል።

**የትምህርት/ የሥልጠና መሣሪያዎች**

- የጋዜጣ ገጾች
- ሙዚቃ እና ስፒከር (ወይም ሁሉም መስማት እንዲችል የሚያደርግ መሣሪያ ---ወዘተ፡፡

**ልምምድ**

- በመሃላቸው ክፍተት በመተው ጋዜጣ  መሬት ላይ ያንጥፉ። በርካታ ጋዜጣዎችን ይጠቀሙ። እያንዳንዱ ጋዜጣ አንድን ደሴት ይወክላል። ሙዚቃ ያጫውቱ እና ተማሪዎች/ሠልጣኞች ደሴቶቹን ሳይረግጡ በደሴቶቹ ዙሪያ በእግራቸው እንዲራመዱ ይጠይቋቸው። ሙዚቃው ሲያቆም ቶሎ ደሴቶቹ ላይ እንዲቆሙ ያድርጉ። ልምምዱን በማስቀጠል አለፍ አለፍ እያሉ ሙዚቃውን ያስቁሙ።
- ቀስ በቀስ የደሴቶቹ ብዛት ሙሉ በሙሉ እንዲቀንስ እና እያንዳንዱ ደሴት ይበልጥ በሰው እንዲጨናነቅ ሙዚቃውን እንደገና ማጫወት በጀመሩ ቁጥር አንድ ደሴት ይቀንሱ። በስተመጨረሻ ለሁሉም ተማሪዎች/ሠልጣኞች የሚሆን ቦታ ይታጣል፤ ደሴቱ ላይ መቆም ያልቻሉት ተማሪዎች/ሠልጣኞች ከጨዋታው ውጭ ይሆናሉ። አንድ ደሴት እስከሚቀር እና አብዛኛዎቹ ተማሪዎች/ሠልጣኞች ከጨዋታው ውጭ እስከሚሆኑ ድረስ ጨዋታውን ያጫውቷቸው።
- ጨዋታው ሲጠናቀቅ፣ ምን እንደተፈጠረ ከተማሪዎች/ሠልጣኞች ጋር ውይይት ያድርጉ። እንደ ጥያቄ ሊቀርቡ የሚችሉ አንዳንድ ጥያቄዎች እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡
    - ጥቂት ደሴቶች በቀሩ ጊዜ ምን ተፈጠረ?
    - ሰዎች ምን ዓይነት አፀፋ ምላሽ ሰጡ?
    - ደሴቱ ላይ መቆም ሳትችሉ ስትቀሩ እና ከጨዋታው እንድትወጡ ስትደረጉ ምን ተሰማችሁ?

- የራሳችሁን ቦታ እንዴት ነበር ያስጠበቃችሁት?
- ሌሎችን አግዛችሁ ነበር?
- በእውነተኛ ሕይወት ከሚያጋጥመን ጋር ይህ ተመሳሳይነት አለው? በምን ዓይነት መንገድ?

- ጨዋታውን ከእውነተኛ ሁኔታዎች ጋር ያዛምዱት እና ለመኖር የተፈጥሮ ሃብቶችን ከመጋራት፣ ከአካታችነት፣ ተጋላጭ ለሆኑት ጥበቃ ከማድረግ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ውይይት ከተማሪዎች/ከሠልጣኞች ጋር ያድርጉ።

- ግጭቶች የተለመዱ እንደሆኑ ነገር ግን ሰዎች ሀብትን አናጋራም ሲሉ ለመተባበር ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ እና ከሌሎች ጋር ሲያብሩ ግጭቶቹ ከፍተኛ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለተማሪዎች/ለሠልጣኞች ይንገሯቸው። እርስ በርስ ባለን ግንኙነት ላይ ግብረገብነትን መጠበቅ እንድንችል ምን ሊያግዘን እንደሚችል እንዲወያዩ ያድርጉ።

**ተማሪዎች/ሰልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- ከልምምዱ በዋነኛነት የተማሯቸውን ነጥቦች ለመግለጽ ተማሪዎች/ሠልጣኞች የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር እንዲጠቀሙ ያድርጉ።

## መንታ አስተሳሰብ መኖር

**ዓላማዎች**

- የተለያዩ ግብረገብ ነክ አማራጭ ብቻ ያላቸው ጥያቄዎች ሥነ ምግባራዊ የውሳኔ አሰጣጥ እና የሥነ ምግባር መርሆዎችን ተፈጻሚ ለማድረግ።

- ለውሳኔ አስቸጋሪ የሆኑ አሻሚ ሃሳቦች/ ሁለት አማራጭ ብቻ ያላቸው  የግብረገብ ጥያቄዎች ላይ መፍትሔ ለመስጠት።

**ውጤት፡-**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ሁለት አማራጭ ብቻ ያለው አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ ግብረገብነትን የጠበቀ ውሳኔ ሰጥተዋል።

> ሥነ ምግባራዊ ሁለት አማራጭ ብቻ ያለው አጣብቂኝ  በግብረገብ ድንጋጌዎች መካከል ግልጽ የሆነ ግጭት ሲፈጠር የሚያጋጥም ሁኔታ ነው፤ የአንዱ ፍላጎት ግስጋሴ የሌላውን መብት ሲጥስ ይታያል።

**የትምህርት/የሥልጠና መሣሪያዎች ፡-**

- ለውሳኔ አስቸጋሪ የሆኑ አንድ ወይም በርካታ አማራጭ ያላቸው ሁኔታዎች ቅጂ፣

- በጥቁር ሰሌዳ፣ በፍሊፕ ቻርት ወረቀት ላይ የተጻፉ ወይም የታተሙ የውሳኔ አሰጣጥ ማብራሪያዎች ቅጂ ለእያንዳንዱ ቡድን የሚሰጥ ያዘጋጁ።

ልምምድ፡-

- ተማሪዎችን/ሠልጣኞችን ከ3 እስከ 5 በሚደርሱ ቡድኖች ይመድቧቸው እና ለእያንዳንዱ ቡድን ግብረገባዊና ለውሳኔ አስቸጋሪ የሆኑ አሻሚ/ሁለት አማራጭ ብቻ ያላቸውን ማብራሪያዎች ይስጡ።

- ለውሳኔ አስቸጋሪውን ሁኔታ በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ እና መፍትሔው ላይ የጋራ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ 30 ደቂቃ ይስጡዋቸው። በመቀጠል፣ ውሳኔያቸውን ለሌሎቹ ቡድኖች እንዲያካፍሉ ያድርጓቸው።

- ለተማሪዎች/ለሠልጣኞች ከዚህ በታች የቀረቡትን ሥነ ምግባራዊ የውሳኔ አሰጣጥ ማብራሪያዎች ያስተዋውቋቸው። ተማሪዎች/ሠልጣኞች አስቀድመዉ በማብራሪያዎች ላይ ይወያያሉ፤ በመቀጠልም ውሳኔዎቻቸውን ለመገምገም ይጠቀሙባቸዋል።

**ግብረገባዊ/ሥነ ምግባራዊ የውሳኔ አሰጣጥ ማብራሪያዎች፡-**

ውሳኔ መስጠት ያለብዎት አንድ አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥምዎ ጥሩ ምርጫ ለመምረጥ እንዲያግዝዎት ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች ይጠቀሙ፡-

- ውሳኔው በሌሎች ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋልን? በማን ላይ?
- የእርስዎ ውሳኔ በእርስዎ እምነት ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋልን?
- የእርስዎ ውሳኔ በሌሎች ሰዎች እምነት ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋልን?
- የእርስዎ ውሳኔ ሌሎች ከፍላጎታቸው ወይም ከእምነታቸው ውጭ እንዲንቀሳቀሱ ሊያዳርጋቸው ይችላልን?
- የእርስዎ ውሳኔ የሌሎችን የተለየ እምነት ወይም ባህል የሚያከብር ነውን?
- የእርስዎ ውሳኔ ከእርስዎ የተለዩ ሰዎችን መጥፎ ምስል ያሳያልን? (ከሥርዓተ ጾታ፣ ሃይማኖታዊ አቋም ወይም የተለየ ሁናቴ አንጻር)
- የእርስዎ ውሳኔ የሰውን ልጅ ክብር ያዋርዳልን?
- የእርስዎን ውሳኔ በግልጽ ለቤተሰብዎ፣ ለጓደኞችዎ ወይም ለመምህራንዎ ሊያካፍሉ ይችላሉን?
- የእርስዎ ውሳኔ ለችግሩ መፍትሔ እየሰጠ ነው ወይስ ችግሩን እየደበቀው ነውን?
- የእርስዎ ውሳኔ ወደፊት የሚስከትላቸው አሉታዊ መዘዞች አሉት?

- የማብራሪያዎቹ መቅረብ የቡድኑን ውሳኔ እንደለወጠው ወይም እንዳልለወጠው እንዲወያዩ ያድርጉ።

- የሰብአዊ መብት ዕውቀታቸው በውሳኔያቸው ላይ ተጽዕኖ አሳርፏል?

- የሥነምግባራዊ የውሳኔ አሰጣጥ ማብራሪያዎች ተማሪዎች/ሠልጣኞች ሙሉ በሙሉ የመቀየር ፍላጎት አሳይተው ነበር?

**ተማሪዎች/ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- አንድ ጉዳይ በርካታ እና እርስ በርስ የሚጋጩ አመለካከቶችን ሊያስነሣ እንደሚችል ተማሪዎች/ ሠልጣኞች ሐሳባቸዉን የሚያንፀባርቅበትን ጊዜ በበላይነት ይምሩ። ጉዳዮችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች የማየት አስፈላጊነትንና የሚነሡ ነጥቦች ካሉም ከጠቀሜታዎች አንጻር ግምት ውስጥ በማስገባት አስፈላጊነቱ ላይ እንዲወያዩ ያድርጉ።

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች በራሳቸው ሕይወት ላይ ያጋጠማቸውን ለውሳኔ አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎች ለይተው እንዲያወጡ ይጋብዟቸው እና የትኛው የተሻለ የውሳኔ ሐሳብ ሊሆን እንደሚችል በእነርሱ የትምህርቱ ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር ላይ የተለያዩ መከራከሪያ ነጥቦችን እንዲጽፉ ያድርጓቸው።

**ግብረገባዊ የሞራል ችግር ምሳሌ፡ውሸትን መደበቅመንታ አስተሳሰብ ምሳሌ፦ ውሸት እንዳይታወቅ መከላከል**

ራሄል ዕድሜዋ 15 ዓመት ነው። እናቷ በቤተሰቡ ዳቦ መጋገሪያ መደብር ከትምህርት ቤት መልስ እናቷን በሥራ ካገዘች በኋላ በአንድ የኢትዮጵያ የሙዚቃ ባንድ ወደተዘጋጀ ልዩ ኮንሰርት መግባት እንደምትችል ቃል ገብታላታለች። ለዚህም እናትየዋ በየቀኑ እሷ ባገዘች ቁጥር 20 ብር እንደምትሰጣት ተስማምታለች። በዚህም መንገድ ራሄል 200 ብር ለመቆጠብ ችላለች፤ ይህ ገንዘብ የኮንሰርቱ መግቢያ 150 ብር ብቻ እንደመሆኑ ከሚያስፈልገው በላይ ገንዘብ አግኝታለች። ሆኖም ግን የራሄል እናት ሐሳቧን ቀየረችና ገንዘቡን ለትምህርት ቤት መጽሃፍት መግዣ ማዋል እንዳለባት ነገረቻት።

ራሄል በእናቷ ውሳኔ ተከፍታለች እና የመጣው ቢመጣ ኮንሰርቱ ላይ ከመግባት ወደ ኋላ እንደማትል በግሏ ወስናለች። ትኬት ገዛች እና በኮንሰርቱ ላይ ታደመች። እዚህ ላይ ለእናቷ ዋሽታታለች፤ ለእናቷ የነገረቻት ቀኑን ከጓደኛዋ ጋር እንደምታሳልፍ ነበር። እናትየዋ ምን እንደተፈጠረ ሳታውቅ አንድ ሳምንት አለፈ።

ራሄል ለታላቅ እህቷ ለዘነበች ኮንሰርቱን እንደገባች እና መግባቷን በተመለከተ ለእናታቸው እንደዋሸቻት ነገረቻት። ዘነበች ይህንን ነገር ለእናቷ መናገር እንዳለባት እና እንደሌለባት መወሰን ግራ ገብቷታል።

- ታላቅ እህቷ ዘነበች ለእናታቸው ራሄል ስለ ኮንሰርቱ እንደ ዋሸች መናገር አለባት ወይስ ዝም ማለት አለባት? በምን ምክንያቶች ላይ ተመርኩዛ መወሰን አለባት?
- ዘነበች በጣም ታማኝነትዋ ለእናትዋ ነው ወይስ ለእህቷ? ለምን?
- ራሄል ገንዘቡን ራሷ ሠርታ ያገኘችው መሆኑ እዚህ ጉዳይ ላይ አስፈላጊ ነውን? ለምን?
- እናትየዋ ገንዘቡን ሠርታ ካገኘች ወደ ኮንሰርቱ መግባት እንደምትችል ለራሄል ቃል ገብታላት ነበር። እናትየዋ ቃሏን አለማክበሯ ከግምት መግባት ያለበት አስፈላጊ ቁም ነገር ነውን? ለምን?
- በአጠቃላይ አነጋገር ቃልን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ለምን?
- ቃል የሚገባው ሰው ለእናንተ ቅርብ ሰው መሆኑ ወይም የማታውቁት ሰው መሆኑ የሚፈጥረው ልዩነት አለ?

# ራስን ማወቅ

**ዓላማ**


- የራስን ሁለንተናዊ ማንነት ለመዳሰስ

**ውጤት**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የራሳቸውን ሁለንተናዊ ማንነት በመዳሰስ እንዲሁም እንዴት ለዓለም ራሳቸውን ማቅረብ እንደሚፈልጉ ተገንዝበዋል።
- ተማሪዎች/ ሠልጣኞች ጠንካራ፣ ጤናማ የራስ ግምትንና የጤናማነት ስሜት መንፈስን ለይተው በተግባር አሳይተዋል።

**የትምህርት/ የሥልጠና መሣሪያዎች**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች የራሳቸውን ማስታወሻ ደብተር መጠቀም።
- ለእያንዳንዱ ተማሪ/ሠልጣኝ እስክርቢቶ ወይም እርሳስ ወይም
- ባለ ቀለም እርሳሶች--- ወዘተ መጠቀም።
- ኮምፒውተር፣ ላፕቶፕ፣ ታብሌት መጠቀም፡፡




**ልምምዶች**

- የአንድን ሰው ማንነት እሴቶች እና ገጽታዎች ይገምግሙ (ክፍል 3ን ይመልከቱ)። የአንድ ሰው ማንነት ምን ነገሮችን እንደሚያሟላ ይጠይቋቸው። እዚህ ላይ የቀረበውን ምስል እንደ ማጣቀሻ ይጠቀሙበት። በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሆነ ያላችሁት ይህን ምስል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይሣሉት እና ተማሪዎች/ሠልጣኞች የሚሰጡዋቸውን ሐሳቦች እንዲካተቱ ያድርጉ፤
- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ለራሳቸው ምን ዓይነት ግምት እንደሚሰጡ እና እንዴት ራሳቸውን እንደሚያዩ እንዲሁም ለዓለም ራሳቸውን እንዴት ማሳየት እንደሚፈልጉ በተመለከተ የውስጥ ስሜታቸውን እና ሐሳባቸውን እንዲያፀባርቁ ይጠይቋቸው። እንዲሁም የራሳቸውን የማንነት ምስል እንደሚሥሉ ይግለጹላቸው፤
- የተሳለው ማንነትን ገላጭ ምስል በሌሎች የክፍል ጓደኞቻቸው እንደሚታዩ እና እነርሱም ካሳዩዋቸው ምስል ላይ በመነሣት በፍጥነት ከራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንደሚደርሱ ለተማሪዎች/ለሠልጣኞች ያስታውቧቸው፤

- ስለ ራሳቸው ማንነት በግልጽ እና ትርጉም ባለው መንገድ ሲያወሩ ምቾት እንዲሰማቸው በሌሎች ተሞክሮ የማጋራት እንቅስቃሴዎች ቀደም ብለው እርስ በርስ ለመተዋወቅ የሚችሉበትን ዕድል አግኝተው ከሆነ በበለጠ ጠቃሚ ይሆናል። በልምምዱ ወቅት ተማሪዎች/ሠልጣኞች እርስ በርሳቸው እንዲነጋገሩ እና እንዲወያዩ ይፍቀዱላቸው፣ ያበረታቷቸው፤

- ለተማሪዎች/ለሠልጣኞች ባለ ቀለም እርሳሶች ወይም ማርከሮችን፣ ወረቀት ይስጧቸው ወይም ንድፋቸውን ለመሥራት የራሳቸውን የግል ማስታወሻ ደብተሮች እንዲጠቀሙ ያድርጉ። ተማሪዎች/ሠልጣኞች የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲጠቀሙ ያበረታቷቸው። የማንነት ግራፍ ለምሳሌ የቀረበ እንደሆነ እና በትክክል አስመስለው መገልበጥ እንደሌለባቸው ያብራሩላቸው። ለምሳሌ፡- «የእኔ ማንነት» ከሚለው ሥር የአባታቸውን ወይም የራሳቸውን ስም ከመጻፍ ይልቅ የራሳቸውን ሥዕል መሣል ይችላሉ፤

- ሁሉም ተማሪዎች/ሠልጣኞች ሠርተው ሲጨርሱ ወይም 10 ደቂቃ ብቻ ሲቀር የትምህርት ክፍለ ጊዜውን ማጠቃለያ ሰጥተው ያጠናቅቁ። ተማሪዎች/ሠልጣኞች በሣሉት ሥዕል ላይ ያላቸውን ውስጣዊ ስሜት እና ሐሳብ እንዲሁም ስለ ራሳቸዉ ማንነት ምን እንደሚገልፅ ሐሳባቸውን እንዲያንፀባርቁ ያድርጓቸው። ጥቂት ተማሪዎች/ሠልጣኞች ሥዕላቸውን ለሌሎች እንዲያሳዩ ያድርጉ። ጊዜ የሚፈቅድ ከሆነ ተማሪዎች በዴስኩ ላይ ሥዕላቸውን እንዲያስቀምጡ እና የሌሎችን ሥዕሎች ለማየት በክፍሉ ውስጥ ተዟዙረው እንዲመለከቱ ያድርጓቸው፤

- እኛ ማን እንደሆንን እና ሌሎችም ማን እንደሆኑ ዋጋ የመስጠት አስፈላጊነትን፣ ልዩነቶችን ማክበር እና ብዝኃነትን የመቀበልን ጠቀሜታ በማብራራት ልምምዱን ያጠናቅቁ።

**ተማሪዎች/ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ስለ ራሳቸው የተማሩትን  እና ስለ ሌላ ግለሰብ ያወቁትን አዲስ ነገር (የሌሎችን ሥዕሎች ለማየት በክፍሉ ውስጥ ተዘዋውረው ከነበረ) እና ለራስ እንዲሁም ለሌሎች በልምምዱ ከተገኘው ትምህርት ላይ በመመርኮዝ ዋጋ መስጠትን በተመለከተ የተማሩትን አንድ አዲስ  ነገር በእነርሱ የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ።

## ራስን በሌሎች ቦታ አስቀምጦ ማዬት

**ዓላማ**

- ችግር በደረሰባቸዉ በሌሎች ሰዎች ተሞክሮዎች እና ስሜቶች ውስጥ ራስን በማድረግ የሚሰማንን የውስጥ ስሜት ለመግለፅ።

**ውጤት**

- ተማሪዎች/ ሠልጣኞች የሌሎችን ተሞክሮዎች ዕውቅና ሰጥተዋል።
- ተማሪዎች/ ሠልጣኞች ለሌሎች እንዴት አዛኝነትንና አሳቢነት ማሳለበት እንደሚቻል በተግባር ተረድተዋል።

**የትምህርት /የሥልጠና መሳሪያዎች**

- የጫማ/የእግር ቅርጽን ቆርጠው ማውጣት የሚችሉበት የተጣለ ካርቶን ወይም ወረቀት ለእያንዳንዱ ተማሪ/ሠልጣኝ
- ትንሽ ገመድ፣ ክር ወይም ምናባዊውን ጫማ ለማሰር የሚችል የጨርቅ ቁራጭ
- መቀሶች
- እስክርቢቶዎች ወይም እርሳሶች



**ልምምዶች፡-**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች በደንብ ከማያውቁት እና ስለ እሱ ይበልጥ ማወቅ ከሚፈልጉ ሌሎች ተማሪዎች/ሠልጣኞች ጋር ጥንድ ሆነው እንዲቀመጡ ይጋብዙዋቸው።
- እያንዳንዱ ተማሪ/ሠልጣኝ የአጋሩን እግር/ጫማ ቅርጽ በካርቶኑ ላይ ይሥልና ቆርጦ ያወጣል።
- ጥንድ ጥንድ የሆኑት አጋሮች ፀጥ ያለ ቦታ አንድ ላይ ተቀምጠው ስለ አጋራቸው የበለጠ ከማወቅ ፍላጎት ጋር እርስ በርስ ቃለ መጠይቅ ይደራረጋሉ። ትርጉም ያለው ቃለ ምልልስ እንዲኖራቸው ለማገዝ ከዚህ በታች እንደ ምሳሌ የቀረቡትን ጥቂት ጥያቄዎች ይመልከቱ።

**ጥያቄዎች**

- ባንተ/ባንቺ ሕይወት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ሰዎች እነማን ናቸው?

- አንተ/አንቺ በጣም የምትኮራበት/ሪበት ነገር ምንድን ነው?
- ምን ያስደስትሃል/ሻል?
- ሌሎች ሰዎች እንዴት እንዲያዩህ/ሽ ትፈልጋለህ/ጊያለሽ?
- አንተ/አንቺ ያለህ/ሽ በጣም ትልቅ ራዕይ ወይም ተስፋ ምንድን ነው?

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ራሳቸው ቃለ መጠይቅ አድራጊ በሚሆኑበት ጊዜ በአክብሮት ጥያቄ መጠየቅ በንቃት ማዳመጥ እና አጋራቸው የሆነ የግል ጉዳይ ለመነጋገር ካልፈለገ ምርጫውን ማክበር እና እነርሱ ደግሞ ቃለ መጠይቅ ተደራጊ በሚሆኑበት ጊዜ ሊናገሩ የማይፈልጉትን ርዕሰ ጉዳይ መልስ ሳይሰጡ መዝለል እንደሚችሉ ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን ያስታውሷቸው።

- እርስ በርስ ቃለ መጠይቅ አድርገው እንደጨረሱ ባዘጋጁት የአጋራቸው እግር ንድፍ ላይ ያገኙዋቸውን ዋነኛ ነጥቦች ገላጭ የሆኑ ምልክቶችን እንዲሥሉ ወይም በቃላት እንዲጽፉ ይጠይቋቸው።

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች በካርቶኖቹ ላይ ቀዳዳ እንዲያበጁ እና ስለ ጓደኛቸው ያዘጋጁትን ካርቶን በራሳቸው እግር/ጫማ ላይ ለማሰር ገመድ/ቁራጭ ጨርቅ እንዲጠቀሙ ያድርጉ።

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ቀስ ብለው እየተራመዱ በክፍሉ ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ በቃለ መጠይቁ ላይ በመመርኮዝ ለአጋራቸው ሕይወት ምን ልትመስል እንደምትችል በውስጣቸው እያሰቡ «በሌላው ሰው ቦታ ራሳቸውን አድርገዉ እንዲያስቡ» ይጠይቋቸው።

- ከልምምዱ በኋላ ከተሞክሮ በመነሣት ያገኙትን ትምህርት ለሌሎች እንዲያጋሩ ተማሪዎችን/ሠልጣኞችን ይጋብዟቸው። ስለ አሳቢነት፣ ስለሩህሩህነት፣ ለሌሎች አዛኝ ስለመሆን  ምን ሊያግዘን ወይም ምን አጋዥ እንዳንሆን ሊያደርገን እንደሚችል ተወያዩ።

**ተማሪዎች/ ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- አንድ ግለሰብ ሩህሩህነትን እንዲያዳብር ሊያግዘው የሚያስችል የውስጥ ስሜቱን እና ሐሳቡን ለማንፀባረቅ የእርሱን የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር እንዲጠቀም ይጠይቁ፡፡

## የሚያመሳስሉንን ነገሮች መለየት


**ዓላማ**

- የግል ጥያቄዎችን በመጠየቅ የአንድን ሰው ማንነት ገጽታዎች ለመገምገም።

**ውጤት**

- ተማሪዎች/ ሠልጣኞች የራሳቸውን እና የሌላውን ማንነት ገጽታዎች ይደርሱባቸዋል።
- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ከእነርሱ የተለዩ ሌሎች ሰዎች እንዴት ተመሳሳይነት ያላቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ አዉቀዋል።

**የትምህርት/የሥልጠና መሣሪያዎች**



- ወረቀት ወይም ማስታወሻ ደብተሮች፤
- እስክርቢቶ ወይም እርሳስ፤
- ባለ ቀለም ክሮች፤
- ኮምፒውተር፣ ላፕቶፕ፣ ታብሌት

**ልምምዶች**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ሙሉውን ወረቀት ወይም ማስታወሻ ደብተር ሙሉውን ገጽ የሚሸፍን ባለ አምስት ጫፍ ኮከብ እንዲሥሉ ያድርጓቸው። ምሳሌ እንዲጠቀሙበት አንድ ኮከብ ሥለው ያሳዩ።
- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ስለራሳቸው ምን መረጃ አስፈላጊ እንደሆነ እና ለአምስቱ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ያድርጉ። ለቡድኑ ስብጥር ተስማሚ የሆኑትን ጥያቄዎች መምረጥ ወይም የሚከተሉትን አምስት ጥያቄዎች መጠቀም ይችላሉ፦
    - በጣም የምትወደው/የምትወጅው ሙዚቃ፣ ዘፈን ወይም ምግብ ምንድን ነው?
    - በጣም የምትወደው/የምትወጅው ልዩ ቦታ ምንድን ነው?
    - በጣም ዋጋ የምትሰጠው/የምትሰጪው ተሞክሮ የትኛው ነው?
    - በጣም አስፈላጊ የሆነ እምነቱ/ቷ(አቋም) ምንድን ነው?
    - ማድረግ ደስ የሚለው/ላት ነገር ምንድን ነው?
- በእያንዳንዱ የኮከቡ ጫፍ ላይ የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ እንዲጽፉ ያድርጉ።
- ኮከቡ ላይ ጽፈው ሲጨርሱ አብረው ቁጭ ብለው መልሶቻቸውን የሚካፈሉትን አጋር እንዲያዩ ያርጓቸው።
- ጥንድ-ጥንድ ሆነው ከተቀመጡ በኋላ ኮከቡን ፊት ለፊታቸው እንዲያስቀምጡ እና በክፍሉ ውስጥ እየተዘዋወሩ የሌሎችን ኮከቦች በማየት ቢያንስ ሁለት ተመሳሳይ መልሶችን ለማግኘት እንዲሞክሩ ያድርጉ። እያንዳንዱ ተማሪ/ሠልጣኝ ቢያንስ አንድ

ተመሳሳይ የሆነ አንድ የተለየ ወይም አንድ ደስ የሚል ነጥብ ከሚያገኙት ሌላኛው ተማሪ/ሠልጣኝ ኮከብ ላይ ማግኘት  አለባቸው።

- መቀላቀልን ያበረታቱ እና በየአራት ደቂቃው የሚደወለውን የደወል ድምፅ ሲሰሙ ወደ ሌላ አዲስ ተማሪ/ሠልጣኝ እንዲሄዱ ያድርጉ። ለእያንዳንዱ ተማሪ/ሠልጣኝ ቢያንስ ከአምስት ሌሎች ተማሪዎች/ሠልጣኞች ጋር የሠራውን/ችውን ሥራ ማሳየት እንዲችል በቂ ጊዜ ይስጡ።

- ክብ ለመሥራት አመቺ የሆነ ቦታ ተማሪዎች/ሠልጣኞች በክብ ተቀምጠው ስለ አንዱ እንዲያወሩ፣ ምን አንድ የሚያደርጋቸው፣ ምን የጋራ ነጥብ እንዳላቸው ወይም ምን ነጥብ ላይ የተለያየ አቋም እንዳላቸው ወይም ያገኙትን አስደሳች ነገር እንዲያብራሩ ያድርጓቸው። መናገር ለሚጀምረው/ለምትጀምረው ተማሪ/ሠልጣኝ ክር የተንጠለጠለበት ኳስ ይስጡት/ይስጧት እና ክሩን ግን ራሳቸው ይዘው በመቆየት ስለ እሱ/እሷ ሲያወሩ ለነበሩት ተማሪ/ሠልጣኝ ኳሱን እንዲያቀብሉ ያድርጉ።

- ሁሉም ተማሪ ሐሳቡን ሲያካፍል ኳሱ ሁልጊዜ ስለእሱ/እሷ ወዳወሩት ተማሪ/ሠልጣኝ መተላለፍ አለበት፤ ትልቅ ድር በስተመጨረሻ እንዲፈጠር የክሩን ጫፍ እንደያዙ መቆየት አለባቸው። ተማሪዎች/ሠልጣኞች ክሩን በእጁ ላልያዘ ተማሪ/ሠልጣኝ ኳሱን እንዲያቀብሉ ያድርጓቸው እና  ከሌላ ጓደኛ ጋር ያላወራ ተማሪ/ሠልጣኝ ካለ ከሌሎች እገዛ እንዲያገኝ ያድርጉ።

- ቡድኑ ብዙ ከሆነ ከጥንድ ልምምዱ በኋላ በሚደረገው ውይይት እና ሐሳብን የማካፈል ክፍለ ጊዜ በሁለት ትላልቅ ቡድኖች ተከፍሎ ሊደረግ ይችላል፤ ስለዚህ ሁሉም ተማሪዎች/ሠልጣኞች ባለው ጊዜ ውስጥ ሐሳባቸዉን እንዲያካፍሉ መፍቀድ ይችላሉ።

- ሁሉም ሰው ሐሳቡን አካፍሎ ከጨረሰ እና ድሩ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ ምን እንዳዩ፣ ድሩ ምንን ሊወክል እንደሚችል እና ከሚያዩት ድር ምን ትምህርት ሊቀስሙ እንደሚችሉ ጥያቄዎች በማንሳት ውይይት እንዲካሄድ ያድርጉ።

- የብዝኃነትን ዋጋ፣ የሰውን ልጅ ቅርብ ግንኙነት እና የኡቡንቱ ፅንሰ ሐሳብን በአፅንኦት በአጭሩ በመግለጽ ክፍለ ጊዜውን ያጠናቁ።

**ተማሪዎች/ሠልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ፦**

- ተማሪዎች/ሠልጣኞች ስለ ክፍል ጓደኞቻቸው የተማሩትን አዲስ ነገር፣ ለብዝኃነት እና የእርስ በርስ መልካም ግንኙነት ዋጋ መስጠትን በተመለከተ ያወቁትን አዲስ ነገር ለመጻፍ  የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተራቸውን እንዲጠቀሙ ያድርጓቸው።

## የራስ መለያ ምልክት

**ዓላማ**

- የአንድን ሰው የውስጥ ፍላጎቶች፣ ጥንካሬዎች እና የሕይወት ፍልስፍና ለይቶ ለማወቅ።

**ውጤት**

- ተማሪዎች የራሳቸውን ሕይወት ጥንካሬዎች እና አንዳንድ ውስጣዊ ፍላጎቶች ለይተው ያውቃሉ።


**የስልጠና መሳሪያዎች ፦**

- ወረቀት ወይም ማስታወሻ ደብተር፤
- እስክርቢቶ ወይም እርሳስ፤
- ኮምፒውተር፣ ላብቶፕ፣ታብሌት፡፡

> ባለ ጋሻ ዓርማ
>
> ባለ ጋሻ ዓርማዎች በመካከለኛው ዘመን በመሳፍንቶች ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው ለመለየት ጥቅም ላይ ያውሏቸው ነበር። እንደ Tech4Leanring (2019) አባባልባለ ጋሻ ዓርማ

**ልምምድ፦**

- ተማሪዎችን ባዶ ነጭ ወረቀት እንዲያዘጋጁ እና በላዩ ላይ ስማቸውን እንዲጽፉ ይጠይቋቸው።
- አራት ክፍሎች ያሉትን ጋሻ ከሰንደቅ ጋር እዚህ ላይ እንደሚታየው አድርገው ይሣሉ።



- በእያንዳንዱ የጋሻው ክፍል ላይ የሚከተለውን ይጥቀሱ፦
    - የእኔ ትላልቅ ስኬቶች
    - የእኔ ግቦች/ፍላጎቶች (ቢያንስ ሁለት)
    - እንዲህ ያለው ሁኔታ ውስጥ ስሆን በጣም ይሳካልኛል (የእኔ ጥንካሬዎች)...
    - በእኔ ሕይወት ውስጥ በጣም አስፈላጊው(ዎቹ) ሰው(ዎች)
- ከጋሻው በታች ባለው ሰንደቅ ላይ ተማሪዎች የእነርሱን መሪ መፈክር ወይም የሕይወት ፍልስፍና ማለትም ሕይወታቸውን የሚመሩበት አስተሳሰብ እንዲጠቅሱ ይጠይቋቸው።
- ተማሪዎቹን በአራት ወይም በአምስት አባላት ያላቸው ቡድኖች ያደራጁቸው እና ተማሪዎቹ የጋሻውን የተለያዩ አካላት አንዱ ለሌላው እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው።
- ከብዙ የዕድሜ አቻዎቻቸው ጋር በተለያዩ የጋሻው ክፍሎች ላይ ያላቸውን ሐሳብ አንዱ ለሌላው ማካፈል እንዲችል አዳዲስ ቡድኖችን በመፍጠር ልምምዱ እንዲደጋገም ያድርጉ።

- ተማሪዎቹ ከዚህ ልምምድ ምን እንደተማሩ ሰንደቁ ላይ እና በጋሻው የተለያዩ ክፍሎች ላይ የሚጻፈውን በመምረጥ ላይ ያጋጠሟቸውን አንዳንድ ተግዳሮቶች እና በመጨረሻም እንዴት የሚጻፈውን እንደመረጡ ከተማሪዎቹ ጋር ውይይት ያድርጉ።

**ሰልጣኞች ወይም ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- ስለ ስኬታቸው፣ ግቦቻቸው/ምኞታቸው፣ ጥንካሬያቸው እና መሪ መፈክር/የሕይወት ፍልስፍናቸው በተመለከተ በእነርሱ የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር ላይ እንዲጽፉ ተማሪዎቹን ይጋብዟቸው። ይህ ሂደት እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል እንዲጽፉ ይጠይቋቸው።

## ጭንብሎን መልበስ

**ዓላማ**

- ተራ ስያሜዎች እና የተዛቡ አመለካከቶች ሌሎችን በምናይበት መንገድ ላይ አንዳንድ ጊዜም በአሉታዊ መንገድ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ለማንፀባረቅ።

**ውጤት**

- ተማሪዎች የተለያዩ ዓይነት ማኅበራዊ ማንነቶችን እንዴት በማኅበረሰቡ ሊታዩ እንደሚችሉ ተረድተዋል።
- ተማሪዎች የገዛ ራሳቸውን ማንነት የተለያዩ መለያዎች ይበልጥ ተገንዝበዋል።

**የስልጠና መሳሪያዎች**

- ካርቶን
- መቀስ
- ክር እና ሌሎች

**ልምምድ**

- ተማሪዎች ካርቶኑን ቆርጠው ፊታቸውን እንዲሸፍኑበት እና ጭንቅላታቸው ላይ ካርቶኑን ለማሰር ክር እንዲጠቀሙ ያድርጓቸው።
- ለምሳሌ እናት፣ አባት፣ ፖሊስ፣ የሃይማኖት መሪ፣ ሴት፣ ወንድ፣ ፖለቲከኛ፣ አስተናጋጅ ወዘተ የመሳሰሉ የተለያዩ ማኅበራዊ ሚናዎችን ለመግለጽ የሚያገለግሉ የተለያዩ የማንነት ስያሜዎችን አስቀድመው ያዘጋጁ። ጠንካራ የመማር ማስተማር ተሞክሮ እንዲኖር በማኅበረሰቡ ውስጥ እንዲገለሉ የሚደረጉትን እና/ወይም እንደ አወዛጋቢ ሆነው የሚታዩትን ማካተትዎን እርግጠኛ ይሁኑ።

- ጭንብል ያደረገው ተማሪ በላዩ ላይ የተለጠፈበትን ስያሜ እንዳያውቅ ተማሪዎች ጭንብላቸው እንዲያደርጉ እና ከተዘጋጁት ስያሜዎች መካከል አንዱን በጭንብሉ ላይ እንዲለጥፉባቸው ይጠይቋቸው።

- ተማሪዎች በክፍሉ ውስጥ እንዲዘዋወሩ እና ከማን ጋር እየተገናኙ እንዳሉ ለማየት ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እንዲገናኙ ይጋብዟቸው። በላዩ ላይ ስያሜ የተለጠፈበትን ተማሪ ሲያገኙ እንዲህ ያለውን ሰው በተለምዶ ራሳቸው/ማኅበረሰቡ በሚያስተናግዱበት መንገድ አፀፋ ምላሽ መስጠት ይችላሉ፤ ለምሳሌ ፖለቲከኛ ሰውን መጨበጥ፣ የአካል ጉዳት ያለበትን ዐይቶ እንዳላዩ ማለፍ ወዘተ።

- በሚያገኙት አፀፋ ምላሽ ላይ በመመርኮዝ ተማሪዎች ምን ዓይነት የማንነት ስያሜ በላያቸው ላይ እንደተለጠፈባቸው ለማወቅ መሞከር አለባቸው። ተማሪዎች እንዲቀላቀሉ እና በተቻለ መጠን ከብዙ ተማሪዎች ጋር መገናኘት እንዲችሉ በቂ ጊዜ ይስጧቸው።

- ከተቀላቀሉ በኋላ ክብ ይሥሩ እና ያገኙትን ተሞክሮ እና ከተሞክሮው ምን ሊማሩ እንደሚችሉ ይወያዩ።

- ልምምዱ አሁን እንደ መገባደዱ ስያሜዎቹን ወይም ልምምዱን እርስ በርስ መዘላለፍ ከአግባቡ ውጭ መጠቀም እንደሌለባቸው ወይም ለምሳሌ በልምምዱ ወቅት ተማሪው ተሰጥቶት በነበረው ስያሜ መጥራትን መቀጠል የመሳሰለ በማናቸውም መንገድ ሌላ ተማሪ መጥፎ ስሜት እንዲሰማው ማድረግ እንደማይገባ አፅዕኖት መስጠት እንዳለብዎ ያስታውሱ።

- በልምምዱ ወቅት ምን እንደተፈጠረ ተወያዩ፤ ሰዎች በሆነ መልኩ በተለየ መንገድ ሲስተናገዱ ምን ዓይነት ስሜት ሊሰማቸው እንደሚችል ይጠይቋቸው፤ የእነርሱን ተሞክሮዎች እና ግልጽ የወጡ ስሜቶች እና ሐሳቦች ለሌሎች እንዲያካፍሉ ይፍቀዱላቸው።

- በመጨረሻ የተለያየ ማንነት ያላቸውን ተማሪዎች ወደ ፊት እንዲመጡ ይጋብዙ፤ ለምሳሌ የፖለቲከኛ፣ የሁለት ልጅ እናት፣ ባሏ የሞተባት ሴት፤ አባት፣ የአካል ጉዳት ያለበት ሰው ወዘተ እና እነዚህ ስያሜዎች በአንድ ግለሰብ ላይ እንዴት ተፈጻሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተወያዩ፡፡ ለምሳሌ አንድ ግለሰብ በርካታ ስያሜዎች ሊኖሩት ይችላሉ። ተማሪዎች ስለ ተራ አነጋገሮች አንዳንድ ጊዜ በአሉታዊ መንገድ እርስ በርሳችን በሚኖረን ግንኙነት ላይ እንዴት ተጽዕኖ ሊያሳርፉ እንደሚችሉ ወይም ሰዎች ያልሆኑትን እንደሆኑ  አድርጎ መሰየም እና ሰዎች በማንነታቸው እንዴት የተለያዩ ባሕሪያት ሊኖራቸው እንደሚችሉ እንዲረዱ ያግዟቸው።

- ከዚህ ተሞክሮ ተማሪዎች የቀሰሟቸውን ዋነኛ ትምህርቶች በተመለከተ የሚሰማቸውን

ስሜት እና ሐሳብ እንዲያንፀባርቁ እና በተማሩት ላይ በመመርኮዝ እንዴት ሌሎችን በተለየ መንገድ ሊቀርቡ እንደሚችሉ ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ይጋብዟቸው።

**ሰልጣኞች ወይም ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- ተማሪዎች ተሸክመዋቸው የሚዞሩትን የማንነት ስያሜዎች (ጭንብሎች) ለይተው እንዲያወጡ ይጠይቋቸው።

## ድር ቢያብር

**ዓላማ**

- የትብብርን እና የአብሮነትን አስፈላጊነት በሰው ትስስር ልምምድ አማካይነት ለመሳል።

**ውጤት**

- ተማሪዎች አንዱ በሌላው ላይ ያለው መደጋገፍ እና በጋራ የሚያጋጥሙ ፈተናዎች ለመወጣት በአንድነት የመሥራት አስፈላጊነትን በተመለከተ ሐሳባቸውን ያንፀባርቃሉ።

**የማሰልጠኛ መሳሪያዎች**

- ምንም

**ልምምድ**

- በግምት ከ10 እስከ 15 የሚደርሱ ተማሪዎች ባሉዋቸው ቡድኖች ተማሪዎችን ያደራጁ እና ክብ እንዲሠሩ ይጠይቋቸው።

  እያንዳንዱ በክቡ ውስጥ ያለ ተማሪ እጁን ዘርግቶ ሌሎች በክቡ ውስጥ ያሉ ሁለት ተማሪዎችን በመያዝ «ሰንሰለት» ይፈጥራሉ። የእጆች ሰንሰለቱ ሳይሰበር ራሳቸውን ነጻ በማውጣት እንደ ቡድን «ሰንሰለቱን» ለማቋረጥ ይሞክራሉ።

- ቀኝ እጃቸውን ወደ ላይ እንዲያወጡ እና በመቀጠል በክቡ ውስጥ በሌላኛው አቅጣጫ ያለውን ሌላ ተማሪ ቀኝ እጅ እንዲይዙ ይንገሯቸው።

  ማስታወሻ፡- በቀኛቸው ወይም በግራቸው ያለውን ተማሪ ቀኝ እጅ ወዲያውኑ መያዝ የለባቸውም።

- ይህንን ልምምድ በግራ እጅ ደግሞ ያስደግሙት፤ አሁንም የሚይዙት እጅ የተለየ ሌላ ተማሪ እጅ እንደሆነ እና እንዲሁም አጠገባቸው ያለውን ተማሪ ቀኝ ወይም ግራ እጅ እንዳልሆነ ማረጋገጥ ይኖርብዎታል።

- ሁሉም ተማሪ የተለያዩ ሁለት ሰዎችን እጆች መያዙን ለማረጋገጥ እና በአጠገባቸው ያለውን ሰው ቀኝ ወይም ግራ እጅ እየያዙ ያለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ፍተሻ ያድርጉ።

- አሁን «ሰንሰለት» ፈጥረዋል፤ የእጅ ሰንሰለቱ ሳይበጠስ ራሳቸውን ከሰንሰለቱ ለማውጣት

መሞከር አለባቸው፡፡ ለምሳሌ ራሳቸውን ለመፍታት እጃቸው ከሌላ ጋር እንዳይያያዝ ማድረግ አይችሉም። ይህን ፈተና ለማጠናቀቅ የተወሰነ ጊዜ ይፍቀዱ (ብዙውን ጊዜ ከአሥር እስከ ሃያ ደቂቃ በቂ ነው)። ጉዳት እንዳይደርስ ቀስ ብለው እንዲንቀሳቀሱ ተማሪዎቹን ያስታውሷቸው። ተማሪዎች እርስ በርስ እንዳይጓተቱ ወይም እንዳይገፋፉ ይጠይቋቸው። ፈተናውን በቅርበት ይከታተሉ እና ማቆም ካለባቸው ያስቁሟቸው።

የእጆች ሰንሰለቱ የሆነ ቦታ ላይ ከተቋረጠ ቡድኑ እንደገና መጀመር አለበት።

- አንድ ቡድን ራሱን «ከሰንሰለቱ ነጻ ካወጣ» ወይም የተመደበው ጊዜ ካበቃ፣ እያንዳንዱን ቡድን ልምምዱ እንዴት እንደ ነበረ፣ ራሳቸውን ነጻ ለማውጣት ምን እንደረዳው እና ምን ፈተና እንደሆነበት እንዲያብራሩ ይጠይቁ።

- እያንዳንዱ ቡድን ለማብራራት በቂ ጊዜ ካገኘ በኋላ፣ ወደ ሙሉ ቡድኑ/ክፍሉ ይመለሱ እና እያንዳንዱ ቡድን በተናጠል ያብራራውን ነገር ጥቂት ነጥቦች መርጦ ለሁሉም እንዲያካፍል ይጠይቁት።

- በማኅብረሰባችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች መፍትሔ ለመስጠት የትብብርን እና የአብሮነት አስፈላጊነትን ለመወያየት ከዚህ ልምምድ የተገኘውን ተሞክሮ ይጠቀሙበት።

**ሰልጣኞች ወይም ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- ከሌሎች ጋር በአንድነት ለመሥራት ምን ዓይነት ክህሎትን ማጎልበት እንዳለባቸው ተማሪዎች ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ይጠይቋቸው።

## ወንዙን መሻገር

**ዓላማ**

- ፈታኝ በሆነ የቡድን ጨዋታ ላይ የቡድን ሥራን አስፈላጊነት ለማሳየት።

**ውጤት**

- ተማሪዎች ከጋራ ግብ ላይ ለመድረስ የራሳቸውን ተግባቦት እና ትብብር ክህሎት አጎልብተዋል።

**የስልጠና መሳሪያዎች**

- አሮጌ ጋዜጣዎች፣

- ወረቀት እና ሌሎች፡፡

**ልምምድ**

- ተማሪዎችን ከ 8 እስከ 16 አባላት ባሉት ቡድን ይመድቧቸው። ሐሳቡ ወደ 2 ሜትር በ 6 የሆነ ቦታ ለእያንዳንዱ ቡድን እንደ ወንዝ ሆኖ እንዲያገለግል ለማግኘት ነው።

**ጨዋታው**

- የወንዙ ሁለት ጎኖች አንድ ጊዜ ምልክት ከተደረገባቸው በኋላ በወንዙ መሃል ላይ አራት ጋዜጣዎችን እንደ «ደሴቶች» ሆነው እንዲያገለግሉ ያስቀምጧቸው። በተጨማሪ ለእያንዳንዱ ቡድን እንደ «አለት» ሆነው እንዲያገለግሉ ከሁለት እስከ አራት የሚደርሱ ቁራጭ ወረቀቶችን ይስጡ። ሁሉም የቡድን አባላቱ ከወንዙ አንደኛው ዳርቻ ወደ ሌላኛው ተሻግረው የጨረሰ ቡድን አሸናፊ ይሆናል። ሁሉም ቡድን ከ«ወንዙ» አንደኛው ዳርቻ ይጀምር እና ባሉት ውስን ደሴቶች እና አለቶች ላይ ብቻ መራመድ ይችላል።

**ተማሪዎች ማክበር ያሉባቸው ህግ**

- አንተ እና የአንተ ቡድን አባላት በአንድ መርዛማ፣ ገዳይ የሆነ ወንዝ ዳርቻ ላይ ናችሁ። ወንዙ ኃይለኛ መርዛማነት ያለው ሲሆን የአንድ ሰው ቆዳ ወይም ልብስ ወንዙን ከነካ ሰውዬው ወዲያውኑ ይሞታል! በእናንተ ቡድን ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው ከገዳዩ ወንዝ አንደኛው ዳርቻ ወደ ሌላኛው ዳርቻ መሻገር መቻል አለበት። 20 ደቂቃ አላችሁ።

- የማንም ሰው ቆዳ፣ ልብስ ወይም የግል ዕቃ ወንዙን መንካት የለበትም። በወንዙ ላይ በሕይወት መትረፍ የሚችሉ ነገሮች ደሴቶች እና አለቶች ብቻ ናቸው።

- ደሴቶች እና አለቶች ለደህንነት አስተማማኝ ቦታዎች (ሊነኩ የሚችሉ) ናቸው።

- በወንዙ ላይ ያሉት ደሴቶችን ከቦታ ወደ ቦታ ማንቀሳቀስ አይቻልም።

- አለቶች አንድ ጊዜ በወንዙ ላይ ከተቀመጡ በኋላ ማንቀሳቀስ አይቻልም።

- ቡድኖቹ አንድ ጊዜ መሻገር ከጀመሩ በኋላ በቡድኑ ውስጥ የሚታዩትን ሥነ እንቅስቃሴዎች በጥንቃቄ ይመልከቱዋቸው። በንቃት እና በጥንቃቄ መታየት ካለባቸው ነገሮች መካከል፦

  - አንድ ምክክርን ለማድረግ ምን ያክል ጊዜ ይወስዳል?

  - መናገር የሚፈልግ ሰው ሁሉ እንዲናገር እኩል ዕድል አግኝቷል?

  - ጥቆማ ሐሳቦች ሲሰጡ፣ ምላሽ ወዲያው፣ ወዲያው ይሰጥ ነበረ? (ወይም የአንዳንድ ሰዎች ሐሳብ ተደማጭነት ሲኖራቸው የሌሎች ችላ ተብለው ታልፈዋል?)

  - ዕቅድ ተዘጋጅቷል? የዕቅዱን ሐሳብ ያመነጨው ማን ነው? ዕቅዱን በማዘጋጀት ላይ ስንት ሰዎች ተሳትፈዋል?

- ምርጥ የመፍትሔ ሐሳቦችን ለማግኘት ምክክሮች ተደርገዋል?
- ከተማሪዎቹ መካከል አንደኛቸው የሚደረገው ውይይት ላይ የመሪነት ሚና ሳያውቁት ተጫውተዋል?
- ስምምነት ላይ እንዴት ነበረ የተደረሰው? በዕቅዱ መሠረት እርምጃ መውሰድ ከመጀመሩ በፊት በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ መፈጠሩን እና ከስምምነት ላይ መደረሱን ቡድኑ አረጋግጧል?
- ዕቅዱ ሥራው እንዴት መጀመር እና እንዴት መጠናቀቅ እንዳለበት የተሟላ ሥዕልን ይሰጣል?
- አንድ መሪ ወይስ በርካታ መሪዎች ነበሩ? አመራሩ እንዴት ነበረ የተመረጠው? አመራሩ የሚሰጠው ትዕዛዝ ተከብሯል?
- ተማሪዎች አንዱ በሌላው ላይ ለመተማመን፣ እርስ በርስ ለመረዳዳት እና በአካል ለመደጋገፍ ምን ያህል ፈቃደኛ ነበሩ?
- ያስቀመጡት ግብ ተሳክቷል? ምን ያህል ጊዜ አስፈልጎ ነበረ? ግቡን ለማሳካት ወይም እንዳይሳካ ቁልፍ ምክንያት ምን ነበረ?
- በልምምዱ መጨረሻ ላይ ልምምዱ ስለ ምን እንደሆነ ለተማሪዎች ገለጻ ይስጧቸው።
- በጨዋታው ላይ ምን ታዘባችሁ?
- ከዚህ ተሞክሮ ምን ልንማር እንችላለን?

**ተማሪዎች ወይም ሰልጣኞች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- የቀሰሙትን ትምህርት በእውነተኛ የሕይወት ገጠመኞች ላይ እንዴት ተፈጻሚ ማድረግ እንደሚቻል ለመጻፍ የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተርን እንዲጠቀሙ ያድርጓቸው።

## በባህሎች መካካል ያለ ግንኙነት

(«Albatross» ከሚባለው የበይነ ባህላዊ ማስመሰያ ጨዋታ ላይ በመመርኮዝ ተመጥኖ የተዘጋጀ)

**ዓላማ፦**

- የበይነ ባህላዊ ውይይቶችን ውስብስብነት እና የበይነ ባህላዊ ተግባቦትን አስፈላጊነት በሚና ጨዋታ አማካይነት ለማሳየት።

**ውጤት**

- ተማሪዎች የተለያዩ ወጎችን፣ ባህሎችን እና ልማዶችን ተርጉመዋል፤ እንዲሁም ከአክብሮት ጋር ምላሽ ሰጥተዋል።

- ተማሪዎች በግጭት በሚና ወክሎ ጨዋታ የበይነ ባህላዊ ተግባቦትን ተፈጻሚ አድርገዋል።

**የስልጠና መሳሪያዎች ቁሳቁሶች**

- ጥቂት ስኒ ውሃ፣
- ጥቂት ከረሜላ፣
- እንደ ማራገቢያ ለመጠቀም ቅጠሎች ያሉት የዛፍ ቅርንጫፍ፣
- ወንበሮች እና ሌሎች፡፡

**ልምምድ**

- ሰልጣኞቹ ወይም ተማሪዎቹ የሚጎበኙት ማኅበረሰብ የተለዩ ባህላዊ ልማዶች ያሉበት ለመጀመሪያ ጊዜ እየገቡ እንዳለ ያስመስላሉ። ይህ ልምምድ ማስመሰል እንደሆነ እና ተማሪዎች እንዲወክሉ የተሰጣቸውን ሚና በሚገባ መጫወታቸው አስፈላጊ እንደሆነ ያብራሩላቸው።

- የባህል ልውውጥ የሚያደርጉ ሁለት የተለያዩ የማኅበረሰብ ቡድኖችን ለመፍጠር ተማሪዎቹን ከ8 እስከ 10 አባላት ባሏቸው (ሴት እና ወንድ ተማሪዎች የተቀላቀሉባቸው) በሁለት ቡድኖች ይክፈሏቸው። የተቀሩት ተማሪዎች በመስተጋብሩ ወቅት የሚታዩ ለውጦችን እንዲታዘቡ እና ምን እንደተፈጠረ በማስታወሻቸው ጽፈው እንዲይዙ ያድርጉ።

- የሚኖራቸውን የየራሳቸውን ዳራ (ድኅረታሪክ) እና ባሕሪ ለመንገር ሌላኛው ቡድን መስማት ወይም ማየት በማይችልበት ሁኔታ ሁለቱን የማኅበረሰብ ቡድኖች ለየብቻ ያግኙዋቸው። በዚህ ግንኙነት ላይ ለእያንዳንዱ ቡድን የሚመለከተውን የራሱን መመሪያ መስጫ ወረቀት ይስጡት፣ወረቀቱ ባህሉን ያብራራል። እንዲጫወቱት የተሰጡዋቸው ሚና እና ባሕሪ ግልጽ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ለማማሮ እና ዛምቦ ማኅበረሰቦች የተሰጡትን መመሪያዎች ከዚህ በታች ይመልከቱ።

**ማግሮ ማኅበረሰብ**
ማግሮዎች ሴቶች የማኅበረሰቡ መሪዎች የሆኑባቸው ረዥም ታሪክ ያላቸው ማኅበረሰቦች ናቸው። የሚግባቡበት ቋንቋ የላቸውም እና መልእክት ለመለዋወጥ የሚጠቀሙት ምላሳቸውን እንጢ፣ እንጢ እንዲል በማድረግ ብቻ ነው። ሁለቴ ምላስን እንጢ እንዲል ማድረግ መስማማትን/መፍቀድን ሲያሳይ አንድ ጊዜ እንጢ ማድረግ ደግሞ አለመስማማትን/አለመፍቀድን ያሳያል።

እንግዶችን የሚቀበሉት በሴቶች ሆኖ ሰላምታ አሰጣጡ በመጀመሪያ ሴቶች እጆቻቸውን በእንግዶቹ ትከሻ ላይ በማድረግ እንግዳው መልሶ እጆቹን በእነርሱ ትከሻ በማኖር ሰላምታ እስኪሰጣቸው ድረስ ይጠብቃሉ። ወንዶች በሰላምታ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ላይ አይሳተፉም።

ማግሮዎች መሬት እና ውሃ የሕይወት ምንጭ እና ጠባቂ ስለሆኑ የተቀደሱ ናቸው ብለው ያምናሉ። ሴቶች እንደ ማኅበረሰቡ መሪነታቸው ብቻ ቅዱስ ነገሮችን እንዲቀርቡ እና እንዲሁም በመደበኛ የማኅበረሰቡ ስብሰባዎች ላይ መሬት ላይ እንዲቀመጡ ይፈቀድላቸዋል።

መጤዎች መሪዎቻቸውን በመርዝ ለመግደል ለበርካታ ጊዜ ከሞከሩባቸው ጊዜ ወዲህ አሁን በመጀመሪያ ወንዶች ምግብ ወይም የሚጠጣውን ነገር ይቀምሱ እና ቢበላ ወይም ቢጠጣ ችግር እንደሌለው ምልክት ለመስጠት ሴቶቹ እግር ሥር ያስቀምጡታል።

**ዛምቡ ማኅበረሰብ**
ዛምቡዎች ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ውስጥ ካለ ቦታ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ሲሆኑ ዛፎች ሰዎችን ለመባረክ እና ለመፈወስ ልዩ ኃይል አላቸው ብለው ያምናሉ። እንግዶችን ሲቀበሉ፣ ቅጠል ባለው የዛፍ ቅርንጫፍ ቁራጭ ሦስት ጊዜ እንግዳው ላይ ያራግቡ እና በቅርንጫፉ የእንግዳውን ጭንቅላት አንድ ጊዜ በቀስታ መታ ያደርጋሉ።

በራሳቸው ቋንቋ ይግባባሉ። «ሙ» የሚለው ቃል መስማማትን/መፍቀድን ሲገልጽ «ቡ» የሚለው ቃል ደግሞ አለመስማማትን/አለመፍቀድን ይገልጻል። በመደበኛ ስብሰባዎች ላይ ሁሉም ሰው እንደ ዛፎች መንፈሳዊ ልጅነቱ በእኩልነት ይታያል እና በረጃጅም ወንበሮች ላይ መቀመጥ የአክብሮት ምልክት ተደርጎ ይቆጠራል።

ዛምቡዎች ከመብላታቸው ወይም ከመጠጣታቸው በፊት በመጀመሪያ የሚበሉትን ምግቦች ለዛፎች ይሰጡ እና ይህን ካደረጉ በኋላ ብቻ ራሳቸው መመገብ ይጀምራሉ። አንዱ የሌላው ጥገኛ መሆኑን ዕውቅና ለመስጠት በጭራሽ በገዛ እጃቸው ምግባቸውን አይመገቡም፤ ይልቁንስ እርስ በርስ ይጎራረሳሉ።

- እያንዳንዱ ቡድን እንዲስማማ እና የተሰጠውን ባህላዊ ባሕሪ እንዲለማመድ እንዲሁም ለሚመጡት እንግዶች አቀባበል ለማድረግ እንዲዘጋጅ 10 ደቂቃ ጊዜ ይስጡ። እያንዳንዱ ቡድን ወደ ሌላኛው ቡድን ሄዶ ጉብኝት የሚያደርጉትን ሦስት፣ ሦስት አባላትን በተለያዩ ሦስት አጋጣሚዎች ላይ ተወካዮቻቸው እንዲሆኑ እንዲመርጡ ይጠይቃቸው።
- **የጉብኝት ዙር 1፦ የመጀመሪያ ጉብኝት እና ሰላምታ (15 ደቂቃ)** ሁለቱም ማኅበረሰቦች የየራሳቸው እርስ በርስ ሰላምታ የሚለዋወጡበት መንገድ አላቸው። ወደ እያንዳንዱ

ማኅበረሰብ የሚሄዱት ሁለቱም ጎብኝ ቡድኖች አዲሱን ማኅበረሰብ መጎብኘት እንዲችሉ ተገቢነት ባለው መንገድ ምላሽ መስጠት አለባቸው።

ከ10 ደቂቃዎች በኋላ ጎብኚዎቹ ወደራሳቸው ማኅበረሰብ እንዲመለሱ እና የነበራቸውን ተሞክሮ ላልሄዱት እንዲያካፍሉ እንዲሁም ከቡድናቸው ጋር የሌላኛው ማኅበረሰብ ሥነ እንቅስቃሴዎች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ እንዲወያዩ ይጠይቋቸው።

- **የጉብኝት ዙር 2፦ አቀማመጥ** (15 **ደቂቃ**) ሁለት አዳዲስ ጎብኚዎች አቀባበል ይደረግላቸውና መስተንግዶ አድራጊ በሆነው ማኅበረሰብ አንድ ላይ እንዲቀመጡ ይጋበዛሉ። የእንግዳ ተቀባዩ ማኅበረሰብ አባላት ጎብኚዎች የእነርሱን እምነቶች እንዲያከብሩ የአቀማመጥ ሥርዓትን በተመለከተ እነርሱ እንደሚያደርጉት እንዲያደርጉ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሲሆን ብቻ ለእንግዶቹ የሚበላ ነገር ያቀርባሉ።

  ከ10 ደቂቃዎች በኋላ ጎብኚዎቹ ወደ ራሳቸው ማኅበረሰብ እንዲመለሱ እና የነበራቸውን ተሞክሮ ላልሄዱት እንዲያካፍሉ እንዲሁም ከቡድናቸው ጋር የሌላኛው ማኅበረሰብ ሥነ እንቅስቃሴዎች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ እንዲወያዩ ያድርጓቸው።

- **የጉብኝት ዙር 3፦ ምግብን መቋደስ** (15 **ደቂቃ**) በዚህ የመጨረሻ ዙር ላይ ሦስተኛው ጎብኚ ጥንዶች አቀባበል ይደረግላቸውና ምግብ ለመመገብ አብረው ይቀመጣሉ። መስተንግዶ የሚያደርገው ማኅበረሰብ ምግቡን የሚያቀርበው ባለው ባህል እና እምነት ላይ ተመርኩዞ ነው።

  ከ10 ደቂቃ በኋላ እንደገና ጎብኚዎቹ ወደ ራሳቸው ማኅበረሰብ እንዲመለሱ እና በሦስቱም የጉብኝት ተሞክሮዎች ላይ በመመርኮዝ ስለ ጎበኙት ማኅበረሰብ ሥነ እንቅስቃሴ እንዲወያዩ ያድርጓቸው።

- ሦስቱም ዙር ጉብኝቶች እንደተጠናቀቁ ተማሪዎቹ በሙሉ አንድ ላይ እንዲሰበሰቡ እና በሦስቱ ጉብኝቶች ወቅት የተፈጠረውን እና ከእነዚህ ተሞክሮዎች በመነሣትም ስለሌላኛው ማኅበረሰብ ምን እንደተማሩ በአጭሩ ለሌሎች እንዲናገሩ ይጋብዟቸው። ከዚህ በኋላ ሌላኛው ማኅበረሰብ ከእምነት፣ ከእሴት እና ከባሕሪ አንጻር የራሱን ዳራ (ድኅረ ታሪክ) ለሌላው ቡድን እንዲያካፍል ይፍቀዱ። በማኅበረሰቦቹ መካከል ያለውን የሥርዓተ ጾታ ሥነ እንቅስቃሴ (dynamics) የእምነቶች እና የባህላዊ ልማዶች ልዩነቶችን ተወያዩ።

- ከሌላኛው ቡድን ተማሪዎች አጋር እንዲያገኙ እና ከልምምዱ የቀሰሙትን ትምህርት እንዲወያዩ ይጋብዟቸው፤ ስለ ትምህርታቸው በተማሪዎች መካከል የሚደረገውን ውይይት ያስተባብሩ።

- ሌላ የተለየ ባህልን በማክበር ምን ዓይነት ልዩነት ለእነርሱ ፈታኝ እንደነበረ እና ልዩነት

ሲያጋጥም መልዕክት ለመለዋወጥ የሚቻልበት ምርጥ መንገድ ምን እንደሆነ ከተማሪዎች ጋር ይወያዩ።

**ሰልጣኞች ወይም ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- የተለየ ባህል ወይም ኃይማኖታዊ ዳራ ያላቸውን ሰዎች ሲያገኙ ምን ማድረግ እንዳለባቸው የሚገልጹ ከአንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች ጋር ለራሳቸው ደብዳቤ ለመጻፍ የእነርሱን የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር እንዲጠቀሙ ይጋብዟቸው።

## ማኅበረሰብን አሳታፊ ፕሮጄክቶች

ይህ ልምምድ በክፍል ውስጥ ካሉ ተማሪዎች ወይም እንደ ትምህርት ቤት ክበብ አንድ አካል ሊከናወን ይችላል።

**ዓላማዎች**

- የአዎንታዊ ማኅበራዊ ለውጥ ፕሮጄክትን ለመቅረጽ።
- ጥልቅ አሳቢነትን እና የችግር አፈታት ክኅሎቶችን በእውነተኛው ዓለም መፍትሔ አሰጣጥ ላይ ተፈጻሚ ለማድረግ።

**ውጤቶች**

- ተማሪዎች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ያለን ችግር ትንታኔ ሰጥተው፣ መዝነው ተገቢነት አለው የሚሉትን መፍትሔ ያዘጋጃሉ።
- ተማሪዎች የሚወስዱት እርምጃ በማኅበረሰባቸው ውስጥ አዎንታዊ ለውጥን ሊፈጥር እንደሚችል ያውቃሉ።

**ቁሳቁሶች (ማቴሪያሎች)**

- ምንም ዓይነት የተለዩ ቁሳቁሶች አያስፈልጉም፡፡

**ልምምድ**

- በትምህርት ቤታቸው፣ በቤተሰባቸው፣ በሰፈራቸው፣ በከተማቸው ወይም በአገራቸው ሊሆን ይችላል፤ ተማሪዎች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ያለን ችግር ወይም አስቸጋሪ ሁኔታ ለመለወጥ የሚያግዝ ፕሮጀክት ይዘው እንዲመጡ ይጠይቋቸው። ፕሮጀክቱ በጊዜ ገደብ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት፤ ለምሳሌ በጥቂት ወራት ውስጥ ሊደረግ የሚችል መሆን አለበት። ተማሪዎች በትላልቅ ቡድኖች ውስጥ ወይም አንድ ላይ ሁሉም እንደ ክፍል ፕሮጀክት ሊሠሩ ይችላሉ።
- አንዳንድ ፕሮጀክቶች ሕጋዊ ሥርዓቱን የጠበቀ ፕሮግራም ለመጀመር የትምህርት ቤት

አመራርን፣ የወላጆችን እና የማኅበረሰብ መሪዎችን ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ይህም ተማሪዎች በተጨማሪ በፕሮጀክቱ ውስጥ እንዲሳተፉ ያስችላቸዋል። ከዚህም በላይ ለፕሮጀክቶቹ አንዳንድ ግብዓቶችን ማግኘት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

- ፕሮጀክቶች የተወሰኑ መስፈርቶችን ማሟላት መቻል አለባቸው፤ እነዚህ መስፈርቶች በተማሪዎቹ ሊወሰኑ ይችላሉ። ፕሮጀክቱ ለምሳሌ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡፡
    - የተለያዩ ማኅበረሰቦችን ማሳተፍ፤
    - ተጨባጭ እና ግልጽ መሆን፤
    - ሥነ ምግባራዊ አሠራር ልማዶችን ማስቀደም፤
    - የተወሰነ አስቸጋሪ ሁኔታን ለመለወጥ ማገዝ፤
    - አዲስ ሐሳብን የሰነቀ እንዲሆን ማድረግ እና
    - መፍትሔ ተኮር እንዲሆን ማድረግ ናቸው፡፡
    - ልዩ ዝግጅትን ያዘጋጁ ወላጆችን እና ልዩ እንግዶችን ይጋብዙ እና ተማሪዎችም ፕሮጀክታቸውን እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው።

**የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- የቀሰሟቸውን ዋነኛ ትምህርቶች ለይተው እንዲያወጡ እና በሚቀጥለው ጊዜ በተለየ መንገድ ምን እንደሚያደርጉ እንዲያስረዱ ተማሪዎችን ይጋብዟቸው።

## በትውልዶች መካከል የሚደረግ ውይይት

**ዓላማ**

- ተማሪዎች ለእነርሱ ፋይዳ ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ በበይነ ትውልዳዊ (በተለያየ ዕድሜ እርከን ውስጥ ባሉ ሰዎች መካከል የሚደረግ) ውይይት ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ።

**ውጤቶች**

- ተማሪዎች ታሪኩን ጨምሮ ስለ ማኅበረሰባቸው የተለየ አዲስ አመለካከት ይኖራቸዋል።
- ተማሪዎች ስለ ማኅበረሰቡ ችግሮች ያላቸውን አመለካከት ለመሪዎች ይገልጻሉ።

**ቁሳቁሶች (ማቴሪያሎች)**

- ለዝግጅቱ የግብዣ ደብዳቤዎች (በቃልም ሊሆን ይችላል)፤
- አስተባባሪ(ዎች)፤
- ጥያቄዎች ወይም የውይይቱ መነጋገሪያ አጀንዳዎች፤

- ለቤተ ሥዕላት ዐውደ ርዕይ ቀራቢ ዝግጅቶች (የግድ ያልሆነ)፤
- ሥዕል ወይም ፖስተሮች።

**ልምምድ**

- ይህ ልምምድ በተማሪዎች እና በማኅበረሰብ መሪዎች ተሳታፊነት ለሚደረገው ውይይት ምቹ የሆነ ለደኅንነት አስተማማኝ የሆነ ቦታ ላይ መደረግ አለበት። ይህ ቦታ ትምህርት ቤት፣ የማኅበረሰቡ መሰብሰቢያ አዳራሽ ወይም የአካባቢው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሕንጻ ወዘተ ሊሆን ይችላል። የግብዣ ወረቀቶች በጥንቃቄ መዘጋጀት እና ለማኅበረሰቡ መሪዎች ቦታ እንዲሰጡት እና ከተማሪዎች ጋር ትርጉም ባለው መንገድ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የውይይቱን ዓላማ እና የማኅበረሰቡን ፍላጎትና ጥቅም በግልጽ የሚያሳይ ሆኖ መተላለፍ ይኖርበታል።

- ይህ በግብዣው በተካተተው አጀንዳ ላይ የሚመረኮዝ ሆኖ ከአንድ ሰዓት ተኩል እስከ ሦስት ሰዓታት እንደሚወስድ ተደርጎ ዕቅድ ሊያዝለት ይችላል። የርዕሰ ጉዳዩ ትኩረት ከሁሉም የሚመለከታቸው ጋር ለምሳሌ የእኛን ማኅበረሰብ እንዴት ይበልጥ ደኅንነቱን መጠበቅ ይችላል የሚል ዓይነት ርዕስ ላይ በምክክር አስቀድሞ መስማማት ይቻላል።

- በይነ-ትውልዳዊ የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት፣ በይነ-ትውልዳዊ ፓናል፣ አንድ ለአንድ ውይይቶች፣ የትናንሽ ቡድን እንቅስቃሴዎች ወይም ሌላ የተለያዩ አሳታፊ ቅርፆች ሊኖረው ይችላል።

- ሁሉም ሰው ትርጉም ባለው መንገድ ከሌላው ጋር እንዲነጋገር ፤ከሁሉም ዕድሜ ክልል የመጡ ተሳታፊዎች እኩል ጊዜ ተሰጥቷቸው እንዲናገሩ እና እንዲያዳምጡ እንዲሁም ጥልቀት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ለመወያየት እንዲቻል ውይይቱን ለማስጀመር የወጣቶች ተሳትፎ አስፈላጊነትን የሚረዳ(ዱ) አንድ ወይም ሁለት አስተባባሪ(ዎች) ለውይይቱ ማግኘት አስፈላጊ ነው። በአንዳንድ ዓውዶች ውስጥ ሁለት አስተባባሪዎችን (አንድ ዐዋቂ ሰው እና አንድ ወጣት ሰው) ማካተትን ከግምት ማስገባት ይችላሉ።

- ሁሉን አካታች እንዲሆን እና ሁሉም ተማሪዎች የየራሳቸውን አመለካከቶች እንዲያካፍሉ ለማረጋገጥ ከዝግጅቱ በፊት ውይይቱን ይበልጥ ለማስፋት ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል በወጣቶች አስቀድሞ የተዘጋጀ ከውይይቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለው የሥዕል ወይም የፖስተሮች የቤተ-ሥዕላት ዐውደ ርዕይ ወይም የሚቀርብ ዝግጅት በማካተት ተጨማሪ ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ።

- እንዲህ ያሉ ውይይቶች በማኅበረሰብ ውስጥ ወጣቶች ሊሳተፉ የሚችሉበትን መድረክ ሊፈጥሩ ይችላሉ፤ አመራር ላይ የተቀመጡ ወጣቶች የያዙዋቸውን አነስተኛ ፕሮጀክቶች ወይም ሌላ ዓይነት የሥራ ውጥኖች ክትትልና ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል።

- ስለ ልምምዱ ማብራሪያ በመስጠት ተማሪዎቹ ከጠበቁት አኳያ ልምምዱ ምን ያክል የጠበቁትን እንዳሟላላቸው፣ ከገጠሟቸው ተግዳሮቶች ምን እንደተማሩ እና በተለየ ሁኔታ ምን መደረግ እንዳለበት እንዲወያዩ ያድርጓቸው።

**የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- የቀሰሟቸውን ዋነኛ ትምህርቶች ለይተው እንዲያወጡ እና በሚቀጥለው ጊዜ በተለየ መንገድ ምን እንደሚያደርጉ እንዲያስረዱ ተማሪዎችን ይጋብዟቸው።

## የ2030 ዘላቂ ልማት ግቦች

(ከ World's Largest Lesson ተመጥኖ የተወሰደ http://worldslargestlesson.globalgoals.org/all-lesson-plans/)

**ዓላማዎች**

- በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች እያጋጠሟቸው ያሉ ችግሮችን በየኤነታቸው ለይቶ ለመመደብ።
- ለዘላቂ ልማት ግቦች /Sustainable Development Goals (SDGs)/ አስተዋፅኦ ማድረግ የሚቻልባቸውን መንገዶች ለይቶ ለማወቅ።

**ውጤቶች**

- ዓለማችን እየተጋፈጠቻቸው ያሉ አንዳንድ ቁልፍ ችግሮችን ለመፍታት እንዴት የዘላቂ ልማት ዕቅዶች /SDGs/ ተግባር ተኮር እርምጃዎችን እንደሚያበረታቱ ተማሪዎች ይረዳሉ።
- ተማሪዎች ለSDGs አስተዋፅኦ ማድረግ የሚችሉባቸውን መንገዶች ያገኛሉ።

**ቁሳቁሶች**

- የዘላቂ ልማት ዕቅዶች ፖስተር፤
- ጥቁር ሰሌዳ ወይም የፍሊፕቻርት ወረቀት፤
- ጠመኔ፣ ማርከሮች ወይም እስክርቢቶዎች፤
- የተማሪ ማስታወሻ ደብተሮች፣ ወረቀት እና
- የሚለጠፍ ማስታወሻ መያዣ ወረቀት(ግዴታ ያልሆነ)፡፡

**ልምምድ**

- በትምህርቱ መጀመሪያ ላይ፣ የሚከተሉት ጥያቄዎች በጥቁር ሰሌዳ ወይም ፍሊፕቻርት

ላይ እንዲጻፉ ያድርጉ፦ «በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሰዎች በብዛት እያጋጠሟቸው ያሉ ችግሮች ምንድን ናቸው?»

- ተማሪዎች ጥያቄው ላይ ያላቸውን ሐሳብ እንዲያንፀባርቁ እና ቢያንስ የራሳቸው ቅን መልሶች እንዲጽፉ ይጠይቋቸው። ተማሪዎች የተለያዩ መልሶችን አንዱ ለሌላው እንዲያካፍል እና ሁሉንም መልሶች አሰባስበው እንደ ዝርዝር በጥቁር ሰሌዳው ወይም በፍሊፕቻርት ላይ አንድ ዓይነት መልስ ሳይደጋገም እንዲጽፉ ያድርጓቸው። በአማራጭነት መልሶቻቸውን እንዲጽፉባቸው የሚያጣብቁ ማስታወሻ መያዣ ወረቀቶችን ሊሰጡዋቸው እና ሲጨርሱ ተለጣፊ ወረቀቶቹን በሰሌዳው ላይ አንድ ዓይነት የሆኑትን መልሶች በአንድ ላይ በመመደብ እንዲለጥፉ ሊያደርጓቸው ይችላሉ።

- የዘላቂ ልማት ዕቅዶችን /SDGs/ ምን እንደሆኑ ያስተዋውቋቸው፤ ፖስተር ወይም የ 17 SDGs ቅጂ (ከዚህ በታች ያለውን ምስል ይመልከቱ) መያዝ ይጠቅማል። ተማሪዎቹን እያንዳንዱን 17 SDGs ያስተዋውቋቸው። በመጀመሪያ ተማሪዎች እያንዳንዱ ምንድነው ብለው እንደሚያስቡ እንዲናገሩ እና ትርጉሙን እንዲያብራሩ ይጠይቋቸው።

- ተማሪዎችን ከ 4 እስከ 6 አባላት ባሉት ቡድን ውስጥ ይመድቧቸው እና በሰሌዳው/ፖስተሩ ላይ ካሉት ችግሮች አምስቱን እንዲመርጡ ይጠይቋቸው። እያንዳንዱ ችግር ከየትኛው SDGs ተዛማጅነት እንዳለው ለይተው እንዲያወጡ ይጠይቋቸው። እያዳንዱ ቡድን ለሙሉው ክፍል ተማሪ አንድ ችግርን እና ተዛማጅነት ያላቸውን SDGs እንዲያቀርብ ጊዜ ይስጡት።

- በተከፋፈሉት ቡድኖች ውስጥ፣ እንደ «SDGs ለምን ያስፈልጋሉ እና ለምንስ አስፈላጊ ናቸው?» የሚሉ ጥያቄዎች በመጠየቅ ውይይት እንዲጀመር ያድርጉ። የተለያዩ ዓይነት ተማሪዎች ሐሳባቸውን እንዲገልጹ መድረኩን ያመቻቹላቸው። የሚከተሉት ጥያቄዎች ውይይቱን ይበልጥ ለማስፋፋት ሊያግዙ ይችላሉ፡፡

    - አገሮች የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ለምን እርስ በርስ መተባበር ያስፈልጋቸዋል?
    - በእኛ አገር ውስጥ በ ዘላቂ ልማት ግቦች ላይ የሚወሰዱትን እርምጃዎች በኃላፊነት የሚመራው ማን ነው? የትኞቹ ተቋማት?
    - መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶች ሳይሟሉ እና ዘላቂ ልማት ሳይተገበር ሲቀር የእኛ ማኅበረሰብ ሊያጋጥሙት የሚችሉት ችግሮች ምንድን ናቸው?
    - የልማት ችግሮች በአገራችን ውስጥ እንዴት ከግጭቶች እና ዐመፅ ከተሞሉ ፅንፈኛ እንቅስቃሴዎች ጋር ይዛመዳሉ?
    - ሁሉም ሰው ለSDGs አስተዋፅኦ ማድረግ እንዳለበት እና ከእነዚህ ግቦች ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ልዩ የሥልጣን መብቶች የተሰጧቸው ልዩ ተቋማት እንዳሉ እንዲረዱ ተማሪዎቹን ያግዟቸው።

## የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ

- በትምህርቱ መጨረሻ ላይ አስተዋፅኦ ሊያደርጉበት የሚፈልጉትን SDG ለይተው እንዲያውቁ እና በሳምንቱ ውስጥ ሊያከናውኑት የሚችሉትን አነስተኛ እርምጃ ዕቅድ እንዲያወጡ ተማሪዎቹን ይጋብዟቸው።




*ምንጭ፦ የተባበሩት መንግሥታት፣ SDG ፖስተር፣ እዚህ ላይ ይገኛል፦*
https://www.un.org/sustainabledevelopment/news/communications-material/

ስለ SDGዎች እዚህ ላይ ተጨማሪ ይረዱ፦
https://www.un.org/sustainabledevelopment/sustainable-development-goals/

***«ያለችን አንዲት ፕላኔት ብቻ ናት። ሌላ የትም የምንሄድበት ቦታ የለንም። ያለንን የፈጠራ ጉልበት በአግባቡ ከተጠቀምንበት ደግሞ የትም ሌላ ቦታ መሄድ አያስፈልገንም። በአግባቡ ከተንከባከብናት እና እርስ በራሳችን ከተረዳዳን ሁሉም የሚያስፈልገን ነገር እዚሁ አለ»***

ሰር ኬን ሮቢንሰን

## የምርጫ ልምምድ

**ዓላማ**

- በመለማመጃ ምርጫ የሚና ወክሎ ጨዋታ አማካኝነት ዴሞክራሲያዊ ልምምዶችን ለመግለፅ።

**ውጤት**

- እንደ ምርጫ ያሉ ዴሞክራሲያዊ ልምምዶች የሚያመጧቸውን መልካም ዕድሎች እና ተግዳሮቶች ተማሪዎች ለይተው ያውቃሉ።
- ተማሪዎች የራሳቸውን እና የሌሎችን ፍላጎቶች እና ለሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች የመፍትሔ ሐሳቦችን በተሻለ ይገልጻሉ።

**ቁሳቁሶች**

- ለምርጫ ካርዶች የሚሆኑ አነስተኛ መጠን ያላቸው ወረቀቶች እና እስክርቢቶዎች ወይም እርሳሶች እና
- ለምርጫ  ካርዶች ማስገቢያ ሣጥን፡፡

**ልምምድ**

- ለከተማው ምክር ቤት የመለማመጃ ምርጫ በተለያዩ ኃላፊነቶች ላይ ለመሥራት ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎችን ጥሪ ያቅርቡላቸው። የሚኖሯቸው ሚናዎች እና ኃላፊነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡
    - **የምርጫ ቦርድ፡-** አምስት አባላት የሚኖሩት ሲሆን ምርጫውን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ያስፈፅማል በመጨረሻም ውጤት ያሳውቃል፡፡
    - **ዕጩዎች፡-** ከ2 እስከ 4 ተማሪዎች ዕጩዎች ሆነው ይቀርባሉ፣ እነዚህ ለምርጫው የሚወዳደሩ እና ለመመረጥ የምርጫ ድምፅ ለማግኘት የሚሞክሩ ዕጩዎች ናቸው፡፡
    - **የዕጩ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን (በአንድ ዕጩ 5 ተማሪዎች)፡-** ቡድኑ ድጋፍን እና የምርጫ ድምፅን ለዕጩዎቻቸው ለማግኘት ቁልፍ የሆኑ መልዕክቶች ለይቶ በማውጣት የዕጩውን የዘመቻ ቅስቀሳ በበላይነት ለመምራት ኃላፊነት የሚወስድ ቡድን ነው።
    - **የፖሊሲ አማካሪዎች (1 ተማሪ በአንድ ዕጩ)፡-** ዕጩው 3 ከፍተኛ የፖሊሲ ችግሮችን ወይም የማኅበረሰብ ችግሮችን ለይቶ እንዲያውቅና የምርጫ ቅስቀሳውን በእነዚህ ዙሪያ እንዲያደራጅ የማገዝ ኃላፊነት ያለባቸው ናቸው።
    - **የዕጩ ደጋፊዎች (5 ተማሪዎች በአንድ ዕጩ)፡-** የራሳቸውን ዕጩ አሉታዊ ጎኖች ችላ ብለው ለማየት እና በምርጫ ቅስቀሳው ዘመቻ ላይ ለማገዝ ፈቃደኛ

የሆኑ የእያንዳንዱ ዕጩ ጠንካራ ደጋፊዎች እንዲሳተፉ ማድረግ ያስፈልጋል።

- **አስመራጭ ኮሚቴ** (3 **ተማሪዎች**)፡- ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫ እንደተደረገ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።
- **የአካል ጉዳተኞች መብት ተከራካሪ** (1 **ተማሪ**)፡- በእያንዳንዱ ዕጩ ከሚቀርቡት መፍትሔ የሚፈለግላቸው ከፍተኛ 3 ችግሮች መካከል የአካል ጉዳተኞች መብት ጉዳይ አንዱ እንዲሆን ማድረግ ነው ፡፡
- **የወጣት የስፖርት ቡድን** (5 **ተማሪዎች**)፡- ለማኅበረሰቡ አዲስ የስፖርት ስቴዲዮም እንዲገነባ ማስደረግ ይፈልጋል።
- **አቤቱታ አቅራቢዎች** (2 **ተማሪዎች**)፡- እነዚህ በምርጫ ላይ ያላቸውን እምነት ያጡ እና የምርጫ ሂደቱን እንደ እርባና ቢስ ሥራ አድርገው የሚተቹ የማኅበረሰቡ አባሎች ናቸው።
- **ሰፊው ሕዝብ** (**ሁሉም ሌሎች ተማሪዎች**)፡- በዕጩዎች ምርጫ ቅስቀሳ ተማርከው ድምፅ ሊሰጡ የሚችሉ ማንን መደገፍ እንዳለባቸው ያልወሰኑ ድምፅ ሰጪዎች ናቸው።

የሚከተሉትን ሂደቶች በመከተል የማስመሰያ ምርጫውን ያከናውኑ፡፡

- **ዕቅድ አወጣጥ**፦ አንድ ጊዜ ሁሉም ሚናዎች ተመድበው እንደተጠናቀቁ ለእያንዳንዱ ቡድን ለምርጫው ዕቅድ እንዲያወጣ እና እንዲዘጋጅ 15 ደቂቃ ይስጧቸው።
- **የምርጫ ቅስቀሳ ጊዜ**፦ ለምርጫ ቅስቀሳ 15 ደቂቃ ይስጡ።
- **ድምፅ አሰጣጥ**፦ እያንዳንዱ የማኅበረሰብ አባል 1 ድምፅ ይኖረዋል እና የዕጩው ቍጥር የተጻፈባቸው የድምፅ መስጫ ወረቀቶች (ካለ በሣጥን ውስጥ) ወይም በአስመራጭ ኮሚቴው ይሰበሰባሉ።
- **የምርጫ ውጤቶች**፦ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ የምርጫው አሸናፊ ማን እንደሆነ ያሳውቃል።
- **የምርጫ ውጤት ቅቡልነት ማረጋገጫ ንግግር**፦ በአሸናፊው እና በተሸናፊው ዕጩዎች የሚሰጡ አስተያየቶች።
- ከመለማመጃ ምርጫው በኋላ ያጋጠሙ ማናቸውንም አስገራሚ ክስተቶችን፣ በምርጫው ወቅት ምን እንደተሰማቸው፣ ማን ጥሩ እንደሠራ እና ማን ጥሩ እንዳልሠራ ማብራራት እንዲችሉ የተለያየ ሚና ከነበሯቸው ተማሪዎች መካከል አንዳንዶቹን በመጋበዝ የተገኘውን ትምህርት እንዲከለስ ያድርጉ። ከመለማመጃ ምርጫዎች ምን ልንማር እንደምንችል ተማሪዎች እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። ምርጫዎች ማኅበረሰቡ ሰላማዊ እንዲሆን ለማድረግ መቻላቸውን ለማረጋገጥ ምን ማድረግ ይቻላል?

**የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- በብሔራዊ ምርጫ ላይ ለመሳተፍ ብዙ ከነበሩ የትኛውን ዕጩ መምረጥ እንዳለባቸው ለመወሰን የተጠቀሙባቸውን መስፈርቶች ዝርዝር ለመጻፍ የእነርሱን የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር እንዲጠቀሙ ለተማሪዎቹ ይጋብዟቸው።

## የባህል ብዝኃነት ክብረ በዓላት

**ዓላማ**

- በባህሎች መካከል ያሉትን መመሳሰሎች እና ልዩነቶች ለማነጻጸር።

**ውጤት**

- ተማሪዎች ስለ ሌላ ባህሎች ያላቸውን ግንዛቤ በተግባር  አጎልብተዋል።

- ተማሪዎች ብዝኃነትን የማድነቅ እና የማክበር ስሜትን ገልፀዋል።

**ቁሳቁሶች**

- በአማራጭነት የሚያዙ፦ ሥዕሎችና ገላጭ ምስሎች፣ ሙዚቃ፣  መዝናኛዎች፣ የ«ባዛር» ጠረጴዛዎች ፣ የፓናል ውይይቶችና ጥናታዊ ጽሑፎች ናቸው፡፡

**ልምምድ፦**

- የሌላ ማኅበረሰብን ወግ ወይም ሃይማኖት ለመካፈል እና ተሞክሮ ለመለዋወጥ የባህል ቀናት መልካም አጋጣሚን ይፈጥራሉ።  የባህል ቀኑ/ዝግጅቱ ባህላዊ ምግቦች፣ አልባሳት፣ ሙዚቃ እና ጭፈራ እንዲሁም የተለያዩ ማኅበረሰቦችን መልካምድራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ኢኮኖሚያዊ እውነታዎችን የሚያሳዩ ገላጭ ነገሮችን ሊያካትት ይችላል።

- ተማሪዎች ከተለያዩ ባህላዊ ዳራዎች የመጡ ካልሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ማኅበረሰቦችን ወይም ባህሎችን ለማጥናት እና በመቀጠል ለዝግጅቱ ያጠኑትን ማኅበረሰብ ወክለው ለመቅረብ የሚያስችላቸው እና  ዕድል የሚያስገኝላቸው ጥሩ አጋጣሚ ነው።

- ይህ ዝግጅት ተማሪዎች ሀላፊነትን እንዲወስዱ እና   ዝግጅት በማድረግ ላይ ልምድ እንዲያገኙ ዕድል ይሰጣቸዋል። ተማሪዎቹ ድጋፍ እያገኙ የፕሮግራሙን አጠቃላይ ክፍሎች ምን መሆን እንዳለባቸው መወሰን እና ማደራጀት አለባቸው።

- ለቤተሰብ፣ ለጓደኞች፣ እና ለአካባቢው የተከበሩ ሰዎች አስቀድሞ ግብዣዎችን በመላክ ጥሩ ተሳታፊዎች  እንደሚገኙ ያረጋግጡ።

- ለዝግጅቱ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ማግኘት ላይ ተማሪዎች ከተቸገሩ፣ የማኅበረሰብ መሪዎች ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ጥያቄ እንዲያቀርቡ ጥቆማ ሐሳብ ይስጧቸው።

- በዝግጅቱ ላይ የተለያዩ ባህላዊ ኩነቶችን የሚያከብሩ ከሆነ፣ እያንዳንዱ ቡድን በአንድ

የየራሱ ጠረጴዛ ሊወከል የሚችልበት «ባዛር» ማዘጋጀት የሚቻልበት ዕድል አለ። እንግዶች ከአንዱ ጠረጴዛ ወደ ሌላ በመሄድ እንዲታዩ የቀረቡትን ቅርሶች እና ባህላዊ ቁሳቁሶች ይመለከታሉ፤ እንዲህ እያደረጉም የተለያዩ ምግብና መጠጦችን በመቀማመስ እና የተለያዩ ባህሎችን ሙዚቃ በማዳመጥ ይዝናናሉ። በተመሳሳይ ጊዜ ከጠረጴዛዎቹ በቅርብ ርቀት ላይ የተለያዩ ዝግጅቶች እና ትርዒቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

**የተማሩትን ትምህርት ማንፀባረቅ**

- ከዝግጅቱ በኋላ ተማሪዎቹ ምን እንደተሰማቸው ፣ ዝግጅቱ እንዴት እንዳለፈ እና ከተለያዩ ባህሎች ምን እንደተማሩ ከተማሪዎቹ ጋር ውይይት ያድርጉ። በግላቸው የተማሩትን ትምህርት በእራሳቸው የትምህርት ዕለታዊ ማስታወሻ ደብተር እንዲያሰፍሩ ይጠይቋቸው።

## የሰላም ክበብን ማቋቋም

(ከ Peace Club Guidelines (2014) ለዚህ ሰነድ እንደሚመጥን ተደርጎ የተወሰደ፦ National Cohesion and Integration Commission (NCIC) & Ministry of Education, Science and Technology — Kenya.)

**ዓላማዎች**

- ሰላምን፣ አክብሮትን እና ብዝኃነትን በእውነተኛ የሕይወት ኅዳናዎች ላይ ለማስተዋወቅና ለማበረታታት።

- ውጤታማ የትምህርት ቤት የሰላም ክበባትን በመጠቀም በትምህርት ቤት ውስጥ እና ውጭ ለሚከሰቱ አለመግባባቶች እና ግጭቶች መፍትሔ ለመስጠት።

**ውጤት**

- ተማሪዎች የዜግነት ግንዛቤያቸውን ያጎለብታሉ፤ የጋራ ችግሮችን መፍትሔ ለመስጠት በጋራ ይሠራሉ።
  - የሰላም ክበቦች ተማሪዎች ከመማሪያ ክፍል ውጭ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ ጠንካራ መንገዶች ሲሆኑ በራሳቸው በተማሪዎች ፣ በትምህርት ቤቶች እና በአጎራባች ማኅበረሰቦች መካከል መልካም ግንኙነቶችን እና አብሮነትን ያበረታታሉ ተብለው ይታመንባቸዋል።
  - ክበቦቹ ተማሪዎች ስለ ብዝሀነት እንዲገነዘቡ ለመረዳት ሊሄዱ የሚችሉባቸው መንገዶች እንዲቀርቡላቸው እና ለብዝኃነት እና ለመቻቻል ጥሩ ስሜት እንዲኖራቸው የሚያደርጋቸውን አመለካከት በተማሪዎቹ ላይ ለማስረጽና ያላቸው የብሔርና የሃይማኖት ልዩነት ከግምት ሳይገባ በስምምነት አብረው መኖር እንዲችሉ ለማድረግ ያስችሏቸዋል ተብሎ ይታመናል።
  - ክበቦቹ ብዝኃነት ባላቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ የሚኖሩ ወጣቶች ብዝኃነቱን እንዲያከብሩ መምራት መቻል አለባቸው።

**መዋቅር**

- በሰላም ክበቡ ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ፍላጎቱ ካላቸው ተማሪዎች መካከል የአመራር ቡድን መመረጥ አለበት። ልጃገረዶች፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሕፃናት፣ የተገለሉ ሰዎች ፣ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው እና ዝቅተኛ ግምት የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በቡድኑ ውስጥ እና በአመራሩ ላይ ጭምር መሳተፍ እንዳለባቸው አሠልጣኞች አፅዕኖት መስጠት አለባቸው።

**ስብሰባዎች**

- የሰላም ክበብ አመራር እና አባላት ስለእንቅስቃሴዎቻቸው ዕድቅ ለማውጣት እና ተፈጻሚ ለማድረግ በተወሰነ ጊዜ ልዩነት በመደበኛነት መሰብሰብ አለባቸው። የስብሰባ አደራረግ ዑደቱ በእናንተ ትምህርት ቤት ካሉት ሌሎች ክበቦች ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል።

**ፕሮግራሞች**

- የሰላም ክበብ አባላት በትምህርት ቤት ውስጥ የተማሯቸውን ክኅሎት እና እሴቶች ለመላው ማኅበረሰብ ማሳየትና ማስተማር እንዲችሉ መጠነ ሰፊ ዕድሎችን ለመፍጠር የተለያዩ የማኅበረሰብን መዳረሻ ፕሮግራሞችን እንዲያቋቁሙ መበረታታት አለባቸው። በማኅበረሰብ መዳረሻ ፕሮግራሞች በኩል የሰላም ክበብ አባላት ከማኅበረሰብ አባላት ጋር መስተጋብር በመፈጸም ጥሩ ዝምድናን በማቆየት፣ ትስስርን በመፍጠር እና ሰላማዊ አብሮ መኖርን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉባቸው ይችላሉ። የማኅበረሰብ መዳረሻ ፕሮግራሞች በተጨማሪ የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ያግዛሉ። የክበቡ አባላት የሰላም መልእክቶችን ከእነርሱ የትምህርት ተቋማት ውስጥ እና ውጭ ለማስተላለፍ ሊጠቀሙባቸው ከሚችሏቸው የማኅበረሰብ የቤት ለቤት ፕሮግራሞች መካከል አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፦

    - በሕዝባዊ ዝግጅቶች እና ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ፤
    - እንደ የሰላም ቀን፣ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛቀን፣ የወጣቶች ቀን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ እና ብሔራዊ በዓላትን ማክበር፤
    - የአካባቢ ማጽዳት እንቅስቃሴዎችን ማደራጀት፤
    - የሰላም አደባባዮች እና የተፈጥሮ መዝናኛ ቦታዎችን ማዘጋጀት፤
    - በጐ ፈቃደኝነት እና የማኅበረሰብ አገልግሎት መስጠት፤
    - የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት እና
    - የሰላም ጉዞዎች እና ሩጫ ውድድሮች/የእግር ጉዞዎችን ማድረግ ዋና ዋና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት

Alliance for Peacebuilding. (2013). *Selected Definitions of Peacebuilding.* ከዚህ ላይ የተወሰደ https://allianceforpeacebuilding.org/2013/08/selected-definitions-of-peacebuilding/

Anderson, R. D. (2002). Reforming science teaching: What research says about inquiry? *Journal of Science Teacher Education*, 13(1), 1-12.

Arigatou Foundation. (2015). *Report on the Systematic Implementation, Monitoring and Evaluation of the Learning to Live Together Programme in Kenya.* Geneva: Arigatou Foundation.

Arigatou International. (2008). *Learning to Live Together: An Intercultural and Interfaith Programme for Ethics Education.* ከዚህ ላይ የተወሰደ https://ethicseducationforchildren.org/images/zdocs/Learning-to-Live-Together-En.pdf

Asian-Pacific Cultural Center for UNESCO. (2012). History of Hope. ከዚህ ላይ የተወሰደ http://www.accu.or.jp/esd/hope/

Barrow, A. (2010). UN Security Council Resolutions 1325 and1820: constructing gender in armed conflict and international humanitarian law. *International Review of the Red Cross*, 92, 877. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.icrc.org/en/doc/assets/files/other/irrc-877-barrow.pdf

Beasley, C. (1999). *What is Feminism?: An Introduction to Feminist Theory.* London: Sage.

Bloom, E. Hill, F., & Krathwohol, D. (1956). *The Classification of Educational Goals. Handbook I: Cognitive Domain*. New York, Longmans.

Bowker, Lee Harrington (ed.) (1998). Masculinities and Violence. London, New Delhi: Sage.

Boyle, Elizabeth H. and Kristin Carbone-Lopez. (2006). Movement Frames and African Women's Explanations for Opposing Female Genital Cutting. *International Journal of Comparative Sociology*, 47, 435-65.

Brahm, E. (2003). Conflict Stages. In G. Burgess and H. Burgess (Eds.), *Beyond Intractability. Conflict Information Consortium*. University of Colorado, Boulder. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.beyondintractability.org/essay/conflict-stages

Buchbinder, D. (2013). *Studying Men and Masculinities.* New York: Routledge.

Caritas Internationalis. (2002). *Peacebuilding: A Caritas Training Manual*. Vatican City, Caritas. http://www.eprpinformation.org/wp-content/uploads/peacebuilding-caritas-training-manual-1of3-1.pdf

Center for Development Consulting. (2011). National Capacity Assessment for Prevention and Response to Gender Based Violence (GBV) in Schools. Addis Ababa, Ethiopia.

Cockburn, C. (2004). The Continuum of Violence: A Gender Perspective on War and Peace. In W. Giles and J. Hyndman (Eds.), *Sites of Violence: Gender and Conflict* Zones, 24-44. Los Angeles: University of California Press.

Connell, R.W. (2005). *Masculinities* (2nd ed.). Berkeley, CA: University of California Press.

Connell, R.W. and Messerschmidt, J.W. (2005). Hegemonic Masculinity. Rethinking the Concept. In *Gender & Society,* 19(6), 829-859. **ከዚህ ላይ የተወሰደ** https://student.cc.uoc.gr/uploadFiles/181-KMMK397/Connell%20and%20Messerschmidt-Hegemonic%20masculinity.pdf

Covey, S. (2013). 7 *Habits of Highly Effective People*. New York: Simon & Schuster.

Dart, J. J. and Davies, R. J. (2003). A dialogical story-based evaluation tool: the most significant change technique*, American Journal of Evaluation*, 24(2), 137-155.

Druckman. D. (2007). Negotiation in the international context. In I. W. Zartman (ed.), *Peacemaking in International conflict: Methods and Techniques,* 111-162. Washington: USIP Press Book.

Engdaw, T. (2018). *Peace Education for Youth Violence Prevention in Africa: Holistic and Integrated Approach*, *Case Study of Ethiopian Schools*. Germany: LAP LAMBERT Academic Publishing.

Enloe, C. (2004). *The Curious Feminist: Searching for Women in The New Age of Empire*. London: University of California Press.

Fisher, S., Abdi, D.I., Ludin, J., Smith, R., Williams, S. & Williams, S. (2000). *Working with Conflict: Skills and Strategies for Action. Responding to Conflict.* London: Zed Books.

Fountain, S. (1999). *Peace Education in UNICEF* (Working Paper). **ከዚህ ላይ የተወሰደ** https://www.unicef.org/lifeskills/files/PeaceEducationUNICEF.pdf

Freire, P. (1970). *Pedagogy of the Oppressed*. New York: Continuum.

Galtung, J. (1969). Violence, peace, and peace research. *Journal of Peace Research*, 6(3), 167-191.

Galtung, J. (1990). Cultural violence. *Journal of Peace Research*, 27(3), 291-305.

Giles, W. and Hyndman, J. (Eds.). (2004). *Sites of Violence: Gender and Conflict Zones*. Berkeley: University of California Press.

Gra, J. L. (2016). *Commodity Systems Assessment Methodology for Value Chain Problem and Project Identification*. ከዚህ ላይ የተወሰደ http://repiica.iica.int/docs/B4232i/B4232i.pdf

Hart, R. (1992). *Children's Participation from Tokenism to Citizenship*. Florence: UNICEF Innocent Research Centre.

Hart. R. (1997). *Children's Participation: The Theory and Practice of Involving Young Citizens in Community Development and Environmental Care*. New York, UNICEF.

IOM. (2017). Durable Solutions Strategy 2017-2020: The Durable Solutions Strategy of the Somali Regional Government of Ethiopia. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.humanitarianresponse.info/sites/www.humanitarianresponse.info/files/documents/files/171117_final-durable_solutions_strategy_for_somali_region_2017-2020.pdf

IOM. (2019). *Category: Ethiopia.* ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.globaldtm.info/category/east-africa/ethiopia/

IIRR. (2009). *Culture at Crossroads: Ethiopian women in peace-building*. Nairobi, Kenya: International Institute of Rural Reconstruction. ከዚህ ላይ የተወሰደ http://docplayer.net/38763416-Culture-at-crossroads-ethiopian-women-in-peace-building.html

Johnson- Freese, J. (2019). *Women, Peace and Security: An introduction*. New York: Routledge.

Kolb, D.A. (1984). *Experiential Learning: Experience as the Source of Learning and Development.* New York: Prentice Hall.

Leal, S. (2016, March 8). 6 Matriarchies Still Functioning Today. *Marie Claire.* ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.marieclaire.com/culture/a19105/matriarchies-still-exist-today/

Lerner, G. (1986). *The Creation of Patriarchy.* New York: Oxford University Press.

Lerner, K. L., Lerner, B. W., & Lerner, A. W. (2007). Gender Issues and Sexuality: Essential Primary Sources. Thomson Gale.

Life & Peace Institute, Peace and Development Center. (2016). *Making Peace in Ethiopia: Nine Cases of Traditional Mechanisms of Conflict Resolution*.

Miller, C. E. (2005). *A Glossary of Terms and Concepts in Peace and Conflict Studies* (2nd ed.). University for Peace. **ከዚህ ላይ የተወሰደ** http://twbonline.pbworks.com/f/Peace+and+Conflict+Studies+Glossary.pdf

Brahm, E. (2003). Is it A Multicultural Education Instructor's Reflective Self-Analysis: Facing the Challenge of Teaching and Learning. *Multicultural Education,* 11(2), 42-45. **ከዚህ ላይ የተወሰደ** https://files.eric.ed.gov/fulltext/EJ775332.pdf

Office of the United Nations High Commissioner for Human Rights. (2006). *Frequently Asked Questions on Human Rights-based Approach to Development Cooperation.* **ከዚህ ላይ የተወሰደ** https://www.ohchr.org/Documents/Publications/FAQen.pdf

Pavanello S. and Scott-Villiers, P. (2013). Conflict resolution and peacebuilding in the drylands in the Greater Horn of Africa. *Technical brief prepared by the Technical Consortium for Building Resilience to Drought in the Horn of Africa hosted by the CGIAR Consortium in partnership with the FAO Investment Centre.* **ከዚህ ላይ የተወሰደ** https://cgspace.cgiar.org/bitstream/handle/10568/27612/tc_brief6.pdf?sequence=2

Peace Women. (n.d.). Serbia NAP. **ከዚህ ላይ የተወሰደ** https://www.peacewomen.org/content/serbia-nap

Professional Warranty Service Corporation. (2016). Arbitration vs. Litigation — There IS a Difference!. *Professional Warranty Service Corporation.* **ከዚህ ላይ የተወሰደ** https://www.pwsc.com/blog/arbitration-vs-litigation-difference/

Ramsbotham, O., Woodhouse, T., and Miall, H. (2016). *Contemporary Conflict Resolution* (4th ed.). Cambridge: Polity Press.

SADC Centre of Communication for Development Harare and Food and Agriculture Organization of the United Nations. (2004). Situation Analysis Framework in PRCA. *Participatory Rural Communication Appraisal: Starting with the People: A Handbook* (2nd ed.).

Scott-Villiers, P., Ungiti, H.B., Kiyana, D., Kullu, M., Orto, T., Reidy, E, and Sora A. (2011). *The Long Conversation: Customary Approaches to Peace Management in Southern Ethiopia and Northern Kenya*. **ከዚህ ላይ የተወሰደ** https://www.future-agricultures.org/publications/working-papers-document/the-long-conversation-customary-approaches-to-peace-management/#

Barrow, A. (2007). *Identity and Violence: The Illusion of Destiny*. New York: W.W Norton & Company.

Tutu, D. (2000). *No Future without Forgiveness*. New York: Doubleday.

UNESCO. (2001). UNESCO Universal Declaration on Cultural Diversity. ከዚህ ላይ የተወሰደ http://portal.unesco.org/en/ev.php-URL_ID=13179&URL_DO=DO_TOPIC&URL_SECTION=201.html

UNESCO. (2003). *UNESCO's Gender Mainstreaming Implementation Framework: Baseline definitions of key concepts and terms*. ከዚህ ላይ የተወሰደ http://www.unesco.org/new/fileadmin/MULTIMEDIA/HQ/BSP/GENDER/PDF/1.%20Baseline%20Definitions%20of%20key%20gender-related%20concepts.pdf

UNESCO. (2006). *UNESCO Guidelines on Intercultural Education.* Paris: UNESCO. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000147878

UNESCO. (2011). *Media and Information Literacy: Curriculum for Teachers.* ከዚህ ላይ የተወሰደ https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000192971

UNESCO-IBE. (2012). *General Education System Quality Analysis/Diagnosis Framework (GEQAF).* ከዚህ ላይ የተወሰደ http://www.ibe.unesco.org/sites/default/files/resources/geqaf-2012_eng.pdf

UNICEF/UNESCO. (2007). *A Human Rights-Based Approach to Education*. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000154861

United Nations. (2019). Sustainable Development Goals- Goal 5: Achieve gender equality and empower all women and girls. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.un.org/sustainabledevelopment/gender-equality/

United Nations Economic and Social Council. (2010, July 23). *Resolution 2010/29 Mainstreaming a gender perspective into all policies and programmes in the United Nations system.* ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.un.org/en/ecosoc/docs/2010/res%202010-29.pdf

United Nations General Assembly. (1948, December 10). *Universal Declaration of Human Rights* (217 [III} A). Paris. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.un.org/en/universal-declaration-human-rights/

United Nations General Assembly. (1989, November 20). *Convention on the Rights of the Child*. United Nations Treaty Series, 1577(12), 3. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.ohchr.org/en/professionalinterest/pages/crc.aspx

United Nations General Assembly. (1998, January 15). *Resolution adopted by the General Assembly: Culture of Peace* [A/RES/52/13]. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://undocs.org/en/A/RES/52/13

UN Women. (2019). Gender Mainstreaming. ከዚህ ላይ የተወሰደ https://www.unwomen.org/en/how-we-work/un-system-coordination/gender-mainstreaming

Wangari, M. Nobel Lecture. (2004, December 10). *Nobelprize.org.* Nobel Media AB. 2014. ከዚህ ላይ የተወሰደ http://www.nobelprize.org/nobel_prizes/peace/laureates/2004/maathai-lecture-text.html

# የሰላም ግንባታ ሥልጠና

# ማኑዋል ለኢትዮጵያ

ይህ ዕትም በሰላም ግንባታ ረገድ በኢትዮጵያ ውስጥ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥም ሆነ ከትምህርት ሥርዓቱ ውጭ ባሉ የተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት የተዘጋጀ የሥልጠና መመሪያ ነው። ለኢትዮጵያ ዓውድ በሚሰማማ መልኩ የተዘጋጀ እና የተሻሻለ መመሪያ ሰነድ ነው።

የሥልጠና መመሪያው ሰነድ አንባቢው ሌሎችን ለምን እና እንዴት ስለ ሰላም ግንባታ ማስተማር እንዳለበት መረጃ እና አቅም የማጎናጸፍ ዓላማ አለው። የግጭት ትንታኔ እና የሰላም ግንባታን መሠረታዊ እሳቤዎች የሚያቀርብ ሲሆን ለሰላም ትምህርት እና ለማኅበረሰብ ተሳትፎ የሚጠቅም ተማሪውን ማዕከል ያደረገ የማስተማሪያ ዘዴን ያብራራል።

የሥልጠና መመሪያ ሰነዱ ግብ ሌሎችን እንደ ሰላም ገንቢዎች ያላቸው ሙሉ አቅም አውጥተው መጠቀም እንዲችሉ ለመደገፍ ከሚያስፈልገው ጠባይ፣ ዕውቀት፣ ክኅሎት እና ቁርጠኛ ተነሣሽነት ጋር ጥሩ አሠልጣኝ እንዲወጣው አንባቢውን መደገፍ ነው።